# ገላጭ ጥናት



## ገላጭ ስብከት ለማዘጋጀት የሚረዳ ተግባራዊ መመሪያ


## ጆኤል ጀምስ

ዮናታን ስምዖን እንደተረጎመው

ገላጭ ጥናት

ገላጭ ስብከት ለማዘጋጀት የሚረዳ ተግባራዊ መመሪያ

የቅጅ መብት ©2008 እ.አ.አ፤ ጆኤል ጀምስ      ተርጓሚ፦ ዮናታን ስምዖን

በልዩ ሁኔታ ካልተጠቀሰ በስተቀር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ (በአማርኛው ትርጉም) የተጠቀምናቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከ1954 የቀ.ኃ.ሥ ትርጉም እና ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው።

**የጸሓፊው አበርክቶት**

ለወላጆቼ

የጠንካራ ሠራተኝነት ሥነ-ምግባር ላስተማረኝ አባቴ፤ በሁሉም የጽሑፍ ሥራዎቼ ቀዳሚ አርታኢ ለሆነችው እናቴ። ለሁለታችሁም ክርስቶስንና ቤተ-ክርስቲያኑን እንድወድ ስላስተማራችሁኝ።

## ማውጫ


1. ለእግዚአብሔርን መስበክ 4
2. ገለባ ሳይሆን ስንዴ፡ እግዚአብሔር የሚወደው ዓይነት ስብከት 11
3. መጽሐፍ ቅዱስ የጸሐይ ብርሃን ነው ወይስ ጭጋግ? 16
4. መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት መተርጎም እንደሚቻል 23
5. ሰዋሰው እና አገባብ፤ የሰባኪ ጓደኞች 46
6. ዐረፍተ ነገር መቀነስ 57
7. ስዕላዊ/ዋና ንድፍ ማውጣት 60
8. የምንባብ ክፍል ዝርዝር ማውጣትና ማጠቃለል 71
9. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትረካን ማጥናት 77
10. የትረካ ዝርዝር ንድፍ ማውጣት 93
11. ምሳሌን ማጥናት 100
12. መዝሙረ ዳዊትን ማጥናት 118
13. ማጠቃለያ 132

አባሪዎች 136

ስዕላዊ ንድፍ የማውጣት መልመጃ 136

በለ ብዙ ቁጥር ስሞች

# ምዕራፍ አንድ

# ለእግዚአብሔርን መስበክ

አባቴ አናጺ ነው። ቀጥ ያሉ በርዶችን፣ በትክክል የሚገጣጠሙና የሚሰኩ አራት ማዕዘኖችን የሚሠራ አናጺ። በቤታችን ጎን አጎንብሰን የምንገባበትን የእንጨት ቤት የሠራንበትን ክረምት መቼም አልረሳውም (እርግጥ የሠራው እርሱ ነው፤ እኔ ምስማርና ሌሎች ለሥራው የሚያስፈልጉ እቃዎችን በማቀበል ረድቼዋለሁ)። ሥራውን ልናጠናቅቅ ተቃርበን ሳለ አባቴ አንዱ ማዕዘን ከቤቱ ጋር በትክክል እንደማይገጥም አወቀ። በሁለቱ መገጣጠሚያዎች መካከል የአንድ ሰንቲ ሜትር ልዩነት ነበረው፤ ይህ ደግሞ ለእርሱ በጎርፍ እንደተጥለቀለቀው የዛምባዝ ወንዝ ሰፊ ነው።

አባቴ ጠማማ ነገር ከመሥራት አውራ ጣቱ በሚስማር ቢመታ የሚመርጥ ሰው ነበረና እኔን እያየኝ "*እርግጠኛ ነኝ በትክክል እንደሰራሁት ግን እንዴት ነው ሊገጥም ያልቻለው?*" ሲል አለቀሰ። እኔም "*አባዬ ይህ እኮ ምንም አይደለም ደግሞም ማንም አያየውም*" ስል መለስኩለት። የማይረባ አስተያዬት ነው የሰጠሁት። በአባቴ ግምት አናጽዎች ስህተት በሰሩ ቁጥር "ይህ እኮ ቀላል ስህተት ነው" በማለት የማይረባ ምክንያት በመዘርዘር የሚያጉረመርሙ በለሙያዎች በቀጭኑ ተከታትፈው የአዞ እራት መሆን አለባቸው።

ለአባቴ ብዙም የምረዳው ስላልመሰለኝ በሠራው ማዕዘን የተከሰተው የአንድ ሰንቲ ሜትር ልዩነት እንዴት ሊከሰት እንደቻለ ችግሩን ማግኘቱንና የማስተካከሉን ኃላፊነት ለእርሱ በመተው እርሱ ያንን በሚያደርግበት ጊዜ እኔ ወደ ቤት ገብቼ ማንበብ ቀጠልኩኝ። ከግማሽ ሰዓት በኋላ ፈገግታ በተሞላ ፊት ከኋላ በር በኩል መጣ፤ ክፍተቱ እንዳለ ነው፤ ነገር ግን የእርሱ ጥፋት አልነበረም፤ የእርሱ ሥራ ቀጥ እንደለ ነው።

ያለመታደል ሆኖ አባቴ ከግንባታ ክህሎቶቹ ለእኔ ምንም አላስተላለፈም። ይህን እናዘዛለሁ፤ አናጺነትን በተመለከተ አሰቃቂ ጥፋቶችን የምፈጽም ሰው ነኝ። ያስተላለፈልኝ ነገር ግን አለ፤ የአናጺዎች ልክ ምን እንደሆነ፣ ለሀቀኝነት ፍቅር እንዲኖረኝ፣ በልህቀት እንድደሰት ሆኛለሁ። አባቴ የሠራው በእንጨቶች ነው፤ እኔ የምሰራው በእግዚአብሔር ቃል ነው፤ ነገር ግን ሁለታችንም በቀጥታ መቁረጥን በተመለከተ ጥልቅ ስሜት አለን።

ይህ ጥልቅ ስሜት ጳውሎስ በእምነት ልጁ ለሆነው ጢሞቴዎስ "የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ።" (2ጢሞ 2፡15) ሲል በሕይወቱ ብቁ ባለሙያ እንዲሆን ማያያዝ/ማቀጣጠል የፈለገው ስሜት ነው። *የእውነትን ቃል በቅንነት*

*የሚናገር* የሚለው ሐረግ *የእውነትን ቃል ቀጥ አድርጎ የሚቆርጥ* ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። እንደ ድንኳን ሰፊ ጳውሎስ የሰራው በቆዳ ነው በእንጨት አይደለም (ሐዋ ሥ 18፡3)። ነገር ግን በአባቴ እንሆነው ሁሉ ትክክለኝነት የጳውሎስም ሥራ መለዮ ነው። ደግሞም ጳውሎስ ልክ እንደ አናጺ ጢሞቴዎስም የእግዚአብሔርን ቃል ትርጉም በተመለከተ ትክክል እንዲሆን ያነዋቀዋል።

ጢሞቴዎስ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን እንዳደረገው ሁሉ፤ እኔና አንተ የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል የመቁረጥ ኃላፊነት አለብን። ለምን? ምክንያቱም አንተና እኔ ለመስበክ ስንቆም አንዳች እጅግ ጠቃሚ ነገር እያደረግን ነው፤ ለእግዚአብሔር እየሰበክን ነው።

## ሰባኪው አምላክ

እግዚአብሔር ሰባኪ ነው። ብሉይ ኪዳን እንደሚነግረን ከሆነ፤ እግዚአብሔር ለከዋክብት፣ ፕላኔቶች፣ ለመሬት፣ ለሰው ልጆች መናገሩን ከጨረሰ በኋላ ምላሱ ዝም አላለችም። እግዚአብሔር በመናገሩ ቀጥሏል፤ ሲናገር ደግሞ እየሰበከ ነው። በትዕይንት የተሞላው ትልቁ የእግዚአብሔር ስብከት የታየው በሲና ተራራ አስርቱን ሕጎች በሰጠ ጊዜ ነው። የሲናው ስብከት በዓለም ታሪክ ውስጥ ትልቁ የአየር ላይ ስብከት ክስተት ነበር። ከሁለት ቀናት ዝግጅት በኋላ፤ ወደ ሁለት ሚልዮን የሚጠጋ ሕዝብ በተራራው ዙሪያ ተሰበሰበ። ቅዱሱን እግዚአብሔር መቅረብ ለሰውም ሆነ ለእንስሳ ሞት የሚያስከትል ስለነበረ ወደ ተራራው እንዳይጠጉ ሙሴ ያሰመረውን ድንበር በጥንቃቄ ማክበር አለባቸው። ታዲያ ሁለት ሚልዮን ሕዝብ ላለበት ጉባኤ መስበክ የሚችለው ማንነው? እግዚአብሔር ብቻ!

እርሱም አደረገው። ተራራው ምስባክ/ መድረክ ነበረ፣ ስብከቱ አስር ነጥቦች ነበሩት፣ እግዚአብሔር እራሱ ሰባኪ ነበረ፤ ለሚንቀጠቀጠው ጉባኤ በሚያምር መለኮታዊ ድምጽ ተናገረ። ሕዝቡ በሩቅ ቆመው ወደፊት እግዚአብሔር በሙሴ በኩል እንዲናገራቸው መማጸናቸው የሚያስገርም ነውን? እግዚአብሔር ሲሰብክ፤ በኃይል ይሰብካል።

ከሲናው ክስተት በኋላ በነበሩ መቶ ክፍለ-ዘመናት እግዚአብሔር መስበኩን ቀጥሏል፤ በሚሰማ መለኮታዊ ድምጽ ሳይሆን ታማኝ በሆኑ የነቢያት ድምጾችና እስትንፋሰ መለኮት ባዘሉ መልዕክቶቻቸው። እንዲያውም፣ ኤርምያስ እግዚአብሔር በየማለዳው እንደሚነሣ፣ በትጋት፣ በታማኝነት፣ በጽናት ነቢያትን ወደ እስራኤል እንደሚልክ ተናግሯል። ሕዝቡ የነቢያትን የልመና ድምፅ ለመስማት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው፣ እግዚአብሔር “አልሰሙኝም” (ኤር 7፡26) ሲል አዘነ። እግዚአብሔር በሲና ሰበከ፤ በነቢያትም በኩል መስበኩን ቀጠለ።

ሁለተኛው የስላሴ አካል፤ እግዚአብሔር ወልድ ስጋ ለብሶ በመጣ ጊዜም አባቱ እየሰበከ ነበረ። በዮሐ 1፥1 ሐዋርያው ዮሐንስ ኢየሱስን *ቃል* ብሎ ጠርቶታል። ዮሐንስ ኢየሱስን ሎጎስ በሚለው ቃል ወሰን ውስጥ ስብከቱ ይለዋል። "ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን።" (ዕብ 1፡1-2)። እግዚአብሔር የሚሰብክ አምላክ ነው፤ ታላቁ ስብከቱ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

በኢየሱስ ክርስቶስ፤ እግዚአብሔር አሁንም የሲና አምላክ ነው፤ የሚሰብክ አምላክ። ከኢየሱስ አገልግሎቶች ውስጥ እንደ ልዩ ሐብቴ የማየው የተራራውን ስብከት ነው። ቀላል ያለ አለባበስ የለበሰ አናጺ በሣር፣ በአበቦች፣ በአለትና በገሊላ ወፎች ታጅቦ፤ በስልጣን የተሞላ መለኮታዊ ህጉን ለጋበዛቸው አድማጮቹ ያውጃል። ከሲናው የተሸለ ጸጥታ ነበረበት፤ እንደ ሲናው በትዕይንት/ድራማ የተሞላ አልነበረም። እሳት አልነበረም፣ ጭስ አልነበረም፣ የመሬት መንቀጥቀጥ አልነበረም ወይም የሚያሳውር ክብር። ነገር ግን በድጋሚ መድረኩ ታራራ፣ ስብከቱ የእግዚአብሔር ሕግና ራሱ እግዚአብሔር ነበረ፤ ሰባኪው ደግሞ ሁለተኛው የሥላሴ አካል ነበረ። "እርሱም፦ በዚያ ደግሞ ልሰብክ ወደ ሌላ ስፍራ በቅርብ ወዳሉ መንደሮች እንሂድ ስለዚህ ወጥቻለሁና አላቸው።" (ማር 1፡38) ይህ ንግገሩ ኢየሱስ የስብከት አገልግሎቱን ጥቅም ያሰመረበት ንግግር ነው።

## ለእግዚአብሔርን መስበክ

ያኔ እግዚአብሔር ሰብኳል፤ ግና ዛሬም እየሰበከ ነው ወይ? አዎ፤ ሰባኪ አምላክ እንደሆነ ነው ያለው። በሲና ተራራ እንዳደረገው በዘመናችን በሚሰማ ድምጽ አይሰብክም፤ በብሉይ ኪዳን ዘመን እንዳደረገውም በመንፈሱ ቀስቃሽነት በነቢያት መገለጣዊ መልክዕክትም አይደለም ዛሬ የሚሰብከው። በእኛ ዘመን እግዚአብሔር የሚሰብከው ቃሉን፤ መጽሐፍ ቅዱስን በሚያውጁ የታመኑ ሰዎች በኩል ነው። ዛሬ ሰባኪዎች የተጻፈውን የእግዚአብሔር ቃል በትክክል ሲሰብኩ፤ እግዚአብሔር እራሱ በድጋሚ እየተናገረ እንዳለ ይቆጠራል። "*ቃሉን ስበክ*" የሚለው ትዕዛዝ "*ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው*" ከሚለው ከሦስት ቁጥሮች ቀጥሎ መጻፉ በአጋጣሚ የተከሰተ አይደለም (2 ጢሞ 4፥2፤ 3፥16)። የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ማለት ቃሉን ለመስበክ አፋችንን በምንከፍትበት ጊዜ ሁሉ፤ እግዚአብሔር እየሰበከ ወይም እየተናገረ ነው እንደ ማለት ነው።

የእግዚአብሔርን ቃል በታማኝነት ከሰበክን የእግዚአብሔር ድምጽ ይደመጣል፤ በታማኝነት ካልሰበክን ደግሞ አይሰማም። ይህ ከምንሰብክባቸው ምክንያቶች አንዱ ነው፤ እግዚአብሔር ደምጽ ሊኖረው ይገባል።

እግዚአብሔር መደመጥ አለበት። ራሴን የእግዚአብሔር ድምጽ ለመሆን አልመርጥም፤ ማንም ሰው የእግዚአብሔር ደምጽ እንዲሆንም እንደዚሁ። ነገር ግን ሉዓላዊው፣ ሁሉን ቻዩ ሰዎች የእርሱ አንደበት እንዲሆኑ መርጧል፤ ስለዚህ የኢሣያስን ትህትና አስተጋባለሁ፤ "እነሆኝ እኔን ላካኝ"።

እግዚአብሔር ሰዎችን፤ በጌታ የዳኑ ክርስቶስን የሚወዱ ሰዎችን መጠቀሙ እንዴት የሚያስደንቅ ነው። ዛሬ እኔ ንጉስ ወይም አጼ ብሆን፤ እንደ ሰባኪ ቢሮዬን አልሰጥም። ለእግዚአብሔር መናገር ንጉስ ሆኖ ሀገር ከመምራት የሚበልጥ ሥራ ነው። ይህንን ስራ በተሳሳተ መንገድ ብትራዳው ምን የሚከሰት ይመስልሃል? ለእግዚአብሔር ስትሰብክ ትክክል ባልሆነና በተሳሰተ መንገድ ብትሰብክሳ? እግዚአብሔር ያላለውን ነገር ብትናገርሳ?

## ለእግዚአብሔር ማጥናት

ለእግዚአብሔር መስበክ እንዴት ያለ ታላቅ ዕድል ነው! አንድ ሰው ማርቲን ሉተር በጋለ ስሜት "እኔ ንጉስ ብሆን እንደ ሰባኪ ቢሮዬን ለማንም አልሰጥም"[1] ያለው አባባል ይገበዋል። ለእግዚአብሔር መናገር ሀገር ከመምራት የበለጠ ተግባር ነው። ነገር ግን በትክክል ሳትረዳው ብትቀርሳ? ለእግዚአብሔር ስትሰብክ፤ በተሳሳተ መንገድ ብትሰብክሳ? እግዚአብሔር ያላለውን ነገር ብትልሳ?

እግዚአብሔር ከናፍርቶችህን የእርሱን ስብከት ለመስበክ የሚጠቀም ከሆነ፤ በትክክል ልትረዳው ይገባል። ኦ! ለቀጥተኛው መገለጥ! ነቢያት እግዚአብሔር ያለውን በትክክል እንዲናገሩ ተዘዋል፤ ምክንያቱም እርሱ ቃሉን በአንደበታቸው ያስቀመጠው፤ ቅዱሳት መጽሐፍትን ባደረገበት መንገድ ነው። "ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።" (2 ጴጥ 1፥21፤ ኤር 1፥9)። ነገር ግን እኛ ቅዱሳት መጽሐፍት የጻፉ ሰዎች በተቀበሉት መንገድ የተገለጠልን ሰባኪዎች አይደለንም።

እንደዚያ ከሆነ፤ የእግዚአብሔርን ቃል የምንሰብክበት መንገድ የለም ማለት ነው? በእርግጥ ተስፋ አለ። የእግዚአብሔር ቃል እስትንፋሰ መለኮትነት አስተምህሮ ማለት መጽሐፍ ቅዱስ በምትከፍትበት ጊዜ ሁሉ በትክክል ተርጉመው፣ በትክክል አብራራው ማለት ነው። ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ቃሎች እራሱ እግዚአብሔር እንደሚሰብክ አድርገህ መስበክ አለብህ። እግዚአብሔር ለሙሴ፣ ለኢሣይያስ፣ ለማቴዎስ፣ ለጳውሎስ እና ለጴጥሮስ በብዕራቸው በኩል የሰበከውን በድጋሚ ስትሰብክ የእርሱ ድምጽ ይደመጣል።

---

[1] Fred W. Meuser, Luther the Preacher (Minneapolis: Augsburg Publishing House, 1983), 39, quoted in John Piper, The Legacy of Sovereign Joy: God's Triumphant Grace in the Lives of Augustine, Luther, and Calvin (Wheaton, Ill.: Crossway Books, 2000), 86

እግዚአብሔርን መስበክ ታላቅ እድል ነው፤ ግን ደግሞ እግዚአብሔርን ለመስበክ አስቀድመህ ለእግዚአብሔር ማጥናት አለብህ። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን “ቃሉን ስበክ” (2 ጢሞ 4፥2) ሲል አዟል። ጢሞቴዎስ ይህንን ትዕዛዝ በስኬት መፈጸም የሚችለው፤ “የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ።” (2 ጢሞ 2፥15) የሚለውን ትዕዛዝ ቀድሞ ሲፈጽም ብቻ ነው። ብዙ ጊዜ በአፍሪካ ይህንን የጳውሎስ ትዕዛዝ ስንተላለፍ እንገኛለን፤ ብዙ ሰባኪዎች ከበስተጀርባቸው እንደማያሳፍር ሠራተኛ ዓይነት ትጋት የለባቸውም። ድምጻችንን ከፍ አድርገን እንሰብክ ይሆናል፣ ለሰዓታት እንሰብክም ይሆናል፣ ስንሰብክ ሰዎች የተነኩ ሊመስል ይችላል፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃሎች በትክክል እግዚአብሔር የእኔ ቃሎች ናቸው በሚለው መንገድ ካልሰበክን፤ ለእግዚአብሔር አልሰበክንም ማለት ነው። ዛሬ እግዚአብሔር የሚሰብከው እኔ፣ አንተና መሰል ወንድሞች ህያው የሆነውን፣ የሚነደውን፣ የሚፍለቀለቀውን፣ ኀይለኛ የሆነውን መለኮታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃሎች በታማኝነት ስንሰብክ ብቻ ነው።

እዚህ ጋር ጥያቄ አለ፤ እግዚአብሔር ያለውን ቃል በድጋሚ በትክክል ለማለት የትኛው ዓይነት የጥናት ዘዴ ነው ዋስትና ሊሰጠን የሚችለው? በዚህ አገባብ የትኛውም ሰው እግዚአብሔርን መስበክ አይችልም፤ ማቱሳላ ሽማግሌ አይደለም፣ ሰለሞን በቂ ጥበብ የለውም። ነገር ግን ስብከትህ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ የተናገረውን ደግመህ እንድትል በሚያስችልህ መንገድ የተዘጋጀ ከሆነ የእግዚአብሔር ድምጽ ወደ መሆን ትመጣለህ። በሌላ መንገድ ለመናገር፤ ገላጭ ስብከት ገላጭ ጥናት ይጠይቃል።

እግዚአብሔር በቃሉ ያለውን በድጋሚ ለማለት የምትዘጋጀው ስብከት ሂደት የሚፈልግ ነው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈባቸው እናት ቋንቋዎች እያጠናህም ይሁን (ቢቻል የተሸለ ነው) ወይም በእግሊዘኛ፣ በአማርኛ ወይም በሌላ የሀገር ውስጥ ቋንቋዎች፤ በዚህ መጽሐፍ የምትማረው የጥናት ሂደት ግልጽና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከት እንድታዘጋጅ ይረደሃል። የእግዚአብሔርን ቃሎች በሚገባ የሚያብራራና የሚያዛምድ ስብከት።

## ስዕላዊ ንድፍ ማውጣት

ላስተምርህ የፈለግሁት የጥናት ዘዴ ስዕላዊ ንድፍ/መግለጫ ማውጣት የሚል ነው። ይህ አቀራረብ መጽሐፍ ቅዱስ ስታጠና ስለ እያንዳንዱ ነጠላ ጉዳይ ወይም ነጥብ እንዲሁም ስለ አጠቃላይ ክፍሉ እንድታስብ የሚያደርግ አቀራረብ ነው። እግዚአብሔር ያለውን እንድትፈልግ ይገፋፋሃል፤ ይህ ደግሞ እግዚአብሔርን ለመስበክ ቁልፉ ጉዳይ ነው።

ስብከት ከሰባኪ ሰባኪ፣ ከቤተ-ክርስቲያን ቤተ-ክርስቲያንና ከባህል ባህል ይለያያል። በከተማዬ ፕርቶሪያ በምዕራባዊው ቤተ-ክርስቲያን የሚሰራው ስብከት መንደር ውስጥ ባሉ ቤተ-ክርስቲያናት ላይሠራ ይችላል። አፍሪካዊ ጉባኤዎች ከምዕራባዊያን ጉባኤዎች ይልቅ ደጋግሞ መስበክን፣ ከፍ ያለ ድምጽንና ስሜትን ይመርጣሉ። ይህ ተቀባይነት ያለው ነው። ገላጭ ስብከቶች ባህላዊ ይዘቶች አሉአቸው። ነገር ግን ልንለውጠው የማንችለው እግዚአብሔር ያለውን በድጋሚ ለማለት የሚያስፈልገውን ቁርጠኝነት ነው። ይህንን ካላደረግህ ለእግዚአብሔር አልሰበክህም ማለት ነው። ስለሆነም ከባህል ልዩነት በዘለለ ሁሉም ሰባኪዎች እግዚአብሔር እንዲናገር የሚፈቅዱ ስብከቶችን ለማዘጋጀት ማጥናት አለባቸው። ከዋና ንድፍ በመነሳት ስብከት ማዘጋጀት ይህን ለማድረግ ጥሩ መንገድ ነው።

ስዕላዊ ንድፍ ምንድነው? የምንባቡን ትርጉም በምታገኝበት መንገድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላትን ማደራጀት ነው። ለምሳሌ ዘፍጥረት 1፥1ን በሚከተለው መንገድ መንደፍ እንችላለን

በመጀመሪያ

እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ

ማየት ትችላለህ? ማን ፈጠረው፣ ምን ፈጠረ፣ እና መቼ ፈጠረ? ስዕላዊ ንድፍ ምንባቡ ለመናገር የፈለገውን ያሳየሃል። እግዚአብሔር የተጠቀማቸውን ቃላት መሠረት በማድረግ ልቡን ይገልጥልናል። ዘፍጥረት 1፥1ን ስትሰብክ፤ የፍጥረት ጅማሬን በተመለከተ ማን፣ መቼና ምንን ስትሰብክ የእግዚአብሔርን ቃል በድጋሚ እየሰበክህ ነው።

ንድፍ ማውጣት ከባድ ሥራ ነው ወይ? አዎ ነው። እረኛ በተጠሙ በጎቹ ዙርያ እንደቆመ ሳል፤ በጨኸት የተሞላው የበጎቹ ድምጽ ሕይወት የሚያስቀጥል ወሃ የሚጠራቀምበት ጉድጓድ ፍላጎት አጣዳፊ መሆኑን ነው። ይህንን ውሃ ለማግኘት አረኛው ባልዲውን በጠንካራ ገመድ አስሮ ወደ ጉድጓዱ መስደድና ውሃ ይዞ መውጣት አለበት። በዚህ መንገድ እጁ እየተላላጠ ውሃ እያወጣ ሲሰጥ ብቻ ነው በውሃ ጥም የተጎዱ በጎቹን ማርካት የሚችለው።

ይህ እግዚአብሔርን ለመስበክ ማጥናት ምን እንደሚመስል አመላካች ነው። የእግዚአብሔር ቃል ሕይወት ሰጪ ውሃ የሚገኝበት ጉድጓድ ነው። አንተ ሰባኪ ለምዕመንህ አሸዋ መስጠት አትችልም፤ ውሃ ነው መስጠት ያለብህ፤ የእግዚአብሔርን ውሃ። ስለሆነም ልክ ውሃ እንደሚቀዳበት ባልዲ በየሳምንቱ አእምሮህን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ አጥልቀህ አስገባ። ስታጠና ባልዲህን ትሞላለህ፤ ከዚያም አውጥተህ ትሰጣለህ።

በሐሰት የተሞላው የሰው ጥበብ የሚገኝበት ገንዳም እጆችህ አጠገብ አለ። ለሰባኪ ባልዲውን ወደዛ መስደድና በቀላሉ ማውጣት ቀላል ነው፤ ይህ ጠንካራ ሥራ አይጠይቅም፤ ነገር ግን ይህ ውሃ በጎቾን ይመርዛል። ንጹሕ ውሃ የምትፈልግ ከሆነ፤ ባልዲህን ወደ ቅዱስ ቃሉ አጥልቀህ መስደድ ይጠበቅብሃል፤ ትጉህ ሰራተኛ የእውነትን ቃል በትክክል ይይዛል። ይህንን ለማድረግ ታማኝ ከሆንክ፤ በየእሁዱ እግዚአብሔር ድምጽ ይኖረዋል፤ ቃሉን ስትሰብክ በድጋሚ ይናገራል። ይህ እግዚአብሔር ዛሬም የሚሰብክበት መንገድ ነው። ሉተር ንጉስ ከመሆን ይልቅ ሰባኪ መሆን ይሻላል በማለቱ ትክክል ነው። ነገር ግን እግዚአብሔርን ለመስበክ አስቀድመህ ለእግዚአብሔር ማጥናት አለብህ።

# ምዕራፍ ሁለት

## ገለባ ሳይሆን ስንዴ፡ እግዚአብሔር የሚወደው የስብከት ዓይነት

እንደ ሁሉም ክርስቲያኖች አፍሪካዊያን አማኞችም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በአስቸኳይ ይፈልጋሉ። ነገር ግን ሰባኪዎቻችን በሚሰብኩባቸው መድረኮች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን የሚያብራሩት አልፎ አልፎ ነው። የተለመደው ሰባኪው ከስብከቱ በፊት የሚሰብክበትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ያነባል። ነገር ግን ልክ ምንም ሊሰራ እንደማይችል ህጻን ያነበበውን ክፍል ይረሰዋል፤ ከአደራሹ ያስወጠዋል። ሰባኪው የእግዚአብሔርን ቃል በማብራራት ፈንታ ሌላ አእምሮ ወለድ ሀሳቦችን በመጨመር፣ የስብከቱን ጥፍጥና ለመጨመር የሌሉ ታሪኮችን በማያያዝ ከባድ ጫና በመፍጠር ሕዝቡን ያሰክራል። ቀጥሎ ምን ማለት እንዳለበት እርግጠኛ ካልሆነ "አሜን፤ አሜን" ፤ "ሀሌሉያ" የሚሉ ቃላትን ይሰነቅራል። ከዛም ጉባኤው በጩኸት ምላሽ ሲሰጠው ወደ ሚቀጥለው ሀሳቡ ይሸጋገራል።

እግዚአብሔር በክብር ከፍ ያለ እና ፍጹም በለሥልጣን አምላክ ነው። በስብከት ወቅት ቃሎቹ ችላ ሲባሉ ደስ ሊለው አይችልም። እርግጥ የሰው ቃልና የእርሱ ቃል በአንጻራዊነት ሲነጻጸር ፤ እግዚአብሔር የጠየቀው "ገለባ ከስንዴ ጋር ምን አለው?" (ኤር 23፥28) ብሎ ነው። ምንም የለውም። ስንዴ ወደ ጎተራ የምትከተው ነው፤ ገለባ ደግሞ ወደ እሳት። የትኛውን አማራጭ ትመርጣለህ? የእግዚአብሔርን ቃል ታብራራለህ ወይስ ገለባ የሆነውን የሰው ሀሳብ ትበትናለህ?

አንድ ወዳጄ በአንድ ወቅት "ገላጭ ስብከትን ከመማርህ በፊት ምን ታደርግ ነበረ?" የሚል ጥያቄ ቀረበለት። በትህትና መለሰ፦ "ከፍ ያለ ድምፅ አሰማ ነበረ" ሲል። የእግዚአብሔርን ቃል እየሰበከ አልነበረም። ነገር ግን ገለባውን መበተኑ በጉጉት የተደረገ በመሆኑ ሰዎች ያዳምጡ ነበር። በታላቅ ድምፅ መስበክ ምንም ስህተት የለውም ነገር ግን ስህተቱ ሰባኪው ስለ እግዚአብሔርና ስለ ክርስቶስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣናዊ ቃል ይልቅ ግልጽ ያልሆኑ ሃሳቦችን ሲያስተምር ነው።

መንፈሳዊ መሪዎች የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር ፈንታ (ኤር 5፡30-31) በራሳቸው ስልጣን ከተመሩ፤ እግዚአብሔር ይህንን ተግባር "አስፈሪና አሰቃቂ ነገር" ይለዋል። ቃሉን በመስበክ ምትክ ቃላቸውን የሚያስተምሩ ሰባኪዎችን እግዚአብሔር ፈጽሞ ይጠላል። "*የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ትንቢት የሚናገሩላችሁን የነቢያትን ቃል አትስሙ ከንቱነትን ያስተምሩአችኋል ከእግዚአብሔር አፍ ሳይሆን*

*ከገዛ ልባቸው የወጣውን ራእይ ይናገራሉ።.....በምክሬ ግን ቢቆሙ ኖሮ፥ ለሕዝቤ ቃሌን ባሰሙ ነበር፥ ከክፉም መንገዳቸው ከሥራቸውም ክፋት በመለሱአቸው ነበር።"* ( ኤር 23:16, 22 )

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካለው የእግዚአብሔር ቃል ይልቅ የራሱን ሐሳብ ለመስበክ የሚመርጥ ሰባኪ፣ ከዳቦ ይልቅ ድንጋይን፣ ከዓሣ ይልቅ እባብን፣ ከእህል ይልቅ ገለባ ይመርጣል። ለእንደዚህ አይነት ሰዎች ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ይናገራል፡- "ወደ ሕግና ወደ ምስክር ሂዱ! እንዲህም ያለውን ቃል ባይናገሩ ንጋት አይበራላቸውም።" (ኢሳ 8፡20) የእግዚአብሔር ቃል ስንዴ ነው፤ የእግዚአብሔር ቃል ብርሃን ነው። አንድ ሰባኪ ጠቃሚ መልእክት የሚናገረው የእግዚአብሔርን ቃል ድጋሚ ሲሰብክ ብቻ ነው፤ መጽሐፍ ቅዱስን ሲሰብክ።

## ገላጭ ስብከት

የእግዚአብሔርን ቃሎች መልሶ መስበክ ገላጭ ስብከት ይባላል። ገላጭ የሚለው ቃሉ "ስለ አንድ ነገር ጥልቅ ዝርዝር ማብራሪያ ማድረግ ነው።"[2] ስለ ምንም ነገር ጥልቅ ማብራሪያ የማይሰጡ ብዙ ስብከቶች ሰምተህ ይሆናል። ያንን ልማድ ለመለወጥ ጊዜው አሁን ነው። በጆን ማክአርተር አገላለጽ፤ ገላጭ በሆነ መንገድ መስበክ ማለት "የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሙሉ በሙሉና በቀጥታ ትክክለኛ ትርጉም በሚሰጥበት መንገድና በእግዚአብሔር እንደታሰበው ሲሰበክ ነው።"[3] ገላጭ ስብከት እግዚአብሔር ያለውን በድጋሚ ማለት ነው።

ነህምያ 8 የዚህ ዓይነቱን ስብከት ጥንታዊ ምሳሌ ዘግቧል። ነህምያ በፋርስ መንግስት ሥር የይሁዳ ገዢ ሆኖ የተሾመበትና ተልዕኮውን የወሰደበት ጊዜ በ444 ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር። በወቅቱ በይሁዳ የነበረው ቀዳሚ ፍላጐት ኢየሩሳሌምን እንደገና መገንባትና እንደገና መሥራት ነበር። በጣም ግልፅ ያልነበረው የሰዎችን ልብ እንደገና የመገንባት አስፈላጊነት ነበረ። ለዚያ ተግባር, ጡቦች እና ሲሚንቶ አላስፈለጉም፤ የእግዚአብሔር ቃል እንጂ።

ዕዝራ የሕዝቡን ልብ ለመገንባት በነህምያ የተመለመለ የጡብ ሰራተኛ ነበር። ነህምያ ምዕራፍ 8 የዕዝራን ስብከት በሦስት ወሳኝ ድግግሞሾች መዝግቧል። መጥራት ወይም ጮክ ብሎ ማንበብ (4 ጊዜ)፣የሕጉ መጽሐፍ (4 ጊዜ)፣ እና ለመረዳት ወይም ለመለየት (9 ጊዜ)። የነህምያ ማጠቃለያ በ8፡8 ላይ ይገኛል። "የእግዚአብሔርንም ሕግ መጽሐፍ አነበቡ ዕዝራም እግዚአብሔርን ማወቅ ያስተምርና ያስታውቅ ነበር፥

[2] Webster's New World Dictionary, 2nd College ed. (New York: Simon and Schuster, 1984), s.v. "Exposition."

[3] John MacArthur, Jr., "The Mandate of Biblical Inerrancy: Expository Preaching," in Rediscovering Expository Preaching, John MacArthur, Jr. and The Master's Seminary Faculty (Dallas: Word Publishing, 1992), 23-24, emphasis original.

ሕዝቡም የሚነበበውን ያስተውሉ ነበር።" ሕዝቡ ክፍሉን ተረድተው መኖር ይችሉ ዘንድ ዕዝራና አብረውት የነበሩት ሰባኪዎች የሕጉን መጽሐፍ አንብበው ክፍሉን አስረዷቸው። ያ ገላጭ ስብከት ነው፤ እግዚአብሔርም ተጠቅሞበታል። ከዕዝራ ረዳቶቹ ስብከት በኋላ፤ ሕዝቡ የዘጠኝ መቶ ዓመታትን ያለመታዘዝ እስራት ሰበረ፤ ከኢያሱ ዘመን ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ የዳስ በዓልን አከበረ (8፡13-17)።

ይህ በ1ጢሞ 4፥13 ላይ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እንዲጠቀምበት ያሳሰበው የስብከት ዓይነት ነው። "እስክመጣ ድረስ ለማንበብና ለመምከር ለማስተማርም ተጠንቀቅ።" ሂደቱ ምን ነበረ? ጢሞቴዎስ ሁሉም መስማት እንዲችሉ መጽሐፍ ቅዱስን ጮክ ብሎ ማንበብ ነበረበት። ከዚያም በግልጽ ማስረዳትና ማብራራት አድማጮቹም ቃሉን እንዲታዘዙት ማበረታታት ነበረበት።

ከየትኛውም የስብከት ዘዴ በላይ ገላጭ ስብከት ጉባኤው ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በቀጥታ እንዲገናኝ ያደርገዋል። ኃይል ያለውም እዚያ ነው። የእግዚአብሔር ቃል "መዳን ወደሚገኝበት ጥበብ" የሚመራ ነው። የእግዚአብሔር ቃሎች ለእግዚአብሔር የሚመች ሕይወትን ያመርታሉ። "በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነው።" (ዮሐ 17፥17)

የእግዚአብሔርን ቃል በማብራራት እና በመተግበር ላይ የማያተኩሩ ስብከቶች አቅም አልባ ስብከቶች ናቸው። ከእሳት ርቀህ ከተቀመጥህ፤ እሳቱ ሊያሞቅህ የሚችልበት ኃይል አይኖረውም፤ ነገር ግን ወደ ነበልባሎቹ ብትጠጋ ሙቀቱ ያገኝሃል። በተመሳሳይ መልኩ ሰባኪም በስብከቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባትን ባለማብራራት የክርስቶስን ሕዝብ የእግዚአብሔር እሳት ከሆነው ቃሉ ያርቀዋል። ሕዝቡ በቅዝቃዜ ይሞታሉ። ነገር ግን ሰባኪው በስብከቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በማብራራት ሕዝቡን ወደ ቃሉ የሚያስጠጋ ከሆነ፤ ገላጭ ስብከት ሕዝቡን ያሞቃል በመንፈሳዊ ሕይወትም ሕያው ይሆናሉ።

ኀጢአተኞችን ማዳን እና ቅዱሳንን ሊቀድስ የሚችለው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። አለማመን ጠንካራ አረም ነው፤ በሰባኪው ድምጽ አይጠወልግም፤ አይሞትምም። ሰይጣን ብርቱ ልዑል ነው። ሰባኪው አዝናኝ ታሪኮቹን ሲናገር አይፈራም። ሰባኪው ኃይለኛ ስብዕና ካለውና በእሁድ ስብከቱ በሚያሳምን መልኩ በተስፋ የተሞሉ እንፋሎት መሳይ ስብከቶቹን ቢያቀርብ ሕዘቡ ለጊዜውም ቢሆን ኀጢአተኝነታቸውን ይረሳሉ። ሆኖም የራስ ወዳድነት ፍላጎታቸው ከቀድሞ ይልቅ ብርቱ ሆኖ ይመለሳል። በሌላ በኩል የእግዚአብሔር ቃሎች ከሰባኪው ቃል እጅግ የላቁ ናቸው። የአለማመንን አረም ይነቅላሉ። ቃሎቹ የጨለማው ልዑልና የራስን ፍላጎት ይገድባሉ።

## ፈረሶችን እንዴት መመገብ እንደሚቻል

ልጅ ሳለሁ ወላጆቼ ብዙ ፈረሶች ነበሯቸው። በክረምት የኀይለኛ ቅዝቃዜ ወቅት፤ አባቴ ፈረሶቹ እንዳይጎዱ፣ እንዲወፍሩና እንዲጠነክሩ ጥራጥሬ ይመግባቸው ነበረ። ፈረሶቹም ያንን ይወዱ ነበረ። አባቴን ይከብቡትና ሰረቅራቃ ድምጻቸውን ያሰማሉ፤ በለስላሳ ከንፈሮቻቸው ከእጆቹ ጥራጥሬዎቹን ይወስዳሉ። ፈረሶች ብልህ ፍጥረታት ናቸው። የአባቴ እጆች ባዶ መሆናቸውን እንዳዩ፤ አባቴ ምግባቸው ወደሚገኝበት የመኖ ባልዲ እንደሚሄድና እህል ይዞላቸው እንደሚመጣ ያውቃሉ። ይህንን በማየት ፈረሶቹ ባዶ ቀኝ እጁን ችላ ማለትንና እህል የያዘውን ግራ እጁን ማየት ተምረዋል። ወደ መኖ ባልዲ ከገባው ግራ እጁ ሙሉ መኖ መግኘት ሲችሉ፤ ለምን ቀኙን በመላስ ይደክማሉ?

እንደሰባኪ፤ መጽሐፍ ቅዱስህን በአንድ እጅህ ይዘህ፤ ሕዝቡን ከሌላኛው እጅህ አትመግብ። መጽሐፍ ቅዱስ ከያዝክበት እጅ በቀጥታ መግባቸው፤ ከራሱ ከቃሉ። ፍሬ የሌለበት አረንጓዴ ቅጠል አትስጣቸው፤ ይልቅ ከቃሉ ምግብ ጋር በቀጥታ አገናኛቸው። ገላጭ ስብከት የሚሠራው ይህንን ነው። ለእግዚአብሔር ሕዝብ ገለባ መበተን ትተህ፤ እህል ስጣቸው።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ስበት

እግዚአብሔር ራሱ የተናገራቸውን ቃሎች ሳይጠቀሙ፤ ሰዎች የክርስቶስ ልብ እንዲኖራቸው የሚያስተምሩ ሰዎች ሞኞች ናቸው። ጆን ፓይፐር ሥነ መለኮታቸውንና ስብከታቸውን ግልጽ ባልሆነና ከቃሉ ጋር ባልተገናኘ መንገድ የሚወስዱትን ሰባኪዎች የገሰጹት ትክክል ነው።

> *“ስብከታቸውን እንድገመግም የምጠራባቸው ወጣት ሰባኪዎች ትልቁ ችግር የሚናገሩትን ነጥብ የሚያስረዳላቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ አለመጥቀሳቸው ነው። ሰዎች መጽሐፍ ቅዱሳቻቸውን እንዲከፍቱና በምንባባቱ ላይ ጣታቸውን እንዲያሳርፉ ማድረግ አለብን። የምንሰብክበትን ክፍል መጥቀስና ምን እያለም እንዳለ ማብራራት ይጠበቅብናል። የምናወራው ነገር በየትኛው ቁጥር ላይ እንዳለም መንገር አለብን። ሰዎች የሰባኪው ሀሳብ ከየትኛው ክፍል እንደሆነ በመፈለግ የሚደክሙ ከሆነ የመልዕክቱን ሀሳብ ያጣሉ።”*[4]

[4] John Piper, The Supremacy of God in Preaching (Grand Rapids: Baker, 1990), 41.

ምድር ያለማቋረጥ በጸሐይ ዙሪያ እንደምትሽከረከር ሁሉ፤ ስብከትህም በምንባብህ ላይ መሽከርከር አለበት። ቃሎችህ የእግዚአብሔርን ቃል የስበት ማዕከል መዝለል የለባቸውም። ስብከትህ የመጣው ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ሲረዱ፤ የሚሰሙህ ሰዎች የምኑሃል። በስብከቶችህ ንጉሱ የእግዚአብሔር ቃል ነው። በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱሶቻቸውን ማንበብ ይጀምራሉ። ገላጭ ስብከት ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው ዕለት ዕለት መጻሕፍትን የሚመረምሩ (ሐ. ሥራ 17፡11) ሰዎችን ያስገኛል።

ሸክላ ሰሪው በእጁ ያለውን ሸክላ እንደፈለገ አድርጎ እንደሚሰራው፤ ጥሩ ሰባኪ ስብከቶቹን የእግዚአብሔር ቃሎች እንዲቆጣጠሩት ይፈቅዳል። ነገሩ ዋልተር ካስር እንዳለው ነው “*በስብከታችን ውስጥ የመልዕክታችንን ይዘት፣ ምክንያትና እድገት በቀዳሚነት መወሰን ያለባቸው ቅዱሳት መጽሐፍት ናቸው።*”[5] ዒላማቸውን የሳቱ ስንት ስብከቶችን ነው የሰበክሀው ወይም የሰማሀው? በተነበበው የንባብ ክፍልና በስብከት መካከል ያለው ግንኙነት በጣም ደብዛዝ ከከፋ ደግሞ ፈጽሞ የሌለ ከሆነ፤ እግዚአብሔር ስብከትህን እንደራሱ አድርጎ አይወስድም። እግዚአብሔርን መስበክ የምትፈልግ ከሆነ፤ ስብከቶችህን የእግዚአብሔር ቃሎች እንደ ሸክላ ሰሪው አድርገው በሚቀርጹበት መንገድ አዘጋጅ። ይህ መጽሐፍ ስለዚህ ነው።

5 Walter Kaiser, Toward an Exegetical Theology (Grand Rapids: Baker, 1981), 160

# ምዕራፍ ሦስት

## መጽሐፍ ቅዱስ ፀሐያማ ነው ወይስ ጭጋጋማ?

የአንድን መጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ስዕላዊ ንድፍ ማውጣት ከመማራችን በፊት ሁለት መሠረታዊ ጥያቄዎችን መመለስ ያስፈልገናል።

- መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የሆነና ልንረዳው የምንችለው ዓይነት መልዕክት ነውን?
- ከሆነ እንዴት ነው የምንተረጉመው?

ከጥቂት ዓመታት በፊት በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የአንድ ትልቅ የወንጌላውያን ሴሚናሪ አስተዳደር ቦርድ፤ አዲስ የሴሚናሪ ፕሬዝዳንት ሾመ። በሚያሳዝን መልኩ፤ ብዙዎቹ የሴሚናሪው መምህራን በሴሚናሪው የእምነት አቋም መግለጫ በተቀመጠው አስተምህሮ አያምኑም፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶቹንም ማስተማር አቁመው ነበረ። ስለሆነም የፕሬዝዳንቱ የመጀመሪያ ሥራ የነበረው ከሥነ-መለኮት አንጻር ቤቱን ማጽዳትና ለዘብተኛ መምህራንን ማሰናበት ነበረ። አረም መንቀል።

አዲሱ ፕሬዝዳንት የቤት ሥራውን ለመሥራት የተከተለው ቀጥተኛውን መንገድ ነው። ከሁሉም መምህራን ጋር ተገናኘ ሁለት አማራጭም ሰጣቸው። በእምነት መግለጫው ከልብ አምኖ መፈረም አሊያም መልቀቅ። ይህ ግዴታ ሲቀርብላት አንዷ መምህርት እንዲህ አለች “እኔ ለዚያ የእምነት መግለጫ የፈለግሁትን ትርጉም መስጠት እችላለሁ ወይም እኔ የፈለግሁትን ማስባል እችላለሁ” አለች። ፕሬዝደንቱም “ከሥራሽ ተባርረሻል” አላት። መምህርቷም መልሳ “እኔን ልታባርረኝ አትችልም፤ በሴሚናሪው የሚያቆየኝ ውል አለኝ” አለች። ፕሬዝዳንቱም ቀዝቀዝ ብሎ መለሰላት፤ “እኔም ለውሉ የፈለግሁትን ትርጉም መስጠት ወይም እኔ የፈለግሁትን ማስባል እችላለሁ” አላት።

ያች መምህርት ንግግራቸው ለእርሷ እስከጠቀመ ድረስ ግልጽ እንዲሆን አልፈለገችም። የእግዚአብሔር ቃልና የትምህርት ቤቱ የእምነት አቋም በብዙ መንገድ ሊተረጎም እንዲችል ታምናለች። ነገር ግን ደመዎዟን የሚያስጠብቃት ውል ሲሆን፤ ቀጥተኛ፣ ትክክለኛ፣ ሰዋሰዋዊ፣ ታሪካዊ ዓላማ መር ትርጉም ትፈልጋለች። ለራሷና ለኮንትራቷ የምትሰጠውን ለእግዚአብሔር መስጠት አልፈለገችም።

እንደዚያ ዓይነት ሁለት አቋም መቀበል አንችልም። ትክክለኛ፣ መረዳት የምንችለውና አንድ ትርጉም ያለው ተግባቦት በሰው ዘር መካከል በየቀኑ ሊኖር እንደሚችል እንገምታለን። እግዚአብሔር ሲናገርም እንዲዚሁ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የፀሐይ ብርሃን ነው ወይስ ጭጋግ? ጨለማ ወይስ ብርሃን? ግልጽ ነው ወይስ ግልጽ ያልሆነ ውስብስብ? እንደ ሰባኪ መጽሐፍ ቅዱስ የምትከፍተው (ጠንካራ ሥራ ወይም ትጋት ቢጠይቅህም) እግዚአብሔር የተናገረውን ለመረዳት በማሰብ ነው? መጽሐፍ ቅዱስህን ስታጠና የእግዚአብሔርን ትርጉም ማግኘት ይቻላል? መጽሐፍ ቅዱስ በሁሉም ስፍራ ለሚገኙ ሁሉም ሕዝቦች አንድ ግልጽ ትርጉም አለው ለማለት በትንሹ ሰባት ምክንያቶች አሉት።

## 1) መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው እውነትን ለመግለጥ እንጂ ለመደበቅ አይደለም

እግዚአብሔር ቅዱሳት መጻሕፍትን የገለጠው ወንዶችና ሴቶች እንዲያነቡት፣ እንዲረዱትና እንዲታዘዙት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ እራሱ ይናገራል። ዳዊት "የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው....... ሕፃናትን ጠቢባን ያደርጋል።" (መዝ 19፡7) ብሎ ጽፏል። መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ለማድረግ እንጂ ለማወናበድ አልተጻፈም። እግዚአብሔር በኢሣይያስ እንዲህ ብሏል "በስውር ወይም በጨለማ ምድር ስፍራ አልተናገርሁም ለያዕቆብ ዘር። በከንቱ ፈልጉኝ አላልሁም እኔ እግዚአብሔር ጽድቅን እናገራለሁ ቅንንም አወራለሁ።" (ኢሳ 45፥19)፤ እግዚአብሔር የተናገረው ለመሰማትና እንዲረዱት ነው። ሙሴ ከመሞቱ በፊት እስራኤላዊያን እግዚአብሔርን ለመፈለግና ለመታዘዝ ሰማይ መሄድ ወይም ባሕር ማቋረጥ እንደማይጠበቅባቸው ተናግሮአል። የእግዚአብሔር ልብ በግልጽና ልንረዳው በምንችለው መንገድ የተቀመጠው በሕጉ ነው።

"እኔ ዛሬ የማዝዝህ ይህች ትእዛዝ ከባድ አይደለችም፥ ከአንተም የራቀች አይደለችም። ሰምተን እናደርጋት ዘንድ ስለ እኛ ወደ ሰማይ ወጥቶ እርስዋን የሚያመጣልን ማን ነው? እንዳትል በሰማይ አይደለችም። ሰምተን እናደርጋት ዘንድ ስለ እኛ ባሕሩን ተሻግሮ እርስዋን የሚያመጣልን ማን ነው? እንዳትል ከባሕሩ ማዶ አይደለችም። ነገር ግን ታደርገው ዘንድ ቃሉ በአፍህና በልብህ ውስጥ ለአንተ እጅግ ቅርብ ነው።" (ዘዳ 30፥11-14)

እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን የሰጠው እንድንረዳውና እንድንታዘዘው ነው፤ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን መተርጎም ከባድ ሥራ ነው፤ የማይቻል ግን አይደለም።[6] የእርሱ መናገር ዓላማ ሞኙን ጠቢብ ማድረግ፣ መደበቅ ሳይሆን እውነትን መግለጥ ነው።

[6] Dan McCartney and Charles Clayton, Let the Reader Understand: A Guide to Interpreting and Applying the Bible, 2nd ed. (Philipsburg, New Jersey: P & R Publishing 1994, 2002), 38-39.

### 2) እግዚአብሔር ፈጣሪም ተናጋሪም ነው

ግልጽና መረዳት የሚቻል መልዕክት ፍለጋ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ የምንመጣበት ሁለተኛው ምክንያት፤ እግዚአብሔር ፈጣሪም ተናጋሪም ስለሆነ ነው።[7] አንተን የፈጠረህ ያው እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን ተናግሯል። አድማጮችን የፈጠረው ተናጋሪ፤ ሰሚዎቹ ሊረዱት በሚችሉ መንገድ ይናገራል። "አቤቱ፥ መረመርኸኝ፥ አወቅኸኝም። ፍለጋዬንና ዕረፍቴን አንተ መረመርህ መንገዶቼን ሁሉ ቀድመህ አወቅህ።" (መዝ 139፥1፣3)። የሰውን ልጆችና አካሄዳቸውን የሚያውቅ ጌታ፤ እነርሱ የሚረዱትን መልዕክት መጻፍ ይችላል።

### 3) እስትንፋሰ መለኮት የትክክለኛ መልዕክት ዋስትና ነው

መጽሐፍ ቅዱስን ስታጠና የእግዚአብሔርን መልዕክት ማግኘትን ልትጠብቅ ትችላለህ፤ ምክንያቱም እስትንፋሰ መለኮት ለመልዕክቱ ትክክለኝነት ዋስትና ነውና። መጽሐፍ ቅዱስ በጠጠር የተሞላ ኩሬ አሊያም የሚያስተጋባ ነጎድጓድም አይደለም። እስከ እያንዳንዷ ቃል ድረስ ዘልቆ የእግዚአብሔርን ልብ የሚያሳይ መስተዋት ነው።

በ1ኛ ቆሮ 2፥10-12 ጳውሎስ የቃሉ እስትንፋሰ መለኮትነት ለቃሉ ትክክለኝነት እንዴት ዋስትና እንደሆነ ለማሳየት አራት ደረጃዎችን አስቀምጦልናል።[8] እግዚአብሔር አብ ሐሳቦቹን ከመግለጡ በፊት ያውቃቸዋል። እግዚአብሔር ሁሉን ስለሚያውቅና ስለማይዋሽ ሐሳቦቹ በፍጹም እውነት ናቸው። ጳውሎስ ሲናገር የእግዚአብሔር መንፈስ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር እንኳ ሳይቀር ይመረምራል። መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክ ስለሆነ ፤ የእግዚአብሔር አብን ሐሳብ ይረዳል።

ነገር ግን የእግዚአብሔር ሐሳቦች እንዴት ተጻፉ? በሦስተኛ ደረጃ መንፈስ የእግዚአብሔርን ሐሳብ ለሰዎች ገለጠ። "ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም" (2፡12)። ይህም ከእግዚአብሔር ወደ ጳውሎስ ቀጥተኛ መስመር ዘረጋ። ያው የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር እንኳ የሚመረምረው ያው መንፈስ ለጳውሎስ እነዚያን መልዕክቶች አድርሷል።

በአራተኛው የእስትንፋሰ መለኮት ደረጃ፤ ጳውሎስ የጻፈው ወይም የተናገረው እግዚአብሔር የተናገረውን፤ መንፈስ የመራውን መልዕክት ነው። ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ሐሳብ እንዳንጸባረቀ እርግጠና ለመሆን፤ መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስ የትኞቹን ቃላት መጠቀም እንደለበት ተናግሮታል። "መንፈሳዊውን ነገር

---

[7] 7 Francis Schaeffer, He is There and He is Not Silent (Wheaton, Ill.: Tyndale House Publishers, 1972), 72. In this vein, Schaeffer writes, "We are not surprised to find that there is a correlation between the observer and the observed because God made them to go together."

[8] 8 Walter Kaiser, Jr., "A Neglected Text in Bibliology Discussions: 1 Corinthians 2:6-16," Westminster Theological Journal 43 (Spring 1981): 302-319.

ከመንፈሳዊው ነገር ጋር አስተያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይህን ደግሞ እንናገራለን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አይደለም።" (1 ቆሮ 2፥13፤ 2ጴጥ 1፡20-21)። ለነቢያት ወይም ለቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎች የእግዚአብሔር መገለጥ የተሰጠው ይህንን በሚመስል ቀጥተኛ መንገድ ነው፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ጸሐፊዎቹ የሚጠቀሙትን ቃላት ወይም የሚጽፉትን ቃላት ሰጥቶአቸዋል፤ እንዲናገሩ በፈለገበት መንገድም እንዲናገሩ አድርጓቸዋል። እኛም የምንናገረው በሰው ጥበብ በታጨቁ ቃላት ሳይሆን፤ በእግዚአብሔር መንፈስ በተጻፉ ቃላት ነው።[9]

የዚህ አራተኛው ደረጃ ውጤት ምንድነው? በእርግጠኝነት እውቀት ነው። ጳውሎስ ስጽፍ "እኛ ግን ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም።" (2፡12) ብሏል። እስትንፋሰ መለኮት ወደ እግዚአብሔር መልዕክት እውቀት ይመራናል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር የተጠቀማቸውን ቃላት በመግለጥ የእግዚአብሔርን ሐሳብ ይገልጥልናልና።

### 4) በብሉይ ኪዳን የተሰጠው ትንቢት ተፈጽሟል

በብሉይ ኪዳን የተነገሩ ትንቢቶች መፈጸም ለሰባኪዎች መጽሐፍ ቅዱስ በዓላማ መተርጎም እንዲችሉ ማስረጃ ነው። ለምሳሌ ሚክያስ 5፥2 መሲሁ በቤተልሔም እንደሚወለድ ይናገራል። ይህ ትንቢት በማቴ 2፥4-6 ተፈጽሟል። ሚክያስ 5፥2 ለተለያዩ ሰዎች የተለያዩ ነገሮች አይደለም የሚናገረው። መሲሁ የሚወለደው በቤትሳሚስ፣ በቤቴል ወይም በቢታኒያ ነው አላለም። መሲሁ የሚወለደው በቤተልሔም ነው ነው ያለው። የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች መፈጸም መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽና ቀጥተኛ ትርጉም እንዳለው ያረጋግጡልናል።

### 5) የእግዚአብሔር መንፈስ የሰዎችን አእምሮ ያበራል

አምስተኛው መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል መተርጎም እንችላለን ያልንበት ምክንያት፤ የእግዚአብሔር መንፈስ የሰዎች አእምሮና ልብ ቅዱሳት መጽሐፍትን እንዲረዳ አብርሆት መስጠቱ ነው። ሐዋርያው ዮሐንስ መንፈስ ቅዱስ አማኞችን እንደሚያስተምርና አሳቾች በቀላሉ እንዳያታልሏቸው ብርሃን እንደሚሰጣቸው ይናገራል (1 ዮሐ 2፥26-27)። የመንፈስ ቅዱስ እርዳታ እኛን የተሳሳትን ተርጓሚዎች አያደርገንም፤ ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ በመለኮት የሚታገዝ ተግባር ስለሆነ፤ ከፍ ያለና ተጨባጭ ትክክለኝነት መጠበቅ ትችላለህ።[10]

---

9 Wayne Grudem accurately describes the process of inspiration when he writes, "When they actually came to the point of putting pen to paper, the words were fully their own words, but also fully the words that God wanted them to write, words that God would also claim as his own." Systematic Theology (Grand Rapids, Mich.: Zondervan Publishing House, 1994), 81.

10 McCartney, Let the Reader Understand, 74.

### 6) እግዚአብሔር የሚያስበውና የሚናገረው አይቃረንም

ለቅዱሳት መጻሕፍት አንድ ሊታወቅ የሚችል ትርጉም መኖር አለበት። ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚያስበው እና የሚናገረው ተቀራኒ አይደለም። አንድ ነገር የራሱ ተቃራኒ ሊሆን አይችልም። ተቃራኒ አስተሳሰብ የመጀመሪያው የአመክንዮ ህግ ነው። ሀ ያልሆነ ሀ ሊሆን አይችልም። ላም ፍየል ናትን? ውሻስ ድመት ነውን? ቀበሮስ አንበሳ ነው? በጭራሽ! አንድ ነገር ተቃራኒው ሊሆን አይችልም፤ ያ ተቃራኒ አስተሳሰብ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን ሲተረጉሙ ያ አስፈላጊ ነው። አንድ ነገር ተቃራኒው ሊሆን የማይችል ከሆነ፤ እንግዲያውስ መጽሐፍ ቅዱስ ለአንድ አውሮፓዊ አንድ ነገር እና ለአፍሪካዊ ሌላ ትርጉም ሊኖረው አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስ ላም ፍየል ወይም ውሻ ድመት ነው ከማለት የበለጠ ሁለት ነገር ማለት አይቻልም። ለምሳሌ አንድ ጥቅስ መዳን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ በጸጋ እንደሆነ ያስተምራል። መዳን በሥራ ነው ብሎ ሊያስተምር አይችልም። ምክንያቱም ሁለቱም ትክክል ሊሆኑ አይችሉም። እግዚአብሔርም እንዲህ ያስባል፡- “እኔ የምጽፍላችሁ እውነትን ስለማታውቁ አይደለም፤ ነገር ግን እውነትን ስለምታውቁቱና *ከእውነት ምንም ውሸት ስለማይወጣ* ነው።” (1 ዮሐንስ 2:21፣ አጽንዖት ተጨምሯል)። እግዚአብሔር ነገሮችን ስመለከት፤ ስህተት እውነት አይደለም።

አንድ ክበብ በዓይነ ሕሊናህ ይታይህ፤ በክበቡ ውስጥ እግዚአብሔር የሚናገረው ሁሉ አለ፡ ያለ ምንም ልዩነት እውነት ነው። ከክበቡ ውጭ ሁሉም ነገር አለ፣ እግዚአብሔር ከሚለው ጋር የማይስማማው ነገር ሁሉ አለ። በእግዚአብሔር ዘንድ ውስጥ እና ውጪ ያለውን የሚያገናኝ ምንም ነገር የለም። ውሸቶች እውነት አይደሉም፤ እውነቶች ውሸት አይደሉም። ብዙ የሚቃረኑ "እውነቶች" አሉ የሚለው ሃሳብ ብዙህነት/pluralism ይባላል።

እግዚአብሔር በብዙነት አያስብም። ለምሳሌ እግዚአብሔር ሁሉም ሃይማኖቶች እኩል ናቸው ብሎ አያስብም። እግዚአብሔር የሚያስበው ተቃራኒውን ነው፤ ክርስቶስ ብቸኛው የመዳን መንገድ ነው። ሁሉም ሌሎች መንገዶች ወደ ጥፋት ይመራሉ (ዮሐንስ 14:6፤ የሐዋርያት ሥራ 4:12)።

ጄይ አዳምስ “መጽሐፍ ቅዱስን በጥልቀት የሚያጠኑ ሰዎች ተቃራኒ አስተሳሰብን ያዳብራሉ፡- እነርሱ የሚያስቡት በንፅፅር ወይም በተቃርኖ ነው።"[11] ብሏል፤ ትክክል ነው። ይህ አስተሳሰብ በሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ይገኛል ማለት ይቻላል። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ተቃራኒዎች እውነት እና ስህተት፣ ጻድቃን እና ክፉዎች፣ ብርሃንና ጨለማ፣ ቅዱስና ርኩስ፣ ጥበብና ስንፍና …. ዝርዝሩ ማለቂያ የለውም።

---

[11] Jay Adams, A Call to Discernment (Eugene, Oregon: Harvest House, 1987; reprint, Woodruff, South Carolina: Timeless Texts, 1998), 29.

የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም የእግዚአብሔርን አስተሳሰብ የሚያንጸባርቅ መሆን አለበት። ለነገሩ መጽሐፉ እኮ የእርሱ ነው። አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ለአበበ አንድ ትርጉም፤ ለበቀለ ደግሞ ሌላ ትርጉም፣ ለአየለ ደግሞ ሌላ ትርጉም ሊኖራቸው አይችልም። የምዕራባውያን ትርጉም እና የአፍሪካ ትርጉም፣ የከተማ ትርጉም እና የገጠር ትርጉም የለውም። አንድ ክፍል ብዙ ዓይነት ተዛምዶ ሲኖረው ነገር ግን እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንድ ትርጉም ብቻ ነው ያለው። ይህን እግዚአብሔር በቃሉ እንድናውቀው የፈለገው አንድ ትርጉም በቃላት፣ በሰዋሰው እና አገባብ ላይ በመመስረት የሰውን ደራሲዎች ተጠቅሟል። የእግዚአብሔር መጽሐፍ በአንድ ምንባብ ለአንዱ ይህን ለሌለኛው ደግሞ ያንን ማለት አይችልም።

## 7) እግዚአብሔር እኛ መሥራት የምንችለውን ሊሰራ ይችላል

መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የተላከና ልንረዳው የምንችለውን መልእክት እንደያዘ እርግጠኞች መሆን እንችላለን ምክንያቱም እግዚአብሔር እኛ ማድረግ የምንችለውን ማድረግ ይችላል። እግዚአብሔር በምንረዳበት መንገድ የመናገር ችሎታ እንዳለው መካድ አንችልም፤ ምክንያቱም እኛ እራሳችን በየቀኑ ይህንን ችሎታ እንለማመዳለንና። ዛሬ ዛሬ በመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ወጥነት ላይኖር ይችላል የሚባል አባባል እየጨመረ መጥቷል ምክንያቱም ማንም ሰው (እግዚአብሔርን ጨምሮ) የሚናገረውን እርግጠኛ መሆን ስለማንችል ነው ይሉናል። ሆኖም ግን፤ ሁሉም የሰዎች ግንኙነቶች በሚገርም ሁኔታ እርስ በእርስ በመረዳታችን ላይ የተመሠረቱ ናቸው። እንደውም አንዳንዶቹ እንሚሉት ተግባቦቱ ግርዶሽ ቢኖርበት ኖሮ የዕለት ተዕለት የሰዎች ግንኙነት የማይቻል ይሆን ነበር።

የምትጠቀምበት ባንክ ሥራ አስኪያጅ አስር ሺ ብር ዕዳ እንዳለብህ ሲነግርህ፤ የሚናገራቸው ቃላቶች ምንም ግልጽ ትርጉም እንደሌላቸው ለመንገር ሞክር። የማይረባ ንግግርህን እንድታቆም እና እንድትከፍል ይነግርሃል።

የንግድ ኮንትራቶች፣ ቤት የሚሠሩ አሳይመንቶች እና ለቤተሰብ የሚደረጉ የስልክ ጥሪዎች ሁሉም ተጨባጭና ትክክለኛ ተግባቦቶች የተለመዱ እንደሆነ ይገምታሉ። አንዱ አንዱን አለመራዳት የሚከሰት ነው (አንዳንዴ በተደጋጋሚ) ነገር ግን ለሚስትህ የሚቀጥለው ማቅሰኞ ቤት እንደምትመለስ ብትነግራት፤ እርሷ አንተን የምትጠብቀው ማቅሰኞ ነው፤ ሐሙስ አይደለም። ሰዎች ምንም ይበሉ ምን፤ የእለት ተዕለት ሕይወታችን የሠመረው አንዳችን እንዳችንን መረዳት የምንችልበት ተግባቦት ስላለ ነው።

የሚገርመው ነገር አንዳንድ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር የተግባበት አቅሙ ከእነርሱ እንደሚያንስ አድርገው ማመናቸው ነው። እነዚህ ሰዎች በየእለቱ ቤተሰቦቻቸውና ጓደኞቻቸው እንደሚረዷቸው ያስመስላሉ ቢሆንም እግዚአብሔር እንደ እነርሱ በግልጽ እንደሚናገር ለማመን ያቅማማሉ።

በመዝ 50፥21 እግዚአብሔር ክፉውን የሚወቅሰው “እንደ አንተ የሆንሁ መሰለህ” ብሎ ነው። የሚያሳዝነው በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ የጠቀስኳት የሴሚነሪ መምህርት እንኳ ይህንን ስህተት አልሰራችም። ዛሬ ዛሬ በስፋት እንደሚታየው፤ እርሷም እንደሌሎቹ እግዚአብሔርን ከራሷ በታች አስቀምጣለች። እርሷ እግዚአብሔርን የሳለችው፤ ደካማና ግልጽ መልዕክት ለማስተላለፍ ብቃት የሌለው አድርጋ ነው። ነገር ግን ሁሉን አዋቂው፣ በሁሉም ቦታ የሚገኘው አምላክ ግልጽና መረዳት የምንችለውን መልዕክት መናገር አይችልም ብሎ ማሰብ እግዚአብሔርን መሳደብ ነው።

ለግል ጥናትህም ሆነ ለስብከት ለመዘጋጀት መጽሐፍ ቅዱስህን ስትከፍት፤ የእግዚአብሔር መልዕክት የሚገኝ እንደሆነ ማመን ትችላለህ። መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው እውነትን ለመግለጥ እንጂ ለመሰወር አይደለም። ሁሉን በሚያውቀው በእግዚአብሔር የተጻፈ ትክክለኛ መልዕክት ነው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽና መረዳት የምንችለው ከእግዚአብሔር የተላከ መልዕክት ቢሆንም መተርጎምን ይፈልጋል። የእግዚአብሔርን መልዕክት ለመተርጎም ተዓማኒ መመሪያዎች ምንድናቸው?

# ምዕራፍ አራት

# መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት እንተርጉም

እግዚአብሔርን ለመስበክ፤ ለእግዚአብሔር ማጥናት አለብህ። ነገር ግን ባለፉት ዘመናት አንዳንድ ሰባኪዎች ለእግዚአብሔር ከመስበክ የሚያርቋቸውን የጥናትና የአተረጓጎም ዘዴዎች ሲለማመዱ ነበረ። ከዚህ በታች እነዚህን ልናስወግዳቸው የሚገቡ ሁለት ዘዴዎች እንመለከታለን።

## ድብቅ ትርጉም የመፈለግ ዘዴ

አላጎሪ ወይም ድብቅ ትርጉም መፈለግ ማለት በአንድ ምንባብ ውስጥ ገጸ-ባህሪያቱ፣ ክስተቶቹ ወይም ሌሎች ባህሪያቱ የተደበቁ፣ ቀመራዊ ወይም ምሳሌያዊ ትርጉሞች አሏቸው ማለት ነው።[12] ለምሳሌ፣ በማቴዎስ 13፥3-9 ያለው የዘሪው ምሳሌ፣ ክርስቶስ ተኮር አላጎሪ ነው። በምሳሌው ላይ ኢየሱስ ዘሩ ወንጌልን፣ ወፎች ሰይጣንን፤ አፈሩ ደግሞ የተለያዩ ዓይነት ልቦችን እንደሚወክል ተናግሯል። ኢየሱስ በምሳሌው ላይ ያሉ ገፀ-ባህሪያቱ ተምሳሌታዊ ትርጉሞች እንዲኖራቸው አስቦ ነበር። ይህን በ13፡18-23 ነግሮሃል። አብዛኛውን ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲዎች ለምሳሌዎቻቸው ትርጉሙን ያብራራሉ፤ ያንን የሚያደርጉት ምሳሌውን በመገመትና በመላ ምት እኛ እንዳንደክም ነው።

አንዳንድ ሰባኪዎች ግን ሁሉንም መጽሐፍ ቅዱስ በአላጎሪ ወይም ድብቅ ትርጉም በመፈለግ መተርጎም ይፈልጋሉ። ይህንንም ለማድረግ የአንድን ክፍል ግልጽና ታሪካዊ ትርጉም ትተው፤ በምንባቡ ክፍል ውስጥ ያለውን ነገር በአእምሮአቸው ከምስሉት አንድ የክርስቲያኖች ልምምድ ወይም ስነ መለኮታዊ ሐሳብ ጋር ያገናኛሉ። ለምሳሌ አንድ ሰባኪ አንድ ጊዜ በሉቃስ 10 የሚገኘውን የደጉ ሳምራዊ ምሳሌ ለመፍታት የሚከተለውን ግምት ተጠቅሟል። በወንበዴዎች የተመታው መንገደኛ ደህንነት የሚፈልግ ተጓዥ፣ ሰውየውን የደበደቡ ወንበዴዎች ሰይጣን ሰውየው ወደ ድነት እንዳይደርስ የሚያደርገውን ተቃውሞ ይወክላል፣ ደጉ ሳምራዊ ለዚያ ለተጎዳው ሰው የቀባው ዘይትና ወይን መንፈስ ቅዱስንና የኃጢአት ይቅርታን ይወክላል፤ አህያው ወንጌልን ይወክላል ምክንያቱም ሰውየውን ወደ ተሸለ ቦታ ያመጠው አህያ ስለሆነ ሰውየውን ወንጌል ወደ ቤተ-ክርስቲያን ማምጣቱን ይወክላል።

---

12 Roy B. Zuck, Basic Bible Interpretation: A Practical Guide to Discovering Biblical Truth (Colorado Springs, Colorado: Victor, 1991), 221.

ይህ አተረጓጎም የሰውን ብልጠት ለማሳየት ሲል ኢየሱስ ምሳሌውን የነገረበትን ግልጽ ዓላማ ችላ ብሏል። ኢየሱስ “ለመሆኑ ባልንጀራዬ ማንነው?” (ሉቃ 10፥29) የሚለውን ጥያቄ እየመለሰ ነበረ። እርሱ ስለ ድነት ሂደት እያስተማረ አልነበረም። በኢየሱስ ዓላማ በማተኮር ፈንታ፤ ሰባኪው ለክፍሉ የራሱን ትርጉም አሰበ። የእርሱ አተረጓጎም ግላዊ ነው እርሱ ብቻ ሊያየው የሚችለው። ለመጨረሻ ጊዜ ሉቃስ 10ን ስታነብ የሳምራዊው አህያ ወንጌል እንነበረ አስበህ ነበረ? በእርግጠኝነት ሰባኪው የሰበከው የራሱን ምሳሌ ነው፤ የኢየሱስን አይደለም።

በድብቅ ትርጉም ፈላጊ አተረጓጎም ላይ እንደሚደረጉት ሙከራዎች ሁሉ፣ ከላይ ያለው ሙከራም አይሰካም ምክንያቱም በዚያ የደጉ ሳምራዊ ምሳሌ ኢየሱስ የምሳሌው ዝርዝር ሁኔታ ያ ትርጉም እንዲኖረው አስቦ እንደሆነ ማንም እርግጠኛ መሆን ስለማይችል ነው። በተጨማሪም፤ እነዚያን ትርጉሞች ከተቀበላችሁ፣ ለምን ሌሎች አይሆኑም? እንዴት የተደበደበው ሰው ክርስቶስን በመስቀል ላይ ሊወክል አይችልም? ወይንስ የክርስቶስን ደም ሊያመለክት አይችልም እንዴ? ማረፊያው ደግሞ ሰማይን ይወክላል? የምናብ ጨዋታን እስከተጫወትን ድረስ ለምን ቆመ?

አላጎሪያዊ ትርጓሜ ለእግዚአብሔር ማጥናት አይደለም ምክንያቱም ወሰን የለውም፤ ገደብ የለውም። እሱ ከቁጥጥር ዉጪ የሆነ የሰው ምናባዊ ዓለም ነው። በመጨረሻ፣ ኢየሱስ የደጉ ሳምራዊ ምሳሌ የተለየ ትርጉም እንዲኖረው እንደፈለገ ለማመን ምንም ምክንያት የለንም። የምሳሌው ግልጽ ትርጉም ጠላቶቻችሁን ወደዱ፤ ጠላቶቻችሁን እንኳ ቢሆን በፍቅር ያዙ የሚል አይደለምን፤ ይህ በቂ አይደለምን?

ስለ ኃጢአተኞች፣ ስለ ክርስቶስ፣ ይቅርታ፣ ወንጌል እና ቤተ-ክርስቲያን መስበክ ከፈለግህ፤ ይህንን ርዕስ የሚዳስሱ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ፤ ነገር ግን የደጉ ሳምራዊ ምሳሌ ከእነዚህ ክፍሎች አንዱ አይደለም። ለእግዚአብሔር የሚሰብኩ ሰባኪዎች፤ ክፍሉ ሲጻፍ እግዚአብሔርና የሰው ደራሲዎች ክፍሉ እንዲያስተላልፍ የፈለጉትን ዓላማ ይሰብካሉ እንጂ የራሳቸውን አእምሮ ወለድ ምክንያት አይሰብኩም።

## የመንፈስ ቅዱስ ዘዴ

አንዳንድ ሰባኪዎች አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ያነቡና፤ ምንም ጥናት ሳያደርጉ መንፈስ ቅዱስ ወደ ትክክለኛው ትርጉም ይመራናል ብለው በማመን በግምት ትርጉም ይሰጣሉ። ታሪካዊ አውዱን ችላ ይላሉ። በነበቡበት ክፍል ያሉትን የቅርብ ዐውድ ምንባባት ይዘነጋሉ። ክፍሉ ለሙሴ፣ ለማርቆስ፣ ለጳውሎስ ምን ማለት እንደነበረ ይዘነጋሉ፤ ለመለኮታዊና ለሰው ደራሲዎች ምን ማለት እንደነበሩ ይዘነጋሉ። ማንኛውም ክፍሉን

ሲያነቡት ወደ አእምሮአቸው የሚመጣው ነገር ትክክለኛ ትርጉም እንደሆነ ያምናሉ። ይህ ለእግዚአብሔር ማጥናት ነውን?

ይህንን መንገድ የሚከተሉ ሰባኪዎች እንደዚያ ያምናሉ። አብዛኛውን ጊዜ ልምምዳቸውን የሚከላከሉት ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የገባውን ተስፋ በመጥቀስ ነው። *"አሳልፈውም ሲሰጡአችሁ፥ የምትናገሩት በዚያች ሰዓት ይሰጣችኋልና እንዴት ወይስ ምን እንድትናገሩ አትጨነቁ፤ በእናንተ የሚናገር የአባታችሁ መንፈስ ነው እንጂ፥ የምትናገሩ እናንተ አይደላችሁምና።"* (ማቴ 10፥19-20)። ይህንን ዘዴ የሚከተሉ ሰዎች በትጋት ስለማጥናት ሲነሳ ይበሳጫሉ፤ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንናገራለን ብላችሁ አትጨነቁ ስለሚል፤ መንፈሳዊ ሰው ምን እናገራለሁ ብሎ መጨነቅ የለበትም፤ ልክ መድረክ ላይ እንደወጣ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠውን ትርጉም መጠበቅ አለበት ብለው ስለሚያምኑ።

በማቴዎስ 10 ኢየሱስ ባታጠናም እንኳ እሁድ ጠዋት ለስብከት ወደ መድረክ ስትወጣ የእግዚአብሔር መንፈስ ለምትሰብከው ክፍል ትክክለኛ ትርጉም ይሰጠሃል ብሎ ቃል ገብቷልን? ይህንን ለማወቅ ከማቴ 10፡19-20 ቀድመው ያሉ ጥቅሶች ይረዱሃል። ኢየሱስ ለገባው ተስፋ ቅድመ ሁኔታውን ያስቀመጠው በሚከተሉት ቃላት ነው። *"ነገር ግን ወደ ሸንጎ አሳልፈው ይሰጡአችኋል፥ በምኩራቦቻቸውም ይገርፉአችኋልና ከሰዎች ተጠበቁ፤ ለእነርሱና ለአሕዛብም ምስክር እንዲሆን፥ ስለ እኔ ወደ ገዥዎች ወደ ነገሥታትም ትወሰዳላችሁ። አሳልፈውም ሲሰጡአችሁ"* (ማቴ 10፡17-19ሀ)።

ወንጌልን በአንደበተ ርቱዕነት፣ በትክክልና በኃይል ለመስበክ የማታጠናበት ጊዜ አለ። ኢየሱስ እንዳለው ከሆነ መቼ ነው? አሳዳጆቻችሁ መጽሐፍ ቅዱሶቻሁን ከእጃችሁ ነጥቀው እናንተን እስር ቤት ሲወረውሩ፣ በጭካኔ ከመገረፋችሁ የተነሳ ማሰብ ሲከብዳችሁ፤ በእነዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ስለ እምነት እንድትናገሩ ወደ ፍርድ ሸንጎ ሲያቀርቧችሁ፤ "በዚያች ሰዓት የምትናገሩት ይሰጣችኋል" ነው የኢየሱስ ተስፋ። በክርስቶስ ኢየሱስ ምክንያት በከባድ መከራ ውስጥ እያለፍክ፤ የተደራጀ ሙግት ለማቅረብ በማትችልበት ሁኔታ ውስጥ ካለህ፤ በዚያች ሰዓት መንፈስ ቅዱስ አንተን ሉተር፣ ካልቪን፣ ዋይትፊልድ፣ ስፖርጅን እና ሌሎች በታሪክ ተዋቂ ሰባኪዎችን በአንዴ የያዝክ ነበልባል ያደርግሃል። በዚያች ሰዓት መንፈስ ቅዱስ መልዕክት ይሰጠሃል። ታዲያ ይህ በሰላማዊ ቀጠና ከምታገለግለው አገልግሎትና ለእሁድ ስብከት ከመዘጋጀትህ ጋር ምን ያገናኘዋል? ምንም!

የእግዚአብሔር መንፈስ ልዩ በሆኑ ሁኔታዎች ልዩ መንገዶችን ይጠቀማል፤ በመደበኛ ሁኔታዎች ደግሞ የተለመደ መንገድ፤ በትጋት የተሞላ ጥናት። ስድራቁ ሚሳቅና አብድናጎ ብትሆኑና ንጉሱ ላቆመው ምስል እንደማትሰግዱ

መንገር ቢጠበቅባችሁ፤ ወደ እቶኑ እሳት ከመጣላችሁ በፊት፤ የተዋጣለት ስብከት ለማዘጋጀት 15 ሰዓታት ባይኖራችሁም እንኳ መንፈስ ቅዱስ የምትሉትን ትክክለኛ ቃል ይሰጣችኋል። ነገር ግን መንፈስ የሚሰጣችሁ በሰላሙም ጊዜ እግዚአብሔርን እንደምታከብሩበት ዓይነት ቃል ነው። “የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፣ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ” (2 ጢሞ 2፥15)። ሰባኪዎች በእግዚአብሔር መንፈስ መደገፍ አለባቸው፤ ነገር ግን በማጥናት ምትክ ሳይሆን በትጋት እያጠኑ በእግዚአብሔር መንፈስ መደገፍ አለባቸው።

ስውር ትርጉም ፍለጋ የሚደረገው አላጎሪያዊ ትርጉምም ሆነ የመንፈስ ቅዱስ ዘዴ የሚባለው የአተረጓጎም ዘዴ እግዚአብሔርን መስበክን ሊያፈራ አይችልም። በአንዱ የአንተን ድብቅ ምናብ፤ በሌላኛው ደግሞ ግምት ነው የምትሰብከው። እግዚአብሔር የእኔ ነው የሚለው ዓይነት ስብከት ለመስበክ ከፈለግህ ሌላ ዓይነት የአተረጓጎም ዘዴ መከተል አለብህ።

## አስረ ሁለቱ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም መርሆዎች

ለእግዚአብሔርን መስበክ ለእግዚአብሔር ማጥናትን የሚጠይቅ ሂደት ነው። ግን ምስጢራዊ ሂደት አይደለም። ለመለኮታዊ እርደታ በመጸለይ የሚጀምር ነው፤ የመዝሙራኛውን ጸሎት በማስተጋባት። “ከሕግህ ድንቅ ነገርን አይ ዘንድ ዓይኖቼን ክፈት” (መዝ 119፡18) በማለት። እጅግ አስፈላጊ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስን እርዳታ ፈልግ፤ ያለማቋረጥ መፈለግ፤ ከዚያም ሁለት ጊዜ ለክቶ አንዴ የሚቆርጥ ጎበዝ አናጺ ትሆናለህ። የሚለካ እና አንድ ጊዜ የሚቆርጥ አናጺ። ቃላቱን ቀጥ ለማድረግ እየጣርክ አንብብ። ቅዱሳት መጻሕፍት ስታነብ ቃለቶቹን፣ አረፍተ ነገሮችንና አንቀጾችን አጣምመህ ለመቁረጥ የምትሞክር ከሆነ መቼም ለእግዚአብሔር አትሰብክም። ቀጥ አድርገህ ቁረጥ፤ እግዚአብሔርም ድምፅህን የእርሱ ድምፅ ያደርጋል።

እንዴት ነው ለእግዚአብሔር የምታጠናው? በሚገርም ሁኔታ መልሱ ቀላል ነው። መጽሐፍ ቅዱስህን በተቻለህ መጠን በጥንቃቄ አንብብ። መጽሐፍ ቅዱስህን ስታጠና እስትንፋ መለኮት ያለበት መሆኑን ሳትዘነጋ፤ እጅግ ጠቃሚ ጋዜጣ፣ የህክምና መረጃ ያለው ወረቀት ወይም ጠቃሚ ሕጋዊ ሰነድ እንደምታነብ ማንበብ አለብህ። ደራሲው የተጠቀማቸውን ቃላት መሠረት በማድረግ ማለት የፈለገውን ይበል።የደራሲውን አመክንዮ ፍሰት ተከተል። ምናባዊ፣ ምሳሌያዊ፣ ግላዊ ትርጉሞችን አትፈልግ። ትርጓሜውን ዐውደ ምንባቡ ያሳውቅህ።

የሚከተሉት አስራ ሁለቱ መርሆች በጣም አስፈላጊ፣ ረጅም ጊዜ ስምምነት የተደረገባቸው መመሪያዎች ናቸው። ለጥንቁቅ፣ ትርጉም አዘልና ጠቢብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጓሜ የሚረዱ ህጎች ናቸው። የእነዚህ መርሆች

ጥናት ሥነ-ትርጓሜ ወይም ሥነ-አፈታት ይባላል (ሄርሜንዮ ከተሰኘው የግሪክ ግሥ የተወሰደ ሲሆን ፍቺውም ለመተርጎም ማለት ነው)። እነዚህን መመሪያዎች ከተከተልክ፤ ለእግዚአብሔር በማጥናት ሂደትህ ጥሩ ትሆናለህ።

እነዚህ የሥነ-አፈታት/ትርጓሜ መርሆች ሁለት ምንጮች አሏቸው፡- አንደኛ መግባባት ያስቻሉን የዕለት ተዕለት፣ አስተዋይ የቋንቋ ደንቦች፣ ሁለተኛ የእግዚአብሔር ባሕርይ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፤ እግዚአብሔር በሰው ቋንቋዎች ተናግሯል፤ ስለዚህ እርሱን ለመረዳት የቋንቋውን ህግጋት እንከተላለን። ግን እንዲህ ስናደርግም የተናገረው እግዚአብሔር መሆኑን ፈጽሞ አንረሳውም። ሁለቱንም እውነታዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት የሚከተሉትን አስራ ሁለት የትርጓሜ ህጎችን ከራስህ ጋር አዋህድ።

## 1) የመጽሐፍ ቅዱስ ግልጽነት

መጽሐፍ ቅዱስ መረዳት የምንችለው መጽሐፍ ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር እንድንረዳው ነው የተናገረው።[13]

> “ሰማያትን የፈጠረ እግዚአብሔር፥ እርሱም ምድርን የሠራና ያደረገ ያጸናትም፥ መኖሪያም ልትሆን እንጂ ለከንቱ እንድትሆን ያልፈጠራት አምላክ፥ እንዲህ ይላል። እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔም በቀር ሌላ የለም። በስውር ወይም በጨለማ ምድር ስፍራ አልተናገርሁም ለያዕቆብ ዘር። በከንቱ ፈልጉኝ አላልሁም እኔ እግዚአብሔር ጽድቅን እናገራለሁ ቅንንም አወራለሁ።” (ኢሳ 45፥18-19)
>
> “ምሥጢሩ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው የተገለጠው ግን የዚህን ሕግ ቃሎች ሁሉ እናደርግ ዘንድ ለእኛ ለዘላለምም ለልጆቻችን ነው።” ዘዳ 29፥29

ለእግዚአብሔር ማጥናት የሚጀምረው እግዚአብሔር እንድንረዳውና እንድንኖረው ቃሉን እንደገለጠ በማሰብ ነው። ሙሴ እንደተናገረው የተገለጡት ነገሮች ማለትም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት የእግዚአብሔር ቃላት ለእኛ ናቸው። ይህም ማለት ወጥ የሆነ መረዳት የሚቻለውን መልዕክት ፍለጋ የእግዚአብሔርን ቃል ታጠናለህ ማለት ነው። ዋይን ግሩደም እንዲህ ሲል ጽፏል፡- “የመጽሐፍ ቅዱስ ግልጽነት ማለት መጽሐፍ ቅዱስ

13 McCartney, Let the Reader Understand, 38-39.

የእግዚአብሔርን ርዳታ ለመፈለግና ቃሉን ለመከተል ፈቃደኛ የሆኑ ሁሉ ስለምን እንደሚያስተምር ሊረዱት በሚችሉበት መንገድ መጻፉ ነው።"[14]

የመጽሐፍ ቅዱስ ግልጽነት ማለት ሁሉም የቅዱሳት መጻሕፍ ክፍሎች ለመተርጎም ቀላል ናቸው ማለት አይደለም። ሐዋርው ጴጥሮስ እንኳ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰፈሩ ነገሮች ሁሉ በእኩል ለመረዳት አስቸጋሪ መሆናቸውን አስገንዝቧል (2 ጴጥ 3፥15-16)። ስለዚህ ከሥነ-መለኮት አኳያ ግልጽ ያልሆነ ምንባብ ሲያጋጥምህ፤ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለዚህ ጉዳይ በግልጽ የሚናገሩባቸውን ክፍሎች አስቀድመህ እይ። ቢሆንም፤ የተርጓሚው ግምት ሁል ጊዜም ቢሆን እግዚአብሔር ቅዱሳት መጻሕፍትን የተናገረው እንድንረዳው ነው። እውነትን ለመግለጥ እንጂ ለመደበቅ አይደለም።

## 2) የመገለጥ/ አስተርዮ ማረፊያ

ማስማማት ማለት አንድን በተለምዶ የምታደርገውን ነገር ከአንድ ውስን ሁኔታ ጋር እንዲስማማ ማስተካከል ማለት ነው። ለምሳሌ በተለምዶ በአማርኛ የሚሰብክ ሰባኪ በጉባኤው ውስጥ እንግሊዝኛ ተናጋሪ እንግዶች ቢኖሩ፤ ስብከቱን ወደ አማርኛ በማስተርጎም ከስብከቱ ጋር ማስማማት ይችላል። አማርኛ የማይሰሙ ጎብኚዎች ባሉበት ጉባኤ በአማርኛ ብቻ ከመስበክ በሚረዱበት ቋንቋ ስብከቱን በማቅረብ በጸጋ ያስተናግዳቸዋል።

እግዚአብሔርም እንዲሁ ያደርጋል። እርሱ መንፈስ ነው። እኔና አንተ መረዳት በማንችልበት መንገድ መናገር ይችላል። ነገር ግን ለጥቅማችን ሲል እግዚአብሔር መረዳት በምንችለው መልኩ ራሱን መግለጥን መረጠ።[15] ለምሳሌ ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉት በሚታወቁ የሰው ልጆች ቋንቋ ነው። በዕብራይስጥ፣ ትንሽ በአረማይክ እና በግሪክ። እኛም ምንም በማናውቀው አንዳንድ የሰማይ ቋንቋዎች አይደለም።

የመገለጥ መስማማት ወይም መስተንግዶ ማለት እግዚአብሔር መለኮታዊ ጽንሰ-ሀሳቦችን ሲናገር ከራሳችን ጋር ልናገናኘው በምንችለው መንገድ ይናገራል ማለት ነው። ለምሳሌ 2ኛ ዜና 16:9 እንዲህ ይላል "እግዚአብሔር ልቡ በእርሱ ዘንድ ፍጹም የሆነውን ያጸና ዘንድ ዓይኖቹ በምድር ሁሉ ይመለከታሉና" እግዚአብሔር አብ የስጋ ዓይኖች አሉት ማለት ነው? የሉትም። ሌሎች ጥቅሶች እርሱ የማይወሰን መንፈስ እንደሆነ ይነግሩሃል (ዮሐንስ 4፡24)። ታዲያ ለምን እግዚአብሔር ስለ ዓይኖቹ ይናገራል? እግዚአብሔር ዓይን ለሰው ልጅ እጅግ ወሳኝ የስሜት ሕዋስ እንደሆነ ያውቃል፤ ስለዚህ ገደብ የለሽ የማስተዋል ችሎታውን አንተ በምትረዳበት መንገድ

---

14 Grudem, Systematic Theology, 108

15 Bernard Ramm, Protestant Biblical Interpretation: A Textbook of Hermeneutics, 3rd rev. ed. (Grand Rapids, Mich.: Baker Book House, 1970), 99-100.

ይገልፃል። ትንሹ ነገር (የሰው እይታ) እጅግ የላቀውን ነገር (ሁሉን ቻይ የሆነውን የእግዚአብሔርን የማስተዋል ችሎታ) እንድትረዳ ያግዝሃል።

እግዚአብሔር "የእግዚአብሔር እጅ" ብሎ ሲናገር ተመሳሳይ ማረፊያ ወይም ማስማሚያ አድርጓል። እግዚአብሔር አብ እጅ አለው? በፍጹም። ግን ለእኛ እጆች ኃይልን ማለትም አንድን ነገር የመያዝ ችሎታን እንደሚያመለክቱ ያውቃል። ይህንን ስለሚያወቅ እግዚአብሔር የእርሱን ገደብ የለሽ ሐይል እንደ እጁ በጸጋ ይገልጸዋል። ይህ ማረፊያ ነው። ልክ አንድ ትልቅ ሰው ህጻን እነንደሚያናግር፤ እግዚአብሔር በእኛ ደረጃ ጐንበስ ብሎ እኛ በምንረዳው መንገድ ራሱ ይገልጣል።

### 3) የቅዱሳት መጻሕፍት ስምምነት

መጽሐፍ ቅዱስ በ1,500 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ከሠላሳ በላይ በሆኑ የሰው ደራሲያን የተፃፈ ቢሆንም፣ ከራሱ ጋር ይስማማል። በየትኛውም ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሰላሳ ሰዎች ሲጽፉ እርስ በርሳቸው ፍጹም እንደሚስማሙ መገመት ትችላላችሁ? ርዕሰ ጉዳዩ ሃይማኖት ቢሆንስ? እና አንዳንዶቹ ከአንድ ሺ ዓመታት በፊት የኖሩ ቢሆኑስ? የመጽሐፍ ቅዱስ ሥነ-መለኮታዊ ስምምነት አስደናቂ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት የሰዎች ደራሲዎች ጀርባ አንድ መለኮታዊ ደራሲ እንዳለ ስታስታውስ ስምምነቱ በጣም አስደናቂ አይደለም። ምክንያቱም ቅዱሳት መጻሕፍት የተነገሩት ሁሉን በሚያውቅ እና በማይዋሽ አምላክ ነው። መጽሐፍ ቅደስ ከራሱ ጋር ይስማማል፤ ከራሱ ጋር አይቃረንም።

የቅዱሳት መጻሕፍት ስምምነት መሠረታዊ አስተምህሮ ነው። ግን አላግባብ ልንጠቀመው እንችላለን። አንዳንድ ጊዜ ሰባኪዎች አንድን ክፍል መሠረት በማድረግ በሚያምኑትን ነገር ይወሰኑና እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከእነርሱ ምልከታ ጋር እንዲስማማ ለማድረግ መዶሻና ሙጫ ይጠቀማሉ። በአንድ ጽሑፍ ይወስናሉ ከዚያም መዶሻ እና ሙጫ ይጠቀማሉ። በጭራሽ እንደዚያ አታድርጉ። እያንዳንዱ ምንባብ እግዚአብሔር የተናገረውን ይበል፤ ከዚያም በመጨረሻም እርስ በእርሱ ይስማማ። አንዳንድ ጊዜ ሁለት የተለያዩ ክፍሎች ሁለት የተለያዩ ነገር ግን እኩል የሆኑ እውነቶችን ያስተምራሉ (ለምሳሌ እንደ ክርስቶስ ፍጹም አምላክነት እና ፍጹም ሰውነት ያሉ ርዕሶችን)። ሁለቱም ክፍሎች እንዲናገሩ እንፍቀድ። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ መለኮታዊ ደራሲ ስላለው፣ ሥነ-መለኮታዊ ስምምነትን ለማግኘት እየጠበቅን ወደ እርሱ እንምጣ፤ በእርግጥ ይህን እናድርግ።

## 4) መደበኛ ትርጓሜ

በመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ሂደት አብዛኛውን ጊዜ የሰዎች ትልቁ ችግር መጽሐፍ ቅዱስን ባልተለመደ መንገድ ማንበብ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ሲከፍቱ ስለማንበብ የተማሩትን ሁሉ የረሱ ያህል ነው። ዐውዱን ችላ ይላሉ፤ ምስጢራዊና ግላዊ ትርጉሞችን ይፈልጋሉ። በሌላ ጎኑ መደበኛ አተረጓጎም ማለት መጽሐፍ ቅዱስህን ልክ ሌላውን ጠቃሚ መጽሐፍ የምታነበብበትን ልምድ በመከተል ማንበብ ነው።[16]

አንድ የት/ቤት ርእሰ መምህር ለት/ቤቱ የጥገና ባለሙያ በክፍል ቁጥር አስራ አንድ ውስጥ የተበላሸውን የመብራት ፍሎረሰንት ቀይር ብሎ መመሪያ ብጽፍ፤ ይህ ለጥገና በለሙያው አስፈላጊ ሰነድ ነው። እንደነዚህ ያሉትን ችግሮች ማስተካከል የእርሱ ሥራ ነው። የጥገና በለሙያው ሰው ምን ያደርጋል? እርሱ በርዕሰ መምህሩ ማስተወሻ ላይ ምስጢራዊ የሆነ ትርጉም አያነብም፤ የየትኛው ክፍል መብራት እንደተቃጠለ ለማወቅ መመሪያውን በመደበኛ መንገድ እና በጥንቃቄ ያነባል፤ ከዚያም አዲስ አምፖል ለሚያስፈልገው ክፍል ይገጥማል። ይህ የተለመደ ትርጓሜ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳችንን በተመሳሳይ መንገድ ማንበብ ያስፈልገናል።

አንዳንድ ጊዜ ይህ መጽሐፍ ቅዱስን የመተርጎም አካሄድ ቀጥተኛ አተረጓጎም ተብሎ ይጠራል። ቃላቶቹን በቀጥታ ትወስድና አንዳንድ ምናባዊና ሚስጢራዊ ፍቺ በመስጠት ፈንታ ቃላቶቹ ምን እንሚሉ በቀጥታና በትክክል ትረዳለህ።[17] ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ሁሉም ነገር ቀጥተኛ ነውን? መጽሐፍ ቅዱስ የንግግር ዘይቤዎችን አይጠቀምም? መጽሐፍ ቅዱስ ብዙውን ጊዜ ምሳሌያዊ አነጋገርን ይጠቀማል፡ የእግዚአብሔር በግ፣ በበጎች፣ ተኩላዎች፣ ልብስ፣ እግዚአብሔር ዓለታችን፣ ወዘተ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ሁሉም ነገሮች በጥሬው መወሰድ የለባቸውም። እግዚአብሔር በጥሬው ድንጋይ/ ዓለት አይደለም። ለዚህም ነው ይህ መርህ መደበኛ ትርጓሜ ተብሎ የሚጠራው። ጥያቄው እንግዲህ እንዴት ነው አንድ አረፍተ ነገር ቃል በቃል የሚተረጎም ወይም ምሳሌያዊ እንደሆነ የምንወስነው?

እናትህ "የደነደነ በቅሎ ነህ" ብትልህ፤ ጆሮህ ረጅም ነው ማለቷ ነውን? ግራጫ ፀጉር እና ወፍራም ቢጫ ጥርሶች አሉህ ማለቷስ ነውን? በጭራሽ! የአንተን ግትርነት ለመውቀስ የንግግር ዘይቤ እየተጠቀመች ነው። ስዕላዊ አገላለጾችንና ንጽጽሮችን በመጠቀም መግባባት የተለመደ ነው። ግን ሁሉም ነገር የንግግር ዘይቤ ምሳሌአዊ አይደለም። እናትህ "አንድ ኩባያ ሻይ እፈልጋለሁ" ካለች በቃ እሱኑ ማለቷ ነው። ሻይ ድነት፣ ወንጌል ወይም

16 Ibid., 123.
17 Zuck, Basic Bible Interpretation, 147.

ይቅርታ የሆነበት ምሳሌያዊ ትርጉም አላሰበችም። የእናትህን ምሳሌያዊ ንግግር (የደንዳነ በቅሎ) እና ቀጥተኛውን ንግግሯን (አንድ ኩባያ ሻይ ) እንዴት መለየት ትችላለህ? እንደምታስበው ከባድ አይደለም።

በንግግር ዘይቤ እና በቀጥተኛ መንገድ የተደረጉ ተግባቦቶችን በየዕለቱ ትለያለህ። እንዴት? መጀመሪያ በቀጥተኛው ትርጉም ትጀምራለህ፤ ትርጉም አልሰጥህ ካለ ግን ምሳሌያዊ ትርጉም የመፈለግ አማራጭ ትከተላለህ።[18] በሌላ አባባል፤ በመደበኛ ንባብ ወይም ማዳመጥ አንድ ነገር በግልጽ ምሳሌያዊ አገላለጽን ወይም ሌላ የንግግር ዘይቤን እስካልተጠቀመ ድረስ ቀጥተኛ ነው፤ በእርግጥ አንተ ትልቅ ጆሮ፣ ግራጫ ጸጉር ሌላም ሌላ የለህም፤ እንደዚህ ዓይነት ቃላት ለሰው ከገቡ ምሳሌአዊ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን ስታነብ ተመሳሳይ ነገር አድርግ። በምሳሌአዊ አነጋገር እየተጠቀመ እንደሆነ ግልጽ እስካልሆነ ድረስ የእግዚአብሔር ቃል በቀጥታ መወሰድ እንዳለበት አስብ። ለምሳሌ፣ ኢየሱስ፣ “በሩ እኔ ነኝ” (ዮሐንስ 10፥9) ኢየሱስ ከእንጨት የተሠራና ማንጠልጠያ ያለው ነው ብለህ መደምደም የለብህም። አእምሮህ የኢየሱስን አባባል ቀጥተኛ እንዳልሆነ ይገነዘባል። ይህ የተለመደ ንባብ ነው።

በመደበኛ ንባብ ጊዜ አንድ ክፍል ምሳሌያዊ ወይም ሌላ መሆኑ ግልጽ እስካልሆነ ድረስ ሁል ጊዜ በቀጥታ መተርጎም እንዳለበት በማሰብ ትጀምራለህ። በሌላ መልኩ ምሳሌያዊ ንግግርን ለመተርጎምም መጀመር ያለብህ በቀጥታ ነው። በር ምንድን ነው? በሩ ምን ጥቅም ላይ ይውላል? ለምን ኢየሱስ ራሱን ከበሩ ወይም ከመግቢያ ጋር ያወዳድራል? የበሩን ቀጥተኛ ተግባር የስዕላዊ አገላለጹን ትርጉም ይጠቁማል። ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት መግቢያ በር ነው።

## 5) የአንድ ምንባብ አንድ ትርጉም

ሣሩ አረንጓዴ ነው። ይህ ዓረፍተ ነገር ሣሩ ሐምራዊ፣ ቀይ፣ ሰማያዊ ወይም ቢጫ ነው ማለት ነው? ዛፎቹ ቡናማ ናቸው ማለት ነው? ሣሩ አረንጓዴ ከሆነ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ሊያመለክት ይችላል? ምንም ማለት አይደለም። ቋንቋ የሚረዳው አንድ ነገር ሲያመለክት ብቻ ነው እንጂ ሌላ አይደለም። ለምሳሌ አረንጓዴ የሚለው ቃል በትክክል ጠቃሚ ነው ምክንያቱም እሱ ሐምራዊ ፣ ቀይ ፣ ሰማያዊ ፣ ቢጫ ፣ ወይም ብርማ ማለት አይደለም። ሣር የሚለው ቃል በትክክል ይጠቅማል ምክንያቱም ተክሉን ከእነዚያ ዛፎች ብለን ከምንጠራቸው ረዣዥም ዕጽዋዕት በመጠኑ ስለሚለይ ነው። በተመሳሳይ መልኩ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላቶችና አረፍተ ነገሮች ጠቃሚ

[18] Ibid., 145-6.

ናቸው። ምክንያቱም በአንድ ቦታ አንድ ነገር እንጂ ሌላ ማለት ስላይደሉ። የአንድ ትርጉም መርህ ለሁሉም ተግባቦቶች መሠረታዊ ነው። ነገር ግን የአንድ ቃል ወይም ዓረፍተ ነገር ትርጉም የሚወስነው ማን ነው?

ተግባቦታችን ውጤታማ እንዲሆን፤ የሚናገረው ወይም የሚጽፈው ሰው የቃላቶቹን ትርጉም እንዲወስን ሊፈቀድለት ይገባል።[19] ለምሳሌ እኔ ሳድግ እናቴ ብዙ ጊዜ ክፍሌን አንዳጸዳ ትነግረኛለች። ትእዛዙን የሰጠችው እርሷ እንደመሆኗ ትዕዛዟ ምን እንደሆነ ትርጉሙን የምትወስነው እርሷ ነበረች። ለትዕዛዟ ትርጉሙን የምወስነው እኔ ስሆን፤ ክፍልህን አጽዳ ማለት የቆሸሸውን ልብሴን ሁሉ ሰብስቤ አልጋዬ ሥር መወሸቅ ነው። ብዙም ሳይቆይ የእናቴ ትእዛዝ ትርጉም ከእኔ የተለየ እንደሆነ ተረዳሁ፤ በሆነ መንገድ የእሷ ትርጓሜ ሁልጊዜ አሸንፏል! መሆን ያለበት እንደዚህ ነው። ትዕዛዝ ተናገረች። ትርጉሙን የመግለጽ መብት ነበራት።

በተመሳሳይ ሁኔታ፣ እግዚአብሔር ሲናገር የፈለገውን ይገልፃል። "ግን እግዚአብሔር ትርጉሙን ለማስረዳት እዚህ አልመጣም።" ትል ይሆናል፤ እውነት ነው። ስለዚህም የተጻፈውን ቃል በተቻለ መጠን በጥንቃቄና በመደበኝነት መተርጎም አለብን። ቃላቶቹ እራሳቸው፣ የሐሰብ ፍሰቱ እና የሰው ደራሲ ታሪካዊ አውድ እግዚአብሔር የተናገረው ምን እንደሆነና ምን ማለቱ እንደሆነ ይገልፃል።

እናቴ ክፍሌን እንዳጸዳ ስትነግረኝ ሁሉንም የቆሸሹ ልብሶችህን አልጋ ስር አስገባ ማለቷ እንዳልሆነ አውቅ ነበር። ለምን? እጽዳ የሚለው ቃል ለእሷ የሚሰጠው ትርጉም ያ አልነበረም። ንፁህ የሚለው ቃል ለእሷ ምን ትርጉም እንደሚሰጥ የማወቅ እና በዚየው መሠረት እርምጃ የመውሰድ ሀላፊነት የእኔ ነበረ። በተመሳሳይ መልኩ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚ፤ የአንተ ሥራ ቃላቶቹ እና ዓረፍተ ነገሩን እግዚአብሔር በእነሱ በኩል ሊናገር የተጠቀመባቸው ለሰው ዳረሲዎች ምን ማለት እንደነበረ መፈለግ ነው። ለሙሴ፣ ለኢሳያስ ወይም ለጳውሎስ ቃሎች የፈለግነውን ትርጉም የመስጠት ነጻነት የለንም። መስጠት ያለብን ትርጉም እነርሱ ሊሰጡ ያስቡትን ነው።

እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንድ እውነተኛ ትርጉም አለው፤ ትርጉሙም እግዚአብሔር በሰው ደራሲ በኩል ያሰበው ነው። ለእነርሱ ያለው ነው ትርጉሙ። ሣሩ አረንጓዴ ነው የሚለው ሣሩ ቡናማ ነው ማለት ሊሆን ይችላል ካልን፤ ንግግራችን ትርጉም አልባ ይሆናል። የእግዚአብሔር ቃል ከአንድ በላይ ብዙ ትርጉም ካለው እንዲሁ ትርጉም የለሽ ይሆናል።

---

19 McCartney, Let the Reader Understand, 35.

### 6) ዓለም አቀፋዊ፤ ደግሞም የሚዛመድ

አንድ ክፍል አንድ ትርጉም ብቻ ነው ያለው የምንለው መርህ ግራ ካጋባህ፤ አንተ ስለ ተዛምዶ እንጂ ስለ ትርጉም እያሰብክ ላይሆን ይችላል። እርግጥ ክርስቲያኖች “ይህ ጥቅስ ለእኔ ምን ማለት ነው…” ሲሉ ምን ማለታቸው ነው ይህን ጥቅስ ከራሴ ጋር የማዛምደው እንዴት ነው ማለታቸው ነው። ጥቅሱ ለሙሴ፣ ለማቴዎስ ወይም ለጳውሎስ ምን ማለት እንደሆነ ከማወቃቸው በፊት ከራሳቸው ጋር ማዘመድ ይፈልጋሉ። በሌላ አባባል እግዚአብሔር በጥቅሱ ሊናገራቸው የፈለገውን ነገር ሳይረዱ በፊት መተግበር ይፈልጋሉ። ይህ ለክርስቲያኖች አደጋ ነው፤ ለሰባኪዎች ደግሞ አደገኝነቱ እጥፍ ነው። ስለዚህ በትርጓሜና በተዛምዶ መካከል ያለውን ልዩነት በታማኝነት ማስቀመጥ አለብህ።[20]

ትርጓሜ በዋናው ጸሐፊ ታሪካዊው ሁኔታ ውስጥ የታሰበውን ትርጉም ለማግኘት ይጥራል። ለምሳሌ ጳውሎስ ለሮም ቤተ ክርስቲያኖች ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት ሲጽፍ ምን ማለቱ ነበር። ትርጓሜ የጳውሎስ ቃላት ዛሬ በሕይወታችን ላይ ምን ተጽዕኖ አሳደሩ የሚለው አያስጨንቀውም። ያ በጣም ጠቃሚ ነው። ነገር ግን ያ ተዛምዶ የተለየና በሁለተኛ ደረጃ የምናየው ነው። ትርጓሜ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ለሁሉም ሰው፣ በሁሉም ቦታና በሁሉም ጊዜ ያለውን ጠቀሜታ ያሳያል።

በሌላ በኩል ተዛምዶ የሚያመለክተው የዋናው ጸሐፊ አንድ ትርጉም ዛሬ በሕይወታችን በተለያዩ መንገዶች ያለውን ተጽዕኖ ነው። ተዛምዶ የሚያመለክተው የተለያዩ ሰዎች፣ በተለያዩ ጊዜያት፣ በተለያዩ መንገዶች፣ በተለያዩ ቦታዎች አንዱን የክፍሉን ትርጉም እንዴት እንደሚኖሩት ነው። ትርጓሜው አንድ ሰው ወርቅ ወይም የከበረ ማዕድን እስኪያገኝ ድረስ የሚያደርገውን ቁፋሮ ያመለክታል። ተዛምዶ ግን እነዚያን ያገኛቸውን ወርቆች የሚጠቀምበትን የተለያየ መንገድ አመልካች ነው።

## ሦስት ምሳሌዎች

አትስረቅ የሚለውን ትዕዛዝ አስብ። ያ ትዕዛዝ አንድ ትርጉም ነው ያለው፤ የአንተ ያልሆነውን ወይም እንድትጠቀመው ያልተፈቀደልህን ነገር አትውሰድ ማለት ነው። ማንም ሁን፣ የትም ኑር፣ ዘጸ 20፡15ን መቼም አንብብ፤ አትስረቅ የሚለው ትዕዛዝ ግን እውነት ሆኖ ይኖራል።

---

[20] Ramm, Protestant Biblical Interpretation, 113.

ይሁን እንጂ፤ ከአንድ ደመና የሚወጣ ዝናብ በብዙ መስኮች ሊዘንብ ይችላል። በሌላ አገላለጽ፤ አትስረቅ የሚለው ትዕዛዝ አንድ ትርጉም፤ በተለያዩ ቦታዎች፣ በተለያዩ ሰዎች፣ በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ መንገዶች ሊኖር ይችላል። ይህ ትዕዛዝ ለአስር ዓመት ልጅ፤ በለሱቁ ባያይም እንኳ ቸኮሌት ኪሱ እንዳይከት ይከለክለዋል። ይህ ትዕዛዝ ለአዋቂ ሰው በሥራ ሰዓት መተኛትን መከልከል ይሆናል ምክንያቱም የተቀጠርንበትን የሥራን ሰዓት በእንቅልፍ መቀነስ ትክክል ስላልሆነ። እነዚህ የዘጸ 20፡15 አንድ ትርጉም ሁለት የተለያዩ ተዛምዶዎች ናቸው። ያ አንድ ትርጉም በብዙ መንገዶች ለመተገበር ይችላል። ለአዋቂዎችና ለሕጻናት፣ ለወንዶችና ለሴቶች፣ ለአፍሪካዊያንና ለእስያዎች ወዘተ። ነግ ግን የዘጸ 20፡15 ትርጓሜ በፍጹም አይለወጥም። በዚያ መንገድ እንድትጠቀም ያልተፈቀደልህን ወይም የአንተ ያልሆነን ነገር አትውሰድ።

ሁለተኛ ምሳሌ እንጨምር፤ ምሳሌ 15፡1ን እንመልከት *"የለዘበ መልስ ቁጣን ያበርዳል፤ ክፉ ቃል ግን ቁጣን ይጭራል።"* (አ.መ.ት) ይህ ምሳሌ በብዙ መንገዶች ሊተገበር ይችላል። አባት ውጥረት በሞላበት የሽማግሌዎች ስብሰባ ምላሱን በመግራትና ሌሎች በሐሳቡ ሳይስማሙ ሲቀሩ በዝግታ በመናገር ማዛመድ ይችላል። እናት ልጇን እራት እንድትሰራና እንድታግዛት ስትጠይቃት፤ ልጇ ከጓደኞቿ ጋር እየተጫወተች ስለሆነ ብታጉረመርምና ለማገዝ ፈቃደኛ ባትሆን፤ እናት በዝግታ በማውራት ክርክሩን በማቀዝቀዝ ጥቅሱን ማዛመድ ትችላለች። ሴት ልጅ ደግሞ የታናሽ ወንድሟን ስድብና ጉንተላ ባለመመለስ ማዛመድ ትችላለች። ወንድም ደግሞ በኳስ ጨዋታ ሜዳ በሚነሱ ክርክሮችና ጠቦች መካከል ባለመሳተፍና በማለዘብ ይህንን ጥቅስ ማዛመድ ይችላል። እነዚያ ሁሉም የአንድ ጥቅስ የተለያዩ ተዛምዶዎች ናቸው። ነገር ግን ምሳሌ 15፡1 አንድ ትርጓሜ ብቻ ነው ያለው፤ *"የለዘበ መልስ ቁጣን ያበርዳል፤ ክፉ ቃል ግን ቁጣን ይጭራል።"*

መተርጎምንና ማዛመድን መለየት እጅግ ወሳኝ ነውን? አዎ! የእግዚአብሔርን መልዕክት ሳያገኙ ወደ ማዛመድ መቸኮል ጥቅሱን የመቆጣጠርና እንደፈለጉ የማድረግ ፍላጎት ማሳያ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በሁሉም ሰው መተግበርና መዛመድ አለበት፤ ነገር ግን የምናዛምደው የእግዚአብሔር ቃል እንጂ የራሳችን አይደለም። በተጨማሪም አንድ የአስር ዓመት ልጅ አትስረቅ ማለት ቸኮሌት አትውሰድ ማለት ብቻ አድርጎ እያሰበ ቢያድግ፤ በጉልምስናው ዘመን መሥራት ሲገባው ከቀጣሪው ላይ የሥራ ሰዓት በመስረቅ ያሳልፈል። ለምን? አትስረቅ ለሚለው ትዕዛዝ የሰጠው ተዛምዶ የተዛባና ሌላ አማራጭ ያልተከተለ ነበርና ነው።

በ1ኛ ተሰ 4፥3 ጳውሎስ "የእግዚአብሔር ፈቃድ ከዝሙት ርቃችሁ እንድትቀደሱ ነው።" ይላል፤ ይህንን ካነበበ በኋላ ሰባኪው "ይህ ቁጥር የሚናገረው ወሲባዊ የእርቃን ምስሎችን እንዳንመለከት ነው" ቢል፤

የምናዛምደውን ነገር እየሰጠን እንጂ ክፍሉን እየተረጎመው አይደለም።[21] የእርቃን ምስልን አለመመልከት የ1ኛ ተሰ 4፡3 ትርጓሜ ከሆነ፤ ይህ ጥቅስ ከጋብቻ በፊት ከእጮኛው ጋር ለሚተኛ ወጣት ወንድ ምንም አይልማ፤ ከሚስቱ ወጪ ለሚተኛ ጎልማሳ ምንም አይልማ፤ ይህ ትክክል እንዳልሆነ ደግሞ ታውቃለህ።

ተዛምዶንና ትርጓሜን በማምታታት ሳታስበው ብዙ ተዛምዶዎችን ልታስቀር ትችላለህ። አንተ ማለት የምትፈልገውን ሁሉ ትላለህ፤ ነገር ግን ጌታ ያለውን ታስቀራለህ። የ1ኛ ተሰ 4፡3 ትርጓሜ ከእርቃን ምስል እጅግ የሰፋ ነው፤ ከትዳር ውጪ የሚደረግን ማንኛውንም ወሲባዊ ፍላጎት ፈጽሞ አስወግዱ ማለት ነው። ከዚህ በሁሉም ዘመን፣ በየትኛውም ቦታ፣ ለሁሉም ሰው ከሚሰራው አንድ ትርጉም አንተም ሆንክ ጉባኤህ እጅግ ብዙ ተዛምዶዎችን ማውጣት ትችላላችሁ።

ክፍሉን መተርጎምና ክፍሉን ማዛመድ በስብከት ዝግጅት ውስጥ ሁለት የተለያዩ ደረጃዎች ናቸው። ክፍሉ ለመጀመሪያው ደራሲ/ጸሓፊ ምን ማለት ነው የሚለው ቀድሞ ይመጣል፤ ያንን ከተወጣህ በኋላ፤ ያ ክፍል ዛሬ ሕይወታችን ላይ እንዴት እንደሚተገበር እጅግ ብዙ መንገዶችን መጠቆም ትችላለህ።

## ተግባራዊ መልመጃ

የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜን ከተዛምዶ ለመለየት አንድ ተግባራዊ ምሳሌ እንይ። ሮሜ 12፡1-2 እያጠናህ ነው እንበል፤ ሮሜ 12፡1-2ን በራስህ ቋንቋ እንደገና ጻፈው፤ እያንዳንዱን ዓረፍተ ነገር ስትጀምር ጳውሎስ በተጠቀማቸው ቃላት ጻፍ፤ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ያለውን ብቻ ማለትህን እርግጠኛ ሁን። ያ መተርጎም ነው። ያንን ካደረግህ በኋላ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ያለውን የምትተግብርበትን ሦስት መንገዶች ጻፍ። በአንደኛው ክፍለ ዘመን ሮም አልኖርክም ግን እግዚአብሔር ቃሉ ከሕይወትህ ጋር እንዲዛመድ ይፈልጋል። ከመተርጎም ጀምር፤ ቀጥሎም ወደ ማዛመድ ተሸጋገር። ይህንን የቤት ሥራ ሳትሰራ ቀጥሎ ወደተጠቀሰው ውይይት አትግባ።

እንዴት ነበር? ሮሜ 12፡2 “ይህን ዓለም አትምሰሉ” በሚለው የመጀመሪያው ክፍል ላይ በማተኮር የተሳሳተም ሆነ ትክክለኛ ጥረት ምን እንደሚመስል፤ ምሳሌ ልስጥህ። የመጀመሪያው ሙከራ ትርጓሜን ያደናቅፋል እና በቀጥታ ወደ ትግበራ/ ማዛመድ ይሄዳል።

---

[21] Some of the confusion on this issue is due to the fact that the English word mean can be used both of the author's intended meaning of a text and of the implications of that text for the lives of believers. This is a regrettable weakness of English. Meaning and implications are, in fact, two different things.

የተሳሳተ አቀራረብ፡- “ለእኔ ይህ ዓለም አትምሰሉ ማለት፤ ቴሌቭዥን ማየት የለብንም ማለት ነው። እርግጥ ይህ ጥቅስ ሁሉም ቴሌቪዥን ክፉ ነው ይላል፤ ቴሌቪዥን ካለህ ክርስቲያን አይደለህም፤ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች የሚለው ይህንን ነው።”

ሰባኪውን በአብዛኛው የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ላይ ያለውን ጥላቻ ሳጋራችሁ፤ ምንአልባት የተዛምዶ ጋሪውን ከትርጓሜ ፈረስ ያስቀደመ ይመስለኛል። ጳውሎስ የሮሜ ሰዎች ቴሌቪዥን እንዳይመለከቱ አልነገራቸውም እንዲያውም በዚያን ወቅት ቴሌቪዥንም አልነበራቸውም። የሰባኪው ተዛምዶ ጥሩ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ትርጉሙ በጸሐፊው እንደታሰበ ስለመሆኑ እርግጠኞች አይደለንም። የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍል መተርጎም እጅግ አስፈላጊ ነው።

ትክክለኛ አቀራረብ፤ ትርጓሜ። “ጳውሎስ ያለው የሮሜ ክርስቲያኖች በዙሪያቸው በሚገኙ የማያምኑ ሰዎች አስተሳሰብና አኗኗር እንዳይወሰዱና እንዳይከተሏቸው ነው።” ይህ አተረጓጎም ዓለም እና አትምሰሉ የሚሉ ቃላትን ያብራሩልናል። ጳውሎስ ከሰማይ ቢመጣ እንዲህ ይላል “አዎ እንደዚያ ነው ያልኩት አማኞች እንደማያምኑ ሰዎች ማሰብና መኖር የለባቸውም።” ትርጓሜውን ከሰራን በኋላ አሁን ስለማዛመድ ማሰብ እንችላለን። “እንደማያምኑ ሰዎች እንዳስብ መጥፎ ተጽዕኖ ከሚያደርጉብኝ ነገሮች አንዱ ቴሌቪዥን ነው፤ በዓለማዊ አስተሳሰብ ለለመጠቃት ቴሌቪዥን ሳይ በጥንቃቄ መምረጥ አለብኝ፤ ከተቻለም ሙሉ በሙሉ ቲቪ ማየትን ማቆም።”

ትርጉም ማለትም ጌታና ጳውሎስ ያሉት ዛሬ እኔና አንተ እነርሱ በተናገሩት መሠረት እንዴት እንኑር ከሚለው የተለየ ነው። የትርጓሜን እንቁ ለማግኘት አጥልቀህ ቆፍር፤ አንዴ ትርጉሙን ካገኘህ ደግሞ ያንን ሐብት ስለምትጠቀምበት የተለያዩ መንገዶች አስብ። ጎበዝ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚ እነዚህን ሁለት ደረጃዎች የተረዳና በተለይ የሚያስቀምጥ ነው፤ አስቀድሞ መተርጎም፤ ቀጥሎም ማዛመድ።

### 7) አውድ

አውድ ከምታጠናው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አስቀድሞም ሆነ ተከትለው የሚመጡትን ቃላት፣ ዓረፍተ ነገሮችና አንቀጾችን አመላካች ነው። ይህ መርህ ትኩረት የሚሰጠው በምታነበው ክፍል ዙሪያ ያሉትን ሐሳቦች በሚገባ ስትረዳ ብቻ ነው የምታነበውን ክፍል ትርጉም የምትረዳው በሚለው ላይ ነው።[22] እንደማንኛውም ቃላት የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላትም የሆነ ነገር የሚሉት በዙሪያቸው ያሉትን ቃላት መሠረት አድርገው ነው።

---

[22] Zuck, Basic Bible Interpretation, 106.

አምላክ የሚለው ቃል በኣል ከሚለው ቃልና እግዚአብሔር ከሚለው ቃል በኋላ ሲገባ አንድ ዓይነት ትርጉም የለውም። በደቡብ አፍሪካ የሚገኙ ተስዋና የሚባሉ ሕዝቦች “ሰው ሰው የሚሆነው በሌሎች ሰዎች በኩል ነው” የሚል አባባል አላቸው።[23] በሌላ አባባል አንድ ሰው ከቤተሰቡና ከተገኘበት ማህበረሰብ የተለየ ማንነት አይኖረውም ማለት ነው። በተመሳሳይ መልኩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ቃላትም ከቤተሰቦቻቸውና በጎሳቸው ማለትም በዙርያቸው ካሉት ቃላት፣ አረፍተ ነገሮችና አንቀጾች የተለየ ማንነት የላቸውም።

ለምሳሌ ፊልጵስዩስ 2፥3 ላይ “አንዳች አታድርጉ/ አንድ እንኳ አታድርጉ” ይላል። አንዳች አታድርጉ?! እርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ይላልን? ታካች ሰው በዓል ለማክበር ከአልጋው ዘሎ ይወርዳል፤ ታዳጊ ልጅ ድሉን ለማክበር የደስታ ጩኸት ይጮኸል። ይህ እነዚህ ሰዎች የሚጠብቁት የመጽሐፍ ቅዱስ ትዕዛዝ ነው፤ ፊል 2፡23 ላይ ያለው አንዳች/ምንም አታድርጉ የሚለው ጥቅስ ስንፍናን ያበረታታልን? አይልም። ቀሪውን የጥቅሱን ክፍል “በራስ ወዳድነት ምኞት ወይም ከንቱ ውዳሴ ለማግኘት አንዳች አታድርጉ” ይላል። አንዳች አታድርጉ የሚሉ ቃላት ቤተሰብ አላቸው፤ ያንን ቤተሰብ ስታገኙ፤ የትዕዛዙን እውነተኛ ምንነት ታገኛላችሁ።

ፊል 4፥6 “አትጨነቁ” ይላል። አሃ እግዚአሔር ጭንቀታችንን ይታገሳል ብቻ ሳይሆን እንዳንጨነቅም አዞናል። ፊል 4፥6 ጭንቀትን እግዚአብሔር አታድርጉ ብሎ ካዘዘን ኃጢአቶች ዝርዝር ሰርዟልን? አይደለም። ቀሪውን የጥቅሱን ክፍል ስናነበው “በአንዳች አትጨነቁ” የሚል አለበት። በትዕዛዙ ዙሪያ ያሉትን ቃላት ችላ በማለት የእግዚአብሔርን ቃል በጭንቅላቱ ትፈጠፍጠዋለህ፤ እርግጥ ነው አውድን መዘንጋት የእግዚአብሔርን ቃል ወደ አለመታዘዝ ይመራሃል። “አንድ ቃል ትርጉም የሚሰጠው በዙሪያው ካሉት ቃል ጋር ነው” የሚለውን ንግግር ማስታወስ አለብን።

## ምሳሌ ከኢሣይያስ

ኢሣ 1፡10 እንዲህ ይላል፤ *እናንተ የሰዶም አለቆች ሆይ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ እናንተ የገሞራ ሕዝብ ሆይ፥ የአምላካችንን ሕግ አድምጡ።* እግዚአብሔር ለማን እየተናገረ ነው? በኢሣ 1፡10 መሠረት ኢሣይያስ እየተናገረ ያለው በሰዶምና ገሞራ ላሉ ከተሞች ነው ብለህ ትደመድማለህ። ነገር ግን ቁጥር 10 በዙርያው ላሉ ቁጥሮች ይዛመዳል። የኢሣ 1፡10 ዘመዶች ስትገናኝ፤ ስዕሉ ይቀየራል። ለምሳሌ ቁጥር 1ን ስታገኝ ኢሣይያስ የተነበየው አራት ነገስታት በነበሩበት ዘመን እንደሆነ ትረዳለህ፤ በዖዝያን፣ በኢዮአታም፣ በአካዝና በሕዝቅያስ

---

[23] Van der Walt, Understanding and Rebuilding Africa: From Desperation Today to Expectation for Tomorrow (Potchefstroom, South Africa: The Institute for Contemporary Christianity in Africa, 2003), 143, 139.

ዘመን እንደሆነ ትረዳለህ። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ገልጠህ ለጥቂት ደቂቃ ብታይ ደግሞ እግዚአብሔር ሰዶምንና ጎሞራን ከምድር ገጽ ያጠፋው ከ1400 ዓመታት በፊት እንደሆነ ትረዳለህ። ቁጥር 3 ደግሞ ኢሣይያስ የእግዚአብሔርን ቃል ያወጀው ለእስራኤል እንደሆነ ይናገራል፤ ቁጥር 8 ደግሞ የኢሣይያስ አድማጮች የጽዮን ሴት ልጆች እንደሆኑ ይናገራል፤ የጽዮን ሴት ልጆች ለኢየሩሳሌም የተሰጠ ቅኔአዊ ስም ነው። በመጨረሻም ቁጥር 9 "እንደ ሰዶም" "እንደ ገሞራ" የሚሉ ቃላት ይጠቀማል።

አውድ አስፈላጊ ነው። ኢሣይያስ 1፡10ን ብቻ ካነበብህ ኢሣ ምዕራፍ 1 የሚናገረው ለሰዶምና ጎሞራ ብቻ ይመስለሃል፤ አተረጓጎምህም እጅግ ስህተት ይሆናል። ኢሣይያስ እየሰበከ ያለው ለኢየሩሳሌም፣ ይሁዳና እስራኤል ነው፤ ነገር ግን ያንን እያደረገ የነበረው ኢየሩሳሌምንና እነዚያን ሁለት ክፉ ከተሞችን በማነጻጸር ነበረ። ትክክለኛው የኢሣይያስ 1፡10 ትርጉም የሚገኘው ከቁጥሩ በላይና በታች ያሉትን አረፍተ ነገሮች በማግኘት ነው። ይህ ለሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰራ እውነት ነው፤ አውድ ትርጉምን ይወስናል።

## ምሳሌ ከኤርምያስ

ኤርምያስ 29፡11 በክርስቲያኖች የቀን መቁጠሪያና ሌሎች ጥሪዎች ላይ ተዘውትሮ የሚነሳ ተወዳጅ ጥቅስ ነው። "*ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም።*" አንዳንድ ክርስቲያኖች በሕይወታቸው ምንም ክፉ ነገር እንደማይሆን ተስፋ አለን ለሚለው እምነታቸው የሙጥኝ ብለው የሚይዙት ይህንን ጥቅስ ነው። ነገር ግን ኤርምያስ 29 ስታነብ፤ ያ ተስፋ ለሁሉም ክርስቲያኖች የተሰጠ ጠቅላላ ተስፋ እንዳልሆነ ትደርስበታለህ። በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ እንደምናገኘው ዓይነት ተስፋ አይደለም፤ ለምሳሌ በመዝሙር 148፡18 እንዳለው "*እግዚአብሔር ለሚጠሩት ሁሉ፥ በእውነት ለሚጠሩት ሁሉ ቅርብ ነው።*" የኤርምያስ 29፡11ን ዘመዶች፤ ማለትም በዙሪያ ያሉትን ጥቅሶች ስትገናኝ፤ ይህ ጥቅስ ለሁሉም አማኞት የተገባ ቃል ወይም ተስፋ ሳይሆን፤ ኢየሱስ ከመወለዱ 500 ዓመታት በፊት በባቢሎን ምርኮ ለሚገኙ አይሁዶች በኤርሚያስ የተላከ መልዕክት እንደሆነ ትረዳለህ። በዚያ መልዕክት እግዚአብሔር እነዚያ በምክርኮ የሚገኙ አይሁዶች እዛው እንደማይቀሩና ከ70 ዓመታት በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚመለሱ እየተናገረ ነው።

በኤርምያስ 29፡11 ያለው ለተወሰኑ ሰዎችና ከተወሰነ ሁኔታ የማውጣት ተስፋ የክፍሉን ተዛምዶ ውስን ያደርገዋል። ያ ክፍል ሁሉም አማኞች በሕይወት ቀላል መንገድ ይኖራቸዋል የሚል ተስፋ አይደለም። ኤርሚያስ እራሱ በታማኝነት ስለሰበከ ተጠልቷል፣ ተገፍቷል፣ ተደብድቧል፣ ለእስርም ተዳርጓል። ያ ጥቅስ በተወሰነ መልኩ

በእርሱ ሕይወት አልተተገበረም። እግዚአብሔር ከክርስቶስ ልደት በፊት በ6ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ለአይሁዶች የገባው ተስፋ፤ ዛሬ ላሉ ሁሉም አማኞች ቀላልና ምቹ ህይወት የመስጠት ዕቅድ እንዳለው ዋስትና አይሰጠንም። አውድ ትርጉምን ይወስናል።

## 8) ሂደታዊ አስተርዮ/መገለጥ (Progressive Revelation)

እግዚአብሔር የራሱን እውነት የገለጠልን በረዥም የጊዜ ሂደት ነው፤ አንድ ሺ አምስት መቶ በሚያህሉ ዓመታት መካከል። በተፈጥሮ ጊዜ በሄደ ቁጥር የእርሱ መገለጥ እየተብራራ መጥቷል። በቃል ለመግለጥ ከፈለግን አድጓል ወይም በሂደት ጨምሯል ማለት እንችላለን።[24] ከውሸት ወደ እውነት አላደገም (ቃሉ ሁሌም እውነት ነው)፤ ነገር ግን ከከፊል ወደ ሙላት አድጓል፤ ከጥላ ወደ አካል እንደማለት ነው። የዕብራዊያን መልዕክት እንደሚናገረው ያ ሙላት የሚያተኩረው በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ነው። “ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን።” (ዕብ 1፡1-2) በብሉይ ኪዳን ዘመን ሙሴ፣ ዳዊት ወይም ሰለሞን ካወቁት በላይ እኛ እናውቃለን፤ እነርሱ ታላቁን የእግዚአብሔር ስብከት ጠበቁ፤ እኛ ሰማን።

የተሟላ እውቀት የሚክስ ቢሆንም፤ ለዛሬ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች አደጋም ይዟል። የእግዚአብሔር መገለጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ በዝርዝር የማደጉ እውነት ማለት የኋለኛውን መገለጥ ወደ ፊተኛው (ብዙ ጊዜ አዲስ ኪዳንን ወደ ብሉይ ኪዳን) የማንበብ ወጥመድ ማስወገድ አለብህ ማለት ነው።[25] በዘፍጥረት 12፡3 በአብረሃም የምድር ሕዝቦችን/ነገዶችን ሁሉ እንደሚባርክ ተናግሯል። በዚያን ጊዜ ያ በረከት ምን ዓይነት እንደሚሆን እግዚአብሔር ዝርዝር ማብራሪያ አልሰጠም፤ ነገር ግን በኋለኛው መገለጥ በገላ 3 ያ በረከት የአብርሃም እውነተኛ ዘር በሆነው በኢየሱስ የመጣውን ድነት እንደሚያጠቃልል ተናግሯል። አብርሃም እግዚአብሔር በዘፍጥረት 12 የገባለትን ቃል በሙላት እንደተረዳ መገመት ስህተት ነው። ምክንያቱም መገለጡ በጊዜ ሂደት ሲያድግ ነው የእግዚአብሔር የተወሰነ ዕቅድ የታወቀው።

የብሉይ ኪዳን ምንባቦችን በምታነብበት ጊዜ፤ ጸሓፊው በጊዜው ሊያወቀው ከሚችለው በላይ እንዳታነብላቸው ጥንቃቄ ውሰድ። የጸሐፊውን ትርጉም ከታሪካዊ አውዱ አንጻር ካየህ በኋላ ያን ትርጉም ከኋለኛው መገለጥ ጋር መስማማቱን ማረጋገጥ አለብህ። የፈለከውን ወስደህ ቀሪው በመጽሐፍ ቅዱስ እንዳልተጻፈ የምትቆጥርበት

---

[24] James E. Rosscup, "Hermeneutics and Expository Preaching," in Rediscovering Expository Preaching, John MacArthur, Jr. and The Master's Seminary faculty, (Dallas, Texas: Word Publishing, 1992), 131.
[25] Ibid., 132.

ምክንያት የለም። በአንድ በኩል አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በታሪካዊ አውዱ መተርጎም እንዲሁም በሌላ በኩል ደግሞ ያንኑ ክፍል ከኋለኛው መገለጥ መረጃዎች መሙላት፤ ሁለት የተለያዩ የስብከት ዝግጅት ደረጃዎች ናቸው።

## 9) ሰዋሰው

ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ መጣ ማለት ቆሮንቶስ ወደ ጳውሎስ ሄዷል ማለት አይደለም። ለምን አይሆንም? እንግልዘኛ የሚናገሩ ሰዎች የተወሰኑ ሕጎችን ይከተላሉ (የቃላት ፍሰት እና የመሳሰሉትን)፣ በእነዚህም ሕጎች መሠረት ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሄደ ማለትና ቆሮንቶስ ወደ ጳውሎስ ሄደ ማለት አንድ ትርጉም ሊሰጥ አይችልም። በእርግጥ ሕጎችን ካልተከተልህ ቃላቶችህ ትርጉም አልባ ይሆናሉ። ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ አንብብ የአንተን ብዬ ብል፤ ምን ማለቴ እንደሆነ ልትገረም ትችላለህ፤ ነገር ግን የአንተን መጽሐፍ ቅዱስ አንብብ ብዬ ብጽፍ ግን ምን ለማለት እንደፈለግሁ በትክክል ታውቃለህ። ልዩነቱ ለምን ተፈጠረ? በመጀመሪያው አረፍተ ነገር የአጻጻፍ ህግ አልተከተልኩም፤ በሁለተኛው ግን ተከትዬአለሁ።

ሕጎች አስፈላጊ ናቸው። እንዴት ነው የዓለም እግር ኳስ ዋንጫ ውድድር በአራት ዓመት አንዴ ሊደረግ የሚችለው? ምክንያቱም የእግር ኳስ የትም ቢሆን እግር ኳስ ነው። የዓለም እግር ኳስ ዋንጫ ውድድር ማድረግ የተቻለው፤ የእግር ኳስ ውድድር ህጎች በሁሉም የዓለም ክፍል ተመሳሳይ ስለሆኑና ከግለሰብ ግለሰብ ስለማይለያዩ ነው። ከየትኛውም የዓለም ክፍል የሚመጡ ቡድኖች ትርጉም ያለው ውድድር ማድረግ የቻሉት፤ ህጎቹ የትም ተመሳሳይ ስለሆኑ ነው። በተመሳሳይ መንገድ ሁላችንም እንግልዘኛ ወይም አማርኛ መጫወት እንችላለን ምክንያቱም የየቋንቋው ተናጋሪዎች ያወጧቸውና የተስማሙባቸው የተወሰኑ ህጎች ስላሉ። እነዚያ ህጎች ቋንቋን ትርጉም ያለው ያደርጋሉ፤ ቋንቋን መረዳት እንድንችል ያደርጋሉ።

የሰዋሰው አገባብ ማለት አረፍተ ነገርህ የሚለው አንድ ነገር እንጂ ሌላ አለመሆኑን የሚያመለክት ሕግ ነው። ያለ እነዚያ ሕጎች መግባባት ባልኖረና ባልተቻለ ነበረ። በተለይም ደግሞ ሰዋሰው አንድ ነጠላ ቃል ከሌላው ጋር እንዴት እንደሚገናኝ የሚያስተዳድር ህግ ነው። አገባብ ደግሞ ቃላት ከሌሎች ቃለት ጋር የሚጣመሩበት ሕግ ነው።[26] ብዙ ሰዎች በዚህ ዙርያ ምሁራን አይደሉም ግን ለመግባባት የሚበቃቸውን ያህል ያውቃሉ። ሰባኪዎች ከሁሉም ሰዎች ወይም ከመደዴው ህዝብ የሚመደቡ አይደለም። ሰባኪዎች አዋቂዎች እንዲሆኑ ግድ ነው፤

[26] J. William Johnston, "Grammatical Analysis: Making Connections" in Interpreting the New Testament Text: An Introduction to the Art and Science of Exegesis, ed. by Darrell L. Bock and Buist M. Fanning (Wheaton, Ill.: Crossway Books, 2006), 57.

ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ልብ መስበክ ስለሚፈልጉ፣ እግዚአብሔር ደግሞ የልቡን ሐሳብ የገለጠው ትርጉማቸው በሰዋሰውና አገባብ በሚወሰኑ ቃላትና በዐረፍተ ነገሮች ነው።

ሕጎች የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎምን ቀላል ያደርጉታል፤ አንድ ጥቅስ የቋንቋ ሕግ ከሚሰጠው ትርጉም የበለጠም ያነሰም ነገር ማለት አይችልም። እርግጠኛ ለመሆን አውዱ ያንን ትርጉም ይቀርጸዋል። እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ የአነጋገር ዘይቤን ይጠቀማል። አንዳንድ ጊዜ በተፈጥሮ ውስጥ ያለው የቃላት መለዋወጥ እና ግንኙነታቸው ለተርጓሚው በርካታ አማራጮች ይሰጣል። ሰዋሰውና አገባብ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉምን ያቀሉልናል፤ ቃላል ግን አያደርጉም። ቢሆንም እግዚአብሔር ሲናገር የቋንቋ ሐጎችን ስለተጠቀመ፤ እነዚያን ሕጎች መከተል የእግዚአብሔርን ሐሳቦች ወደ መረዳት ይመራሃል።[27]

ብዙ ሰባኪዎች ሰዋሰውንና የቃላት አገባብን እንደ ብሮኮሊ ያያሉ፤ ለእነርሱ ጥሩና ጠቃሚ እንደሆነ ያውቃሉ፤ ነገር ግን በአገባብ አይመገቡትም። እንደዚያ አታስብ። በሥነ-መለኮት ውስጥ ሰዋሰውና አገባብ ያለውን ጥቅም በምሳሌ ላስረዳ። በ1553 ዓ.ም የጄኔቭ ከተማ ሰርቨተስ የተባለ ሰው የኢየሱስ ክርስቶስን መለኮትነት ስለካደ በእሳት አቃጥላለች። የስህተት ትምህርትን ለማረም ማቃጠል ትክክለኛ የአዲስ ኪዳን መንገድ አይደለም (ቲቶ 3፡9-11)፤ የሰርቨተስ ሞት እጠሬ የሰዋሰውንና የቃላት አገባብን አስፈላጊነት በምሳሌ እንደሚያስረዳን ልብ በል።

[ሰርቨተስ] ያረፈው በአገባብ ላይ ከባድ ስህተት ከፈጠረ በኋላ ነው። እንዲህ ብሎ ጮኸ “ኦ! ኢየሱስ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ልጅ” በማለት ፈንታ “ኦ! ኢየሱስ የዘላለም አምላክ ልጅ ምህረት አድርግልኝ” በማለት ጮኸ። ቅጣቱ አንዷት ቅጽል ያለቦታዋ በመጠቀሙ ነበረ። ኑፋቄ ምንም ሳይሆን የሰዋሰው ጥያቄ ነው።[28]

## 10) ታሪካዊ ተገቢነት

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ፤ እየተረጎምክ ያለውን በሁለት ሺ እና በሦስት ሺ አምስት መቶ ዓመታት መካከል የተጻፈውን መጽሐፍ ነው፤ ለአንተ ሥራ ታሪክ አስፈላጊ ነው።[29] በትርጉም ሂደት ውስጥ የታሪካዊ ተገብነት

27 The scholars who have translated the Bible into English (or other languages) know the rules of Hebrew, Aramaic, and Greek grammar—the original languages of Scripture. The English translations that work the hardest to reflect the grammar and syntax of the original languages are The New American Standard (NAS) and its 1995 Update, the English Standard Version (ESV), the New King James Version (NKJV), and the King James Version (KJV). See Leland Ryken, The Word of God in English: Criteria for Excellence in Bible Translation (Wheaton, Illinois: Crossway Books, 2002), 50-55

28 Bernard Cottret, Calvin: A Biography, trans. M. Wallace McDonald, (Grand Rapids: William B. Eerdmans, 2000), 225.

መርህ ከሁለት ስህተቶች ይገርድሃል። የመጽሐፍ ቅዱስ ሁነቶች ትናንት እንደተፈጠሩ አድርጎ ማስብ የመጀመሪያው ስህተት ነው። ለምሳሌ ኢየሱስ ከከተማ ወደ ከተማ ሲጓዝ በታክሲ አልነበረም የሄደው፤ የድምጽ ማጉያ በመጠቀም አልሰበከም። የገሊላን ሐይቅ በሞተር ጀልባ አላቋረጠም። የኢየሱስን አገልግሎት በዚያ መንገድ መግለጽ አስቂኝ ነው፤ በታሪክም ተገቢ አይደሉም።

በተመሳሳይ መልኩ በኤፌ 6፡16 ያለውን *የእምነት ጋሻ* መልበስ የሚለውን እንዳነበብህ፤ ባህላዊ ተዋጊዎች የሚይዙትን ጋሻ ልታስብ ትችላለህ። ነገር ግን ጳውሎስ በነበረበት ዘመን የነበሩ ተዋጊዎች (የሮም ወታደሮች) ያንን ዓይነት ባሕላዊ ጋሻ አይዙም። በኤፌሶን 6፡16 ያለውን ጋሻ በአንተ ዘመን እንዳለው ጋሻ አድርገህ ካብራራህ፤ አተረጓጎምህ ታሪካዊ ተገቢነት ያጣል።

ዘመናዊ ሀሳቦችን ወደ ጥንታዊ ክስተቶችና ቁሶች ከማንበብ ጎን ሁለተኛው ታሪካዊ ወጥመድ፤ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ራሱን የመዘንጋት አደጋ ነው። ለምሳሌ በቀደመው ውይይታችን ኢሣይያስ ምዕራፍ አንድ የተጻፈው ለሰዶምና ጎሞራ ከተሞች እንዳልሆነ አይተናል። እነዚያ ሁለት ከተሞች ኢሣይያስ ከኖረበት ዘመን አንድ ሺ ዓመት ቀድመው በእግዚአብሔር ተደምስሰዋል። ስለሆነም ኢሣይያስ ስብከቱን ያሰማው ለእነዚህ ከተሞች ነው ማለት ከታሪክ ተገቢነት አንጻር ትክክል አይደለም።

በአንድ ወቅት አንድ ሰባኪ በፊልጵስዩስ መጽሐፍ ውስጥ ደስታ የሚለው ቃል ያለውን ጠቀሜታ በትክክል የሚያስረዳበትን ስብከት አደመጥሁ፤ አጽንዖት ለመስጠት ያክል፤ የጳውሎስ ደስታ በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ አልነበረም፤ ሰባኪውም ጳውሎስ ያንን መልዕክት ስጽፍ እስር ቤት እንደነበረ ጠቅሷል። ከዛም ሰባኪው ስለ ጥንታዊው የሮም እስር ቤት ማብራራት ጀመረ። ያ እስር ቤት የተሰራው በትልልቅ የደህንነት ታንኮች ነው፤ ያ ቦታ ደግሞ ደስታ ከሚለው ቃል ጋር በቀላሉ ለማዛመድ የሚመች አይደለም። እንደ ሰባኪው ሐሳብ ጳውሎስ ፊልጵስዩስን ከዚያ ቦታ መጻፉ፤ የጳውሎስ ደስታ በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ አለመሆኑን ያስረዳል።

እንደለመታደል ሆኖ ያ ሰው የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ዘንግቷል። ፊልጵስዩስ የተጻፈው በውሎስ የመጀመሪያ እስሩ ነው፤ የመጀመሪያው እስር ደግሞ በሮም ከተማ በቤቱ ውስጥ የቁም እስረኛ የሆነበት ነው።[30] በዚያ እስሩ ጳውሎስ በአስፈሪው የሮም እስር ቤት አልነበረም፤ በሐዋ ሥራ 28 መሠረት ጳውሎስ ራሱ በተከራየው ቤት ለሁለት ዓመታት የቁም እስረኛ ሆኖ አሳልፏል (የሐዋ ሥራ 28፡30)። የጳውሎስ ደስታ በሁኔታዎች ላይ

---

[29] Ramm, Protestant Biblical Interpretation, 6.

[30] Peter T. O'Brien, The Epistle to the Philippians, in The New International Greek Testament Commentary (Grand Rapids, Mich.: William B. Eerdmans Publishing Company, 1991), 26.

ያልተመሠረተ መሆኑ እውነት ቢሆንም፤ የፊልጵስዩስን መልዕክት የጻፈው ከመሬት በታች ተቆፍሮ በተሰራ፣ ቀዝቃዛ የጨለማ እስር ቤት ነው ማለት ግን ከታሪክ አንጻር ትክክል አይደለም። ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚ፤ የእርሱ ትርጉም በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ከነበረው ታሪክ ጋር መጣጣሙን ያረጋግጣል።

## 11) የቃላት ጥናት

አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ በሚገባ ለመረዳት፤ በምንባቡ ውስጥ ያሉ ቁልፍ ቃላት በትክክል መብራራት አለባቸው። መጽሐፍ ቅዱስ "*በእምነት በጸጋ ድናችኋል*" (ኤፌ 2፡8) ሲል፤ አንተም ሆንክ እኔ ጸጋ፣ ድነት፣ እምነት ለሚሉ ቃላት የራሳችንን ፍቺ የመስጠት ነጻነት የለንም። በዚያ ፈንታ፤ እነዚያ ቃላት ለጳውሎስ ምን ትርጉም ይሰጡታል የሚለውን ማጥናት አለብን። በአንድ የእንግልዘኛ/አማርኛ የቃላት ዝርዝ መጽሐፍ (ኮንኮርደንስ) አንድን ቃል በተመለከተ ሰፊ ጥናት ማድረግ ትችላለህ። እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋለ ስትመለከት፤ በተለያዩ አውዶች ያለውን ትርጉም ትመለከታለህ። የቃላት ጥናት በስብከት ዝግጅት ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው፤ ምክንያቱም ቃላት እንደየአገባባቸው የተለያየ ትርጉም ይሰጣሉና።[31]

ሁሉም ቋንቋዎች አንዳንድ ብዙ ትርጉም የሚሰጡትን ቃላት ለመቆጠብ ይጥራሉ።[32] አንድ ቃል ብዙ ትርጉም ወይ ፍቺ ሲኖረው በጸሐፊው የታሰበው ትርጉም የትኛው እንደሆነ በምን ታውቃለህ? በአውድ። የቃላት ዘመዶች ትርጉሙ ምን እንደሆነ ይነግሩሃል። እኔ ቱቦው ተዘግቷል ብዬ ብል፤ የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦ ይሆን የሽማግሌ ሰው ትምባሆ ማጨሻ ቱቦ እንሆነ እርግጠኛ አትሆንም። ነገር ግን ቱቦው ተዘግቷል የቧንቧ ሰራተኛውም ቱቦውን ሊያጸዳ እየመጣ ነው ብዬ ብል፤ አውዱ (የቧንቧ ሠራተኛ መጠቀሱ) እንቆቅልሹን ይፈተዋል። የቧንቧ ሠረተኛ መጠቀሱ ቱቦው የፍሳሽ እንደሆነና የሰው እንዳልሆነ ግልጽ ያደርግልናል።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌ እንመልከት። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሓፊዎች ስጋ የሚለውን ቃል በብዙ መንገዶች ተጠቅመዋል። የሚበላ ስጋ፣ የሰው ሰውነት፣ የሰው ዘር፣ የሰው ኃጢአተኛ ባህርይ ስጋ ተብሎ ተጠቅሷል። እንደዚህ ዓይነት ብዙ ትርጉም ያለው ቃል ሲገጥምህ ምን ታደርጋለህ? አውዱ ይረዳሃል። አውዱ ስለሚበላው ስጋ ወይም ስለ መብል የሚያወራ ከሆነ፤ ጸሓፊው ያሰበው እርሱን እንደሆነ ትረዳለህ። ስጋ ራጋፊ ነው ቢል ስለ ሰው እያወራ እንደሆነ ትገነዘባለህ፤ እንደ ስጋ ፈቃድ አትመላለሱ የሚል ካነበብህ፤ ስለ ሰው ኃጢአተኛ ባሕርይ እያወራ እንደሆነ እርግጠኛ መሆን ትችላለህ።

---

[31] Rosscup, "Hermeneutics and Expository Preaching," 127.

[32] Darrell L. Bock, "Lexical Analysis," in Interpreting the New Testament Text: An Introduction to the Art and Science of Exegesis, ed. by Darrell L. Bock and Buist M. Fanning (Wheaton, Ill.: Crossway Books, 2006), 138.

አንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የሚጋፈጠው ፈተና የራሱን ትርጓሜ የመጽሐፉ አድርጎ ማንበቡ ነው። ለምሳሌ በአፍሪካ ውስጥ ድነት/ደህንነት የሚለውን ቃል ከስጋ ህመም ወይም ድህነት መዳን እንደሆነ አድርጎ መጠቀም የተለመደ ነው። ደህንነትን እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን ለማዳን የተጠቀመው ቅዱስ መንገድ አድርጎ መመልከት በብዛት የተለመደ አይደለም። ጥያቄው ድነት የሚለውን ቃል እኛ እንዴት እንጠቀመዋለን የሚለው ሳይሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሓፊዎች እንዴት ተጠቀሙት የሚለው ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሓፊ ለአንድ ቃል የሰጠውን ትርጉም ለማወቅ፤ ጸሐፊው ያንን ቃል የተጠቀመባቸውን በታዎች ሁሉ ገምግም።[33] ከዛ ቀጥሎ ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሓፊዎች አጠቃቀም ጋር አስተያይ (ለምሳሌ ጳውሎስ አንድን ቃል ዮሐንስ ወይም ጴጥሮስ ከተጠቀሙበት መንገድ በተለየ መንገድ ሊጠቀመው ይችላል)። አዲስ ኪዳንን እየተጠቀምክ ከሆነ ቃሉ በብሉይ ኪዳን ምን ትርጉም እንደነበረውም ማጥናት አትዘንጋ። አብዛኛዎቹ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች አይሁዶች ናቸው፤ ይህም ማለት ትምህርታቸው ከዘፍጥረት እስከ ሚልክያስ ከለው ቃል መሆኑ ግልጽ ነው። ሥነ-መለኮታዊ ቋንቋቸው ከዚያ ውጪ ከየት ይመጣል ብለህ ታስባለህ?[34]

ዛሬ ዛሬ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት ጋር ያለህን ትግል ለማቃለል የተዘጋጁ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትና ማብራሪያዎች አሉ። እግዚአብሔርን መስበክ የምትፈልግ ከሆነ ከእነዚህ መጽሐፍት በመግዛት ገንዘብህን መቆጠብ ነው፤ ለእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔር ትርጉም በመስጠት ይረዱሃል።

## 12) የማጣራት መርህ

የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ የተጀመረው ትናንት አይደለም፤ አንተም መንፈስ ቅዱስ አብርሆት የሰጠህ ብቸኛ ሰው አይደለህም። ስለዚህ የአንተን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መረዳት ከቀደሙትም ይሁን ከአሁን ዘመን ምሁራን ጋር ማገናዘብ መልካም ልምምድ ነው።[35] ለምሳሌ ባለፉት 500 ዓመታት የነበሩ ክርስቲያኖች ውድቅ ያደረጉትን ትርጓሜ ለመስበክ ሁለቴ ማሰብ ይጠበቅብሃል። በተጨማሪም፤ እንደ አንተና እንደ እኔ ላሉ ሰባኪዎች የአንድን መጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ትርጓሜ የሚወስኑ ታሪካዊ፣ ሰዋሰዋዊና መልከዓ ምድራዊ ሁኔታዎች በሙሉ መረዳት አስቸጋሪ ነው። በዘፍጥረት 10፡4 ላይ ያሉት የያዋን ልጆች ማንናቸው? ስለ እምነት ጋሻ ሲያወራ ጳውሎስ በአእምሮው ውስጥ የነበረው ምን ዓይነት ጋሻ ነበረ? ለእንደነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ

---

[33] Zuck, Basic Biblical Interpretation, 104-5

[34] David Hill, Greek Words and Hebrew Meanings: Studies in the Semantics of Soteriological Terms (Cambridge: Cambridge University Press, 1967), 18.

[35] Rosscup, "Hermeneutics and Expository Preaching," 135.

ለመስጠት የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን እድሜ ዘመናቸውን ሁሉ ማጥናት ይጠበቅባቸው ይሆናል። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ-ቃላት ብትጠቀም የዕድሜ ዘመን ጥናትን ወደ 2 ደቂቃ ማሳጠር ትችላለህ። ያዋን የሚለው የእብራይስጥ ስም በግሪክ ቋንቋ ጸጋ ማለት መሆኑን ወይም የሮም ወታደሮች ጋሻ ምን እንደሚመስል መፈለግ ቀላል ነው።

ልብ በል፤ የማጣራት መርህ በዚህ ሂደት ውስጥ የመጨረሻው መርህ ነው። እንደ ህግ ለአንድ ክፍል አስቀድመህ የራስህን ትርጓሜ ስጥ፤ በመቀጠልም ከሌሎች ሰዎች ሥራ ጋር አነጻጽር። አንዳንድ ጊዜ ከባድ ሥነ መለኮታዊ ሐሳቦችንና ቃላቶችን ለመረዳት በጥናትህ መግቢያም ቢሆን የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ወይም ማብራሪያዎችን ማማከር ትችላለህ። ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎችን ዘወትር መክፈትንና እንደ መጽሐፍ ቅዱስ የማንበብ ወጥመድ አስወግድ። ከዚህ ይልቅ አስቀድመህ የራስህን ጥረት አድርግ። ብቻ በማንኛውም መንገድ ግን የማጣራት ወይም የማመሳከር መርህ ተጠቀም፤ የትርጓሜ ጊዜህን ያድንልሃል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን ለመተርጎም ምንም ጥረት የማታደርግና የማብራሪያዎች ጥገኛ ወደ መሆን እንዳትመጣ ተጠንቀቅ።

## ማጠቃለያ

ሁሉም ጨዋታዎች ሕጎች እንዳሏቸው ሁሉ፤ የእግር ኳስ ጨዋታም ሕግ አለው፤ ኳስ በእጅ መመለስ የሚችለው በረኛው ብቻ ነው፤ ተከላካዮች የተቃራኒ ቡድን አጥቂዎች ግብ ለማስቆጠር ሲመጡ፣ መግፋት፣ ጠልፎ መጣል አይፈቀድላቸውም። ተጨዋቹ ህግ የማያከብር ከሆነ፤ ዳኛው ከሜዳ ያስወጣዋል። እግዚአብሔርም ቃሉን ለለማጥናት ሲሉ ትክክለኛ ትርጓሜ የማይከተሉ ሰባኪዎች ላይ የሚወስደው እርምጃ ተመሳሳይ ነው። “ወንድሞቼ ሆይ፥ ከእናንተ ብዙዎቹ አስተማሪዎች አይሁኑ፥ የባሰውን ፍርድ እንድንቀበል ታውቃላችሁና።”(ያዕቆብ 3፡1)። እነዚህን 12 መርሆች የማትተገብር ከሆነ፤ እግዚአብሔር ለሚቀጥለው ስብከትህ ቀይ ካርድ ሊሰጥህ ይችላል።

# ምዕራፍ አምስት

# ሰዋሰው ና አገባብ፡ የሰባኪ ጓደኞች

በመዝሙር 19፤ ዳዊት የእግዚአብሔርን ክብር ስለሚናገሩ ወይም ስለሚያውጁ ሁለት ነገሮች ጽፏል። ሰማያት እና የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል (ቁጥር 1-6፣ 7-14)። ከሁለቱም ስለ እግዚአብሔር እውነት የሆነውን ነገር በተመለከተ በዝርዝር የሚነግረን የትኛው ነው? የጸሐይ ግባት/መጥለቅ የእግዚአብሔርን ትልቅነት፣ ኀያልነት፣ ለቀለሞች ያለውን ፍቅር ይገልጥልናል፤ ነገር ግን መሠረታዊ አስተምህሮዎችን ሊገልጥልን አይችልም። የጸሐይ መጥለቅ እንዴት እግዚአብሔርን ማስደሰት እንደምንችል ሊገልጥልን ይችላል? አይችልም፤ እርግጥ ጸሐይ ራሷ የሰራት ማን እንደሆነ ልትነግርህ አትችልም። ሰማያት ስለ አምላክ ታላላቅ ነገሮችን እንድታስብ ልያደርጉ ይችላሉ፤ ነገር ግን የምታስበው አምላክ በዓል ቢሆንስ?

እግዚአብሔር ራሱን የገለጠበት ቀዳሚው መገለጥ በቃላት ነው፤ በምስሎች አይደለም። ያንን ያደረገው ለመልካም ዓላማ ነው። ቃላት ትክክለኛ ናቸው፤ ነገሮችን የተሸለ ያብራራሉ። አንድ ስዕል ሺ ቃላትን ይተካል የሚባል የተለመደ አባባል አለ። ይህ እውነት የሚሆነው ቃላት የማይገልጡትን ስሜት ለሚገልጡ ስዕሎች ነው። አንድ ጎዳና የተቀመጠ፣ የተጠቃ፣ የቆሸሸ ወላጅ አልባ ልጅ ስዕል፤ በጋዜጣ ከተጻፈና ሁኔታውን ከሚያብራራ ሺ ቃል በላይ ሩሁሩህ ሊያደርግህ ይችላል።

ቢሆንም ምስሎች ድካም አለባቸው፤ ደስ እንዳለህ ልትተረጉማቸው ትችላለህ። ለዛ ነው ምስሎች ገለጻ የሚፈልጉት፤ ስዕሎችን በትክክል ለመተርጎም ቃላት ያስፈልጉሃል። ለምሳሌ ዓለምን ማን ፈጠረ የሚል ጥያቄ ቢነሳ የጸሐይ መጥለቅ መግለጫ ሊሰጥህ ይችላል። "በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ" እነዚህ አምስት ቃላት ከሚልዮን የጸሐይ መጥለቆች በላይ ጠቃሚ ናቸው ምክንያቱም ዓለማት የተፈጠሩት በበዓል፣ በአላህ ወይም ሌላ አምላክ ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱሱ ያህዌ/እግዚአብሔር እንደሆነ ያረጋግጡልናልና።

ወደ መለኮታዊ መገለጥ/አብርሆት ስንመጣ ቃላት ከምስሎች የተሸሉ ናቸው። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች "በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኖአልና።" (1 ቆሮ 1፡21) ሲል ተናግሯል። ኃጢአተኖች የዳኑት በተሳለው የመልዕክቱ ሞኝነት አይደለም። ድነት ቃላትን ይፈልጋል፤ የቅዱሳት መጽሐፍት ቃላት መነበብ ወይም መሰበክ አለባቸው። በአጭር ቃል እንደ ወንጌል ሰባኪ፤ ከቃላት ጋር መነጋገር አለብህ። እግዚአብሔር ራሱን የገለጠው በምስሎች ሳይሆን በቃላት ስለሆነ፤ ቃለትና ቋንቋ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ መሠረታዊ እውቀት ያስፈልገሃል።

## ጠብመንጃዎች እና ሰይፎች

በሠራዊት ውስጥ ያለ አዲስ ምልምል ወታደር እንኳ አለቃው ቀለዩና ምላጩ የት እንዳለ ካሳየው መተኮስ ይችላል። ነገር ግን በአራት መቶ ሜር የሚገኝን ኢላማ መምታት የሚችለው በሚገባ የሰለጠነ ወታደር ብቻ ነው። ለምን? ተኳሹ ከዚያን ያክር ርቀት የሚሄድ ጥይት መሃል ላይ ጥቂት ሰንቲሜትር ሊዛነፍ እንደሚችል ያውቃል፤ ግን ከልምዱና ከስልጠናው የተነሳ አስር ጥይት ተኩሶ አስሩም ዒላማውን ይጠብቅለታል። አዲስ ምልምሉ ወታደር ግን አስር ጊዜ ተኩሶ አስሩም ዒላማውን ስቶ ከዒላማው ጎን ያለውን ወፍ ይገድላል።

የእግዚአብሔርን ቃል ወደ መተርጎም ስንመጣ ወፍ መግደል አይጠበቅብህም፤ ሁል ጊዜ ዒላማውን ማግኘት ያስፈልግሃል። እንዴት? የጦር መሳሪያህን በማወቅ፤ በዚህ ጉዳይ ጠብመንጃ ሳይሆን ሰይፍ፤ የመንፈስ ሰይፍ (ኤፌ 5፡17)። የእብራይስጥ ይሁን የግሪክ፤ የአማርኛ ይሁን የእንግሊዘኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ስታጠና ሰይፉን በሚገባ ለመያዝና አለቃህን የምታስደስት ሠራተኛ የሚያደርግህን ክህሎት በመያዝ (2ጢሞ 2፡15) ስለ ቋንቋን ህግ በበቂ መጠን ማወቅ ይጠብቅብሃል።

በቀደመው ምዕራፍ እንዳልኩት ወደ ሰዋሰውና አገባብ ስንመጣ አብዛኛዎቹ ሰዎች ብቁ አይደሉም። ስለ ቋንቋ ህግ የሚያውቁት በቂ ነው ብለው የሚያምኑት ጥቂት ነው። ሰባኪዎች በአብዛኛው ሰዉ ተርታ የሚመደቡ አይደሉም። እንደ ሰባኪ የእግዚአብሔርን ቃል ራሱን ትይዛለህ፤ ወደ ቋንቋ ህግ ሲመጣ ዒላማውን እንደማይስት ስልጡን ወታደር መሆን አለብህ፤ የተሳለ ሰይፍ እንደሚይዝ አዳኝ። ስለሆነም በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው ለእግዚአብሔር በማጥናት እግዚአብሔርን መስበክ እንድትችል የሚረዱህን መሠረታዊ የሰዋሰው ህጎች ነው።

አንተን የቋንቋ ምሁር ማድረግ ዓላማዬ አይደለም፤ እኔም አይደለሁም። ነገር ግን ጥሩ ሰባኪ ለመሆን በሁለት ምክንያቶች፤ ከእነዚህ መሠረታዊ ሰዋሰዋዊ ቃላት ጋር መላመድ አለብህ። የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎች አንተ ስለ ሰዋሰውና አገባብ የሚሉትን እንደምታውቅ ስለሚገምቱ ሁል ጊዜ ሰዋሰውና አገባብ ይጠቀማሉ። በማብራሪያዎች ውስጥ ያሉትን ቴክኒካዊ ዋጋ በሙላት ለመረዳት ስለ ሰዋሰው መሠረታዊ ግንዛቤ ያስፈልግሃል። ሁለተኛው ሰዋሰዋዊና ሥነ-አገባብ ቃላትን ማወቅህ በስበከት ዝግጅት የምታደርገውን የጸሐፊውን ሐሳብ የመረዳት፣ የታሪካዊ ዓውዱን የማወቅና አጠቃላይ የጥናት ሥራ ቃላል ያደርግልሃል። እንዴት? የምትፈልገውን ነገር ስም ካወቅህ ጥናትህ ቀላል ይሆንልሃል። ለምሳሌ በሐይቅ ዙርያ ስራመድ ትልቅ፣

ኀይለኛ፣ የጥቁር ቡላ፣ ነጭ አንገት፣ ትከሻና ራስ ያለው ወፍ አይቻለሁ ብዬ ብነግርህ፤ እኔ ያየሁት የአፍሪካ ንስር አሞራ እንደሆነ ፤ትገምት ይሆናል። ነገር ግን እኔ ያየሁትን ወፍ ስም ባውቅ ኖሮ መገመትም ባለስፈለገ ነበረ።

በተመሳሳይ መንገድ፤ ቅዱሳት መጽሐፍትን ስትተረጉም እንዲህ እንዲሉ ብለው የሚጀምሩትን ቃላት እንዲህ እንዲሉ የሚሉ ቃላት ስብስብ ወይም የዓላማ አንቀጽ ብለህ ልትጠራ ትችላለህ። የምትፈልገውን ነገር ስም ማወቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ሥራን ፈጣንና ግልጽ ያደርገዋል። እስቲ አስበው አንድ መካኒክ ለተለያዩ መፍቻዎች የተለያየ ስም ባይኖረው ኖሮ፤ ወደ ቀኝ ከሚሽከረከረው መፍቻ ይልቅ የሶኬት ማስቀመጫ መጠየቅ ቀላል ይሆን ነበረ። ልክ እንደዚሁ የስብከት ዝግጅትህ በተሳለጠ መንገድ የሚሄደው የጋራ ወፎችንና የቋንቋ መፍቻዎችን ስታውቅ ነው።

አሁንም አላሳመነህም? አንድ ጡብ ሰሪ በጡብና አርማታ መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅ ይጠበቅበታል? አዎ ምክንያቱም ለሥራው መሠረታዊ ነገር ነውና። ይህንን ካለወቀ በመጀመሪያ የሥራ ቀኑ በምሳ ሰዓት ነው የምታባርረው። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚ ቃላትና ቋንቋ የአንተ መሠረታዊ መሳሪያዎች ናቸው። የሰዋሰው ሊቅ ወይም ምሁር መሆን አይጠበቅብህም፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ ለመፍታት የሰዋሰውን መሠረታዊያን ማወቅ አለብህ። አንተ ካልቻልክ ከምትሰብከው ጉባኤ ማን ይሰራልሃል?

## ቃላት

ቃላት እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን ለመገንባት የተጠቀማቸው ጡቦችና አርማታ ናቸው። እግዚአብሔር ያለውን በሚገባ ለመረዳትና ለእርሱ ለመስበክ፤ ምን ዓይነት ጡብና አርማታ እንደተጠቀመ ልታውቅ ግድ ነው።

**ስም፡** ስም ሰውን፣ ቦታን፣ ነገርን ወይም ረቂቅ ሀሳብን ይወክላል።

ለምሳሌ፡- ዮሐንስ፣ አፍሪካ፣ ኳስ፣ ፍትሕ

**ተውላጠ ስም፡** ተውላጠ ስም በስም ቦታ ያገለግላል

ለምሳሌ፡ እሱ፣ እሷ፣ እነሱ፣ አንተ፣ እነርሱ

**ግስ፡** ግስ ድርጊትን ወይም ሁኔታን ይወክላል።

የድርጊት ግሶች፡ መሮጥ፣ መዝለል፣ መጻፍ፣ መስበክ

የሁኔታ ግሶች፡ ነው፣ ነበር፣ እኔ

የመሆን ሁኔታ ግሶች የሚያመለክቱት የምታደርገውን ነገር ሳይሆን

የሆንከውን ነገር ነው። ጳውሎስ ሐዋርያው ነው። ጳውሎስ ረዥም ነው፣ ጳውሎስ እነዚያን ነገሮች አያደርግም፤ የሚኖረው በዚያ ክልል ነው። ሁኔታዊ ግሶች እንደ እኩል ምልክት ያገለግላሉ፤ ጳውሎስ=ሐዋርያ። ጳውሎስ = ረዥም

**ቅጽል** ቅጽል ስምን ወይም ተውላጠ ስምን ያብራራል

ምሳሌ፡ ቀዩ ኳስ፣ አሰልቺ መምህር፣ ታላቁ ሰባኪ

**ተውሳከ ግስ** ተውሳከ ግስ ግስን፣ ቅጽልን ወይም ሌላ ተውሳከ ግስን ያብራራል። እንዴት፣ መቼ፣ ለምን፣ የት ወይም ምን ያክል እንደሆነ ይገልጻል።

| | | |
|---|---|---|
| ምሳሌ፡ | በፍጥነት ሮጠ | (እንዴት እንደሮጠ) |
| | ስጀምር ፈርቶ ነበረ | (መቼ እንደፈራ) |
| | እጅግ አሰልቺ መምህር | (እስከ ምን ድረስ አሰልቺ እንደሆነ) |

**መስተዋድድ** መስተዋድድ ከፊትና ከኋላ ያሉትን ቃላት ግንኙነት የሚያሳይ ነው።

ምሳሌ፡ የፈረንሳይ ንጉስ፣ ቢል ወንበሩ ላይ ወደቀ

**ስማዊ ግስ** እነዚህ ድርጊቶችን ወደ ስም የሚቀይሩ ናቸው።

ምሳሌ፡ መዘመር እወዳለሁ፤ ሩጫ የምመርጠው የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ነው

## አረፍተ-ነገሮች

ጡብና አርማታ ቤት ለመገንባት መሠረታዊ ቁሶች ናቸው። ነገር ግን እነዚህን ሁለቱን በማጣመር ግድግዳ፣ ወለል ወይም መግቢያ ልትሰራ ትችላለህ። ቃላትም በተለያየ መንገድ ይጣመራሉ፤ የተለያዩ ትርጉሞችንም ይሰጣሉ። ቢል ኳሷን መታት ማለትና ኳሷ ቢልን መታችው ማለት ተመሳሳይ ትርጉም አይሰጥም። ዐረፍተ-ነገሮችን ለመመስረት ቃላት የምናጣምርባቸው የተለመዱ መንገዶች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

**ግስ**

ትርጉሙ ያለው በግስ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ምን እንደሚል ለማወቅ ከፈለግህ ግሱን ተመልከት። ግሶች አንተን ወደ ጸሓፊው መልዕክት የሚያደርሱህ የመንገድ ካርታዎች ናቸው። ግሶች ንቁ፣ ተግብሮ ወይም ሁኔታዊ ሊሆኑ ይችላሉ።

ቢሊ ኳሱን መታ። (ንቁ)

ቢል በኳሱ ተመታ (ተግብሮ)

ቢሊ ረጅም ነው። (ሁኔታዊ)

**ጥገኛ**

ጥገኛ የዓረፍተ-ነገር አካል ሆኖ አንድ ነገር የሚባልለት ነው።

ቢሊ ወደ ቤት ሮጠ

ዮሐንስ ወንድሜ ነው

ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ታስሮ ነበረ

**ቀጥተኛ ተሳቢ**

ቀጥተኛ ተሳቢ ተቀባይ የዓረፍተ-ነገር አካል ሆኖ የንቁ ግሶችን ድርጊት ተቀባይ ነው።

ቢሊ ኳሷን መታት (ኳሷ የንቁ ግሱን ድርጊት *መመታትን* ተቀብላለች)

እኔ ኢየሱስ አምላክ እንደሆነ አምናለሁ። (የማመንን ድርጊት የተቀበለው ምንድነው?)

በዚህ ዓረፍተ-ነገር፤ ኢየሱስ አምላክ ነው የሚሉ ቃላት የማመንን ድርጊት ተቀባዮች ናቸው። እነዚህ ቃላት እንደ ስም ይሆናሉ። ውስብስብም ይመስላል፤ *ኢየሱስ አምላክ* እንደሆነ አምናለሁ ማለት *እውነቱን አምናለሁ* ከማለት አይለይም።

**የግስ ገላጭ ቅጽል እና የስም ገላጭ ቅጽል**

ሁኔታዊ ግሶች ቀጥተኛ ተሳቢ የላቸውም። ከስም ወይም ከከቅጽል በፊት ይገባሉ። በአረፍተ ነገር ውስጥ የጥገኛ እኩል ናቸው።

ቢሊ ጓደኛዬ ነው።　　　ቢሊ=ጓደኛ (ከስም በፊት )

ቢሊ ረጅም ነው።　　　(ከከቅጽል በፊት)

**ባለቤት አመልካች ስሞች**

ሁለት ስሞች ለአንድ አካል ወይም ነገር ጎን ለጎን ሲገቡ የሚፈጠር ነው።

ለእኔ ከቅዱሳን ሁሉ ለማንስ ይህ ጸጋ ተሰጠኝ።

የእውነትን ቃል የድነታችሁንም ወንጌል ከሰማችሁ በኋላ

**ቀጥታ አመልካች**

ይህ የሚከሰተው አንድ አካል ወይም ሰዎች በስማቸው ሲነገራቸው ነው፤ ከሌሎቹ የዓረፍተ ነገር ክፍሎች ጋር ቀጥተኛ ሰዋሰዋዊ ግንኙነት የለውም።

ወንድሞች ሆይ ልዩ ልዩ መከራ ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት....

**ቃላትን ወይም ገላጮችን ማዳበር**

ቃላትን ማዳበር ቅጽሎችን፣ ተውላጠ ግሶችን እና እነዚህን የመሳሰሉትን ያጠቃልላል። እነዚህ ቃላት አገልጋዮች እንጂ ነገስታት አይደሉም። ሌሎች ቃላትን በመግለጥ ወይም በመወሰን ያገለግላሉ።

ቢል *ቀዩን*ኳስ ያዘ

ቢሊ የተቀራኒ ቡድን ተጨዋች *በጭንቅላቱ ወደ ግብ የመታትን ኳስ* ያዘ።

በሁለቱም ምሳሌዎች ላይ ያለውን *ኳስ* የሚለውን ስም ያደበረው ምድነው? በመጀመሪያው ቀይ የሚለው ቃል ሲሆን፤ በሁለተኛው ደግሞ *የተቃራኒ ቡድን ተጨዋች በጭንቅላቱ ወደ ግብ የመታት* የሚለው ነው። ቢሊ የያዛት ኳስ የትኛዋ እንደሆነች ለመግለጽ የገቡት ቃላት በርካታ ናቸው።

## የቃላት ቡድኖች

እንደ ሌሎቹ ጸሓፊዎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሓፊዎች ቃላትን በተለያያ መንገድ አጣምረው  ሐረጎችን፣ አንቀጾችን በማድረግ ተጠቅመዋል። እነዚህ እግዚአብሔር እውነቱን ወደ ሰዎች ያደረሰበት አውቶብሶች፣ መርከቦችና አውሮፕላኖች ናቸው።

## ሐረጎች

ሐረጎች ግስ የሌላቸውና በአንድ ላይ የሚጣመሩ የቃላት ስብስብ ናቸው። ሐረጎች ግስ ስለሌላቸው የዓረፍተ ነገሩ ዋና አካል መሆን አይችሉም፤ ሥራቸው ሌሎች ቃላትን ማዳበር ነው። ሐረጎች ልክ ከጭነት መኪና በኋላ እንዳሉት ተሳቢዎች ናቸው። ተሳቢዎች በራሳቸው መሄድ አይችሉም።

**ተሳታፊ ሐረግ፡** በጸሎታችን እያስታወስናችሁ ሁል ጊዜ እግዚአብሑርን ስለ ሁላችሁ እናመሰግናለን። (ተሳታፊ ሐረግ ጳውሎስ መቼ ና እንዴት ምስጋና እንደሚያቀርብ ያብራራል)

**መስተዋድዳዊ ሐረግ**   አብዛኛዎቹ መስተዋድዳዊ ሐረጎች ግሶችን ያዳብራሉ።

እኔን በጉጉት ፈልጎኛል    (ማንን እንደፈለገ)

መጥቶም ሰላምን ሰበከላችሁ    (ለማን ሰበከ)

በጸጋ ድናችኋልና    (እንዴት እንደዳናችሁ)

በበደላችን ሙታን ነበርን    (የት ሙታን ነበርን)

አንዳንድ መስተዋድዶች ስሞችን ያዳብራሉ

ጳውሎስ የክርስቶስ ኢየሱስ ሐዋርያ    (የቱ ሐዋርያ)

ስለ ኢየሱስ የሆነ እውነት    (የትኛው እውነት)

ያለ ተስፋ ያሉ ሕዝቦች    (የትኛው ሕዝብ)

## አንቀጽ

አንቀጽ በለቤትና ግስ ያለው የቃላት ስብስብ ነው። አንቀጽ ልክ እንደ አውቶቢስ ነው፤ ከሐረግ ይልቅ ብዙ ተሳፋሪ ይሸከማል፤ ስለዚህም የበለጠ አስፈላጊ ነው። ሐረጋት በሁለት ይከፈላሉ፤ ዋና እና ጥገኛ ሐረጋት።በራሳቸው የሚቆሙት ዋና ሐረጋት ሲባሉ በራሳቸው መቆም የማይችሉቱ ጥገኛ ሐረጎች ይባላሉ።

### ዋና ሐረግ

ዋና ሐረግ ራሱን ችሎ ይቆማል። በራሱ ይነዳል። ለምሳሌ *ጳውሎስ ጸሓይ እስኪ ትጠልቅ ድረስ ሰበከ* የሚለውን አረፍተ ነገር ተመልከት። ጳውሎስ ሰበከ የሚሉ ቃላት ራሰቸውን ችለው መቆም ይችላሉ። ጸሐይ እስክትጠልቅ ድረስ የሚሉትን ቃላት መጨመርም መቀነስም እንችላለን፤ ነገር ግን ጳውሎስ ሰበከ የሚሉ ቃላት ራሰቸውን ችለው መቆም ይችላሉ።

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሰበከ ማለትም እንችላለን። በዚህ አገላለጽ፤ ጳውሎስ ሰበከ የሚለው ቅድመ ሁኔታዊ ግሱን (ለቆሮንቶስ ሰዎች) የሚለውን የሚጎትት ጎታች ነው። በለቤትና ግስ፤ ጳውሎስ ሰበከ የሚሉ ቃላት ብዙ ቋንቋ አይፈልጉም በራሳቸው መቆም ይችላሉ። ነገር ግን እነዚያ ተጎታቾችም ጠቃሚ ናቸው፤ ጳውሎስ የሰበከው ለማን እንደሆነ ይነግሩናል። ዋናው ሐረግ በራሱ ይነዳል፤ ሌሎቹ እርሱን ያገለግላሉ።

## ጥገኛ ሐረጎች

ጳውሎስ ሰበከ ጸሐይ እስክትጠልቅ ድረስ

(ዋና) (ጥገኛ)

ጸሐይ እስክትጠልቅ ድረስ የሚሉ ቃላት ጥገኛ ሐረጎች ናቸው።

እኔ እስክመጣ ድረስ በሕዝብ ፊት ቅዱሳት መጽሐፍትን ለማንበብ ትጋ

(ጥገኛ) (ዋና)

በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ

(ጥገኛ) (ዋና)

የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ።

(ጥገኛ)                                                        (ዋና)

የጸሐፊው ዋና ሐሳብ የት ያለ ይመስልሃል? በዋና ወይስ በጥገኛ አንቀጽ? የሚሸውድ ጥየቄ አይደለም፤ የጸሐፊው ዋና ሐሳብ የሚገኘው በዋናው አንቀጽ ላይ ነው። ስለዚህ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚ ይህንን ለመለየት ችሎታህን ማዳበር እጅግ አስፈላጊ ነው።

## አንቀጾች

አንቀጽ አንድን ርዕስ የሚዳስሱ አረፍተ ነገሮች ጥርቅም ነው። አንቀጽ እንደ አውሮፕላን ነው፤ በውስጡ ሦስት መቶ ተጓዦች አሉ ነገር ግን የሚሄዱት ወደ አንድ መዳረሻ ነው። ለምሳሌ ኤፌ 5፡22-6፡9 ድረስ ያለው ስድስት አጫጭር አንቀጾች ናቸው። እያንዳንዱ የሚያወራው ስለ ስድት የተለያዩ ሰዎች ነው።

| | |
|---|---|
| ኤፌ 5፥22-24 | ሚስቶች |
| ኤፌ 5፥25-33 | ባሎች |
| ኤፌ 6፥1-3 | ልጆች |
| ኤፌ 6፥4 | አባቶች |
| ኤፌ 6፥5-8 | ባሮች |
| ኤፌ 6፥9 | ጌቶች |

ብዙውን ጊዜ የአንድ አንቀጽ ጭብጥ በመጀመሪያ ወይም በሁለተኛው አረፍተ ነገር ውስጥ ይገኛል። ለምሳሌ ባሎችን የተመለከተ አንቀጽ የሚጀምረው “ባሎች ሆይ ሚስቶቻችሁን ውደዱ” (ኤፌ 5፡25) የባል ሚስት የመውደድ ጭብጥ በቀሪዎቹ አረፍተ ነገሮች ክርስቶስ ለቤተ-ክርስቲያን ካለው ፍቅር ላይ ትኩረት በማድረግ እየደበረ የሚሄድ ነው።

## ተሳቢ እና ተጎታች አረፍተ ነገሮች

አንድን መኪና ከተጎታቹ ጋር ለማገናኘት ተሳቢ ያስፈልግሃል። ይህ ለሚዳብር አረፍተ ነገርም ይሰራል። ወደ ዋናው አረፍተ ነገር የሚጎትታቸውን ነገር ይፈልጋሉ። ይህንን አገናኝ እንለዋለን። ወደ አረፍተ ነገራችን እንመለስ፤ ጳውሎስ ጸሐይ እስክትጠልቅ ድረስ ሰበከ።

ጳውሎስ ሰበከ                ጸሐይ እስክትጠልቅ።

ጳውሎስ ሰበከ                ጸሐይ እስክትጠልቅ        *ድረስ*

በዚህ አረፍተ ነገር አገናኙ ድረስ የሚለው ቃል ነው። በተጨማርም አገናኙን ቃል ስትቀይር የአረፍተ ነገሩን ትርጉም ትቀይራለህ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሓፊዎች አገናኝ ቃላትንና የሚያድጉ አረፍተነገሮችን ተጠቅመዋል። እነርሱ የተጠቀሟቸውን አገናኝ ቃላት እስካላወቅህ ድረስ መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል ለመተርጎም ትቸገራለህ። በሚቀጥሉት አረፍተ ነገሮች እጅግ ጠቃሚ የሆኑ አገናኝ ቃላትን እንመለከታለን።

የሚከተሉትን ዓይነት አረፍተ ነገሮችና አገናኝ ቃላትን አጥና፤ አገናኝ ቃላት በደማቁ ተጽፈዋል። እነዚህ አገናኝ ቃላት በአረፍተ ነገሮች መካከል ያለውን ግንኙነት እንደሚወስኑ ሁሉ በአረፍተ ነገሮች መካከልም ያለውን ግንኙነት ይለያሉ።

**የአረፍተ ነገሮች ዓይነት**

**ንጽጽራዊ፡** እንደ ቅጽል ያገለግላሉ፤ ስምን ወይም ተውላጠ ስምን ያብራራሉ። (ማን፣ የቱ፣ የማን፣ ያ) እነዚህ አገናኝ ቃላት አንዳንድ ጊዜ ከማስተዋድድ ጋር ይጠመራሉ። በየት፣ በየትኛው ውስጥ፣ በማን መካከል

**በ** ዓለም ላይ የሚፈርድበትን ጊዜ ወስኗል።

እግዚአብሔር፤ **እርሱ** ሊዋሽ አይችልም።

እግዚአብሔር **እርሱ** ሰማያትንና ምድርን የፈጠረው ሰው በሰራው መቅደስ አያድርም።

**ጊዜያዊ** የዋናው አረፍተ ነገር ድርጊት መቼ እንደሚፈጸም ይናገራል። (መቼ፣ በኋላ፣ ከ፣ ከዚያ፣ ጀምሮ፣ በፊት)

**ውጤት፡** አረፍተ ነገሩ የሚያደብረውን ውጤት ይገልጸል። (ስለዚህ፣ ከዚህ የተነሳ፣ በዚህ ምክንያት)

**ምክንያት፡** ለሚያደብረው ግስ ምክንያቱን ይገልጻል። (ምክንያቱም፣ ለ፣ ጀምሮ)

**ማብራሪያ** የቀደመውን ሐሳብ ያብራራል (ለ፣ አየህ፣ ይህ፣ ይኸውም)

**ተነጻጻሪ** አንድን ነገር ካልነው ነገር ጋር ያነጻጽራል (ነገር ግን፣ ሆኖም፣ ቢሆንም)

**ሁኔታዊ** ዋናው አረፍተ ነገር ከመምጣቱ በፊት እውነት የሆነውን ሁኔታ ያብራራል።

(ካልሆነ፣ ምንም እንኳን፣ የ)

**ቅደም ተከተላዊ** በትረካ ውስጥ የታሪኩን እድገት ይገልጻል፤ ብዙ ጊዜ የምንጠቀመው በትረካ ነው። (ከዚያም፣ አሁን)

**ስም** እንደ ስም የሚያገለግሉ የቃላት ቡድን ነው። የሚገኘውም በብዛት በተቃውሞ ውስጥ ነው። ብዙውን ጊዜ አወቀ፣ ጸሎት በሚሉ ግሶች ጋር ጥቅም ላይ ይውላል። በጸሎት ወይም በእውቀት ይዘት ውስጥ ይገኛል። (ያ፣ ምን)

ማስተወሻ፡ በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ መልመጃ ተቀምጧል።

## ከግስ የሚፈጠሩ ሐረጎች

አገናኝ ቃላት በቀጥታ ከመታወቅ ይልቅ፤ በአውድ ከመለየታቸው በስተቀር ሐረጎች አረፍተ ነገሮች እንደሚሰሩ ይሰራሉ።

**ዓላማ፡** የግሱን አላማ ይገልጻሉ

**ጊዜያዊ፡** የግሱን ጊዜ ይገልጻል

**ምክንያታዊ፡** የግሱ ድርጊት ምክንያት ይገልጸል።

**መሳሪያዊ፡** ድርጊቱ የተከናወነበትን መንገድ ይጠቁማል።

**ሁኔታዊ** ከግስ ጋር በተመሳሳይ ሰዓት የሚከወኑ ነገሮችን ይገልጻል።

# ምዕራፍ ስድስት

## ዓረፍተ ነገርን ማቋረጥ

በሌቦች የተሰረቀ መኪና አይተህ ታውቃለህ? መስተወቱ ወልቆ፣ ቴፑ ተወስዶ፣ ሬድዮኑ ተነቅሎ፣ ወንበሩ ተገንጥሎ፣ ሞተሩና ኮፈኑ ብቻ የቀረ መኪና? ከውጪ በኩል ደግሞ ዝናብ መጥረጊያው፣ ጎማው፣ መብራቶቹ ተነቃቅለዋል። ባትሪው፣ አየር ማጣሪያውም እንዲሁ ተወስደዋል። እርግጥ የቀረው ለማንቀሳቀስ የማይመቸው የመኪናው ክፍል ነው።

እኔ ሁሉንም ዓይነት የወንጀል ድርጊቶች እጸየፋለሁ። በዚህ ክፍል ማስተማር የፈለግሁት አረፍተ ነገርን ስለ መስረቅ ወይም ማቋረጥ ነው። እኔ የፈለግሁት ሁሉንም የአረፍተ ነገሩን ሁለተኛ ክፍሎች ስለመቀነስ ነው። ዋናው ሐሳብ የአረፍተ ነገሩ ዋና ነገር ነው፤ ሌላውን አስወግደህ እርሱ ብታስቀረው ብቻውን ትርጉም ይሰጣል። ካለፈው ምዕራፍ ሁለቱን አረፍተ ነገሮች አስተውስ፤ ጳውሎስ ጸሐይ እስክትጠልቅ ድረስ ሰበከ፤ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሰበከ። የሚያዳብሩ ቃላትን ቀንስ።

ጳውሎስ ~~ጸሐይ እስክትጠልቅ ድረስ~~ ሰበከ።

ጳውሎስ ~~ለቆርንቶስ ሰዎች~~ ሰበከ።

የእነዚህ ሁለቱ አረፍተ ነገሮች ዋና አረፍተ ነገር የትኛው ነው? ያ ለምን ያስፈልጋል? እነዚህን አረፍተ ነገሮች የምትሰብክ ቢሆን ኖሮ፤ ዋናው ጭብጥህ የጸሐይ መጥለቅ ወይም በቆሮንቶስ የሚኖሩ ሰዎች ናቸው። ጳውሎስ ሰበከ የሚለው ሐረግ ዋና መሆኑን ለማሳየት፤ ያለ እዚህ ዓረፍተ ነገር ያለውን ቀሪ ክፍል እንመልከት።

~~ጳውሎስ~~ ጸሐይ እስክትጠልቅ ድረስ ~~ሰበከ~~።

~~ጳውሎስ~~ ለቆርንቶስ ሰዎች ~~ሰበከ~~።

ቀሪዎቹ ቃላት የተሟላ ሐሳብ ይሰጣሉ? በፍጹም። ጳውሎስ ሰበከ የሚለውን ስታወጣ መኪናውን መኪና ያደረጉ ነገሮችን የመኪናውን አካል፣ ሞተር እያጠፋህ ነው። ጥሩ ስብከት ለመስበክ ዋና ሀሳብህ ሁል ጊዜም ቢሆን በዋናው ላይ ማተኮር አለበት።

### መስተዋድዶችን መፈለግና ማቋረጥ

መስተዋድዶች ግንኙነትን የሚያሳዩ ቃላት ናቸው። ብዙዎቹ ቁስአካላዊ ግንኙነቶችን ያሳያሉ፤ በቤቱ ውስጥ፣ ከቤቱ በታች፣ ከቤቱ ጎን፣ ከቤቱ ውጭ። ሌሎቹ መስተዋድዶች ደግሞ የጊዜ ግንኙነትን ያሳያሉ። ከስብከቱ በኋላ፣ ከስብከቱ በፊት፣ በስብከቱ መሃል። ጥቂት መስተዋድዶች ደግሞ ጠቅላላ ወይም ረቂቅ ግንኙነቶችን

ያጎላሉ። ስለ እውነት፣ የጌታ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው። ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዙ መስተዋድዶችን ስታነብ ከየትኛው ምድብ እንደሆነ ትለያለህ።[36]

**ቁስአካላዊ ግንኙነቶች**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| በላይ | ከላይ | ወደላይ | ከታች | በታች | ከ…ሥር |
| አጠገብ | እስከ | ከ…. | ውስጥ | ከ….፣ ለ…..፣ በ….. | በ…. ውስጥ |
| ላይ | ውጭ | በውጭ | ከጎን | በዙሪያ በ… ላይ | በ…. መካከል |
| ከዳር እዳር | በሙሉ | ሙሉ በሙሉ | ያለቀ/ያለፈ | ወደ ከ….. አንጻር | በ |

በ…..ኋላ፣ ሥር፣ ከጀርባ፣ በስተጀርባ

**የጊዜ ግንኙነቶች**

| | | | |
|---|---|---|---|
| በፊት | በ….. ጊዜ | እስከ | በኋላ |

**ጠቅላላ ወይም ረቂቅ ግንኙነቶች**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ያህል፣ ስለ፣ ገደማ | ለ፣ በ፣ ጀምሮ፣ | እንደ | ከ…..በስተቀር | እንደ |
| ከ… ውጭ | ከ፣ ለ፣ በ፣ ሰ | | | |

እነዚህን የተለመዱ መስተዋድዶች ካየን በኋላ ከአረፍተ ነገር ውስጥ እነርሱን በማውጣት፤ ዋና ሐሳብ የማግኘት መልመጃ እንሠራለን። መስተዋድዶቹ በደማቁ ተጽፈዋል።

~~በዚህ ምክንያት~~ ደስ ይለኛል።

ዋና ሐሳብ፡ የጳውሎስ ደስታ

~~ስለ እናንተ ባሰብሁ ቁጥር~~ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።

ዋና ሐሳብ ፡ የጳውሎስን እግዚአብሔርን ማመስገን

36 This list of prepositions is adapted from a list in Wanda C. Phillips, Easy Grammar: Grades 4 and 5 (Scottsdale, Arizona: Easy Grammar Systems, 1996), 1.

~~በእስራቴም ወንጌልንም መመከቻና መጽኛ በማድረግ~~ ሁላችሁ ከእኔ ጋር በጸጋ ተካፋዮች ስለ ሆናችሁ፥ ~~በልቤ ትኖራላችሁና ስለ ሁላችሁ ይህን ላስብ ይገባኛል።~~

ዋና ሐሳብ፡ የጳውሎስና የፊልጵስዩስ ሰዎች አብሮ መሥራት

~~በክርስቶስ ኢየሱስ ፍቅር ሁላችሁን እንዴት~~ እንድናፍቃችሁ ~~እግዚአብሔር ምስክሬ ነውና።~~

ዋና ሐሳብ፡ የጳውሎስ መናፈቅ

አረፍተ ነገሩን ስትቀንስ ወይም ትቆርጥ የሚቀረው፤ የአረፍተ ነገሩ ልብ ነው። ዋና ግሱና ጥገኛው ብቻ ይቀራሉ።

**የሚዳብር አረፍተ ነገር**

በተመሳሳይ መልኩ ከሚዳብር አረፍተ ነገርም ውስጥ ቃላትን በማውጣት ዋናው ሐሳብ እንዲቀር ማድረግ እንችላለን። ይህንን ለማድረግ አጋናኝ ቃላት ያስፈልጉናል።

~~አንዱ ምንም ሳይሆን ምንም የሆነ ቢመስለው~~ ራሱን ያታልላልና።

ሁኔታዊ ጊዜያዊ

በጎ ነገር ከማድረግ አንታክት፤ ~~ተስፋ ካልቆረጥን ጊዜው ሲደርስ መከሩን እናጭዳለን~~።

ጊዜያዊ ሁኔታዊ

~~የኑሮአቸውንም ፍሬ~~ እየተመለከታችሁ ~~በእምነታቸው ምሰሉአቸው።~~

ተዛምዶአዊ

ይህን ስል ስለ ~~ጉድለት አልልም፤ የምኖርበት ኑሮ ይበቃኛል ማለትን ተምሬአለሁና~~።

የሚያብራራ

~~ፍቅራችሁ በእውቀትና በማስተዋል ሁሉ ከፊት ይልቅ እያደገ እንዲበዛ ይህን~~ እጸልያለሁ።

ስም

# ምዕራፍ ሰባት

## ስዕላዊ ንድፍ (መግለጫ)

የሴሚነሪ ትምህርቴን በምከታተልበት ወቅት፤ ከዘመናችን ተላላቅ ሰባኪዎች መካከል አንዱ ከሆኑት ከጆን ማክርተር ሥር ቁጭ ብዬ የመማር እድል አግኝቼ ነበረ። እርሳቸው በሚናገሩበት ጊዜ እግዚአብሔር ራሱ በድጋሚ የሚናገር ይመስላል። ሳልረዳቸው የቆየኋቸው ክፍሎች ግልጽ ሆኑልኝ። ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ክርስቶስ፣ ስለ ደህንነት ከዚህ በፊት አስቤ የማላውቃቸውን ተላላቅ ነገሮች እንዳስብ አደረገኝ። የማይቋረጡ የስበከቶቹን ዝርዝር ወደድኩ፣ ውስብስብ ነገሮችን ሰባብሮ ቀላል ባለ መንገድ የሚያስረዳበትን መንገድ ወደድኩ። ስለ እግዚአብሔር ቃል ወይም በእግዚአብሔር ዙሪያ አልሰበከም። የሰበከው የእግዚአብሔርን ቃል ነው፤ የቅዱሳት መጽሐፍትን ክፍሎች። የእግዚአብሔርን እህል እንጂ የሰውን ገለባ አልመገበንም።

እንዴት ነው ተላላቅ ሰባኪዎች እንደዚያ ማድረግ የሚችሉት? ምስጢራቸው ምንድነው? አንዳንዱ ከሰው አእምሮ በላይ የሆነ መንፈሳዊ ሥጦታ ነው።

ታላላቅ ሰባኪዎች እንዴት ነው እንደዚያ የሚያደርጉት? ምስጢራቸው ምንድን ነው? አንዳንዱ ያልተለመደ የመንፈሳዊ ስጦታ ነው። መንፈስ ቅዱስ የእያንዳንዱን ሰባኪ የመንፈሳዊ ስጦታ ጽዋ እርሱ ወደ መረጠበት ደረጃ ይሞላል። እርሱ የአንዳንድ ሰዎችን ጽዋ እስከ አፋፍ መሙላቱ የሚያስደስት እውነታ ነው። አንተ

እና እኔ ያንን መኮረጅ ወይም መቅዳት አንችልም። ይሁን እንጂ ሰባኪዎች ስብከታቸውን ለማዘጋጀት የሚጠቀሟቸውን ግሩም የሆኑትን የጥናት ዘዴዎች መኮረጅ እንችላለን።

አንዳንድ ሰባኪዎች የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት አሰፋሪ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፤ አንዳንዱን ዘዴ ለትገ፣ተው እንኳ የማትችለው ነው። አንዳንዶች የሚጠቀሙትን ዘዴ እኔ *የጠዋት ዜና ዘዴ* ብዬ እጠረዋለሁ። እነዚህ ሰዎች ስብከታቸውን የሚያዘጋጁት ቴሌቪዥናቸውን ከፍተው የጠዋት ዜና በማዳመጥ ወይም የዕለቱን ጋዜጣ በማንበብ ነው፤ በዜና የሰሙትን መሠረት አድርገው ስብከት ያዘጋጃሉ። ሌሎቹ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን ይጠቀማሉ፤ ነገር ግን ዘዴአቸው የሱቅ ዝርፊያ ዘዴ ይባላል። ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ክፍል ይይዙና ይሮጣሉ። ዐውዱን ችላ ይሉና መላ ስብከታቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሓፊው ሳይሆን እነርሱ ማለት የፈለጉትን ያስተላልፋል።

አንድ ጊዜ የሰማሁትን እስክጨርሰው ድረስ ያስጨነቀኝ ስብከት ነበረ፤ ሰባኪው የጠቀሰውና ያነበበው 2ቆሮ 2፡1-11 ነው። ነገር ግን ሰባኪው በቁጥር 9 ላይ የሚገኘውን “ጽፌ ነበረ” የሚለውን ቃል ነጥቆ፤ ክርስቲያኖች ከጳውሎስ ታማኝ ጸሓፊነትን እንዲማሩ ሰበከ። ይህ ሰባኪ ጳውሎስ የበደን ወንድም ይቅር ስለማለት የጻፈውን ሕይወት ለዋጭ መመሪያ ሙሉ በሙሉ ችላ ብሎት ነበረ። በምትኩ “ጽፌ ነበረ” የሚለውን ቃል በመያዝ ስብከቱን ደብዳቤ ስለመጻፍ አደረገው። ይህ ጥፋት ነው።

ሌላው ከዚህ ጋር የሚቀራረበው ዘዴ ደግሞ፤ የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍል በጥልቀትና የሥነ አፈታት መርሆን በመከተል በማጥናትና የቃሉን ትርጉም በመፈለግ ፈንታ፤ ክፍሉ የራሳችንን ሐሳብ እንድናገር የማስገደድ ዘዴ ነው። ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች “ይህ ክፍል ለእኔ እንዲህ ማለት ነው” ሲሉ ይደመጣል። ከክፍሉ የእግዚአብሔርን ትርጉም በመፈለግ ፈንታ የራሳቸውን ትርጉም ወደ ክፍሉ እየሰደዱ ነው። አንዳንዶች ደግሞ ይህንን ዘዴ፤ የመንፈስ ቅዱስ ዘዴ ካልኩት ጋር በማጣመር ከተጠያቂነት ማምለጥ ይፈልጋሉ።

አንዳንድ ሰነፍ ሰባኪዎች ደግሞ “ጌታ ሆይ እርዳኝ” ስል የጠራሁትን ዘዴ ይጠቀማሉ። እሁድ ስብከት አላቸው፤ ሳምንቱን ሙሉ መጽሐፍ ቅዱሳቸውን አላጠኑም፤ አልተዘጋጁም፤ ራሳቸውን በሥርዓት ቁጭ ብሎ ማጥናትንና መዘጋጀትን አላስደለሙም፤ እናማ ቅዳሜ ማታ “ጌታ ሆይ እርዳኝ” የሚል ጩኸት ያሰማሉ፤ እሁድ ጠዋት ጌታ መልዕክት እንዲሰጣቸው በመጠበቅ። ትጉህ፣ የማያሳፍሩ፣ እግዚአብሔር የመሰከረላቸው ሰባኪዎች ስብከት ለማዘጋጀት እነዚህን ዘዴዎች አይጠቀሙም። ምን ዘዴ ነው እነርሱ የሚጠቀሙት?

## አማራጮች

የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት ቅቡልነት ያላቸው የተለያዩ ዘዴዎች አሉ። ለምሳሌ እኔ በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ሳለሁ፤ ሁለት የጥናት ዘዴዎችን ተምረናል። ከእነዚያ ዘዴዎች መካከል አንዱ አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ለማጥናትና የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታ (ኮመንተሪ) ለመጻፍ ተስማሚ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ለአንዳንድ መምህራኖቼ ይህ ዘዴ ሰርቷል፤ ምንአልባት የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታ ስለምጽፉና በጆርናሎች ጽሑፎቻቸውን ስለሚያሳትሙ ይሆናል። ቢሆንም ይህ ዘዴ ስብከት ለማዘጋጀት ብዙም ጠቃሚ ነው ብዬ አላምንም። ስብከት ለማዘጋጀት ከክፍሉ ጋር በጥልቅ መቆራኘትና የክፍሉን የሀሳብ ፍሰት መከተል እንጂ ብዙ ሐተታ መስጠት ብቻ በቂ አይደለም።

ስለሆነም በሴሚነሪ ትምህርቴ እኔ ወደ ሁለተኛው ዘዴ ያጋደልሁ ነበረ፤ ይህም ዘዴ ሥዕላዊ መግለጫ ይባላል፤ በዚህ ምዕራፍ እናያለን። ሥዕላዊ መግለጫ ምንድነው? የሰዋሰው ና የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አገባብ ሥዕል

ነው። ጸሓፊው ክፍሉን እንዴት እንዳስቀመጠው ያሳይሃል። ይህ ዘዴ የቅዱሳት መጻሕፍት ቃላቶች በአንድ ገጽ ላይ በቀላሉ የማቀናበር መንገድ ነው። በዚህም የጸሐፊው ዋነኛ ሐሳብ ምን እንደሆነና ያንን ሀሳብ እንዴት እንዳደበረ በቀላሉ ማየት ይችላሉ። ሥዕላዊ መግለጫ ማውጣት መቁረጥ ከመጀመርህ በፊት እያንዳንዱን ቁራጭ እንድትለካ ያስገድድሃል።[37] ቶማስ ሼርነር "ሥዕላዊ መግለጫ የማውጣት ዘዴ ጥቅሙ፤ ተርጓሚው ጸሐፊው የተጠቀማቸውን ቃላት በቀስታና በጥንቃቄ እንዲያይ ማስቻሉ ነው" ብሏል።

የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍል ሥዕላዊ መግለጫ ለማውጣት ሁለት የተለያዩ መንገዶች አሉ። የመስመር ንድፍ እና የጽሑፍ ንድፍ ይባላሉ።

**የመስመር ንድፍ**

እዚህ ጋ የመስመር ስዕል አለ

**የጽሑፍ ንድፍ**

በመጀመሪያ

እግዚአብሔር ሰማያትን

እና

ምድርን

ፈጠረ

[37] Thomas Schreiner, Interpreting the Pauline Epistles (Grand Rapids, Michigan: Baker Book House, 1990), 77-78. Schreiner is referring to line diagramming, but his point also applies to block diagramming.

የሁለቱም ዘዴዎች ግብ አንድ ነው፤ አንተ በክፍሉ ውስጥ ስላሉ እያንዳንዱ ቃላት ወይም የቃላት ስብስብ በጥንቃቄ እንዲታስብ ማድረግ። የመስመር ንድፍ ከጽሑፍ ንድፍ ይልቅ እያንዳንዱን ቃል በጥልቀት ስለሚያሳየን ጠንካራ ጎን አለው። ቢሆንም በመጀመሪያዎቹ የአገልግሎት ዘመኖቼ የተጠቀምሁት የጽሑፍ ንድፍን ነው። በሦስት ምክንያቶች። አንደኛ ረዣዥም ክፍሎችን ለመሥራት የመስመር ንድፍ ትንሽ አስቸጋሪነት አለው፤ ሁለተኛ ከጊዜ አጠቃቀም አኳያ የተሻለ ስለሆነ እና ሦስተኛው ከጊዜ አጠቃቀም አንጻር በቀላሉ ለመሥራት ስለሚያስችል፤ ምክንያቱም በመስመር ንድፍ እያንዳንዱን መስመር ስትስል የምትወስደው ጊዜ ብዙ ነው። የመስመር ንድፍ ዘዴን እጠቀማለሁ ካልክ ግን የጌታ ጸጋ ይብዛልህ። በዚህ ምዕራፍ የምንቀጥለው የጽሐፍ ንድፍ በመጠቀም ነው። ይህ ዘዴ ለመማር ቀላል፣ ለመጠቀም ፈጣንና የሚመታውም ግብ አንድ ነው።

ምንድነው የሚያሳካው? ሥዕላዊ መግለጫ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልን አንድ ወጣት የሣር ማጨጃ ማሽን ሞተር እንደሚያየው ነው የሚመለከተው። ተገጣጥሞ ያለን ሞተር ውስጡ እንዴት እንደሚሰራ አናውቅም። ነገር ግን ማሽን ተፈታትቶ ሲታይ እንዴት እንደሚሰራ ማወቅ ይቻላል። ሥዕላዊ መግለጫም የሚያሳካው ተመሳሳይ ነገር ነው፤ ሰባኪው የውስጠኛውን ክፍል እንዲያይው ያደርግለታል፤ አሁን ዘፍጥረት 1፡1 እንዴት እንደሚሰራ አሁን አወቅሁ ይላል። አንድ ክፍል እንዴት እንደሚሰራ በትክክል ካወቅህ እግዚአብሔርን ለመስበክ ተዘጋጅተሃል ማለት ነው።

**ሥዕላዊ ንድፍ/መግለጫ**

ቃላት ውጤታማ ነገሮች ናቸው፤ ነገር ግን ውስንነቶች አሏቸው። ለምሳሌ ስለ ጫማ ክር አስተሳሰር የሚያስተምር ትምህርት ወይም የሚያሳይ ምስል በማየት ጫማ ማሰር ቀላል ነው። ልክ እንደዚሁ ስዕላዊ መግለጫ እያዩ መማር ቀላል ነው። ስለዚህ እንዴት እንደሚሰራ አጭር መግለጫ ቀጥሎ አሳየሃለሁ።

በመጨረሻም፤ በሚቀጥሉት ምዕራፎች በራሳችሁ እንድትሰሩትና እንድትለማመዱት ዕድል ታገኛላችሁ። እመኑኝ፤ ጫማችሁን ማሰር ከቻላችሁ ስዕላዊ ንድፍ ማውጣት ትችላላችሁ።

ስዕላዊ መግለጫ ወይም ንድፍ ማውጣት ሁለት ደረጃዎች አሉት

ዋናውን ሐሳብ ጻፍ፤ ዋናውን ግስ፣ ቅጽሎቹን (ካሉ ሌሎችንም)

ዋናውን ሐሳብ የገነቡ ቃላትን ጻፍ።

ከደረጃ አንድ እንጀምር። በግራ በኩል ባለው ህዳግ ዋናውን ሐሳብ ከመጻፍህ በፊት፤ ዋናው ሐሳብ የቱ እንደሆነ መወሰን አለብህ። ለዚህ ነው ዐረፍተ ነገር ማራገፍን በመጨረሻው ምዕራፍ የተለማመድነው። ዋና ሐሳብ ራሱን ችሎ መቆም የሚችል የአረፍተ ነገር ክፍል ነው። ዘፍጥረት 1፡1ን እንመልከት

ዘፍጥረት 1፥1

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ።

በዚህ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ራሳቸውን ችለው የሚቆሙና ትርጉም የሚሰጡ ቃላት የትኞቹ ናቸው? የተወሰኑ ቃላትን ስታወጣ በመጨረሻም *እግዚአብሔር ፈጠረ* የሚለው ይቀራል። ይህ የዐረፍተ ነገሩ አንኳር ነው። ምንም ሳትጨምር እነዚህን ማለት ትችላለህ። ቀሪዎቹ ቃላት መቼ እንደፈጠረና፤ ምን እንደፈጠረ የሚያብራሩ ናቸው። ስለዚህ የእግዚአብሔር የመፍጠር *ሥራ* ዋናው ሐሳብ ነው።

የዘፍጥረት 1፡1ን ስዕላዊ ንድፍ ማውጣትን ለመጀመር፤ በወረቀትህ የግራ ጠርዝ እግዚአብሔር ፈጠረ የሚለውን ትጽፋለህ። የመፍጠሩ *ሥራ* ዋና ተፈጻሚ የሆኑትን *ሰማያትንና ምድርንም* መጨመር ትችላለህ። እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ሁለት ነገሮች ለማሳየት እንደሚከተለው መጻፍ ትችላለህ።

እግዚአብሔር ፈጠረ ሰማያትን
እና
ምድርን

ቀሪዎቹ ጥቅሶች ምን ይሆናሉ? በሁለተኛው ደረጃ ዋናውን ሐሳብ ያዳበሩ ቃላትን ጻፍ። በዘፍጥረት 1፡1 የሚያዳብሩ ቃላት *በመጀመሪያ* የሚሉ ናቸው። ይኼ የሚያሳየው *ፈጠረ* የሚለው ዋና ሐሳብ ሲሆን *በመጀመሪያ* የሚለው ደግሞ የሚያዳብር ሐሳብ መሆኑን ነው።

እግዚአብሔር ፈጠረ ሰማያትን
እና
ምድርን

በመጀመሪያ

ገላትያ 6፥1

> ወንድሞች ሆይ፥ ሰው በማናቸውም በደል ስንኳ ቢገኝ፥ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየውሃት መንፈስ አቅኑት፤ አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ።

የዚህ ዓረፍተ ነገር ዋና ሐሳብ የትኛው ነው? ይህ ምሳሌ ከዘፍ 1፡1 ትንሽ ከበድ ይላል፤ ምክንያቱም ብዙ ግሶች አሉበትና። በዚህ ክፍል 5 ግስ መሳይ ቃላት እንዳሉ ታያለህ፤ ቢገኝ፣ አቅኑት፣ ጠብቅ፣ እንዳትፈተን። ዋናውን ሐሳብ ለማውጣት እርሳስ ተጠቀም። የቅድ ውሰኔ ሐረጎችንና አዳጊ ግሶችን ስታወጣ እንዲህ ይመጣል።

> ~~ወንድሞች ሆይ፥ ሰው በማናቸውም በደል ስንኳ ቢገኝ፥ መንፈሳውያን የሆናችሁ~~ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው ~~በየውሃት መንፈስ~~ አቅኑት፤ ~~አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ።~~

በእርግጠኝነት ***እናንተ.... እንደዚያ ያለውን ሰው አቅኑት*** የሚለውን አግኝታችኋል። ሌሎቹ ይህንን ሐሳብ የሚያደብሩና በራሰቸው መቆም የማይችሉ ናቸው። ነገር ግን ***እናንተ.... እንደዚያ ያለውን ሰው አቅኑት*** የሚለው ትዕዛዝ ራሱን ችሎ ይቆማል፤ ስለዚህ የጥቅሱ ዋና ሐሳብ ነው። ዋናውን ሐሳብ ስታገኙ ማቅናት ወይም መመለስ የጳውሎስ መልዕክት እንደሆነ ትረዳላችሁ። ምንአልባት ስለ መንፈሳዊነት፣ ስለ መፈተን፣ ስለ የውሃት ለማስተማር ትፈልግ ይሆናል፤ እነዚህ ሁሉ ጥሩ ርዕሶች ናቸው፤ ነገር ግን ጳውሎስ መልዕክቱን ስጽፍ እግዚአብሔር ማስተማር የፈለገው ሐጥአተኛውን ስለማቅናት ወይም መመለስ ነው።

የገላ 6፡ቀ ስዕላዊ ንድፍ ለማውጣት ዋናውን ሐሳብ ከግራ ጠርዝ በመጻፍ ጀምር

እናንተ　　　　እንደዚያ ያለውን ሰው　　　　አቅኑት

ይህንን ካደረግን በኋለ ወደ ሁለተኛው ደረጃ እንሸጋገራለን።ዋናውን ሐሳብ ያዳበሩትን ቃላት በቀኝ ህዳግ ጻፍ።

ወንድሞች ሆይ

እናንተ　　　　እንደዚያ ያለውን ሰው　　　　አቅኑት

መንፈሳዊያን የሆናችሁ　　　　ሰው በማንኛውም በደል ስንኳ ቢገኝ

በየውሃት መንፈስ

እንዳትፈተን

ራስህን ጠብቅ

የገላ 6፡1 እያንዳንዱ ክፍል የሚያጎላውን ዋና ሐሳብ እንደሚጠቁም ልብ በል። *መንፈሳዊያን የሆናችሁ* የሚለው የሚያብራራውን *እናንተ* የሚልውን ነው። ስለዚህም ነው እናንተ ከሚለው ስር የተቀመጠው። ሌሎቹ ቃላት ደግሞ አቅኑት የሚለውን ለማዳበር የገቡ ስለሆነ ከእሱ ስር ተጽፈዋል። አረፍተ ነገሩን ስታነብ እንደዚህ ዓይነት ግንኙነቶችን ለመለየት የአእምሮ ጆሮህን ማሰልጠን አለብህ። እንዴት ያልህ እንደሆነ ዋናውን ግስ ከሌሎቹ በፊት ደጋግሞ በማድረግ።

እናንተ አቅኑት ……… ሰው በማንኛውም በደል ቢገኝ ስንኳ

እናንተ አቅኑት……. በየውሃት መንፈስ

እናንተ አቅኑት……. ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ።

**ብዙ አረፍተ ነገሮች**

አብዛኛውን ጊዜ የምትሰብከው ስብከት የቃል ክፍል ከአንድ አረፍተ ነገር ይበልጣል። በዚህ ጊዜ ስዕላዊ ንድፍ ለማውጣት ሁለት አማራጭ አለህ። ሁሉም አረፍተ ነገሮች በአንቀጹ ውስጥ እኩል ጥቅም ካላቸው በግራ ህዳግ ትጽፋቸዋለህ። ከዚህ ቀጥሎ በምናየው የ1ኛ ተሰሎንቄ 5፡16-18 ውስጥ ያሉት ሁሉም ትዕዛዞች እኩል ጥቅም አላቸው፤ አንዳቸው ሌላውን ለማዳበር የገቡ አይደለም። ስለዚህ ሁሉንም በግራ ህዳግ እናሰፍራለን ትዕዛዞቹን የሚያዳብሩ ቃላት (ለምሳሌ ሁል ጊዜ፣ ሳታቋርጡ፣ በማንኛውም ሁኔታ) አገልጋዮች ናቸው፤ እነርሱ ይዋጣሉ። ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና የሚለውንም እንዲዋጥ አድርጌአለሁ፤ ምክንያቱም የሚሰራው ለመጨረሻው ትዕዛዝ ነውና።

ደስ ይበላችሁ

        ሁል ጊዜ

ጸልዩ

        ሳታቋርጡ

አመስግኑ

        በማንኛውም ሁኔታ

ይህ

የእግዚአብሔር ፈቃድ

ለእናንተ

በኢየሱስ ክርስቶስ

በብዙ ሁኔታዎች አንድ አረፍተ ነገር ሌሎች አረፍተ ነገሮችን ያዳብራል። በመዝሙር 23 የሚገኙትን ሁለት የተሟሉ አረፍተ ነገሮችን እንያለን። *እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም።* በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? ውጤቱ ነው። እግዚአብሔር እረኛዬ ስለሆነ የሚያሳጠኝ የለም። እግዚአብሔር እረኛዬ ነው የሚለው ዋና ሐሳብ ሲሆን፤ ምንም አለማጣት ውጤቱ ነው። በሁለቱ አረፍተ ነገሮች ጸሐፊው የፈለገውን ግንኙነት ለማሳየት መካከል *ከዚህ የተነሳ* የሚለውን ቃል በቅንፍ ውስጥ ጨምሬአለሁ።

እግዚአብሔር እረኛዬ ነው

[ከዚህ የተነሳ]

የሚያሳጣኝም የለም

ሁለት አረፍተ ነገሮች ሙሉ ሲሆኑ፤ ሁለተኛው ቀዳሚውን ያዳብራል። የቀዳሚው አገልጋይ አይደለም፤ እኩል ንጉስም አይደለም። ምንአልባት ልዕል ሊሆን ይችላል። በአረፍተ ነገሮች መካከል ያለው ግንኙነት በአረፍተ ነገሮች ውስጥ ያለውን ግንኙነት ያህል ወሳኝ ናቸው። አብዛኛውን ጊዜ በአረፍተ ነገሮች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመወሰን ጸሓፊዎች ከዚህ የተነሳ፣ ስለዚህ፣ ነገር ግን ወዘተ የሚሉ ቃላትን ይጠቀማሉ።

ሐዋርያው ጳውሎስ አገናኝ ቃላትን የሚወድ ነው። ለምሳሌ ሮሜ 1፡15 እና 16 ሁለት የተለያዩ አረፍተ ነገሮች ናቸው፤ ነገር ግን ቁጥር 16 የሚጀምረው ጳውሎስ ወንጌል ለሮሜ ሰዎች ለመስበክ ለምን እንደጓጓ በማሳየት ነው።

እኔ እጓጓለሁ (ቁ 15)

ወንጌልን ለመስበክ

ለእናንተ

በሮም ለምትኖሩ

ምክንያቱም (ቁ 16)

አላፍርም

በወንጌል

የእግዚአብሔር ሐይል

ለድነት

ለሁሉም

ለሚያምን

በመጀመሪያ ለአይሁድ

ደግሞም

ለግሪክ ሰው

**ማጠቃለያ**

ስዕላዊ ንድፍ ለማውጣት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ለማጥናት እጅግ ጥሩ መሳሪያ ነው፡፡ በዋና ሐሳብና በሌሎቹ መካከል ያለውን ልዩነት በግልጽ ያስቀምትልናል፡፡ ንጉሱን ከአገልጋዩ ይለያል፡፡ አያያዥ ቃላትን በጥንቃቄ በማየት የጸሓፊውን ሐሳብ እንድትደርስበት ይረደሃል፡፡ በጥንቃቄ ለተሞላ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፤ ለወሳኝ ስብከት ጠቃሚ ናቸው፡፡

ተጨማሪ ምሳሌዎች

2 ጢሞ 1፡14

[አንተ] ጠብቅ　　　　መልካሙን አረደራ　　　　　　　　　[ዋና ሐሳብ]

የተሰጠህን

ለአንተ

በመንፈስ ቅዱስ

በእኛ ውስጥ በሚኖረው

1ጢሞ 3፡14

እጽፍልሃለሁ　　　　ይህን ትዕዛዝ

ለአንተ

ለመምጣት ተስፋ እያደረግሁ

ወደ አንተ

ቶሎ

**1 ጢሞ 6፡3-4**

ያ ሰው በትዕቢት ተወጥሯል　　　　　　　　[ሁለት ዋና ሐሳቦች]

ደግሞም

አንዳችም አያውቅም

ቢሆን

ማንም የሐሰት ትምህርት ቢያስተምር　　　　[ዋና ሐሳብ ትክክል መሆኑን ያብራራል]

ደግሞም

[ማንም]

የማይስማማ ቢሆን

ጤናማ ቃላት

ከኢየሱስ ክርስቶስ

እና

ትምህርት

መልካምነትን ከሚያጎለብት

# ምዕራፍ ስምንት

# ክፍሉን መዘርዝርና ማጠቃለል

ጥሩ ስብከት ለማዘጋጀት የሚያስፈልግህ ስዕላዊ ንድፍ ማውጣት ብቻ ነው? አይደለም። ስዕላዊ ንድፍን መስበክ አትችልም። ስለዚህ በንድፍ ያገኘሀውን የምትገልጥበት መንገድ ያስፈልግሃል። ከሁሉ በላይ ያገኘሀውን ነገር ለምትሰብከው ሕዝብ የምትነግርበት ግልጽ፣ ተዓማኒ እና ለመያዝ ቀላል የሆነ መንገድ ያስፈልግሃል። ይህንን ማድረግ የምትችለው እንዴት ነው?

**የትርጓሜ መግለጫዎች**

ሁለት ሰዎች በአጥር ጥግ ቆመው ማሳ ውስጥ ያሉ እንስሳትን እየተመለከቱ ነው። በመስኩ ላይ የተለያዩ አይነት እንስሳት ሳር እያጋጡ ነው። የመጀመሪያው ሰውዬ (ከከተማ የመጣው) ወደ ሁለተኛው ሰው (ገበሬ) በማየት፤ “እነዚያ እንስሳት ያንተ ናቸው?” በማለት ይይቀዋል። ገበሬውም መለሰለት “አዎ የእኔ ናቸው ሰባት ላሞች፣ አስረ አንድ በጎች እና አስራ ሁለት ፍየሎች ናቸው።” ገበሬው ለከተሜው ነገሮችን ቀላል ማድረግ ስለፈለገ እንስሳቱን በሦስት ምድቦች ከፍሎ ነው የነገረው። ላሞች፣ በጎች እና ፍየሎች። የትርጓሜ መግለጫም ለአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚያደርገው ተመሳሳይ ነገር ነው። በአንተ ንድፍ የወጡ የተለያዩ ሐሳቦችን በየምድባቸው ያስቀምጣቸዋል። አብረው የሚሄዱ ነገሮችን አብሮ ማድረግ፤ ላሞችን ከላሞች ጋር፣ በጎችን ከበጎች ጋር ሌላውንም እንዲሁ።

አንድን ክፍል በዝርዝር ማውጣት አስቸጋሪ ሥራ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ንድፍ ማውጣቱ ይረዳሃል። ልክ እንደ በግ ወይም ፍየል የአንተም ስዕላዊ ንድፍ ሐሳብህን በመንጋ አስቀምጦልሃል። በጎች ወደ ቀኝ፤ ፍየሎች ወደ ግራ፤ ላሞች ወደ መሃል። ስለዚህ የትርጓሜ መግለጫ ለማውጣት ስዕላዊ ንድፍህን ታያለህ ከዛም በራስህ ቃላት ታብራራለህ። የዘፍ 1፡1ን ምሳሌ እንጠቀም።

ስዕል አለ

ከላይ ያለው ንድፍ የዘፍጥረት 1፡1 ያለውን መንገ በሦስት ቡድኖች ለይቶ አስቀምጧል። ላሞች፣ በጎች፣በሦስት መንጋ ለይቷል። ዘፍ 1፡1 የሚናገረው ስለ ፈጣሪ ነው፤ ፍጥረታትን ስለፈጠረው ፈጣሪ። ያንን የሚገልጽ መግልጫ ወይም ዝርዝር ለማውጣት፤ እያንዳንዱን ሐሳብ የሚገልጥ ቃል ያስፈልግሃል።

| | |
|---|---|
| ፈጣሪ | እግዚአብሔር |
| ፍጥረታት | ሰማያትና ምድር |
| የዘመን ቅደመ ተከተል | በመጀመሪያ |

የስዕል ንድፉን መስበክ አትችልም፤ ግን የትርጓሜ ማውጫውን ወይም መግለጫውን መስበክ ትችላለህ። አሁን ገላ 6፡1 እንመልከት።

**እዚህ ጋር ስዕልአለ**

ዋናው ግስ ዋናውን ሐሳብ ይመሰርታል። ማቅናት/ማደስ። እንዴት ነው ጥቂት ለየት የሚሉ ቃላትን በመጠቀም የክፍሉን ሐሳብ መዘርዘር ይቻላል?

| | |
|---|---|
| የሚያቀና ኮሚቴ | እናንተ መንፈሳዊያን የሆናችሁ |
| የሚታደሰው/የሚቀናው ጥፋተኛ | በበደል ውስጥ የገባ ሰው |
| የማቅናት ሁኔታ | ሰው በኃጢአት ቢገኝ እንኳ |
| የማቅናት ርህራሄ | በየዋሃት/ገርነት መንፈስ |
| የማቅናት ጥንቃቄ | ራስን መመርመር/መፈተን |

እርግጥ፤ ይህ ያአንተ ማውጫ ነው፤ በአንዳንድ ነጥቦች ሥር ንዑሳን ነጥቦችን ማካተት ትችላለህ። ለምሳሌ የሚያቀና ኮሚቴ በሚለው ሥር፤ ስለ ኮሚቴው መስፈርቶች፣ መንፈሳዊ ብስለት።

በቀደመው ምዕራፍ የዋልተር ካሴርን "ዋና ዓላማው ቅዱሳት መጽሐፍት የመልዕክታችንን ቅርጽ፣ አመክንዮና እድገት እንዲወስኑ ነው።"[38] የሚለውን አባባል ዋቢ አድርጌ ነበር። ያንን የዘፍጥርት 1፡1ን እና ገላ 1፡1ን ማውጫ ስናወጣ አሳክተናል? አዎ። ልክ ሸክላ ሰሪው በእጁ ያለውን ሸክላ ቅርጽ እንደሚያስዘው፤ የእግዚአብሔር ቃል ለእኛ የትርጓሜ ማውጫ ቅርጽ ይሰጣል። አንተ የእነዚህ ክፍሎች ሰባኪ ብትሆን፤ ለእግዚአብሔር ትሰብካለህ ምክንያቱ እርሱ ለሙሴና ጳውሎስ ያለውን በድጋሚ እያልክ ስለሆነ።

---

[38] Walter Kaiser, Toward an Exegetical Theology, 160.

**የብዙ ቁጥር ስም ማጠቃለያ**

ሁለት ሰዎች የእንስሳትን መንጋ ወደ ሚመለከቱበት ታሪክ ወደኋላ እንሂድ። ገበሬው በመንጋዬ ውስጥ ጆሮውን የተቆረጠ አንድ ከብት፣ ቀንዱን የተሰበረ አንድ ቡናማ ፍየል አለ ማለት ይችላል። አንድ ጥቁር እግር ያለው ቢጫ ፍየል አለኝ፣ በቀኝ እግሩ የተሰነጠከ ሰኮና ያለው አንድ በግ ደግሞ አለኝ… ወዘተ እያለ ቢቀጥል። በመስክ ውስጥ ያሉትን እንስሳት ዓይነት ሁሉ እናስተውሳለን? አይመስለኝም። ማጠቃለያ ያስፈልገናል።

ይህ ለስብከትህም ይሠራል። የአድማጮችህ የአእምሮ እግር እንደ ዝንጀሮ ከዛፍ ዛፍ በመንጠልጠል የሄድክበት ሁሉ መሄድ ይደክመዋል። እርግጥ ነው ዝርዝር ነገር ይፈልጋሉ፤ ዝርዝር ነገር ካልተሰጠው ማንም መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ አይረዳውም፤ ነገር ግን ለምትሰብክበት ጉባኤ ዝርዝር ነገር ለመስጠት የተጠቃለለ ሐሳብ መያዝ አለብህ። አንተ የምትሰብከውን ክፍል ለሳምንታት አጥንተሃል፤ ጉባኤው ግን አላጠናም፤ ስለዚህ ስለ ስብከት ክፍልህ ጠቅለል ያለ ነገር ልትሰጣቸው ይገባል።

ጥሩ ሰባኪዎች በስብከታቸው ጅማሮ ላይ ጉድጓድ ይቆፍሩና መንገዳቸው ወዴት እንደሚወስድ ምልክት ያቆማሉ። በመንጋው ስብከቴ ውስጥ ሦስት ዓይንት እንስሳት አሉ (ሦስት ነጥቦች)።

እንደዚህ ዓይነት መግለጫ በስብከትህ ጅማሮ ላይ ማስቀመጥ አንተንም አድማጮችህንም ይጠቅማል። በመጀመሪያ አንተን በደመነፍስ ከመገመት ያድንሃል። የአሰፓልት መንገድ ትተህ በጠጠር መንገድ እንዳትንከራተት ይጠብቅሃል። አድማጮችህም ሀሳብን ሳይዙ እንዳይቀሩ ይረዳቸዋል። የ45 ደቂቃ ስብከት ረጅም ጉዞ ነው ስለሆነም አድማጮችህ በሚገባ እንዲከተሉህ በስብከትህ ጅማሮ የምትሄድበትን መንገድ ካርታ ስጣቸው።

በአንድ ክፍል ያለውን ሐሳብ በአንድ አረፍተ ነገር ለማጠቃለል፤ ብዙ መንገዶች አሉ። አንዱ *የብዙ ቁጥር ስሞች ማጠቃለያ* ይባላል። በምሳሌአችን የተጠቀምነው ገበሬ ጥሩ ማጠቃለያ አረፍተ ነገር ሰጥቶናል። በእንስሳት መንጋዬ ውስጥ ላሞች፣ በጎችና ፍየሎች አሉ በማለት።

ለምንድነው የብዙ ቁጥር ስሞች ተብሎ የሚጠራው? ምክንያቱም በስብከት ውስጥ የሚነሱ ነጥቦች ከአንድ በላይ ስለሆኑ ነው። ሁለት፣ ሦስት ወይም አራት ሊሆን ይችላል። በቅድሙ ምሳሌ ሦስት ዓይነት እንስሳት አሉ፤ ወይም መልዕክቱ ስለ ኢየሱስ አራት እውነቶችን የሚያስተምረን ሊሆን ይችላል። የብዙ ቁጥር ስም ነው፤ ሙሉውን ምንባቡን ወይም ክፍሉን በአንድ አረፍተ ነገር ያጠቃልልልናል።

ወደ ሱቅ ሄደህ አስር ብርቱካኖች ብትገዛና በቦርሳ ወይም በፔስታል ብትይዛቸው፤ ፔስታሉ ጉዞህን ቀላል ያደርግልሃል ምክንያቱም አስሩንም ብርቱካኖች ይዞልሃልና። በዘፍ 1፡1 ሦስት ብርቱካኖች ብቻ ናቸው ያሉት፤ ይህንን እንዲሸከሙ ፔስታል ብትሰጣቸው ለአድማጮችህ ብዙ ነገር አድርገሃል። እስቲ ዘፍ 1፡1ን በአንድ ፔስታል ውስጥ እንዴት እንደምንይዝ እንይ።

| | |
|---|---|
| ፈጣሪው | እግዚአብሔር |
| የተፈጠረው | ሰማያት/ምድር |
| የዘመን ቅደም ተከተል | በመጀመሪያ |

የዘፍጥ 1፡1ን ማውጫ ማጠቃላያ ለመሥራት የምትችልበት አንድ መንገድ አለ። "በዘፍ 1፡1 እንዴት እዚህ እንደደረስክ ለማወቅ እግዚአብሔር ስለ ፍጥረታት የሰጠውን ሦስት እውነቶች ሰጥቶሃል።" ማነው የሰራው፣ ምንድነው የተሰራው፣ መቼ ነው የተሰራው።

## የበለ ብዙ ቁጥር ስሞች ማጠቃላያ ክፍሎች

የብዙ ቁጥር ስም ማጠቃላያ እንዴት ታውቃለህ? ሦስት ክፍሎች አሉት። 1) የዋና ዋና ነጥቦችን ቁጥር የሚሰጠን ስም፣ 2) የክፍሉ ዋና ሐሳብ እጣሬ እና 3) የአድማጮችን ትኩረት ለመያዝ የሚጠቅም ተዛምዶ። ለዘፍ 1፡1 የሰጠነውን ማጠቃላያ በጥንቃቄ ተመልከትና ክፍሎቹን ለመለየት ሞክር።

በዘፍጥረት 1፡1፤ እግዚአብሔር ሦስት እውነቶችን ሰጥቷል.....

ስለ ፍጥረት.....

እንዴት እዚህ እንደደረስክ ለመረዳት የሚያስፈልጉህ።

ይህ ምሳሌ አንድ ጥሩ በለብዙ ቁጥር ስም ማጠቃላያ የሚይዛቸውን ክፍሎች ይዟል። በመጀመሪያ ዋናውን ሐሳብ አጠቃሎ የሚይዝ የብዙ ቁጥር ስም አለ (ሦስት እውነቶች)። ሁለተኛው ፈጠረ በሚለው ግስ ውስጥ ያለውን የፍጥረት ሐሳብ አጠቃሎ ይይዛል። ሦስተኛው ይህንን ስብከት አድማጮች ለምን ማወቅ እንደሚያስፈልጋቸው የሚገልጽ ነገር፤ መረዳት የሚያስፈልጋችሁ...። ትርጓሜም ተዛምዶም በስብከት ውስጥ እጅግ አስፈላጊ ናቸው። ስለዚህ የበለ ብዙ ቁጥር ስም ማጠቃላያ ሁለቱንም ይዟል። ክፍሉ የሚለው ይህ ነው፤ የምታዛምደውም ይኸው ነው።

አሁን በብዙ ቁጥር ስም ማጠቃለያ ውስጥ ያሉትን ክፍሎች እየተረዳህ ነው። ስለዚህ የገላ 6፡1ን አጭር ማጠቃለያ እንስራ። በዚህኛው ፔስታል ውስጥ ያሉት ብርቱካኖች አምስት ናቸው።

የሚያቀና ኮሚቴ

የሚቃና ኃጢአት

የሚቃናበት ሁኔታ

የማቅናቱ ርህራሄ

የምቅናት ጥንቃቄ

በገላ 6፡1 ጳውሎስ ሦስት ምክንያቶችን ዘርዝሯል....

በጌታ ያለ ወንድም ወይም እህት ኃጢአት በምሰሩበት ወቅት ልታውቃቸው የሚገቡ ....

ወደ እውነተኛ የጽድቅ መንገድ መቅናት ያስፈለገበትን።

አምስት ቁጥር ለአድማጮችህ የሚነግረው በገላ 6፡1 ላይ ስንት እንስሳት እንዳሉ ነው፤ በፔስታሉ ውስጥ ስንት ብርቱካኖች እንዳሉ ነው። የመካከለኛው መስመር (ልታውቃቸው የሚገቡ) የሚለው በተዛምዶ ላይ ያተኩራል። ሦስተኛው መስመር ያጳውሎስን ዋና ሐሳብ ያስቀምጣል፤ ኃጢአተኛውን ማቅናት ወይም ማደስን።

ስብከት ማዘጋጀት ልክ ዳቦ እንደመጋገር ነው። ስዕላዊ ንድፍ ማውጣት ጥሬ ስንዴ ያቀርብልሃል፤ ጥሬ መረጃ። የትርጓሜ መግለጫ ያንን መረጃ በመፍጨት ቆንጆ ዱቄት ያደርግልሃል። የብዙ ቁጥር ስሞች ማጠቃለያ ለመበላት የተዘጋጀ ዳቦ ይጋግርልሃል። ከዛስ ውጤቱ? ውጤቱማ ጉባኤው የእግዚአብሔርን ዳቦ ይመገባል።

## ማጠቃለያ

አንድ ጓደኛዬ እንዴት የገላጭ ስብከት ዘዴን የሚጠቀም ሰባኪ ወደ መሆን እንደመጣ መስማት አይሰለቸኝም። ሮበርት ጌታን ያገኘው ቬንዳ በምትባል የደቡብ አፍሪካ ሰሜናዊ ምዕራብ አካባቢ ነው። አንድ ቀን በክርስቲያኖች የሬድዮ ጣቢያ የጆን ማክአርተርን ስብከት ይሰማል። በዚያ ስብከት ተሳበ፤ ቀጥሎም ስብከቶቹን በቋሚነት ማድመጥ ጀመረ። በስብከቱ ጅማሮ ማክአርተር አዘውትሮ የሚለውን ነገር ተማረ፤ ለምሳሌ "በዚህ ክፍል ስለ ደህንነት 5 ነገሮችን እናገኛለን" የሚል ዓይነት።

ሮበርት እንዲህ አለ “በማክአርተር ስብከት ጅማሮ ክፍሉን ሳነበው አምስቱንም ነጥቦች ማግኘት አልችልም፤ ፤ ነገር ግን በእርግጠኝንት ስብከቱን ከጨረሰ በኋላ አገኛቸዋለሁ። ከዚህ በኋለ ሰባኪ የምሆን ከሆነ ጥሩ ሰባኪ ለመሆን እንደዚህ ነጥቦችን ማውጣት የሚያስተምረኝ ሴሚነሪ መሄድ አለብኝ ብዬ ወሰንኩ።” ይላል። እግዚአብሔር ይመስገን፤ ሮበርት ስለ ስብከት ጥሩ ነገር የሚያስተምሩበት ሴሚነሪ ገባ፤ አሁን በቆንጆ ሁኔታ ነጥቦችን የሚያወጣ ሳባኪ ነው።

ንድፍ ማውጣት በዋጋ ሊተመን የማይችል ጥቅም አለው። የመጽሐፍ ቅዱስ አረፍተ ነገሮችን በትክክል መቁረጥ ትችል ዘንዴ ጥሩ ልኬት እንድትማር ያስገድድሃል። የጸሓፊው ዋና ሐሳብ የስብከትህም ዋና እንዲሆን ይረደሃል። ክፍሉ ሸክላ ሰሪ ነው፣ የአንተ ስብከት ደግሞ ሸክላው። እግዚአብሔር ያለውን እንድትል ይገፋሃል። ለምትሰብከው ጉባኤ የእግዚአብሔርን ስንዴ ዳቦ እንጂ የሰውን ገለባ እየሰጠህ እንዳልሆነ ዋስትና ይሰጥሃል።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትረካዎችን ማጥናት

የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዊ ወይም የታሪክ ክፍሎች ከተቀሩት ቅዱሳት መጽሐፍት ጋር ተመሳሳይ ሥነ መለኮት ያስተምራሉ፤ ነገር ግን ይህንን የሚያደርጉት በስዕላዊ መንገድ ማለትም ሥነ መለኮት በተግባር ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች "እውነት በፊልም መልክ" ናቸው።[39] የሚታዩ፣ የሚነኩ፣ የሚቀመሱ፣እና ስሜታዊ ነገሮችን በመውሰድ ጠቀሜታቸውን ለማስረዳት ማብራሪያዎችን ይሰጣሉ።

ለምሳሌ በዘፍጥረት 22 እግዚአብሔር ምስሎቹን በማሳየት የምትካዊ ቤዛዎት አስተምህሮን ያስተምራችኋል። የመማር ሂደቱን ለማቀላጠፍ ምናባችሁን ያሠራል። ታሪኩን ስታነብ የይስሐቅ ጥያቄ ሆድ ላይ ያረፈ ቦክስ ነው፤ "እሳቱና እንጨቱ ይኸው አለ፤ የመሥዋዕቱ በግ ግን ወዴት ነው?" አብርሃም "እግዚአብሔር ያዘጋጃል" ብሎ ሲመልስ እምነቱን ትሰማለህ። አብርሃም የልጁን የአንገት ደምስር በገዳዩ ጫፍ ለመውጋት ክንዱን ባነሣ ጊዜ በቢላዋው ላይ የፀሐይን ነጸብራቅ ትመለከታለህ። በመግቦታዊ ኀይል በአቅራቢያቸው ባለ ቁጥቋጦ የተያዘ ጠቦት በማዘጋጀት እግዚአብሔር ጣልቃ ሲገባ እፎይ ትላለህ። አብርሃም ይስሐቅን ፈቶ እና ከመሰዊያው ላይ አውርዶት በምትኩ የጠቦቱን አንገት ሲያርደው እና ሥጋውን ሲደረድር ካሰላሰልከው ምትካዊ ሞትን ትመለከታለህ። በዘፍጥረት 22 የምትክነትን አስተምህሮ ትሰማለህ፣ ስሜቱን ትረዳለህ፣ ደግሞም ትመለከታለህ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዊ ስብከቶችን ጉባኤ ሁልጊዜ ያጣጥማል፤ ምክንያቱም ትረካዎች ሥነ መለኮትን ለማስተማር ምስልን ይከስታሉ። እውነታው ሁላችንም በልባችን ልጆች ነን፤ ታሪክ እንወዳለን። ባለኝ ልምድ አፍሪካውያን ከተለመደው በላይ ለትረካዎች የተለየ አድናቆት አላቸው። ስለዚህም በአፍሪካ ጥሩ የገላጭ ስብከት ሰባኪ ለመሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትረካዎችን በመስበክ ጥበብ መካን አለብህ። ነገሮችን ግን እግዚአብሔርን ለመስበክ ለእግዚአብሔር ማጥናት አለብህ። እግዚአብሔር እንደሚሰብከው አድርገህ ለመስበክ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪኮች እንዴት ማጥናት ትችላለህ?

---

[39] Kenneth A. Mathews, "Preaching Historical Narratives," in Reclaiming the Prophetic Mantle: Preaching the Old Testament Faithfully, ed. by George Klein (Eugene, Oregon: Wipf & Stock Publishers, 1992), 31-32.

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮችን የመስበክ ዓላማ

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮችን የመስበክ ዓላማ የመጀመሪያው ጸሐፊ ካስተማረው ጋር አንድ የሆነ ሥነ መለኮታዊ ትምህርት ለማስተማር በሚረዳ መልኩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮችን እንደገና ለመተረክ ነው። በትረካ እንኳ እግዚአብሔር የተናገረውን ድጋሚ የማለት ግዴታ አለብህ። ስለዚህ የመጀመሪያ ሥራህ የሚሆነው የእግዚአብሔርን ታሪክ እግዚአብሔር ሲናገረው እንደነበረው በጥንቃቄ፣ በጥልቀት፣ በሚማርክ መልኩ ደግሞ መናገር ነው። ነገር ግን ታሪኩን እግዚአብሔር ለተናገረበት ለዚያው ምክንያት እግዚአብሔር ለፈለገው ሥነ መለኮታዊ ትምህርት መናገር አለብህ። ታሪኩን ድጋሚ ለመናገር በማጥናት እንጀምር።

## ሴራ ወይም የታሪክ ፍሰት

ወደ የትኛውም የዓለም ክፍል ብትሄድ ታሪኮች ተመሳሳይ አቀራረብ አላቸው። በሰላማዊ ሁኔታ ይጀምሩና ችግር ወይም ውጥረት ይጨመርባቸዋል። ለችግሩ መፍትሔ ይፈለጋል፤ በስተመጨረሻም መፍትሔ ቀርቦ ወደ ሰላማዊ ሁኔታ ይመለሳል። ምሁራን ይህንን የታሪክ ፍሰት ወይም ሴራ ብለው ይጠሩታል።[40]

መጽሐፍ ቅዱስም ያንን ፍሰት ይከተላል፤ የችግር–እና–የመፍትሔ ሴራ አለው።* መጽሐፍ ቅዱስን ስታነቡ ፍጹም እውነተኛው ታሪክ የሚጀምረው አብዛኞቹ ታሪኮች ከሚጀምሩበት ሰላማዊ የመነሻ ሁኔታ መሆኑን ታገኛለህ፤ እግዚአብሔር መልካም የሆነ ዓለም ፈጥሮ አዳምን እና ሔዋንን ጠባቂዎች አድርጎ ይሾማል። ነገር ግን እንደ ሁሉም ታሪኮች ችግር ወይም ውጥረት ይከሰታል። በአዳም ኃጢአት ምክንያት የእግዚአብሔር መልካም ዓለም ምስቅልቅል ውስጥ ይዘፈቃል። እግዚአብሔር ይህ ሁኔታ ለዘላለም እንዲቀጥል አልፈቀደም፤ ስለዚህ መፍትሔ መገኘት ነበረበት። ከዘፍጥረት 3 እስከ ራእይ 20 ድረስ እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያተኮረውን መፍትሔውን በጊዜ ሂደት ተግባራዊ ያደርጋል። የኢየሱስ ሞት፣ ትንሣኤ፣ እና የመላለሙ ገዢ ሆኖ ድንገት መመለስ በአዳም የመጣውን ችግር ይፈታል። ጳውሎስ እንዳለው ክርስቶስ ሁለተኛው አዳም ነው። ራእይ 21 እና 22 መፍትሔውን ያቀርባሉ። የኃጢአት ችግር በኢየሱስ ክርስቶስ ተፈቷል፤ ፍጥረትም ወደ መጀመሪያው ሰላማዊ ሁኔታ ተመልሷል፤ በርግጥ የመጨረሻው ሁኔታ ከመጀመሪያው የተሻለ ነው። በአዲሱ ሰማያት እና በአዲሱ ምድር ኃጢአት የማይታሰብ ነው።ሁሉም ታሪኮች የእግዚአብሔርን እውነተኛ የታሪክ

---

[40] Walter C.Kaiser, Jr., Preaching and Teaching from the Old Testament: A Guide for the Church (Grand Rapids, Mich.: Baker Academic, 2003), 66.

*The fact that God structured the Bible in the form of a story doesn't mean that the Bible is fictional or inaccurate. Divine inspiration determines that the Bible is completely true, and its stories are perfectly factual (2 Tim 3:16; Titus 1:2).

መስመር ይከተላሉ። ታሪክን ለጓደኞቻችሁ ወይም ለቤተሰባችሁ የምትናገሩት እንደዚህ አይደል? “ወደ መጋዘን ውስጥ እየተራመድኩ ነበር [መነሻ ሁኔታ] ከቁጥጥር ውጭ የሆነ መኪና መጣብኝ [ውጥረት]። ከመንገዱ ተስፈንጥሬ ወጣሁ፤ [መፍትሔ] ምንም ሳልሆን አመለጥኩ።[የመፍትሔ ውጤት]

እግዚአብሔርም አንተም የምትተርኩት በዚሁ መንገድ ስለሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ጸሐፊዎች ተመሳሳይ መንገድ መከተላቸው የሚደንቅ አይደለም። የዳንኤልን እና የአንበሶቹን ጉድጓድ ታሪክ አስተውል። መነሻ ሁኔታ፥ ልዩ በሆነ ችሎታው እና ትጋቱ ምክንያት ዳንኤል በመላው የፋርስ መንግሥት ከተሾሙት ሦስት ሰዎች አንዱ ተደረገ። ችግር፥ ቅናተኛ ጠላቶች ኢፍትሐዊ ፍርድ አዘጋጅተው በዳንኤል ላይ አሴሩበት። መፍትሔ፥ አንበሶችን በተዓምራት አስገዝቶ ዳንኤልን ለመታደግ እግዚአብሔር ጣልቃ ይገባል። የመፍትሔ ውጤት፥ ኋላ ላይ ክፉ አሳዳጆቹ ራሳቸው ለትልልቆቹ ድመቶች መብል ሆኑ፤ ዳርዮስም የዳንኤል አምላክ ሕያው፣ ዘላለማዊ አምላክ መሆኑን አሳወጀ። ታሪኩ በእነዚህ ቃላት ወደ ጥቁርነት ይደበዝዛል፤ “ስለዚህ ዳንኤል በዳርዮስ ዘመነ መንግሥትና በፋርሳዊው በቂሮስ ዘመነ መንግሥት ሁሉ ኑሮው ተሳካለት።” (ዳን 6፥28–አ.መ.ት)

## ታሪኩን ማጥናት

ታሪክን የመስበክ ዓላማ የእግዚአብሔርን ትረካ ድጋሚ ለመናገር ነው። ሴራውን ወይም የታሪኩን ፍሰት የሚያዋቅሩ ክስተቶችን በጥንቃቄ በመንቀስ ታሪኩን የግድ በጥልቀት ማጥናት አለብህ። የታሪኩን የችግር–መፍትሔ ሴራ ለመንቀስ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትረካዎችን አራት ቁልፍ ነገሮች መመልከት ያስፈልግሃል፤ የታሪኩ መቼት፣ ክስተቶች፣ ገጸ ባሕርያት፣ እና ምልልሶች። ለምሳሌ በሩት መጽሐፍ ላይ እየሠራህ ቢሆንና ምዕራፍ አንድን በመዳሰስ ብትጀምር የሩት መጽሐፍ የመጀመሪያው ቁጥር መቼቱን እንደመዘገበ ታገኛለህ፤ ጊዜው የመሳፍንት ዘመን፣ ቦታው ደግሞ ቤተልሔም እና ሞአብ ነበር። የሩት 1 ክስተቶች ጠቃሚ መሆናቸው ግልጽ ነው፤ በእስራኤል የተከሰተው ድርቅ፣ የኤሊሜሌክ ከቤተሰቡ ጋር ወደ ሞአብ መሄድ፣ የኤሊሜሌክ እና የልጆቹ ሞት፣ እና የኑኃሚን ወደ ቤተልሔም መመለስ።

የታሪኩ ሦስት ቁልፍ ገጸ ባሕርያት መጀመሪያ የተጠቀሱት ሩት 1 ላይ ነው፤ እግዚአብሔር፣ ኑኃሚን፣ እና ሩት። አራተኛው በዔዝ ወደ ታሪኩ የሚገባው በኋላ ነው። እንደ ሁሉም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትረካዎች[41] ምልልስ ለሩት 1 ጠቃሚ ነው። ኦርፋ እና ሩት ወደ ቤተልሔም አብረዋት እንዳይሄዱ የኑኃሚን ክልከላ፣ ከኋላ ላለመቅረት የሩት ተቃውሞ፣ እና ደግሞ ሩት ለእስራኤል አምላክ ለመገዛት የነበራት ወኔ። የሩት 1ን መቼ፣ ክስተቶች፣ ገጸ

[41] Ibid., 71-72.

ባሕርያት፣ እና ምልልሶች በማጥናት የእግዚአብሔርን ታሪክ እንደገና በትክክል ለመናገር እየተዘጋጀህ ነው ማለት ነው። እነዚህ የታሪኩ ቁልፍ ነገሮች ናቸው። ስለ መቼቶች፣ ገጸ ባሕሪያት፣ እና ምልልሶች ጥቂት ምልከታዎችን ልጨምር።

## መቼት

የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካን ታሪካዊ እና መልክዓምድራዊ መቼቱን አውድ ማግኘት ወሳኝ ነው። በርግጥ የአንድን ታሪክ መቼት መመልከት ጥሩ ሰባኪዎችን ከሰነፎቹ ከሚለዩ ነገሮች አንዱ ነው። አብርሃም ይስሐቅን ለመሰዋት ያቀረበው እና እግዚአብሔር ምትክ በግ ያዘጋጀው ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን በሚሠራበት በሞሪያም ተራራ ላይ መሆኑ ጠቃሚ ነው(ዘፍ 22፡2፤ 2 ዜና 3፡1)? መቼቱ ለታሪኩ ስነ መለኮታዊ አስፈላጊነት ወሳኝ ነው። ኢየሱስ በእርሱ ትምህርት እና በሙሴ ሕግ መካከል ስላለው ግንኙነት የተናገረው ከተራራ ላይ መሆኑ መገጣጠም ነው? አብ በሲና ያደረገውን ኢየሱስ በማቴዎስ 5-7 አደረገው። የተራራው ስብከት መቼት ስለ ኢየሱስ ባለሥልጣንነት ኤቨረስት-የመሰለ ማብራሪያ ነው።

## ገጸ ባሕሪያት

የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች ስለ ገጸ ባሕሪያት ጥልቅ መግለጫ አይሰጡም።[42] አብርሃም፣ ሙሴ፣ ጴጥሮስ፣ ወይም ጳውሎስ ምን ይመስሉ ነበር? አናውቅም። ነገር ግን ጸሐፊዎች አልፎ አልፎ ስለ ገጸባሕሪው ጠቃሚ ማብራሪያ ያቀርባሉ፤ ይህን ሲያደርጉ ልዩ ማስታወሻ ውሰዱ። ለምሳሌ በኢዮብ 1፡1 ላይ የተዘረዘረው የኢዮብ ባሕርይ (ነቀፋ የሌለበት፣ ቅን፣ እግዚአብሔርን የሚፈራ፣ እና ከክፋት የራቀ) የሚለው እጅግ ጠቃሚ ነው። ኢዮብ በክፋቱ ምክንያት መከራ እንዳልተቀበለ፣ ጻድቅ ሆኖ እያለ መከራ እንደተቀበለ ከመጀመሪያው ያስቀምጣል። በተመሳሳይ መልኩ የወንጌል ጸሐፊዎች መጥምቁ ዮሐንስ እንደ ነቢዩ ኤልያስ ታጥቆ አገልግሎቱን እንደሚፈጽም ይጠቅሳሉ (ማቴ 3፤4፤ 2 ነገ 1፡8)። ተመሳሳይ ልብስ ተመሳሳይ አገልግሎት ያሳያል። እንደዚህ አይነት ዝርዝሮች ሊታለፉ ይችላሉ። ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች አብዛኛውን ጊዜ ስለ ገጸ ባሕሪያቸው ብዙ መግለጫ አይሰጡም፤ ከሰጡ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል ማለት ነው።

ይህ ሲባል የመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ ባሕርይ ሰዎች ከታሪኩ ዋና ገጸ ባሕርይ ጋር ሲነጻጸሩ፣ በአንበሳ ጀርባ ላይ እንዳለች ዝንብ ናቸው። ስሙ ባልተጠቀሰበት በአስቴር መጽሐፍ እንኳ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ዋና ገጸ ባሕርይ

---

[42] Richard L. Pratt, Jr., He Gave Us Stories: The Bible Student's Guide to Interpreting the Old Testament Narratives (Phillipsburg, New Jersey: P&R Publishing, 1990, 1993), 136-7.

ሁልጊዜ እግዚአብሔር ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ በትክክል ድጋሚ ለመተረክ እግዚአብሔርን መድረኩ መኻል ላይ ማስቀመጥ አለብህ። ታሪኩ ስለ እርሱ ነው፤ ገጸባሕርይ ሰዎች ጠቃሚ የሚሆኑት እርሱን ሲታዘዙት ወይም ሲንቁት፣ ሲወዱት ወይም ሲጠሉት፣ ሲታመኑት ወይም ቸል ሲሉት ብቻ ነው። እነርሱ ዝንቦች ናቸው፤ አንበሳው እርሱ ነው።

## ምልልስ

በመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ ጸሐፊዎች በገጸ ባሕሪዎቻቸው ቃላት ወይም ምልልስ የእነርሱን ታሪክ እና ስነ መለኮት ይናገራሉ።[43]ለምሳሌ የሩት ጸሐፊ ሩት የሞአብን አማልክት ከማምለክ የእስራኤልን አምላክ ያህዌን ወደ ማገልገል እንደተለወጠች በራሱ ቃላት ማስቀመጥ ይችል ነበር። ነገር ግን የሩትን የራሷን ቃላት መጥቀስ ይበልጥ ጠንካራ ነው፤ “ሕዝብሽ ሕዝቤ፣ አምላክሽ አምላኬ ይሆናል” (ሩት 1፥16)።

የምልልስ ጠቀሜታ በዳዊት እና ጎልያድ ታሪክ ውስጥም ተዳሷል። በዳዊት፣ በሳኦል፣ እና በጎልያድ መካከል የተደረገውን ምልልስ ካላካተተ 1ኛ ሳሙኤል 17 ዳዊት በፍልስጥኤማዊው ግዙፍ ላይ የተቀዳጀውን የማይመስል ድል ማጣጣም ብቻ ይሆን ነበር። ከምልልሱ ጋር ግን የእግዚአብሔርን ኃይል ማሳያ ነው።

ሳኦል፡- “ይህን ፍልስጥኤማዊ ለመውጋት ትሄድ ዘንድ አትችልም” (17፥33)።

ዳዊት፡- “ከአንበሳና ከድብ እጅ ያስጣለኝ እግዚአብሔር ከዚህ ፍልስጥኤማዊ እጅ ያስጥለኛል” (17፥37)።

ጎልያድ፡- “ወደ እኔ ና፥ ሥጋህንም ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት እሰጣለሁ” (17፥44)።

ዳዊት፡- “አንተ ሰይፍና ጦር ጭሬም ይዘህ ትመጣብኛለህ፤ እኔ ግን ዛሬ በተገዳደርኸው በእስራኤል ጭፍሮች አምላክ ስም በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ” (17፥45)።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትረካ ስታጠና ለገጸ ባሕርያቱ ቃላት ልዩ ትኩረት መስጠት አለብህ። አብዛኛውን ጊዜ ንግግራቸው ወይም ምልልሳቸው የታሪኩን ስነ መለኮታዊ ነጥብ ይገልጣል።

---

43 Walter C. Kaiser, Jr., "Narrative," in Cracking Old Testament Codes: A Guide to Interpreting the Literary Genres of the Old Testament, ed. by D. Brent Sandy and Ronald L. Giese, Jr. (Nashville, Tenn.: Broadman & Holman Publishers, 1995), 77.

የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎችን ክስተቶች፣ መቼት፣ ገጸ ባሕሪዎች፣ እና ምልልሶች በትኩረት ማጥናት የእግዚአብሔርን ታሪክ በትክክል፣ በሚመስጥ፣ አይን በሚገልጥ፣ እና በአሳማኝ መልኩ እንድትሰብክ ያዘጋጅሃል። በታሪኩ ውስጥ ያለውን የአንድ ነገር ታሪካዊ አውድ እና ስነመለኮታዊ ጠቀሜታውን ጉባዔው መረዳት እንዲችል ያደርጋል ብለህ ስታምን ማብራሪያዎችን እና ትንታኔዎችን በመስጠት ታሪኩን እንደገና ተናገር። ታሪኩን በደንብ ተናገር! በ1ኛ ነገሥት 17 እና 18 ላይ የሚገኘውን የኤልያስን እና የአክአብን ታሪክ ስትሰብክ ጉባዔው በእስራኤል የነበረውን የድርቅ አቧራ ማሽተት አለበት። የኤልያስን መስዋእት እና መስዊያ የበላውን እሳት ሙቀት ማግኘት አለበት። የዳዊትን እና የጎልያድን ታሪክ በምስላዊ መንገድ ስትተርኩ ዳዊት በጎልያድ አስቀያሚ ግንባር ላይ ጠጠሯን ሲወረውር አድማጮቻችሁ ፊታቸውን መከለል አለባቸው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮችን ሳታጋንን ስበክ፤ ነገር ግን ጉባዔው በታሪኩ ወስጥ እየተካሄደ ያለውን እንዲቀምስ፣ እንዲነካ፣ እንዲያሸት፣ እንዲሰማ፣ እንዲያይ፣ እና እንዲለማመድ አድርገህ ስበክ።

## ስነ መለኮታዊ መልእክቱን ማግኘት

ታሪኩ እንደገና መናገር ጠቃሚ ቢሆንም የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን መስበክ ከዚህ ያልፋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ታሪክን የመዘገቡት ጥሩ የሆነ ታሪክ ለመናገር አይደለም። ታሪክን የመዘገቡት ስነ መለኮት ለማስተማር ነው።[44]ለምሳሌ ሐዋርያው ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈው ስለናዝሬቱ ኢየሱስ እውነት የሆኑ ነገሮችን ዝርዝር ለማዘጋጀት አይደለም። የናዝሬቱ ኢየሱስ መሲሕ እና አምላክ እንደሆነ አንባቢዎቹን ለማሳመን ነው፤ “ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ፣ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ [ተአምራዊ ምልክቶች] ተጽፎአል” (ዮሐ 20፥31)። የዮሐንስ ታሪክ ዓላማ ስነመለኮታዊ ነበር። ይህ ለመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ሁል ጊዜም እውነት ነው። ስለዚህ ታሪኩን ለመተረክ ከማጥናት በተጨማሪ ታሪክን በደንብ ለመስበክ ስነመለኮታዊ ትምህርቱን ማለትም ጸሐፊው ታሪኩን ሲጽፍ ማስተላለፍ የፈለገውን ትምህርት መግለጥ የግድ ይላል። የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ጸሐፊዎችን ስነመለኮታዊ ጠቀሜታ ለማግኘት የሚረዷችሁን ስድስት ነጥቦች ልስጣችሁ።

## ቀጥተኛ አንቀጾች

1) ጸሐፊው ለማስተማር የፈለገውን ስነመለኮታዊ ትምህርት በቀጥታ ይናገር እንደሆን ተመልከት። የዚህን ምሳሌ በዮሐንስ 20፥31 ተመልክተናል። የእርሱን ነጥብ እንደማታጣው ለማረጋገጥ ዮሐንስ ወንጌሉን ለምን

[44] Mathews, "Preaching," 25.

እንደጻፈ በትክክል ይናገራል። በዮሐንስ ወንጌል የተመዘገቡት  የኢየሱስ ንግግሮች፣ ሥራዎች፣ እና ተአምራት ሁሉ የተካተቱት ኢየሱስ መሲሕ እና አምላክ መሆኑን እንድታምን ነው። ከዮሐንስ ወንጌል ስትሰብክ የዮሐንስ ዓላማ ያንተን ዓላማ መቅረጽ አለበት።

## አርትኦታዊ አስተያየቶች

2) ጸሐፊው ስነመለኮታዊ ትምህርቱን ለማሳየት ያስገባቸውን አርትኦታዊ አስተያየቶች መዝግብ። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ይህንን መርህ ያብራራል። መክፈቻ ምዕራፎቹ የጥንቷ ቤተክርስቲያን ቅጥልጥል ምስሎች ናቸው፤ የጴንጤቆስጤ ቀን ክስተት፣ የሽባውን መፈወስ፣ የጴጥሮስን ስብከት፣ የጴጥሮስን እና የዮሐንስን መታሰር፣ አስፈልጎቶችን ለማሟላት ንብረት መሸጥን፣ ስለመበለቶች የነበረውን አለመግባባት፣ የእስጢፋኖስን መወገር፣ እና የመሳሰሉትን ያካትታሉ። ይህ የታሪካዊ ክስተቶች ቅልቅል ነው። ሉቃስ እነዚህን ነገሮች ሁሉ እንዴት አጣመራቸው? ጸሐፊው አስተያየቶችን በመስጠት እያንዳንዱ ታሪክ ለአጠቃላዩ መጽሐፍ ያለውን አስተዋጽኦ ይናገራል። ስለ ሉቃስ ስነመለኮታዊ ዓላማ ከእነዚህ የአስተያየት ናሙናዎች የሆነ ነገር ማግኘት ትችል እንደሆን ተመልከት።

የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ። (4፥31)

“ሐዋርያትም የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በታላቅ ኃይል ይመሰክሩ ነበር” (4፥33)

“ዕለት ዕለትም በመቅደስና በቤታቸው ስለ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ማስተማርንና መስበክን አይተዉም ነበር።” (5፥42)

“የእግዚአብሔርም ቃል እየሰፋ ሄደ” (6፥7)

“የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ።” (8፥4)

“…የተበተኑት አማኞች ቃሉን …እየተናገሩ እስከ ፊንቄ፣ እስከ ቆጵሮስና እስከ አንጾኪያ ድረስ ዘለቁ።”(11፥19–መ.ት)

“የእግዚአብሔር ቃል ግን ያድግና ይበዛ ነበር።” (12፥24)

“ጳውሎስም…የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበከ ስለ ጌታ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ ገልጦ ያስተምር ነበር።” (28፥30–31)

“ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።” (2፥47)

“ቃሉን ከሰሙት ብዙዎች አመኑ፥ የወንዶችም ቍጥር አምስት ሺህ ያህል ሆነ።” (4፥4)

“የሚያምኑትም ከፊት ይልቅ ለጌታ ይጨመሩላት ነበር፤ ወንዶችና ሴቶችም ብዙ ነበሩ።” (5፥14)

“በዚህም ወራት ደቀ መዛሙርት እየበዙ ሲሄዱ…” (6፥1)

“…በኢየሩሳሌምም የደቀ መዛሙርት ቍጥር እጅግ እየበዛ ሄደ፤ ከካህናትም ብዙ ሰዎች ለሃይማኖት የታዘዙ ሆኑ።” (6፥7)

“…አብያተ ክርስቲያናት …ይበዙ ነበር።” (9፥31)

“ብዙ ሰዎችም በጌታ አመኑ።” (9፥42)

“የጌታም እጅ ከእነርሱ ጋር ነበረ፤ ቍጥራቸውም እጅግ የሚሆን ሰዎች አምነው ወደ ጌታ ዘወር አሉ።” (11፥21)

እነዚህ አርትኦታዊ አስተያየቶች ወይም ማጠቃለያዎች የሚያሳዩት የሐዋርያት ሥራን ሉቃስ የጻፈው የጥንቷ ቤተክርስቲያን ወንጌል እንድትሰብክ ክርስቶስ ለሰጣት ተልዕኮ ታማኝ እንደሆነች እና እግዚአብሔርም በጥረታቸው በብዙ አማኞች በመባረክ ታማኝ እንደሆነ ለማሳየት ነው። የሉቃስ ስነ መለኮታዊ መልዕክት? ማንኛውም ውስጣዊ ችግር ወይም ውጫዊ ጫና በመንገዷ ቢቆምም ቤተክርስቲያን ሰብካለች ደግሞም አድጋለች። በማቴዎስ 16፥18 ቃላት ስንጠቀልለው ክርስቶስ ቤተክርስቲያኑን ገንብቶአል።

የራሳቸውን አስተያየት ከማስገባት በተጨማሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ጸሐፊዎች አንዳንድ ጊዜ የታሪኩን ስነመለኮታዊ ትምህርት ለመጠቅለል የአንዱን ገጸ ባሕርይ ቃላት ይጠቀማሉ። ለምሳሌ ዳንኤል 4 ላይ ንጉሡ ናቡከደነፆር በቤተመንግሥት ጓሮ ሳር ከመጋጥ ወደ ማስተዋሉ ሲመለስ ስለ ያህዌ እንዲህ ሲል ያውጃል፤ “በሰማይም ሠራዊት በምድርም ላይ በሚኖሩ መካከል እንደ ፈቃዱ ያደርጋል፤ …በትዕቢትም የሚሄዱትን ያዋርድ ዘንድ ይችላልና” (ዳን 4፥35-37)። ዳንኤል በናቡከደነፆር ንግግር ላይ የራሱን አርትኦታዊ መዝጊያ መጨመር አላስፈለገውም። የናቡከደነፆር ቃላት ስነመለኮታዊ ትምህርቱን በደንብ ይጠቀልላል።

አንደኛ ነገሥት ስነመለኮታዊ ትምህርትን በገጸ ባሕርዩ ቃላት የሚገልጽ የሌላ ጸሐፊን ምሳሌ ያቀርባል። በ1ኛ ነገሥት 17፤1 ኤልያስ የተባለ የማይታወቅ ሰውዬ በእስራኤል ሸንጎ ድንገት ተከስቶ እርሱ (ኤልያስ) እስከሚናገር ድረስ ዝናብ እንደማይዘንብ ለንጉሡ ለአክአብ ይናገራል። ከዚያም ለንጉሡ ለአክአብ እንደሆነው ሁሉ

ለአንባቢም እንቆቅልሽ የሆነው ኤልያስ ይደበቃል፤ ከዚያም የሰረፐታዋ መበለት ጋር ይቆያል። ኤልያስ ልጇን ከሞት ካስነሣው በኋላ መበለቷ እንዲህ ስትል ትጮኻለች፤ "የእግዚአብሔር ሰው እንደሆንህ፥ የእግዚአብሔርም ቃል በአፍህ እውነት እንደሆነ አሁን አወቅሁ" (1 ነገ 17፥24)። የልጁ ከሞት የመነሣት ታሪክ በራሱ ለአንደኛ ነገሥት ጠቃሚ አይደለም፤ ነገር ግን የእናትየው አግራሞት ጸሐፊው ያካተተበትን ምክንያት ይገልጣል። የታሪኩ ጸሐፊ አንተ በትክክል እንድታገኘው የፈለገውን የኤልያስን አመለካከት የመበለቲቱ ቃላት ይገልጻሉ። መበለቲቱ አንድ ጊዜ ከተናገረች በኋላ ኤልያስ እንቆቅልሽ መሆኑ ይቀራል፤ እርሱ የእግዚአብሔር ሰው፣ ነቢይ፣ መለኮታዊ ሥልጣን የተሰጠው ሕጋዊ ሰው ነው። ብዙ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች የታሪኮችን ስነመለኮታዊ ትምህርቶች በእንደነዚህ ዓይነት ማጠቃለያዎች ይገልጻሉ፤ አንዳንድ ጊዜ የራሳቸውን ቃላት በመጠቀም ሌላ ጊዜ ደግሞ ከአንዱ ገጸባሕርይ በመጥቀስ።

## መዋቅር

3) ጸሐፊው ታሪኩን በጋራ ለማስቀመጥ የተጠቀማቸውን ቋንቋዊ እና መዋቅራዊ መሳሪያዎች መዝግብ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ታሪኮችን የሚያዋቅሩት የታሪኩን ስነመለኮታዊ ትምህርቶች ለማድመቅ ነው።[45] ለምሳሌ አንዳንድ ጊዜ ታሪኮችን በቡድን በማዋቀር አንድን ነጥብ ያሳያሉ፤ በወንጌላት የተጠቀሱ ተአምራቶች ለዚህ ግልጽ ምሳሌዎች ናቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ታሪክ ጸሐፊዎች "ሄድ መለስ" ሀ-ለ-ሐ፣ ሐ-ለ-ሀ መዋቅር ይጠቀማሉ። ለምሳሌ ዘፍጥረት 7-8ን ስታጠና ሙሴ በእያንዳንዱ የጥፋት ውሃ ደረጃዎች 7፣ 40፣ 150፣ 150፣ 40፣ እና 7 ቀናት ላይ የእግዚአብሔርን ፍጹም ሉዓላዊነት ለማሳየት ታሪኩን በዓላማ እንዳዋቀረ ታገኛለህ፤ ሙሴ ያዋቀረው የጥፋትን ውሃ ቁልፍ ስነመለኮታዊ ትምህርት ያደምቃል፤ ለሰዎች ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ዓለማቀፍ መቅሰፍት የሚመስለው ለእግዚአብሔር ግን በጥብቅ ቁጥጥር እየተመራ ልክ እንደታቀደው የሚከናወን ክስተት ነው። ዳዊት ያንን ትምህርት በመዝሙር 29፥10 ላይ ጠቅለል አድርጎ ይገልጸዋል፤ "እግዚአብሔር በጎርፍ ላይ ዙፋኑን ዘርግቶ ተቀምጦአል፤ እግዚአብሔር በንጉሥነቱ ለዘላለም በዙፋኑ ላይ ይቀመጣል"(አ.መ.ት)። ጥብቅ የሆነው የጥፋት ውሃ "ሄድ መለስ" ቅርጽ በጠቅላላው ክስተት ላይ የእግዚአብሔርን ንግሥና ያደምቃል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ጸሐፊዎች አንዳንዴ የሚጠቀሙት መዋቅር *ማካተት* ይባላል። ማካተት የሚያመለክተው የሆነን የመጽሐፍ ክፍል በተመሳሳይ ሐረግ ወይም ዐ.ነገር ጀምሮ የመጨረስን ተግባር ነው።

[45] Pratt, He Gave Us Stories, 213-219

ማቴዎስ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ያቀርባል። ማቴዎስ 4፥23 እና 9፥35 አንዱ ለሌላው እንዴት መስታወት እንደሆነ ተመልከት።

“ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በገሊላ ሁሉ ይዞር ነበር።” (ማቴ 4፥23)

“ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ፥ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ፥ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ፥ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዞር ነበር።” (ማቴ 9፥35)

የማቴዎስ ድግግሞሽ በሁለቱ ምሰሶዎች 4፥23 እና 9፥35 መካከል ወዳለው ጭብጥ ትኩረት ይስባል። ክፍሉን አተኩሮ መመልከት ከተራራው ስብከት (የኢየሱስ ትምህርት እና የወንጌል ስብከት ምሳሌ) እና የፈውስ ሰንሰለት (እንደ ቁምጥና፣ ትኩሳት፣ ሽባነት በአጋንንት መያዝ፣ ሞትንም ጭምር) ያካተተ መሆኑ የሚገርም አይደለም። በ4፥23 እና 9፥35 ማካተትን በመጠቀም ማቴዎስ አንባቢዎቹ ኢየሱስ መሲሕ ለመሆኑ ሁለቱ የማቴዎስ ማስረጃ ለሆኑት ለኢየሱስ ትምህርት እና የፈውስ አገልግሎት ትኩረት እንዲሰጡ ይማጸናል።

## የተደጋገሙ ቃላት ወይም ሐሳቦች

4) የታሪኩን ስነመለኮታዊ ትምህርት የሚያሳዩ ተደጋጋሚ ቃላትን እና ሐሳቦችን ተመልከት።[46] ለዚህም ሉቃስ የጥንቷን ቤተክርስቲያን ስብከት እና በቁጥር መብዛት በተደጋጋሚ ከሚጠቅስበት ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ጥሩ ምሳሌ አይተናል። ሉቃስ እነዚህን ሐሳቦች ደርዘን ጊዜ ከደጋገመ የእርሱ ትኩረት ነው ማለት ነው። ዮናስ 4 ላይ ርህራሄ የሚለው ቃል ሦስት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል። 4፥2 ላይ ዮናስ በምዕራፍ አንድ ላይ የኮበለለበት ምክንያት እግዚአብሔር በአሰራውያን ላይ ቁጣውን ሳይሆን ርህራሄውን እንደሚያፈስ በማወቁ እንደሆነ ይናገራል። በ4፥10–11 ላይ ዮናስ ለደረቀችው ቅል ካሳየው ርህራሄ ጋር እግዚአብሔር ለነነዌ ኃጢአተኞች ካሳየው ርኅራሄ ጋር ተመሳስሎአል። ርህራሄ የሚለው ቃል መደጋገሙ ለመጽሐፉ አጠቃላይ ስነመለኮታዊ መልዕክት ፍንጭ ይሰጣል።

በመጀመሪያ ዕይታ አንድ ሰው የነህምያ መጽሐፍ መክፈቻ ምዕራፎች ይቻላል በሚለው አስተሳሰቡ የኢየሩሳሌምን ቅጥር በሚገርም ሁኔታ በአምሳ ሁለት ቀናት ስለጨረሰው ተሰጥኦ ስላለው መሪ ሰው እንደሆነ በስህተት ሊያስብ ይችላል። ነገር ግን ይህ ድምዳሜ በተደጋጋሚ የተጠቀሰውን የእግዚአብሔርን እርዳታ ችላ ያለ

---

46 Kaiser, Preaching and Teaching, 73.

ነው፤ “መልካሚቱ የአምላኬ እጅ በእኔ ላይ ነበረችና ንጉሡም ፈቀደልኝ።” (2፥8–አ.መ.ት) “እንዲሁም መልካሚቱ የአምላኬ እጅ በእኔ ላይ እንደ ነበረችና ንጉሡም ምን እንዳለኝ ነገርኋቸው።” (2፥18–አ.መ.ት) “ይህም ሥራ በእግዚአብሔር እንደ ተደረገ አወቁ” (6፥16 እንዲሁም 2፥20፤ 4፥20፣ እና 1፥11፤ 2፥4፤ 4፥4፣ 9፤ 6፥9፣ 14 ላይ ያለውን የነህምያን ጸሎት ተመልከት)። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ብዙ ጊዜ ተደጋጋሚ ቃላትን እና ሐሳቦችን ወደ ታሪኩ ስነመለኮታዊ ትምህርት እንደሚጠቁሙ የመንገድ ምልክቶች ይጠቀሟቸዋል።

## መልስ አዘል ጥያቄዎች

5) ጸሐፊው ሊያስተላልፍ ወደፈለገው ስነመለኮታዊ ትምህርት የሚጠቁሙ መልስ አዘል ጥያቄዎችን መዝግብ።[47] መልስ አዘል ጥያቄ (rhetorical question) መልሱ በጣም ግልጽ ስለሆነ መልስ የማይፈልግ ጥያቄ ነው። በዮናስ መጽሐፍ የመጨረሻው ቁጥር ላይ ለዚህ ግልጽ ምሳሌ እናገኛለን። መጽሐፉን ለመዝጋት እግዚአብሔር ዮናስን ይጠይቀዋል፤ “እኔስ … ለነነዌ አላዝንምን?” (ዮና 4፥11)። ጥያቄው መልስ አያስፈልገውም። ያልተገባቸውን የነነዌ ሰዎች ለመማር ባለ ጸጋ፣ ሩህሩህ፣ ለቁጣ የዘገየ፣ ምህረትን ለማድረግ ፍቅሩ የተትረፈረፈ ለሆነው አምላክ ፍጹም ተገቢ ነው። የእግዚአብሔር መልስ አዘል ጥያቄ ትንቢተ ዮናስ ስለ ነጭናጫ ነቢይ እና ስለ አሳ ነባሪ እንዳልሆነ ግልጽ ያደርጋል። በእርግጥ ባልተገባቸው ኃጢአተኞች ላይ ስለተገለጠው የእግዚአብሔርን ርህራሄ ትልቅ ስነመልኮታዊ ትምህርት ነው።

## የቁስ ምርጫ

ስነመለኮታዊ ትምህርቱን ለማግኘት ጸሐፊው ያካተተውን እና ያላካተተውን መረጃ መዝግብ። የወንጌላት ጸሐፊዎች ስለ ኢየሱስ ልጅነት እና ወጣትነት በጣም ጥቂት መረጃ ብቻ ያካተቱት ለምንድነው? ኢየሱስ ምን ይመስል እንደነበር ያልነገሩን ለምንድነው? አራቱም ወንጌላት ለኢየሱስ ተአምራት፣ ለስቃዩ ሳምንት፣ በተለይም ደግሞ ለሞቱ እና ለትንሣኤው ሰፊ ቦታ የተሰጡ ለምንድነው?

የኢየሱስን የልጅነት ጊዜ እና የዐይኖቹን ቀለም የተመለከተ መረጃ የማያስፈልገንን ነገር ለማወቅ ያለንን ጉጉት ብቻ ነው የሚደርሰው። ኢየሱስ መሲሑ መሆኑን ለማረጋገጥ ምንም አይፈይድም። የወንጌል ጸሐፊዎች እንደ የኢየሱስ ውጫዊ በገጽ ያሉ ቀላል ነገሮችን ችላ በማለት የእየሱስን ተአምራት የያዙ ታሪካዊ ምንባቦችን በማከታተል አጀንዳቸውን መግለጥ ይመርጣሉ፤ የናዝሬቱ ኢየሱስ በእግዚአብሔር የተሾመ መሲሕ መሆኑን ማረጋገጥ። በተመሳሳይ መንገድ የኢየሱስ ጸጉር መልክ እና ርዝመት ለክርስትና መልዕክት ምንም የማይጠቅም

[47] Kaiser, Toward An Exegetical Theology, 72.

ነው። ነገር ግን የኢየሱስ ሞት እና ትንሣኤ እንደዚህ አይደሉም። የወንጌል ጸሐፊዎች ሲመዘግቡ ያካተቱት እና ያላካተቱት መልዕክት ወደ ወንጌላት ስነመለኮታዊ ተልዕኮ ይጠቁማል።

እግዚአብሔርን ለመስበክ እግዚአብሔርን ማጥናት አለብህ። ይህ በትረካ ምንባቦች ሁለት ትርጉሞች አሉት። አንደኛ እግዚአብሔር የተናገረውን ታሪክ ደግመህ ለመናገር ታሪኩን በጥንቃቄ ማጥናት አለብህ — መቼቱን፣ ክስተቶችን፣ ገጸ ባሕርያትን፣ እና ምልልሶችን። ደግሞም እንደ ጥሩ መርማሪ ወደ ጸሐፊው ስነ መለኮታዊ ትምህርት የሚጠቁሙ ፍንጮችን ማነፍነፍ አለብህ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታሪኮች ታሪክ ብቻ አይደሉም። ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ እግዚአብሔር ልጅ፣ እና ስለ እግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ የሚያስተምሩ እውነተኛ ታሪኮች ናቸው።

## ትረካን ለማስተማር አምስት ተጨማሪ ነገሮች

በመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ ላይ ጥሩ ስብከት መስማት የተለመደ አይደለም። ይህን ችግር ለማስተካከል ተስፋ በማድረግ የእግዚአብሔርን ታሪኮች በልህቀት እንድትሰብክ የሚረዱ አምስት ተጨማሪ ነገሮችን ልስጣችሁ።

### የተሟላ ታሪክ አስተምር

የአንድን ታሪክ ምን ያህል ክፍል መስበክ አለብህ? የተሟላ ታሪክ የችግር እና የመፍትሔ መስመሩን ጠብቀህ መስበክ ሁልጊዜም ምርጥ ነው። ለምሳሌ አጠቃላይ የዮናስን መጽሐፍ መስበክ ተፈጥሯዊ ሊሆን ይችላል፤ የተሟላ ታሪክ ነው። ይህ ማለት ግን ትረካዎችን ስትሰብክ የመጽሐፍ ቅዱስን አንድ ሙሉ መጽሐፍ መስበክ አለብህ ማለት አይደለም። የትልቁ ታሪክ ክፍል የሆነውን ትንሽ ታሪክም መስበክ ትችላለህ። ለምሳሌ ያህል የሐዋርያት ሥራን ሙሉ መጽሐፍ በአንድ ስብከት ማቅረብ ቢቻልም ብዙ የሐዋርያት ሥራ ትንንሽ ታሪኮችን ተራ በተራ ነው በይበልጥ የምትሰብከው። ይህን ማድረግ ፍጹም ተቀባይነት አለው፤ ምክንያቱም እያንዳንዱ የሐዋርያት ሥራ ትንሽ ታሪክ የራሱ የሆነ የችግር—መፍትሔ ሴራ ወይም የታሪክ ፍሰት አለው።

አጠቃላይ የችግር—መፍትሔ ሴራ ከማግኘት በተጨማሪ በትልቁ ታሪክ ጊዜ እና ቦታ ውስጥ የተከሰቱ ወሳኝ ለውጦችን ለመመልከት ሌላኛው መንገድ ትንንሽ ታሪኮችን በትልቁ ታሪክ ውስጥ ማግኘት ነው።[48] ለምሳሌ በዮሐንስ 3 ኢየሱስ በይሁዳ እየሰበከ ነው። በዮሐንስ 4 ይሁዳን ትቶ በሰማርያ በኩል ወደ ገሊላ መሄድ ጀመረ። የተካሄደው የቦታ ለውጥ ዮሐንስ 3 እና ዮሐንስ 4 በትልቁ የዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የሚገኙ ሁለት የተለያዩ

48 Ibid., 66.

ታሪኮች መሆናቸውን ይጠቁማል። ዮሐንስ 5 ደግሞ የጊዜን እና የቦታን ለውጥ በማስተዋወቅ ይጀምራል። "*ከዚህ በኋላ* የአይሁድ በዓል ነበረ፥ ኢየሱስም *ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ*።" (5፥1) ብዙ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ከአንድ ታሪክ ወደ ሌላኛው የተደረገውን ሽግግር ለማሳየት መልክዓ ምድራዊ ለውጥ ወይም ከእነዚህ ነገሮች በኋላ፣ እንዲህም ሆነ፣ ከብዙ ቀናት በኋላ፣ አሁን፣ ወይም ኢየሱስም እነኚህን ተናግሮ ከጨረሰ በኋላ የሚሉ ሐረጎችን ይጠቀማሉ። እነዚህን ሽግግሮች መመዝገብ በአንድ ስብከት ምን ያህል ትረካ ማቅረብ እንዳለብህ መወሰን እንድትችል ይረዳሃል።

## በተገቢው መንገድ ከክርስቶስ ጋር አገናኝ

በአዳም ኃጢአት ለተፈጠረው ችግር የእግዚአብሔር የመጨረሻው መፍትሔ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን እንዳትረሳ። ስለዚህ የብሉይ ኪዳንን ትረካ ስታስተምር ወደ ላይ ከፍ በማለት ይህ ታሪክ በትልቁ ታሪክ ውስጥ እንዴት እንደሚገጥም፣ ለእያንዳንዱ የሰው ውድቀት የመጨረሻ መፍትሔ ክርስቶስ መሆኑን ለጉባኤው አሳይ።[49] በሚያሳዝን ሁኔታ አንዳንድ ሰባኪዎች በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ ሰው፣ እያንዳንዱ ክስተት፣ እያንዳንዱ ነገር ክርስቶስን እንደሚወክል በማሰብ ከክርስቶስ ጋር ማገናኘትን ልማድ አድርገዋል። ለምሳሌ እንደዚህ አይነቱ ሰባኪ በ1ኛ ሳሙ 21 ዳዊት እና ሰዎቹ ከሳኦል በሸሹ ጊዜ ያበረታቸው እንጀራ መንፈሳዊ ብርታት የሚሰጠንን የሕይወት እንጀራ የሆነውን ክርስቶስን እንደሚወክል ሊናገር ይችላል። ስለ ሕይወት እንጀራ ማስተማር ከፈለክ ከ1ኛ ሳሙኤል 21 ሳይሆን ከዮሐንስ 6 አስተምር። የብሉይ ኪዳን ትረካ ዝርዝር ነገሮችን ከክርስቶስ ጋር ለማገናኘት የተጭበረበረ ሙከራ በማድረግ ማመናፈስ አላስፈላጊ እና የማይጠቅም ነው። ብዙ ጊዜ እንደዚህ አይነቱ ግንኙነት የሰባኪው ምናባዊ እሳቤ ነው እንጂ ከሰዋዊው እና ከመለኮታዊው ጸሐፊ ሐሳብ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ያሰባቸው ብዙ የክርስቶስ ምሳሌዎች አሉ፤ እግዚአብሔር ያሰባቸው የሚለው ቁልፍ ነው። ስለዚህ በዳዊት ኮሮጆ ውስጥ ለነበሩ አምስት ጠጠሮች፣ በቤተመቅደሱ ውስጥ ለነበረው ለእያንዳንዱ ልብስ፣ ዋንጫ፣ እና በትር ያልተረጋገጡ እና ሊረጋገጡ የማይችሉ "መንፈሳዊ" ትርጉሞችን የመስጠት ፈተናን ተቋቋም።[50] የብሉይ ኪዳን ትረካዎችን ከኢየሱስ ጋር ለማገናኘት በምታደርገው ጥረት የሚመሩህ ሁለት መመሪያዎች። መጀመሪያ ምሳሌዎችን ስትለይ ሙሉ በሙሉም ባይሆን በዋናነት እግዚአብሔር ያሰባቸው የክርስቶስ ምሳሌዎች ብሎ አዲስ ኪዳን

[49] Bryan Chapell, Christ-Centered Preaching: Redeeming the Expository Sermon, 2nd ed. (Grand Rapids, Mich.: Baker Academic, 1994, 2005), 15.

[50] Eugene H. Merrill, "History," in Cracking Old Testament Codes: A Guide to Interpreting the Literary Genres of the Old Testament, ed. by D. Brent Sandy and Ronald L. Giese, Jr. (Nashville, Tenn.: Broadman & Holman Publishers, 1995), 106.

ምሳሌዎች ራስህን ገድብ። ሁለተኛ በብሉይ ኪዳን ታሪክ ዋና የሆነ ነጥብ ወስደህ ተገቢ በሆነ መንገድ ከክርስቶስ ጋር አገናኝ እንጂ ዝርዝር መገጣጠሞችን እታገናኝ። በሌላ አገላለጽ ክርስቶስ ለኃጢአት እውነተኛ መፍትሔ፣ የአብርሃም ተስፋ ሙላት፣ የመጨረሻው ዳዊታዊ ንጉሥ፣ ወዘተርፈ በመሆኑ ሐቅ ላይ ትኩረት አድርግ። እነዚህን እውነታዎች ማጣቀስ ክርስቶስን ተገቢ በሆነ መንገድ ወደ ስብከትህ ያመጣዋል፤ ምናባዊ ሐሳቦችህን ደግሞ ያርቃቸዋል።

## ትረካ እና ተግባር

ብዙ ሰባኪዎች ትረካዎችን ሲያስተምሩ ከገጸ ባሕርያት ጸባይ የዘለለ ማየት አይችሉም፤ እዚህ ጋር ዳዊት ጥሩ ነው፤ እንደ ዳዊት ሁኑ። እዚያ ጋር ሳኦል መጥፎ ነው፤ እንደ ሳኦል አትሁኑ።[51] አንደኛ ቆሮንቶስ 10፥6፣ ሮሜ 15፥4፣ ያዕቆብ 5፥10–11 ከመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ ባሕሪዎች ጸባይ ትምህርቶችን ማውጣት በጣም ትክክል እንደሆነ ያሳያሉ። ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ ዋናው ገጸ ባሕርይ እግዚአብሔር እንደሆነ መርሳት የለብህም። የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ቁልፍ ትምህርት ሁልጊዜ ስለ እግዚአብሔር ነው እንጂ ስለ ሰው አይደለም።[52]

የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች ቁልፍ ትምህርት ሁልጊዜ ስለ እግዚአብሔር በመሆኑ ምክንያት ተግባራዊ ናቸው። እግዚአብሔር አይለወጥም፤ ስለሆነም ያዕቆብ፣ ኢዮሳፍጥ፣ ዕዝራ፣ ውሃ ጉድጓድ ጋር የነበረችው ሴት፣ እንዲሁም አናንያ እና ሲጳራ በታሪካቸው ውስጥ የተማሩት ነገር ዛሬም ድረስ እውነት ነው። በተጨማሪ አብርሃም፣ ሙሴ፣ ሩት፣ ኢዮብ፣ እና ጳውሎስ የተጋፈጡትን ፈተና ትጋፈጣለህ። የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች የሚናገሩት ስለ አንዱ እግዚአብሔር፣ ስለ ተመሳሳይ ዓለም እና ዛሬ ላይ ስለሚኖሩ ተመሳሳይ ሰዎች ነው፤ ስለሆነም ዘላቂ የሆነ ተግባራዊነት አላቸው።[53]

ስነ ምግባራዊ መርሆዎችን ስታወጡ ይህን አድርግ፤ ያንን አታድርግ፤ በትረካ ውስጥ የመጽሐፉ ትምህርት ክፍል ዒላማ ያደረከው ጸባይ ጥሩ ወይም መጥፎ፣ ልትከተለው የተገባ ነው ወይስ አይደለም ብሎ በግልጽ እንደሚናገር እርግጠኛ ሁን። ለምን? የመጽሐፍ ቅዱስ ጀግኖች ድርጊታቸው የተካተተው የተለዩ ሰዎች ስለሆኑ

---

[51] David C. Deuel, "Expository Preaching from Old Testament Narrative," in Rediscovering Expository Preaching, John MacArthur, Jr. and The Master's Seminary Faculty (Dallas, Texas: Word Publishing, 1992), 283.
[52] Mathews, "Preaching," 34-5.
[53] Pratt, He Gave Us Stories, 324. Copyright © Joel James, 2008. Used by permission.

አይደለም።[54] ለምሳሌ ዳዊት ብዙ ሚስቶች ነበሩት፣ ዝሙት ፈጽሟል፣ ኃጢአቱን ለመደበቅ ሰው ገድሏል። ልንከተላቸው የሚያስፈልጉ ስለ ዳዊት ብዙ ነገሮች አሉ፤ እነዚህ ግን ከእነዚያ ውስጥ አይደሉም። ለምንድነው የማይሆኑት? የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ክፍሎች ይህ በእግዚአብሔር የተጠላ ጸባይ እንደሆነ ይነግሩሃል።

በተመሳሳይ መንገድ የመጽሐፍ ቅዱስ ድርጊቶች በአብዛኛው የአንድ ጊዜ፣ የማይደገሙ ድርጊቶች ናቸው። ሁሉም ሰው እንደ ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት መነጋገር አለበት? ኢየሱስ ያደረገውን ነገር ሁሉ ማድረግ አለብን? በቅርቡ ውሃ ላይ ለመራመድ ሞክረህ ታውቃለህ? በሌላ አገላለጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ ባሕርይ ያደረገውን ነገር አንተም ማድረግ አለብህ ማለት አይደለም። ያንን ነገር እንድታደርግ እና ጀግናውን እንድትከተል እግዚአብሔር እንደሚጠብቅብህ አስቀድመህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እርግጠኛ ሁን።

## ትረካ እና አስተምህሮ

ከመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ አስተምህሮ ስታዘጋጅ ጥንቃቄ ማድረግ ተለማመድ።[55] ትረካዎች የመለኮት እስትንፋስ ያለባቸው እና ባለ ሥልጣን ናቸው። ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ስለ ስነመለኮታዊ ጉዳይ ሁሉንም ነገር አይናገሩም። ዝርዝር ያለመስጠታቸውን ክፍተት ለአደገኛ ትምህርት መወለድ አትጠቀም። ትረካዎች ብዙ ጊዜ እንዲያስተምሩ ያልታሰቡለትን ነገር "ለማስረገጥ" ይጠመዘዛሉ። አንድን አስተምህሮ ስታዳብር ርእሰ ጉዳዩን በቀጥታ ከሚዳስሱ ትምህርታዊ የምንባብን ክፍሎች ጀምር፤ ከዚያ ይህ አስተምህሮ የተብራራበትን ምንባብ ተመልከት።

## በደንብ ስበክ!

የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ተረት አይደሉም። ገጸ ባህሪዎቹ እነዚህ ነገሮች የደረሱባቸው እውነተኛ ሰዎች ናቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎችን ስትሰብክ ይህን ማስታወስ አለብህ። በጊዜው ብትኖር ኢዮብ በልጆች ሞት ምክንያት በኀዘን ልብሱን በቀደደ ጊዜ ከምንጮቹ ላይ እምባውን ልትጠርግለት ትችል ነበር። ያንተም ሕዝብ ኢዮብ 1–2 ስትሰብክ ያ ኀዘን ሊሰማቸው ያስፈልጋል። ምናባዊ እሳቤህ መጽሐፍ ቅዱስ ያልሰጠውን እና ያልጠቀሰውን ዝርዝር ወደ መፍጠር እንዲሮጥ አትፍቀድለት። ነገር ግን እውነት መሆኑን በሚያሳይ መንገድ ድጋሚ ተናገረው። ታሪኩን እንደገና ስትናገረው ጸሐፊው የፈለገውን ስነመለኮታዊ ትምህርት አስተምር፤ ያም እግዚአብሔር ትረካውን ሊሰብክ በሚችልበት መንገድ መስበክ ነው።

---

54 Deuel, "Expository Preaching," 284.
55 Ibid., 284.

ትረካ የመስበክ ችሎታህን ለመቅረጽ የሚከተሉትን ምንባቦች አንብበህ በዚህ ምዕራፍ የተማርካቸውን መርሆዎች እንዴት እንደሚያሳዩ መዝግብ።

**ተደጋጋሚ ቃላት እና ሐረጎች**

ዕዝ 7፥6፣ 9፣ 28፤ 8፥18፣ 21–23፣ 31

ኢዮ 1፥1፣ 8፤ 2፥3

መሳፍንት 17፥6፤ 18፥1፤ 19፥1፤ 21፥25

**ማካተቻ**

1ኛ ሳሙኤል 15፥34፤ 16፥13

በጸሐፊው ቃላት ላይ አርትዖታዊ ማጠቃለያ

2ኛ ነገሥት 17፥7–23

መሳፍንት 13፥1፤ 14፥3

በገጸ ባሕርዩ አንደነት የተሰጠ ማጠቃለያ

ዘፍጥረት 45፥5–7፤ 50፥20

ዮሐንስ 4፥42

# ምዕራፍ አሥር

# ትረካን መመሰል እና ማውጫ ማዘጋጀት

በምስላዊ መግለጫዎች አምናለሁ፤ ግን የዳዊትን እና የጎልያድን ታሪክ ለመስበክ ስትዘጋጅ የአንደኛውን ሳሙኤል 17 አምሳ ስምንቱንም ምዕራፎች በስዕል መግለጽ አለብህ? ስለ ጎልያድ የራስ ቁር፣ የጦር ዕቃ፣ ጭሬ የሚናገሩ ጥቅሶችን በምስል ማቅረብ ክፍሉን በጥንቃቄ ከማንበብ የተሻሻለ ግልጠት አይሰጥም። ታዲያ ለረጃጅም ምንባቦች ሲሆን ምስላዊ መግለጫዎችን መተው አለብህ? አይደለም። ምስላዊ መግለጫዎች ሲዘጋጁ የረጃጅም ትረካዎች ሁሉም ጥቅሶች የግድ አስፈላጊ አይደሉም። ረጅም የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ ለመስክና ስትዘጋጅ እነዚህን ሁለት ደረጃዎች በታማኝነትና መወጣት አለብህ።

### ለታሪኩ ማውጫ አዘጋጅ

1. ታሪኩን በዝርዝር አዋቅር። ያለፈው ምዕራፍ እንድታደርግ እንዳስተማረህ መቼቱን፣ ክስተቶችን፣ ገጸ ባሕርያትን፣ ምልልሶችን፣ አርትዖታዊ አስተያየቶችን፣ መልስ አዘል ጥያቄዎችን፣ እና ታሪኩን የሚገነቡ ሌሎች ነገሮችን መዝግብ።[56] ይህ ማውጫ በአንድ መልኩ የአንተ ምስላዊ መግለጫ ነው። የምንባቡ የተለያዩ ክፍሎች ታሪኩን ለማስኬድ በትብብር እንደሚሠሩ ያሳያል። በ1ኛ ሳሙኤል 17 ከሚገኘው የዳዊት እና የጎልያድ ታሪክ ከታች ቀለል ላለ ማውጫ ምሳሌ ነው።

1–3 የእግዚአብሔር ኀይል ስፍራ ( መልክዓ ምድራዊ መቼት)

4–11 የእግዚአብሔር ኀይል ተገዳዳሪ (ጎልያድ)

12–22 የእግዚአብሔር ኀይል መገለጫ (ዳዊት)

23–30 የእግዚአብሔር ኀይል ድፍረት (የዳዊት ፍርሃት አልባ አስተሳሰብ)

31–39 የእግዚአብሔር ኀይል ችላ የማለት ተስፋ መቁረጥ (ሳኦል ዳዊትን ለመጠቀም መፍቀዱ)

40–47 ስለ እግዚአብሔር ኀይል ውይይት (የዳዊት እና የጎልያድ ንግግር)

---

[56] Kaiser, "Narrative," 80.

48–50 የእግዚአብሔር ኀይል መገለጥ (ያልተጠበቀው የዳዊት ድል፤ በተሻለ አገላለጽ የተጠበቀው የእግዚአብሔር ድል)

ይህ ማውጫ የምንባቡን ሰዋሰው አያሳይም፤ እንደዚህ ዓይነቱ ምስላዊ መግለጫ ለአጠቃቀም የማይመች ውዝፍ ይሆናል። ቢሆንም ግን ምስላዊ መግለጫ የምንባቡን ክፍሎች በሚያስቀምጥበት በተመሳሳይ መንገድ ይህ ማውጫ የታሪኩን ክፍሎች ያስቀምጣል።

በረጃጅም የትረካ ክፍሎች ዝርዝር ማውጫ የአንተ ምስላዊ መግለጫ ነው። ግን በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ውስጥ በምስል ማስቀመጥ የሚገባህ የተደበቀ ወርቃማ ጭብጥ፣ ትንሽ የሆነ፣ ጠቃሚ ስነመለኮታዊ ክፍል አለ። በዚህ ምክንያት ሁለተኛ ደረጃ እመክራለሁ።

## ቁልፉን ክፍል በምስል ግለጽ

ቁልፍ ስነመለኮታዊ ክፍሎችን ወይም የታሪክ ክፍሎችን በምስል ግለጽ። በአብዛኞቹ ትረካዎች ምልልስ እና አርትዖታዊ ማጠቃለያ የጸሐፊውን መልእክት እንደሚያስተዋውቅ ደማቅ ጽሑፍ ይኖራል። ያ ክፍል እንቁላሉ ነው፤ የታሪኩ ስነመለኮት ቢጫ አስኳል የሆነውን ምግብ ለማግኘት እርሱን መስበር አለብህ። ስለዚህ ትረካዎችን ሳጠና የታሪኩን ወሳኝ ክፍሎች ምስላዊ በሆነ መንገድ ማስቀመጥን ልማድ አድርጌአለሁ። ለምሳሌ አንደኛ ሳሙኤል 17ን ስሰብክ ታሪኩን አጥንቼ ማውጫ አዘጋጀሁለት (ከላይ በተቀመጠው መልክ)። ጸሐፊው 17፥50 ላይ“በዳዊትም እጅ ሰይፍ አልነበረም።” ብሎ ስለ ዳዊት የሰጠውን አርትዖታዊ አስተያየት በልዩነት መዝግቤአለሁ። ዳዊት 17፥34–37 እና 17፥45–47 ላይ የተናገራቸውን ወሳኝ ስነመለኮታዊ ዐ.ነገሮች ስዕላዊ በሆነ መንገድ አስቀምጬዋለሁ። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተነገሩት የዳዊት ቃላት የታሪኩን ስነመለኮታዊ ትምህርት ይሸከማሉ። ቁልፍ የሆነው ክፍል 17፥45–47 ከታች በምስላዊ መንገድ ቀርቧል። በዳዊት ንግግር ውስጥ የያህዌን ልዩ ኀይል ማግኘት ትችል እንደሆን ተመልከት።

አንተ

ሰይፍና

ጦር

ጭሬም ይዘህ

ትመጣብኛለህ፤

እኔ ግን ዛሬ

በተገዳደርኸው

በእስራኤል ጭፍሮች አምላክ ስም

በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም

እመጣብሃለሁ።

እግዚአብሔር

ዛሬ

አንተን

በእጄ አሳልፎ ይሰጣል፤

እመታህማለሁ፥

ራስህንም ከአንተ አነሣዋለሁ፤

የፍልስጥኤማውያንንም ሠራዊት ሬሶች ለሰማይ ወፎችና ለምድር አራዊት ዛሬ እሰጣለሁ።

ይኸውም [ዓላማው]

ምድር ሁሉ በእስራኤል ዘንድ አምላክ እንዳለ ታውቅ ዘንድ፤

ይህም ጉባኤ ሁሉ እግዚአብሔር

በሰይፍና በጦር የሚያድን እንዳይደል ያውቅ ዘንድ ነው።

ሰልፉ ለእግዚአብሔር ነውና፤

እናንተንም

በእጃችን አሳልፎ ይሰጣል።

*እግዚአብሔር ዛሬ አንተን በእጄ አሳልፎ ይሰጣል* የሚለው ሐረግ የዳዊትን እና የጎልያድን ታሪክ ስነመለኮታዊ ትምህርት ይገልጣል። ትንሽ ልጅ ትልቁን ሰውዬ ሲመታው የሚያሳይ ደስ የሚል ታሪክ አይደለም። ታሪኩ ዳዊት ግዙፉ ላይ ስለተቀዳጀው ያልተጠበቀ ድል አይደለም። ሦስት ሜትር ቢረዝምም ከቁብ በማይቆጠረው ሰው ላይ ተጠባቂ ስለነበረው የእግዚአብሔር ድል ነው። የዳዊት ንግግር ትምህርቱን ያደምቃል። የእግዚአብሔር ኀይል ከጎልያድ ኀይል ከንጽጽር በላይ የላቀ ነው። የእግዚአብሔር ኀይል የቀጭኔን ያህል የሚረዝም ሰው በያዘው ሰይፍ እና ጭሬ የማይበገር ነው። በርግጥ በዳዊት ንግግር ምክንያት ለታሪኩ የምንሰጠውን ርእስ ዳዊት እና ጎልያድ ከማለት እግዚአብሔር እና ጎልያድ ወደማለት እንቀይራለን።[57] ብዙ ሰባኪዎች ዳዊት ከሳኦል እና ከጎልያድ ጋር ባደረገው ምልልስ ውስጥ ለጸሐፊው ስነመለኮታዊ ትምህርት በቂ ትኩረት ስላልሰጡ የእግዚአብሔርን እና የጎልያድን ታሪክ በተሳሳተ መልኩ አስተምረውታል። ነገር ግን የዳዊትን ንግግር በምስላዊ መግለጫ ብናስቀምጠው እያንዳንዱ የስነመለኮት ጠብታ ተጨምቆ ይወጣል፤ አንተም የጸሐፊውን ስነመለኮታዊ መልእክት ማግኘት ትችላለህ።

## የብዙ ቁጥር ስም ማውጫዎች

የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማውጫዎች ትኩረት የሚያደርጉት የታሪኩ መቼት፣ ክስተቶች፣ ገጸ ባሕርያት፣ እና ምልልሶች ላይ ነው። ለምሳሌ የሚከተለው ማውጫ በአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ሕይወት ውስጥ አራት ቁልፍ ነገሮችን ይለያል። (ሐዋ 11፥19–30፤ 13፥1–3)

### 1) የወንጌል ስብከታቸው

“ከእነርሱ ግን የቆጵሮስና የቀሬና ሰዎች የነበሩት አንዳንዶቹ ወደ አንጾኪያ መጥተው የጌታን የኢየሱስን ወንጌል እየሰበኩ ለግሪክ ሰዎች ተናገሩ። የጌታም እጅ ከእነርሱ ጋር ነበረ፤ ቍጥራቸውም እጅግ የሚሆን ሰዎች አምነው ወደ ጌታ ዘወር አሉ። ወሬውም በኢየሩሳሌም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ስለ እነርሱ ተሰማ፥ በርናባስንም ወደ አንጾኪያ ላኩት” (11፥20–22)

### 2) ልምምዳቸው

* The fact that no one can stand against David, God's anointed, reminds us that no one will be able to stand against David's greatest son, the ultimate God-appointed king, Jesus Christ. If God's power worked through David, how much more so through Christ? That's a legitimate connection to Christ, made from the story's main point.

“በርናባስም ሳውልን ሊፈልግ ወደ ጠርሴስ መጣ፤ ባገኘውም ጊዜ ወደ አንጾኪያ አመጣው። በቤተ ክርስቲያንም አንድ ዓመት ሙሉ ተሰበሰቡ፥ ብዙ ሕዝብንም አስተማሩ፤ ደቀ መዛሙርትም መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ።” (11፥25–26)

**3) አገልግሎታቸው**

“በዚያም ወራት ነቢያት ከኢየሩሳሌም ወደ አንጾኪያ ወረዱ፤ ከእነርሱም አጋቦስ የሚሉት አንድ ሰው ተነሥቶ በዓለም ሁሉ ታላቅ ራብ ሊሆን እንዳለው በመንፈስ አመለከተ፤ ይህም በቀላውዴዎስ ቄሣር ዘመን ሆነ። ደቀ መዛሙርትም እያንዳንዳቸው እንደ ችሎታቸው መጠን አዋጥተው በይሁዳ ለሚኖሩት ወንድሞች እርዳታን ይልኩ ዘንድ ወሰኑ፤ እንዲህም ደግሞ አደረጉ፥ በበርናባስና በሳውልም እጅ ወደ ሽማግሌዎቹ ሰደዱት።” (11፥27–30)

**4) ተልዕኳቸው**

“በአንጾኪያም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ነቢያትና መምህራን ነበሩ፤ እነርሱም በርናባስ፥ ኔጌር የተባለው ስምዖንም፥ የቀሬናው ሉክዮስም፥ የአራተኛው ክፍል ገዥ የሄሮድስም ባለምዋል ምናሔ፥ ሳውልም ነበሩ። እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ፦ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ። በዚያን ጊዜም ከጦሙ ከጸለዩም እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው።” (13፥1–3)

ይህ ማውጫ በቀላሉ ራሱን ለብዙ ቁጥር ስም ማጠቃለያ የሰጠ ነው፤ "በዚህ ምንባብ ቤተክርስቲያናችንን ጠንካራ የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ለማድረግ ልንከተል የምንፈልጋቸውን አራት ተግባሮች ከአንጾኪያ ቤተክርስቲያን እናገኛለን።" ይህ ግልጽ እና ቀላል የሆነ ማውጫ ግልጽ እና ውጤታማ ስብከት እንድትሰብክ ይረዳሃል።

ከነህምያ 4–6 ለማንበብ ጊዜ ብትወስድ እነዚያ ምዕራፎች በዚህ ማውጫ ሊጠቀለሉ እንደሚችሉ ታገኛለህ።

4፥1–6 ስድቦች

4፥7–23 ወረራ

5፥1–19 ውስጣዊ ቀውስ

6፥1–14 ሴራዎች

6፥17–19 መሹለክ

በነህምያ 4–6 ያሉትን አምስት ብርትኳኖች በአንድ ከረጢት ውስጥ ማስቀመጥ እንችላለን፤ “በነህምያ 4–6 ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንደገና ሲሠራ እግዚአብሔር ነህምያ እንዲያሸንፍ የረዳው አምስት አይነት ተቃውሞዎች አሉ።” የትረካው ስነ መለኮታዊ ነጥብ በ6፥16–16 ሕዝቡ ቅጥሩን በአምሳ ሁለት ቀን እንዳጠናቀቀ በጻፈው ይጠቃለላል፤ ከዚያም ይህንን ይጨምራል “ጠላቶቻችንም ሁሉ ይህን በሰሙ ጊዜ … በራሳቸውም አሳብ እጅግ ተዋረዱ፥ ይህም ሥራ በእግዚአብሔር እንደ ተደረገ አወቁ።” (6፥16)

## የምንባብ ወሳኝ ነገሮች ማውጫ

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች ወደ ብዙ ቁጥር ስም ማጠቃለያ እንዳይጨፈለቁ በመቋቋም ይገግማሉ። ያን ጊዜ ስለ ብዙ ቁጥር ስሞች ፈጽሞ አትጨነቅ፤ ታሪኩን እንደገና የሚናገር ማውጫ ተጠቀም። አንድን ትልቅ ታሪክ በማይሠራለት የብዙ ቁጥር ስም ለምን ታቀነጭረዋለህ? ታሪኮች የራሳቸው የሆነ ተፈጥሯዊ ግስጋሴ አላቸው፤ እሱ እንዲሠራልህ አድርግ።[58] ከታሪኩ እንደገና የሚናገረው ማውጫ የታሪኩን ክስተቶች፣ ገጸ ባሕሪዎች፣ ምልልሶች እና ሌሎችንም ለማጠቃለል የምንባብ ወሳኝ ነገሮች የተባሉ ቃላትን እና ሐረጎችን ይጠቀማል።

ከላይ ቀርቦ የነበረው የአንደኛ ሳሙኤል 17 ማውጫ ይህንን አካሄድ ያብራራል። በዚያ ማውጫ ውስጥ የምንባቡ ወሳኝ ነገሮች ስፍራው፣ ተገዳዳሪው፣ መገለጫው፣ ድፍረት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ውይይት፣ እና የእግዚአብሔር ኀይል መገለጥ ናቸው። እነዚህ ነገሮች የእግዚአብሔርን እና የጎልያድን ታሪክ እንደገና ይናገራሉ። ሰብከት ከእንዱ ክፍል ወደሌላው ክፍል ሲሸጋገር ለጉባኤው ምን መመልከት እንዳለበት ይናገራሉ። በተጨማሪ የእግዚአብሔር ኀይል የሚለውን ቃል በእያንዳንዱ ቃል ላይ በመጨመር አድማጮቹ ስነመልኮታዊ ትምህርቱን ከመመልከት ፈጽሞ እንዳይስቱ ያረጋግጣል።

የሚከተለው የማቴዎስ 26፥57–68 ማውጫ ኢየሱስ በታሰረበት ምሽት በአይሁድ አለቆች ፊት የነበረውን የክስ ሂደት እንደገና ይናገራል። በሂደቱ ቁልፍ ክስተቶች እና ገጸ ባሕርያት ላይ ያተኩራል። ክሱ እና መቃወሚያው የታሪኩን ስነ መለኮታዊ ትምህርት ያደምቃል፤ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ለራሱ መሰከረ።

57 ተከሳሽ (ኢየሱስ)

58 Mathews, "Preaching," 42.

58 ተመልካች (ጴጥሮስ)

59 ከሳሽ (ሸንጎ)

59–62 ምስክር (የሃይማኖት መሪዎች ሐሰተኛ ምስክሮች)

63 ክስ (ኢየሱስ መሲሕ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ስለመሆኑ መናገሩ)

64 የተከሳሽ ቃል (የኢየሱስ ክሱን መቀበል)

65–68 ፍርድ (ስቅላት)

ለታሪክ የምንባብ ወሳኝ ነገሮችን ማውጫ ማዘጋጀት የእግዚአብሔርን ታሪክ እንደገና ለመናገር ውጤታማ መንገድ ነው። የምንባባዊ ወሳኝ ነገሮች ድክመት እንደ ብዙ ቁጥር ስም ማጠቃለያ የታሪኩን ስነ መለኮታዊ ትምህርት አጠቃሎ አይዝም። ስለዚህ ምንባባዊ ወሳኝ ነገሮችን የምትጠቀም ከሆነ በስብከት የጸሐፊውን ስነ መለኮታዊ ትምህርት በተገቢው ቦታ እንደምታደምቅ እርግጠኛ ሁን። ባለ ብዙ ቁጥር ስም ማጠቃለያ አልያም ምንባባዊ ወሳኝ ነገሮችን ተጠቅመህ ከምንም በላይ የእግዚአብሔርን ታሪክ እንደገና ተናገር፤ በጸሐፊው የታሰበውን ስነ መለኮታዊ ትምህርት አስተምር፤ ያ ነው ትረካን እግዚአብሔር እንደሚሰብከው አድርጎ መስበክ።

# ምዕራፍ አስራ አንድ

# ምሳሌዎችን ማጥናት

ጓደኛዬ ስኮት ሊያገባ ካሰባት ሴት ጋር እጮኝነት ሲጀምር ሁለት መቶ ኪሎሜትር ያህል ርቀት ላይ ቢኖርም የልጅቷ አያት የስኮትን መንፈሳዊ እድገት ተመልክቶ ደስተኛ ሆኗል። በመጀመሪያው ጉብኝቱ ወቅት ስለ ግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እየተወያዩ ሳለ ይህ ጠቢብ ሽማግሌ ወደ ጠረጴዛው በማዘንበል የስኮትን መጽሐፍ ቅዱስ ከእጁ በመንጠቅ ብርሃን ላይ በአንድ ደቂቃ መረመረው። ጠርዙ ወርቅማ የተቀባ አዲስ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ሽማግሌው ምርመራውን አጠናቆ መጽሐፍ ቅዱሱን ሲመልስለት ከምርመራው ምን እንደተረዳ ነገረው። የጓደኛዬ መጽሐፍ ቅዱስ የኋለኛው ሩብ ገጾች ወርቅማ ቅብ ለቆ ነበር። የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ገጾች ብዙ የተገለጡ እና በተደጋጋሚ የተነበቡ በመሆናቸው ታጥፈዋል፣ ቆሽሸዋል። ነገር ግን የጓደኛዬ መጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያዎቹ ሦስት አራተኛ ገጾች አዲስ እና አብረቅራቂ ወርቅማ ቅባቸውን እንደጠበቁ ነበር። ሽማግሌው ወዳልተነካው መካከለኛ ክፍል በመግለጥ በተለይ ደግሞ ወደ ምሳሌ እና መዝሙር መጻሕፍት በመጠቆም እንዲህ አለ፤ "ልጄ ሆይ በቀጣይ የጉብኝት ጊዜዬ እነዚህ ገጾች እንደ አዲስ ኪዳን ገጾች ቆሽሸው ማግኘት እፈልጋለሁ።"

ብዙ አያቶች እንደዚህ አይነት ምክሮችን እንዲሰጡ እመኛለሁ። በርግጥ ብዙ ሰባኪዎች ይህን ምክር ለግል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታቸው ብቻ ሳይሆን ለስብከታቸውም ቢወስዱት ጥሩ ነው። መጽሐፈ ምሳሌ ሕይወት ለዋጭ መጽሐፍ ነው፤ የመዝሙር መጽሐፍ የእግዚአብሔርን ትልቅነት ጮክ ብሎ የሚናገር መጽሐፍ ነው፤ ነገር ግን የሚመረምሯቸው ጥቂት ሰባኪዎች ብቻ ናቸው። መመርመር? አብዛኞቹ ፈጽሞ አይሰብኳቸውም። ለጉባኤያቸው ሁለቱ የታሰሩ አንበሶች ናቸው። ቀላል፣ ኃይለኛ፣ በጦር ሜዳ ተወዳዳሪ የሌላቸው፣ ጥበብ እና አምልኮ ታጥሮባቸው በዝምታ ያያሉ፤ አርቆ የሚመለከቱ ዐይኖች፣ እስኪለቀቁ ድረስ ይጠብቃሉ፤ ነገር ግን ሰባኪው መደረክ ላይ ሰብኳቸው በማያውቅ ገጾች ውስጥ ተቆልፎባቸው እስረኞች ሆነው ይቆያሉ። ጥበብ እና አምልኮ ማድረግ የሚችሉት ሰባኪው አንድ ቀን ከምሳሌ እና ከሊዝ መጽሐፍ እንደሚሰብክ ተስፋ በማድረግ በጉባኤው ሞኝነት እና ስለ እግዚአብሔር ባላቸው ዝቅተኛ አመለካከት ላይ ጥፍራቸውን እና ጥርሳቸውን ለማሳረፍ ጡንቻዎቻቸውን እያላቀቁ፣ እያፍታቱ መጠበቅ ነው። ነገር ግን ሰባኪው ቁልፉን አይከፍትም ኃይላቸውም ባክኖ ይቀራል ማለት ነው።

ምናልባት ሰባኪው በፍርሃት ተይዞ ሊሆን ይችላል። ተመሳሳይ የአዲስ ኪዳን ዳገት በመውጣት እና ወንዝ ዳር በመዝናናት ለለመደ ሰባኪ ምሳሌ እና መዝሙር አባጣ ጎርባጣ ይሆንበታል። እንዲህ አይነቱ ፍርሃት አሳዛኝ ነው፤ ሰባኪው የምሳሌን ጠባብ ግን ቀጥተኛ መንገድ እንዲሁም የመዝሙርን የተራራ ጫፍ እና የሸለቆ ጥግ ለመጓዝ የተበረታታ እንዲሆን አስደናቂ እይታዎች ይጠብቁታል። በምሳሌ እና መዝሙር መጽሐፍት እንግዳነት ወይም በአዲስ ኪዳን ገጾች መጠመድ (ጥሩ ነገር ነው!) የእኔ ዓላማ በዚህኛው እና በሚቀጥለው ምዕራፍ አንተን በበር አስወጥቶ በአዲስ ጎዳና ማስኬድ ነው። የምሳሌ እና የመዝሙር አንበሶች ይለቀቁ! ያለ መጽሐፈ ምሳሌ ጉባኤህ እንዴት ጠቢብ ይሆናል? ያለ መዝሙር መጽሐፍ እንዴት በአምልኮ የተሞሉ ይሆናሉ? ከምሳሌ እና ከመዝሙር መጽሐፍ ስበክ፤ የጉባኤው ኃጢአት እና ጣኦት ከአንበሳ ፊት እንደደነበረ የሚዳቆ መንጋ ሲበተን ታያለህ። ሰባኪ እንደመሆኔ ምሳሌ የሚያነቃቃኝ መጽሐፍ ነው። ይህ ምዕራፍ ምሳሌን እንዴት ማጥናት እንዳለብን ማውጫ ያቀርባል፤ የሚቀጥለው ደግሞ የመዝሙር መጽሐፍ ላይ ያተኩራል።

## የምሳሌ መጽሐፍ ሕይወት ነው

ከየትኛውም መጽሐፍ በላይ የምሳሌ መጽሐፍ በዕለት ተዕለት ሕይወትህ — ማክሰኞ ማለዳ አስራ ሁለት ሰዓት ላይ ከአልጋ ለመውረድ ጊዜው ሲሆን፣ ሐሙስ ከሰዓት ዘጠኝ ሰዓት ላይ ልጆችህ መጥፎ ጸባይ ሲያሳዩ፣ አርብ ከምሽቱ አምስት ሰዓት ላይ ወንበዴ ችግር ሊፈጥር ሲል — እንዴት ክርስቶስን መምሰል እንዳለብህ ያስተምራል። የምሳሌ መጽሐፍ ክርስቶስን የሚመስል ሕይወት እንድትኖር የሚያስተምርህ ግንኙነቶችህ ከእግዚአብሔር እርሱን በመፍራት) እና ከሰዎችም ጋር ያለህን እንዴት መያዝ እንዳለብህ በማሳወቅ ነው። ይህ መጽሐፍ በሚያተኩርበት ልክ ለግንኙነቶቻችን ትኩረት መስጠት ተገቢ ነው? አዎ። ህይወትን ጥሩ ወይም መጥፎ የሚያደርጉት ግንኙነቶችህ ናቸው፤ ገንዘብ፣ የምትኖርበት ቤት፣ የምትለብሰው ልብስ አይደለም፤ ከእግዚአብሔር፣ ከአጋርህ፣ ከልጆችህ፣ ከሰፊው ቤተሰብህ፣ በየቀኑ ከምትገናኛቸው ሰዎች ጋር ያሉህ ግንኙነቶች ናቸው። ሰሎሞን ራሱ “የጐመን ወጥ በፍቅር መብላት የሰባ ፍሪዳን ጥል ባለበት ዘንድ ከመብላት ይሻላል።” (15፥17) ሲል የግንኙነቶች ጠቃሚነት ላይ ያሰምራል። ጎመን እና ፍቅር ከጮማ እና ከጥል ይሻላሉ።

## የፍቺ ጠበቃ እና የጋብቻ አማካሪ

ምሳሌን ከሙሴ ሕግ ጋር በማነጻጸር የምሳሌን ጠቃሚነት ለማብራራት ወደድኩ። ሕጉ እንደ ፍቺ ጠበቃ ነበር፤ ከአንድ ሰው ጋር ያለህ ግንኙነት ከፈረሰ በኋላ አንተ መከተል ያለብህን ሕጋዊ አካሄዶች ይዘረዝራል። ምሳሌ ግን እንደ ጋብቻ አማካሪ ነው፤ ግንኙነቶችህ ከመፍረሳቸው በፊት እንዴት ማስተካከል እንደምትችል ያስተምርሃል።

አንተ የብሉይ ኪዳን እስራኤላዊ እንደሆንክ እናስብ፤ የዝናብ ውሃ የምታጠራቅምበት ጉድጓድ እየቆፈርክ ነበር፤ ነገር ግን ጉድጓዱን ለማጠር ወይም ለመሸፈን ችላ አልክ። በአሳዛኝ ሁኔታ የጎረቤትህ አህያ ምግብ ፍለጋ ሲዞር ጉድጓዱ ውስጥ ወድቆ ሞተ። እንዲህ ሲሆን ምን ምን መደረግ እንዳለበት የሙሴ ሕግ በቀጥታ ነግሮሃል። ዘጸአት 21፥33-34 የአህያውን ትክክለኛ ካሳ ለጎረቤትህ መክፈል እንዳለብህ እና የፍጡሩንም አካል ማስወገድ የአንተ ኃላፊነት እንደሆነ ይናገራል።

በሌላ አነጋገር ሙሴ በዋነኛነት የተናገረው አስቀድሞ ስለተበላሹ ግንኙነቶች ነው። ከመጀመሪያው ደረጃ እንዳይበላሽ እንዴት መጠበቅ እንዳለብህ ለማስረዳት የሰጠው ቦታ ትንሽ ነው። ያ የምሳሌ መጽሐፍ ተግባር ነው። በውሃ ጉድጓድ ችግር ምክንያት የሚመጡ ሕጋዊ መዘዞችን እንዴት መያዝ እንዳለብህ ሙሴ ነግሮሃል፤ ነገር ግን አህያው የሞተበት ጎረቤትህ በንዴት እየጮኸ የቤትህን በር ላይ ቢቆም ምን ማድረግ እንዳለብህ አይነግርህም። ምሳሌ የተጻፈበት ምክንያት ይህ ነው። አህያው የሞተበት ጎረቤትህ ደጅህ ላይ ሲቆም ሰሎሞን ልብሱን አጣጥፎ እጁን በጉጉት እያሻሸ ጥበብን ያሰናዳል "ሰነፍ ሰው ቍጣውን ሁሉ ያወጣል፤ ጠቢብ ግን በውስጡ ያስቀረዋል" (29፥11) "ለሰነፍ እንደ ስንፍናው አትመልስለት" (26፥4) "የለዘበች መልስ ቍጣን ትመልሳለች" (15፥1) "ስለዚህ ጠብ ሳይበረታ አንተ ክርክርን ተው።" (17፥14) "ከክርክር ይርቅ ዘንድ ለሰው ክብሩ ነው፤ ሰነፍ ሁሉ ግን እንዲህ ባለ ነገር ይጣመራል።" (20፥3)

ሙሴ የነገረህ ያልጨረስከውን የውሃ ጉድጓድ ለመክደን መስነፍ የሚያስከትለውን ቅጣት ሲሆን፣ ሰሎሞን ግን ትጋት እና እንደ ጉንዳን መሥራት ስንፍናን እና ላብ መጥላትን እንደሚተካ ያስተምርሃል (6፥6–11፤10፥4)። የወሲብ ንጽሕና፣ ገንዘብ፣ ዕዳ፣ የጋብቻ ውስጥ ሚና፣ ልጆችን ማሳደግ፣ ውሳኔ መስጠት፣ ሰው ማክበር፣ ውሸት፣ ግትርነት፣ ትዕቢት — የምሳሌ መጽሐፍ ክርስቶስን ለሚያከብሩ ግንኙነቶች ተግባራዊ የሆኑ ጥበቦችን ያጨቀ ነው። ምሳሌን መስበክ አለብህ።

## ምሳሌን ለማጥናት ስድስት መርሆዎች

ምሳሌዎች በቀላሉ የሚዋጡ ውጤታማ መድኃኒት — በኪኒን መልክ የቀረቡ ጥበብ ናቸው። በርግጥ አንዳንድ ጊዜ ከምሳሌ መጽሐፍ ስሰብክ ጥፋተኝነት ይሰማኛል። ዕይታዎቹ ስብከት እስከማያስፈልጋቸው ድረስ በጣም ግልጽ፣ በጣም ቀላል፣ ወዲያው ተግባራዊ የሚደረጉ ናቸው። መድረክ ላይ ቆመህ፣ "ሞኝ ሁልጊዜ ይጋጫል" የሚለውን ቃል አንብበህ በጸሎት መዝጋት ትችላለህ። ከዚህ በላይ ምን ያስፈልጋል? በርግጥ የበለጠ ያስፈልጋል። ማብራሪያዎች፣ መግለጫዎች፣ ማጣቀሻዎች፣ እና የክርስቶስን ቦታ ጨምሮ ሁሉም አስፈላጊ

ናቸው፤ እውነታው እና ደስ የሚለው ነገር ደግሞ ምሳሌዎች በአንድ ዐ.ነገር የቀረበ ስብከት ስለሆኑ እነርሱን መስበክ አስደሳች ነው።

ነገር ግን መፈክራችን እንደሚያስታውሰን እግዚአብሔርን ለመስበክ መጀመሪያ እግዚአብሔርን ማጥናት አለብህ። ከምሳሌ መጽሐፍ ስብከት በምታዘጋጅበት ጊዜ ልንገነዘባቸው የሚገቡ ልዩ መርሆዎች አሉ? ስድስት ልስጥህ።

### 1) ለትይዩነት ትኩረት ስጥ

የአማርኛ ግጥም የሚጻፈው ተመሳሳይ ድምጽ ባላቸው ቤት መምቻዎች ነው። *ገጣሚ ነኝ፤ እወቅልኝ*። የዕብራይስጥ ግጥም ቤት መምቻዎችን ቢጠቀምም አብዛኛውን ጊዜ ለተመሳሳይ ሐሳቦች እና አወቃቀሮች ላይ ማተኮር ይመርጣል።[59] ዕብራውያን ገጣሚዎች ሁለት ስንኞችን በተመሳሳይ ቤት መምቻ ከማገናኘት ይልቅ በተመሳሳይ ሐሳብ እና ቃላት ማያያዝ ይመርጣሉ፤ ይህም ትይዩነት ይባላል። የምሳሌን መጽሐፍ ለማጥናት የሚጠቅሙ አራት የትይዩነት አይነቶች አሉ።[60]

### አቻዎች

**1. *የተመሳሳይ ትይዩነት።*** ይህ የሚሆነው የምሳሌው ሁለተኛ ስንኝ ጥቂት የቃላት ለውጥ በማድረግ የመጀመሪያውን ስንኝ መመሪያ ወይም ሐሳብ ሲደግም ነው። ሲ. ኤስ. ልዊስ ጉዳዩን “አንድን ነገር በተመሳሳይ ቃላት ሁለት ጊዜ መናገር ነው”[61] ሲል ይገልጸዋል፤ ከነጥቡ አልራቀም። ሁለቱ ስንኞች ከአቻነት በላይ ከልዩነት በታች ናቸው ማለት ይበልጥ ትክክል ይሆናል። ሁለቱን ቃላት በማጣመር የሁለቱን ስንኞች ግንኙነት ውጤታማ በሆነ መንገድ መረዳት ትችላለህ። ምሳሌ 16፥18 ውሰድ፤ “ትዕቢት ጥፋትን፥ [በተጨማሪም] ኵሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል።” በምስላዊ መግለጫ ሲቀመጥ ትይዩነቱ ምን እንደሚመስል ተመልከት።

ትዕቢት ጥፋትን [ይቀድማል]

ኵሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል

---

59 Bruce K. Waltke, The Book of Proverbs, 2 vols., The New International Commentary on the Old Testament (Grand Rapids, Mich.: William B. Eerdmans Publishing Company, 2004), 1:41.

60 These four categories are taken from C. Hassel Bullock, "The Book of Proverbs," in Learning from the Sages: Selected Studies on the Book of Proverbs, ed. by Roy B. Zuck (Grand Rapids, Mich.: Baker Books, 1995), 31-33.

61 C. S. Lewis, Reflections on the Psalms, reprinted in The Inspirational Writings of C. S. Lewis (New York: Inspirational Press, 1987), 134.

ከአቻነት በላይ ከልዩነት በታች። ዕብራይስጡ ለተመሳሳይ ቤት መምቻ ድምጽ ቦታ አልሰጠም፤ ነገር ግን ሰሎሞን ተመሳሳይ ሐሳቦችን እና ቃላትን በዚህ ምሳሌ ውስጥ ለማካተት ጥረት አድርጓል። ሁለቱም ስንኞች ተመሳሳይ ሐሳብ አላቸው፤ ትዕቢት እና የሚያስከትለው አደገኛ ጥፋቱ። በዚያ ላይ ሰሎሞን የተጠቀማቸው ቃላት (ትዕቢት እና ኩሩ መንፈስ፣ ጥፋት እና ውድቀት) ትክክለኛ ሚዛን ይሰጣሉ። ድግግሞሽ፣ ሚዛን፣ እና ተመጣጣኝነት የታሰበበት ነው፤ ሰሎሞን በግልጽ እንደፈለገው ምሳሌውን በአዕምሮ ለመያዝ ቀላል ያደርጉታል። ለተመሳሳይ ትይዩነት ተጨማሪ ሁለት ምሳሌዎችን ተመልከት።

ሌላ ያመስግንህ እንጂ አፍህ አይደለም

ባዕድ ሰው እንጂ ከንፈርህ አይደለም (27፥2)

ትዕግሥተኛ ሰው ከኃያል ሰው ይሻላል

በመንፈሱም ላይ የሚገዛ ከተማ ከሚወስድ ይበልጣል። (16፥32)

**ተቃራኒዎች**

**2. ተጻራሪ ትይዩነት።** ተጻራሪ የሚለው ቃል ተቃርኖን ያሳያል። ስለዚህ በተጻራሪ ምሳሌዎች ውስጥ ሁለተኛው ስንኝ የመጀመሪያው ስንኝ ተቃራኒ ነው። በምሳሌ 13፥20 ተቃራኒዎቹ መጥፎ ጓደኞች ያሉት ሰው የሚከተሉት እና ጥሩ ጓደኞች ያሉት ሰው የሚከተሉት ውጤቶች ናቸው።

ከጠቢባን ጋር የሚሄድ     ጠቢብ ይሆናል

ግን

የሰነፎች ባልንጀራ     ክፉ መከራን ይቀበላል። (13፥20)

ጠቢብ ወይም ሞኝ ጓደኛ ውጤታቸው ፍጹም ተቃራኒ ቢሆንም የሁለቱም ስንኞች ትምህርት ጓደኞችህን በጥበብና የመምረጥ ጠቀሜታ መሆኑን አስተውል። ይህ ለተጻራሪ ትይዩነት አይነተኛ ምሳሌ ነው። ሁለት ርእሰ ጉዳዮች የቀረቡ ይመስላል፤ ነገር ግን አንድ ትምህርት ብቻ ነው በአንዱ ስንኝ በአሉታዊ መንገድ፣ በአንዱ ስንኝ ደግሞ በአሉታዊ መንገድ እየተሰጠ ያለው። ሌላ ምሳሌ ተመልከት (ትይዩነቱን ይበልጥ በግልጽ ለማሳየት ቃላትን ቦታ አቀያይሬአለሁ።

በበትር ከመምታት የሚራራ ሰው　　ልጁን ይጠላል

ተግቶ ይገሥጻዋል　　ልጁን የሚወድድ ግን (13፥24)

ተቃራኒዎቹን አያችሁ? የሚያስቸግሩ ልጆችን ለመቅጣት ወይም ላለመቅጣት ሁለቱ ማነቃቂያዎች ፍቅር እና ጥላቻ ናቸው። የሚያጣምራቸው ትምህርት ደግሞ ልጆችህን የመቅጣት ጥቅም ነው። በሚቀጥለው ምሳሌ በዕዳ እና በሽልማት መካከል ያለው ንጽጽር እንዴት አንድን መልዕክት፣ ለእግዚአብሔር ቃል ያለህ አመለካከት ጠቀሜታ እንደሚያስተምር ተመልከት።

ምክርን　　የሚያቃልል　　በራሱ ላይ ጥፋት ያመጣል

ግን

ትእዛዝን　　የሚያከብር　　ወሮታን ይቀበላል። (13፥13–አ.መ.ት)

እንደተመለከትከው ተጻራሪ ምሳሌዎችን ማግኘት ከባድ አይደለም፤ አብዛኛውን ጊዜ በመካከላቸው ግን የሚለው ቃል ይኖራል። እነርሱን ስታጠና (በምሳሌ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ ናቸው) ሁልጊዜም የሚነጻጸሩ ሁለት ተቃራኒዎችን እና የሚያስተምሩትን አንዱን ትምህርት አግኝ።

**መደመር**

**3. ጥምር ትይዩነት።** ማጣመር የሚለው ቃል ሁለት ነገሮችን ማገናኘት ነው፤ መደመርን ያሳያል። ስለዚህ ጥምር ትይዩነት ማለት የምሳሌው ሁለተኛ ስንኝ በሁለተኛው ስንኝ ላይ አዲስ ሐሳብ ተጨማሪ ሲያደርግ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ሁለተኛው ስንኝ የመጀመሪያውን ስንኝ ያሰፋዋል፣ ያጎላዋል፣ ይተገብረዋል፣ ወይም ያብራራዋል። እንደ ተመሳሳይ ትይዩነት ሁሉ ስሜቱን ለማግኘት ቃላቱን እና ሌሎች ይዘቶቹን መደመር ትችላለህ። 10፥28 ላይ ሰሎሞን ጥላቻን በገሰጸበት ላይ በመጨመር ሐሜትን ይኮንናል።

ጥልን የሚከድን ሐሰተኛ ከንፈር አለው

ሐሜትንም የሚገልጥ ሰነፍ ነው። (10፥18)

ቀጥሎ ባለው ምሳሌ ላይ ሰሎሞን አስቀድሞ ትዕቢትን ሲገስጽ፣ ከዚያም ስለ ትዕቢት አደገኞች መዘዞች ሐሳብ በመጨመር ትምህርቱን ሲያጎላ እናገኛለን።

በልቡ የታበየ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ርኩስ ነው

እጅ በእጅም ሳይቀጣ አይቀርም። (16፥5

ፌዘኛ ሰው የሚዘልፈውን አይወድድም

ወደ ጠቢባንም አይሄድም። (15፥12)

**ያልተጠበቁ አቻዎች**

**4. አወዳዳሪ ትይዩነት።** የሚከተሉት ምሳሌዎች እንደ የሚለውን ቃል በመጠቀም በሰው እና በተፈጥሮ መካከል ያልተጠበቀ ውድድር ያደርጋሉ። ለምሳሌ ምሳሌ 25፥25 መልካም ዜናን እና ቀዝቃዛ ውሃን እንዴት እንዳወዳደረ ተመልከት።

,የቀዘቀዘ ውኃ ለተጠማች ነፍስ ደስ እንደሚያሰኝ፥ ከሩቅ አገር የመጣ መልካም ምስራች እንዲሁ ነው። (25፥25)

ብረት ብረትን ይስለዋል፥ ሰውም ባልንጀራውን ይስላል። (27፥17)

ሆምጣጤ ጥርስን፥ ጢስም ዓይንን እንደሚጐዳ፥ እንዲሁም ታካች ለላኩት። (10፥26)

የሒሳብ ዝንባሌ ካለህ የተለያዩ የትይዩነት አይነቶችን በሒሳባዊ ምልክቶች ማስቀመጥ ትችላለህ። በተመሳሳይ ትይዩነት የመጀመሪያው እና ሁለተኛው ስንኝ አቻ ናቸው ማለት ይቻላል፤ ሀ=ለ ብለን ልንገልጸው እንችላለን። ተጻራሪ ትይዩነት ንጽጽርን ያካትታል፤ ሀ≠ለ ብለህ ልትገልጸው ትችላለህ። ጥምር ትይዩነት በሁለተኛው ስንኝ አዲስ ሐሳብ ስለሚጨምር ሀ+ለ ነው። አወዳዳሪ ትይዩነት በሁለት ነገሮች መካከል አስገራሚ ተመሳሳይነት ይጠቁማል (ለምሳሌ ሰነፍ ሰባኪ እና ወይን መጠጣት!) ስለዚህ ሀ=ለ! ተብሎ ሊደገም ይችላል።

**ሁለት፣ አራት፣ ወይም ስድስት**

በአንዳንድ ሁኔታ ምሳሌዎች መጽሐፉን የሞሉትን የሁለት ስንኝ ውቅር በመጣስ ባለ አራት ወይም ባለ ስድስት ምሳሌዎችን ይሰጡሃል። ከታች ያሉት ምስላዊ መግለጫዎች እንደሚያሳዩት የትይዩነት ሕግ ገዢ ነው።[62]

ከቍጡ ሰው ጋር ባልንጀራ አትሁን

ከወፈፍተኛም ጋር አትሂድ፥

[ውጤቶቹ]

መንገዱን እንዳትማር

ለነፍስህም ወጥመድ እንዳታገኝህ። (22፥24–25)

ልጄ ሆይ፥ በክፉ ሰዎች አትቅና፥

ከእነርሱ ጋርም መሆንን አትውደድ፤

[ውጤቶቹ]

ልባቸው ግፍን ታስባለችና፥

ከንፈራቸውም ሽንገላን ትናገራለችና። (24፥1–2)

በመጽሐፈ ምሳሌ ውስጥ ሌሎች ብዙ አወቃቀሮች አሉ (ለምሳሌ የይሻላል ምሳሌዎች፤ 17፥1፣ 21፥9፤ 27፥5፤ 28፤6፤ ወዘተረፈ) ከላይ የተገለጹት የትይዩነት አወቃቀሮች በጣም የሚታወቁ ናቸው። ጥምር ወይም ተጻራሪ ትይዩነት የሚሉ ሙያዊ ቃላትን በመጠቀም ጉባኤህን አታስደብረው። ጉባኤህ ምንባቡን እንዲረዳው የሚያግዙ ከሆነ ብቻ እነዚህን ቃላት ተጠቀም። ነገር ግን ሰባኪ እንደመሆንህ ከእነርሱ ጋር መተዋወቅ አለብህ። ስለዚህ የተለያዩ የትይዩነት አይነቶችን የመለየት ክህሎትህን ለመገንባት የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመሳሳይ፣ ተጻራሪ፣ ጥምር እና አወዳዳሪ ትይዩነት ብለህ ሰይም። የዚህን መልመጃ መልስ በመዕራፉ መጨረሻ ላይ ይገኛል።

18፥21 17፥27 29፥17 19፥21 24፥16 27፥17

62 Bullock, "The Book of Proverbs," 32.

25፥15 17፥28 29፥25 26፥21 29፥11 25፥28

25፥21 28፥13 17፥17 29፥25 25፥23 16፥28

29፥23 21፥25 26፥14

ትይዩነት ቁልፍ መገለጫዎች ቢሆንም መጽሐፉ በሚጠናበት ጊዜ መታወስ ያለባቸው ቢያንስ አምስት ጠቃሚ መርሆዎች አሉ።

**2) አንድን ትምህርት የሚያስተምሩ የምሳሌዎችን ቡድኖች ተመልከት**

ብዙ ምሳሌዎች ከቅዱሳት መጻሕፍት ገጾች ለመወሰድ እንደሚጠብቁ የመለኮታዊ ጥበብ ወርቃማ ጭብጦች ብቻቸውን ይቆማሉ። ግን ዐይኖችህን ሁልጊዜ አንድን ርእሰ ጉዳይ ተደራሽ የሚያደርጉ ምሳሌዎች ላይ አድርግ። ለምሳሌ ያህል ምሳሌ 23፥1–28 ርእሶቹ ጠቢብ ሰው አይመኝም፣ ገንዘብን ቢሆን (ቁ.4–5)፣ የስስታምን ድግስ (ቁ. 6–8)፣ የጎረቤትን መሬት (ቁ. 10–12)። አስረኛውን ትዕዛዝ እንዴት ተግባራዊ እንደምታደርግ የሚያስተምሩ ምሳሌዎች ስብስብ ነው። በተመሳሳይ መልኩ ምሳሌ 26፥17–28 ግንኙነቶችን ስለሚያበላሹ አስተሳሰቦች እና ድርጊቶች፦ በቀልድ መልክ የሚደረግ ተንኮል፣ ጠብ አጫሪነት፣ የጥላቻ ልብ፣ እና ውሸታም ከንፈሮችን የሚያሳይ ክፍል ነው።

በአንዳንድ ቦታዎች የምሳሌ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን ጥበብ ለማስተማር ግጥም፣ መዝሙር፣ ወይም ሌላ ስነጽሑፋዊ መንገድ ይጠቀማል። በእነዚህ ጊዜዎች ከዚያ የምንባብ ክፍል አንድ ጥቅስ ብቻ መስበክ የለብህም፤ ሙሉውን ክፍል ቁጥር በቁጥር መስበክ አለብህ። የሚከተሉትን ምሳሌዎች ተመልከት።

1፥1–7 የምሳሌ መጽሐፍ መግቢያ እና መፈክር

1፥10–19 ሰውን ከማስደሰት ስለመጠንቀቅ

ምዕራፍ 1–9 ጥበብን እንዲፈልጉ እንጂ ሞኝነትን እና የድግሷን የሻገተ እንጀራ እና የተሰረቀውን ውሃ እንዳይመኙ ሰሎሞን ልጆቹን ለማሳመን ያደረገው ጥረት።

7፥1–27 ሞኝ ወጣት ወደ ዝሙት ኃጢአት የሚሄድበት መንገድ

23፥29–35 ሰካራምነንትን የሚቃወም ግጥም

27፥23–27 የመተባበርን ጥቅሞች የሚያወድስ ግጥም

24፥30–34 ትምህርት ከሰነፍ እርሻ

31፥10–3 አድናቆት ለብርቱ ሴት

**3) የመንፈሳዊ ለውጥን አካሄድ ተመልከት**

በድነት ጊዜ ኃጢአተኞች በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት በኩል ጻድቃን እንደሆኑ በእግዚአብሔር ይታወጅላቸዋል። ነገር ግን የታወጀላቸው ቅዱሳን እንዴት ነው በየዕለቱ ቅዱሳን የሚሆኑት? የታወጀላቸው ጻድቃን እንዴት ነው በጽድቅ መኖር የሚጀምሩት? ሐዋርያው ጳውሎስ ኤፌሶን 4፥22–24 ላይ ይነግርሃል። የታወጀላቸው ቅዱሳን የየዕለት ቅዱሳን የሚሆኑት በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል ባለ ሦስት ደረጃ የለውጥ ሂደት ተግባራዊ በማድረግ የራሳቸውን መዳን ሲፈጽሙ ነው። አሮጌውን የኃጢአት አስተሳሰብ እና ተግባር ያወልቃሉ ወይም ይተዋሉ፤ መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት አዕምሯቸውን ያድሳሉ፤ አዲሱን እንደ ክርስቶስ አይነት አስተሳሰብን እና ተግባር ይለብሳሉ።[63]

ታዲያ ይህ ከምሳሌ መጽሐፍ ጋር ምን ያገናኘዋል? በብዙ ይገናኛል። ኤፌሶን 4–5 ካየህ ጳውሎስ በቅርጽም በይዘትም ምሳሌን የሚመስል ክፍል 4፥22–24 ይከተላል። አጭር፣ ቀጥተኛ፣ ምሳሌያዊ በሆኑ ተከታታይ ትዕዛዞች፣ ጳውሎስ ውሸት እውነትን በመናገር እንዲተካ (4፥25)፣ ስርቆት ተግቶ በመሥራት እና በማካፈል እንዲተካ ይናገራል። ክፉ ቃላት በጸጋ ቃላት ይወገዳሉ (4፥29፤ 5፥3–4)፤ ቁጣ በርህራሄ እና ይቅር በማለት ይሸነፋል (4፥31–32)። በስተመጨረሻም ሞኝነት በጥበብ (5፥15–17) መተካት አለበት። ይህ ጳውሎስ ነው ወይስ ሰሎሞን?

4፥22–24ን መሠረት በማድረግ የኃጢአትን ስር ለመንቀል የምሳሌ መጽሐፍ ምርጥ ከሆኑ መሳሪያዎች መካከል እንደሆነ ጳውሎስ በግልጽ ያምናል። ይህ ስሜት ይሰጣል፤ መጽሐፈ ምሳሌ የጳውሎስን የማውለቅ እና የመልበስ መርህ ይኖረዋል፣ ይመገባል፣ ደግሞም ይተነፍሰዋል። የሚከተሉትን ምሳሌዎች የማውለቅ እና የመልበስ ክፍሎችን መለየት ትችል እንደሆን ተመልከት።

ሰው በጥበቡ ይመሰገናል፤ ልቡ ጠማማ የሆነ ሰው ግን ይናቃል። (12፥8)

ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል። (28፥13)

[63] Jay Adams, Competent to Counsel (Grand Rapids, Mich.: Zondervan Publishing House, 1970), 218

ሰውን ትዕቢቱ ያዋርደዋል፤ መንፈሱን የሚያዋርድ ግን ክብርን ይቀበላል። (29፥23)

የምሳሌ መጽሐፍ በጣም በተደጋጋሚ የኃጢአትን አስተሳሰብ እና ድርጊት የሚተኩ መልካም አመለካከቶችን እና ተግባሮችን ያስተምራል፤ መልካም አንደበት እንደምላጭ የተሳሉ ቃላትን ይተካል፤ ኑዛዜ እና ንስሐ ኃጢአትን አለመቀበልን ይተካሉ፤ ትህትና ትዕቢትን ይተካል። መጽሐፈ ምሳሌን በውጤታማነት ለማጥናት እና ለመስበክ የማውለቅን እና የመልበስን መርህ ለማየት ዐይንህን ለመተግበር ልብህን ማሰልጠን አለብህ። ጳውሎስ በኤፌሶን የሰበከውን ሰሎሞን ከብዙ ጊዜ በፊት ፈጽሞታል።

## 4) የድርጊትን እና ውጤቱን የመቀበልን ሕግ ተመልከት

የውጤት ሕግ በእነዚህ የሐዋርያው ቃላት ጥቅለል ተደርገው ይቀርባሉ፤ "አትሳቱ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና፤" (ገላ 6፥7) መሬትህ ላይ ስንዴ፣ ገብስ፣ ወይም ማሽላ ከዘራህ በመኸር ወቅት የምታጭደው ያንኑ ነው። አረም እና እንክርዳድ ከዘራህ አረም እና እንክርዳድ ታጭዳለህ። ይህ በግብርና ላይ ተግባራዊ የተደረገ የውጤት ሕግ ነው፤ መሬት ውስጥ ያኖርከው ነገር ነው ከመሬት ውስጥ የሚወጣው። ተመሳሳይ የምክንያት እና የውጤት መርህ በመንፈሳዊ ነገሮች ላይም ይሠራል። ለምሳሌ ሰሎሞን እንዲህ ይላል፤ በትዕቢት ጎዳና ብትጋልብ መጨረሻው ወደሚታወቅ ውድቀት ወደተባለ ከተማ ትደርሳለህ። "ትዕቢት ጥፋትን፥ ኵሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል" (ምሳሌ 16፥18)። እሳት እንደሚያቃጥል እርግጥ እንደሆነው ሁሉ ትዕቢት ወደ ጥፋት ይመራል።

መጽሐፈ ምሳሌ ተገማች ወደሆኑ (ግን ሁልጊዜም ችላ የሚባሉ) የውሳኔዎች መዘዞች በመጠቆም ሕይወትን ይመሠርታል። ገንዘብ፤ "ባለጠጋ ድሆችን ይገዛል፥ ተበዳሪም የአበዳሪ ባሪያ ነው" (22፥7)። ወዳጆች፤ "ከጠቢባን ጋር የሚሄድ ጠቢብ ይሆናል፤ የሰነፎች ባልንጀራ ግን ክፉ መከራን ይቀበላል" (13፥20)። ውሸት፤ "ሐሰተኛ ምስክር ሳይቀጣ አይቀርም፥ በሐሰትም የሚናገር አያመልጥም።" (19፥5)

## ጸባይ፣ ምግባር፣ ውጤቶች

በመጽሐፈ ምሳሌ ጸባይ ምግባርን ያመጣል፤ ምግባር ደግሞ ውጤቶችን ያስከትላል።[64] ሰነፍ ሰው የነበረ ምሳሌ ነው። ሰነፍ ሰው ዝርክርክ ነው ቀላል ነገር ይወዳል፤ የራሱ አገልጋይ መሆኑ፣ ደስታን የማፍቀሩ ጸባይ የስንፍናን

---

64 Waltke, Proverbs, 1:73.)

* Christians in Western congregations also struggle with not taking responsibility for the bad consequences of their sinful character and conduct. However, in their case the culprit is usually the influence of psychology, not witchcraft

ምግባር ማስከተሉ የማይቀር ነው። ሣንቃ ከመቃኑ ጋር በማጠፊያ እንደሚያያዝ፣ እርሱም ከአልጋው ጋር የተያያዘ ነው (26፥14)። ምንም እንኳ የሚያቀርበው ሰበብ የታመመ ቢሆንም ላለመሥራት ሁልጊዜ ምክንያት ማቅረብ ይችላል ("በመንገድ ላይ አንበሳ አለ!")። ውሃ ቁልቁል እንደሚወርድ የምግባሩ ውጤቶችም የታወቁ ናቸው። መሬቱ በፈራረሰ ግንብ የታጠረ እና በአረም ወረራ የታነቀ ነው (24፥30–34)። እንዳያርስ ከአልጋው ጋር የታሰረ ስለሆነ በመኸር ወቅት ምንም አያጭድም፤ ወደ ድህነትም ይወድቃል (20፥4)። መጽሐፈ ምሳሌ ለወጣቱም ለሽማግሌውም ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፤ ጸባይህን ከመንከባከብህ እና ምግባርህን ከመምረጥህ በፊት የሚያስከትላቸውን መዘዞች አስተውል። በመጽሐፈ ምሳሌ ስለ ወሲብ ንጽሕና ከተሰጠው መመሪያ በላይ የምግባር እና የመዘዞቹ ግንኙነት የትም ቦታ ላይ በግልጽ አልታየም፤

በጉያው እሳትን የሚታቀፍ፥ ልብሶቹስ የማይቃጠሉ ማን ነው? በፍም ላይ የሚሄድ፥ እግሮቹስ የማይቃጠሉ ማን ነው? ወደ ሰው ሚስት የሚገባም እንዲሁ ነው፤ የሚነካትም ሁሉ ሳይቀጣ አይቀርም። (6፥27–29)

አመንዝራነትን ዝራ፤ መታመምን ታጭዳለህ። የሚያቃጥል ፍም የደረትህ ቆዳ ላይ ሲጫን እንደሚያሳምም ሁሉ አመንዝራም ለጥቂት ደቂቃዎች ደስታ ሲል የዕድሜ ልክ ዋጋ ይከፍላል። መጽሐፈ ምሳሌ ስለ መዘዞች ማውራት ዋና ርእሱ ነው፤ "አትሳቱ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና።"

**አፍሪካዊ ትግበራ**

መጽሐፈ ምሳሌ በውጤቶች ላይ ያለውን መመሪያ አጥብቆ መያዝ አፍሪካ ውስጥ ለሚያገለግሉ ሰባኪዎች ይበልጥ ጠቃሚ ነው። አብዛኞቹ የጉባኤያችን አባላት የመጡት መጥፎ ነገሮች ከተቆጡ ቅድመ አያቶቻቸው ወይም እንዲረግማቸው ለጠንቋይ በከፈሉ ቅናተኛ ጠላቶቻቸው እንደሚመጣ ከሚታሰብበት የኋላ ታሪክ ነው። መጽሐፈ ምሳሌ ግን ከእንዲህ አይነቱ ገለጻ ዘወር በማለት ጸባይ እና ምግባር እንዴት ወደ ውጤት እንደሚያደርሱ ነው።* ለምሳሌ የሰለጠነበትን ተቋም ሊጎበኝ ሲሄድ አፍሪካዊው ጓደኛዬ የተወሰነ ማንበብ እና ሽምደዳ የሚፈልገውን የመጽሐፍ ቅዱስ ዳሰሳ የተባለውን ትምህርት መሥራት ያልቻለው ተማሪ ሲያማርር እየሰማ ነበር። ተማሪው እምባ ቀረሽ ተረቱን እንዲህ በማለት ጨረሰ፤ "የሆነ ሰው ረግሞኛል፤ ይህንን ትምህርት ማለፍ ያልቻልኩት ለዚያ ነው።" መጽሐፈ ምሳሌን የሚያውቀው ጓደኛዬ የዚህን ሁኔታ ትርጓሜ አልተቀበለም። ጥቂት ጥያቄዎችን ከጠየቀ በኋላ ተማሪው ከነጻ ጊዜው አብዛኛውን የሚያሳልፈው ከማንበብ ይልቅ

በአቅራቢያው በሚገኝ መዝናኛ ነው። ተማሪው ተታሏል፤ በጠንቋይ ሳይሆን ቀለል ለማለት እና ለመዝናናት ባለው ፍቅር። ምሳሌ 10፥4 ወደ ችግሩ ትክክለኛ መንስኤ ይጠቁመዋል፤ "የታካች እጅ ችግረኛ ታደርጋለች፤ የትጉ እጅ ግን ባለጠጋ ታደርጋለች።" ቀለል የማለት ፍቅር ወደ አለማንበብ ምግባር ይመራል፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ዳሰሳን አለማለፍ ያስከትላል። መጽሐፈ ምሳሌን በምታጠናበት ጊዜ ሁሉ አንድ ዐይንህን በውጤት ሕግ ላይ አድርግ፤ በመላው ምሳሌዎች ውስጥ ይገኛል።

**ፍጹም እውነቶችን ከሚታመንባቸው እውነቶች ለይ**

ከታች ሁለት ምሳሌዎች አሉ፤ አንደኛው ሁል ጊዜ እውነት ነው፤ ሌላኛው ደግሞ ብዙ ጊዘ እውነት ነው። የቱ የትኛው እንደሆነ ለይ።

"የታካች እጅ ችግረኛ ታደርጋለች፤ የትጉ እጅ ግን ባለጠጋ ታደርጋለች።" (10፥4)

"የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው።" (9፥10)

ጥበብ እግዚአብሔርን ከመፍራት መጀመሩ (9፥10) ፍጹም እና ሁልጊዜም እውነት ነው። በንጽጽር ደግሞ 10፥4 ላይ ያለው የሰሎሞን ምልከታ ፍጹም አይደለም። 10፥4 ላይ ሰሎሞን የተናገረው ነገር አብዛኛውን ጊዜ እውነት ስለሆነ ነገር ነው። በእግዚአብሔር ዓለም በግልጽ የሚታየውን መንገድ እየለየ ነው፤ በጥረት እና በስኬት መካከል ጥብቅ ግንኙነት አለ። አንዳንድ ጊዜ ሀብታም የሆነ ሰነፍ ሰው ወይም ትጉ ግን ከጓደኞቹ ይበልጥ ድሃ የሆነ ሰው ልታገኝ ትችላለህ፤ ነገር ግን እነዚህ ክስተቶች ያልተለመዱ ናቸው። በሌላ አገላለጽ መጽሐፈ ምሳሌ ሁለት የተለያዩ አይነት ምልከታዎችን ይይዛል፤ እነርሱም ሁልጊዜ እውነት የሆኑ እና አብዛኛውን ጊዜ እውነት የሆኑ ናቸው። ምሳሌዎችን በስህተት መተርጎም እና ተግባራዊ ማድረግን ለማስወገድ ሁለቱን መለየት ያስፈልጋል።[65]

ሁል ጊዜ እውነት የሆኑ የመጽሐፈ ምሳሌ ዐ.ነገሮች ፍጹም እውነት ተብለው መጠራት ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል 16፥5 እንዲህ ይላል፤ "በልቡ የታበየ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ርኩስ ነው"። ይህ ፍጹም እውነእት ነው። እግዚአብሔር በዘላለማዊነቱ ትዕቢትን በኀዘኔታ ወይም በርህራሄ አንዴ እንኳ ተመልክቶ አያውቅም፤ ትዕቢት ሁል ጊዜም እችሱን ይገፋዋል። ምሳሌ በተጨማሪ እንዲህ ይላል፤ "እግዚአብሔርን መፍራት ክፋትን ይጠላል"

65 Ted A. Hildebrandt, "Proverbs," in Cracking Old Testament Codes: A Guide to Interpreting the Literary Genres of the Old Testament, ed. by D. Brent Sandy and Ronald L. Giese, Jr. (Nashville, Tenn.: Broadman & Holman Publishers, 1995), 246-48.)

(8፥13)። ይህ ሁሌም፣ ሁሌም እውነት ነው፤ እግዚአብሔርን መፍራት መቼም፣ መቼም ክፉትን አይወድም። እነዚህ ሁለት ምሳሌዎች ፍጹም የሆኑ እውነቶችን፣ ሁል ጊዜ እውነት የሆኑ ነገሮችን ያስተምራሉ።

**የታመነባቸው ምሳሌው**

ሌሎች ምሳሌዎች ግን ጥበብን በተለየ መንገድ ነው የሚያስተምሩት። ፍጹም እውነቶችን ሳይሆን አካሄዶችን ያሳያሉ፤ በእግዚአብሔር ዓለም ነገሮች በተለምዶ እንዴት እንደሚሠሩ ያመለክታሉ።[66] በሌላ አገላለጽ የሚታመኑ እውነቶችን ያስተምራሉ። የሚታመን ማለት የማይካድ፣ እውነት መሆኑ በስፋት የሚታይ፣ እውነት መሆኑን ለማሳመን ሙግት የማይፈልግ ነገር ነው። መጽሐፈ ምሳሌ በእነዚህ በእግዚአብሔር ዓለም ባሉ ምልከታዎች የተሞላ ነው።

ለምሳሌ ትኩረት ያደረግንበትን ጥቅስ፣ ምሳሌ 10፥4ን አስተውል። በዚያ ቁጥር የሰሎሞንን ምልከታ ትክክለኛነት የማሳመን ግዴታ አለብኝ? አብዛኛውን ጊዜ ትጉ ሠራተኞች ከቸልተኛ ሰነፍ ይልቅ ስኬታማ እንደሚሆኑ ማስረዳት ይጠበቅብኛል? በእግዚአብሔር ዓለም በአብዛኛው ሰነፍ ተማሪዎች ዝቅተኛ ውጤት እንደሚያገኙ፣ ሰነፍ ሠራተኞች አነስተኛ ክፍያ እንደሚቀበሉ፣ ሰነፍ ባሎች የተናጋ ጋብቻ እንደሚኖራቸው፣ ሰነፍ ሰባኪዎች የደከመ ስብከት እንደሰብኩ የማይካድ ነው። ሁላችንም አካሄዱን ተመልክተናል፤ አብዛኛውን ጊዜ ስኬት ጥረትን ይከተላል። 10፥4 ላይ ያለው የሰሎሞን ምልከታ በአብዛኛው እውነት ቢሆንም ግን ፍጹም የሆነ እውነውት አይደለም።

**ይህ አስፈላጊ ነው?**

ፍጹም የሆነን ምሳሌ እና የሚያመንበትን ምሳሌ ለይቶ ማወቅ በሁለት ምክንያቶች ጠቃሚ ነው። የመጀመሪያው ጥረት ውጤት የሚያስመዘግብ ሰነፍ ተማሪ ወይም ጥሩ ክፍያ የሚያገኝ ሰነፍ ሠራተኛ ሲያጋጥምህ ተታለህ ከመንገድ ከመውጣት ይጠብቅሃል። ለምሳሌ የኢዮብ ወዳጆች ከመስመር ወጥተው ነበር። እግዚአብሔር ጻድቁን በብልጽግና ከሚባርክበት እና ክፉውን ደግሞ ከጫማው በታች ከሚረግጥበት መንገዱን የተለየ አሠራር እንደሌለ ተቀብለው ነበር።[67] ኤልፋዝ፣ ብልዳዶስ፣ እና ዞፋር ምሳሌዎችን እንደ ምሳሌ 13፥21 ይወዱታል፤ "ክፉ ነገር ኃጢአተኞችን ያሳድዳቸዋል፤ ጻድቃን ግን መልካሙን ዋጋ ይቀበላሉ።"

[66] Duane A. Garrett, Proverbs, Ecclesiastes, Song of Songs, in The New American Commentary (Nashville, Tenn.: Broadman Press, 1993), 57

[67] Derek Kidner, The Wisdom of Proverbs, Job, & Ecclesiastes (Downers Grove, Ill.: Intervarsity Press, 1985), 62.

በጠቅላላው እውነት ቢሆንም ያ ምሳሌ ግን በኢዮብ ሕይወት ጉዳይ ትክክል አልነበረም። ነቀፋ የሌለበት እና ጻድቅ ነበር፤ ቢሆንም ግን የጅብ መንጋ ሚዳቆን እንደሚከታተል ክፉ ነገር ተከታትሎታል። ብዙ የምሳሌ መጽሐፍ ምሳሌዎች የታመነባቸው እንደሆኑ መረዳትህ በልዩ ሁኔታዎች እንዳትደናቀፍ እንዲሁም በኢዮብ እና በጓደኞቹ እንደሆነው ሁሉ ሌሎችንም በመጥፎ ምክርህ ከማደናቀፍ ያድንሃል።

በልዩ ሁኔታዎች እንዳትደናቀፍ ከመጠበቁ በተጨማሪ ፍጹም የሆኑ እና የታመነባቸውን ምሳሌዎች ለይቶ ማወቅ የሚጠብቅህ ምሳሌያዊ ምልከታዎችን ወደ መለኮታዊ ተስፋ ከመቀየር ነው። ቴድ ሂልድብራንት እንደጻፈው፣ “ምሳሌዎች ሲተረጎሙ ምሳሌን ከተስፋ ጋዜጠኛ አቻ ማድረግ የተለመደ እና መሠረታዊ ችግር ነው።”[68] ለምሳሌ ያህል ከምወዳቸው ምሳሌዎች አንዱ መልካም ምላስ ቁጣን ታበርዳለች ይላል 15፥1)። ይህ በብዙ ሁኔታዎች እውነት ነው። አልፎ አልፎ ግን በተረጋጋ፣ በለዘበ፣ መልካም ቃል እንኳ የቁጣው እሳት የማይበርድለት ሰው ያጋጥምሃል። ምሳሌ 15፥ 1 አይደለም የተሳሳተው። ሰሎሞን ተስፋ እየሰጠ አልነበረም፤ በእግዚአብሔር ዓለም ግንኙነቶች በአብዛኛው እንዴት እንደሆኑ መለኮታዊ እስትንፋስ ያለበት የጠቢብ ምልከታ እያደረገ እንጂ። ፍጹም የሆነ እውነት ባይሆንም እንደ  ክርስቶስ አይነት ቆፍጣናነት የቁጣን ፈንጅ ያመክናል።

በተመሳሳይ መንገድ ምሳሌ 22፥6 መሄድ ያለበትን መንገድ የሰለጠነ ልጅ ሲያረጅም በዚያው መንገድ እንደሚቀጥል ይናገራል። በሥርዓት እየተማረ ያደገ እያንዳንዱ ልጅ በጽድቅ ጎዳና እንደሚራመድ ይህ ጥቅስ ፍጹም ማረጋገጫ ሰጥተዋል? ሰሎሞን እንደዚህ አይነት ማረጋገጫ እየሰጠ አይደለም። የልጆችን ወላጆች ለማነሣሣት የሚታወቅ መንገድ እየጠቆመ ነው፤ ልጆችህን የጥበብ መንገድ ስታስጀምራቸው እዋቂ ከሆኑ በኋላ እንኳ ያንን መንገድ መከተል ይቀጥላሉ።

ፍጹምም ቢሆኑ ወይም የታመነባቸው፣ የእግዚአብሔር ምሳሌዎች በሥልጣን እና በኃይል መነገር አለባቸው። ጥርስ እና ጥፍሩን በጉባኤህ ሞኝነት እና ኃጢአት ላይ እንዲያሳርፍ ጥበብን ከታሰረበት ልቀቀው፤ ፍጹም እውነት የሆኑ ምሳሌዎችን ፍጹም እንደመሆናቸው ስበክ፤ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ትዕቢትን ይጠላል፤ እግዚአብሔርን መፍራት ሁልጊዜም የጥበብ መጀመሪያ ነው። የታመነባቸውን ምሳሌዎች በደንብ ደግሞም በሙሉ ልብ መስበክ አለብህ፤ የሚጠቁሟቸው መንገዶች ጠቃሚ በመሆናቸው እነርሱን ችላ ማለት ሞኝነት እና ጥፋት ነው። መጥቷል ቃላት ቁጣን ያነሣሣሉ፤ የተረጋጉ መልሶች ግን ያቀዘቅዙታል፤ ጥንቃቄ የጎደላቸው፣

---

68 Hildebrandt, "Proverbs," 247.

የማይታመኑ ሠራተኞች በእርግጥም የስንፍናቸውን ውጤት ይሸከማሉ። ፍጹም ምሳሌዎችን እና የታመኑ ምሳሌዎችን ሕይወት የሚሰጥ ጥበብ እንደመሆናቸው ስበካቸው።

ከምሳሌ መጽሐፍ የተወሰዱ ጥቅሶች ከታች አሉ። እያንዳንዱን ምንባብ ተመልከትና ሁልጊዜም እውነት ወደሆነ ነገር ወይስ አብዛኛውን ጊዜ እውነት ወደሆነ ነገር እንደሚጠቁም ለይ።ፍጹም የሆነን እውነት ነው ወይስ የሚታመንበትን እውነት ነው የሚያሳየው? መልሱን የያዘው ቁልፍ በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ አለ።

6፥16-19 3፥3-4 3፥9-10 23፥4-5

21፥31 28፥23

**6) በአንድ ርእስ ላይ የመጽሐፈ ምሳሌን ጥበብ ፈልግ**

በሁለተባው ነጥብ ስር እንደተቀመጠው አንዳንዴ የምሳሌ ምንባቦች ቁልፍ በቁጥር መነገር አለባቸው፤ እርስ በርስ የተያያዙ አንድ አካል ናቸው። ነገር ግን ከመጽሐፈ ምሳሌ የምታዘጋጃቸው አብዛኞቹ ስብከቶች በባሕሪያቸው ርእሳዊ ነው የሚሆኑት። ምክንያቱ ግልጽ ነው፤ በአንድ ርእስ ላይ የምሳሌ ጥበብ በመጽሐፉ ውስጥ ተበታትኖ ስለሚገኝ ነው። ለምሳሌ በቸኮሌት ገበታ ላይ እንዳለ ቸኮሌት ልጆችን ስለማሳደግ የተሰጡ የሰሎሞን መመሪያዎች በመጽሐፉ ውስጥ ተበትነው ይገኛሉ። አንድ ጉርሻ ሁሉንም አያስገኝም። ስለ ልጆች አስተዳደግ ሁሉንም የሰሎሞን ጥበብ ጣዕም ለመቅመስ አንድ ጥቅስ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ መጽሐፉን መብላት አለብህ።

በአንድ ርእስ ላይ የምሳሌን ሙሉ መጽሐፍ አለመመልከት በጣም አደገኛ ነው። ለምሳሌ ምሳሌ 17፥8 ላይ ሰሎሞን እንዲህ ይላል፤ “ገንዘብ ባደረገው ፊት መማለጃ እንደ ተዋበ ዕንቍ ነው፥ ወደ ዞረበትም ስፍራ ሁሉ ሥራውን ያቀናል።” ይህ ጥቅስ ብቻውን ከተወሰደ ስኬታማ ለመሆን ጉቦ መስጠት ሕጋዊ መንገድ መሆኑን የሚያበረታታ ይመስላል። ነገር ግን ሌሎች ምሳሌዎች እንደ ጉቦ ባሉ ሕገወጥ መንገዶች ትርፍ ማግኘት ያልተጠበቁ እና የሚያሳምሙ መዘዞች እንዳሉት ይናገራሉ፤ “ትርፍ ለማግኘት የሚሳሳ ሰው የራሱን ቤት ያውካል፤ መማለጃን የሚጠላ ግን በሕይወት ይኖራል።” በቤትህ ውስጥ ሁከት ትፈልጋለህ? ከሚስትህ እና ከሱሰኛ ልጆችህ ጋር መጣላት? እንግዲያውስ ወደፊት ጉቦ ተጠቀም። ብልህ ሰው 17፥8ን ከ15፥27 ጋር በማስተያየት የሚያስከትለውን የሚያሳምም መዘዝ እና ስለታም ጫፍ የጉቦ ጣፋጭነት እንደሚደብቅ ያስተውላል።

በተመሳሳይ መንገድ ምሳሌ 10፥15 “የባለጠጋ ሀብት ለእርሱ የጸናች ከተማ ናት” የሚለውን ከምሳሌ 18፥11 “ለባለጠጋ ሰው ሀብቱ እንደ ጸናች ከተማ ናት፥ በአሳቡም እንደ ረጅም ቅጥር።” ከሚለው ጋር ሳታስተያይ የመጀመሪያው ላይ ትኩረትህን መቸንከር የለብህም። ኢዮብ በምስራቅ ሀባታሙ ሰው ነበር፤ ሀብቱም ከመጣበት አድጋ ሊያስጠልለው አልቻለም። የኢዮብ የባንክ ሒሳብ ሐሰተኛ ግንብ ከነበረ ያንተም እንደዚያው ይሆናል።

በአንድ ችእሰ ጉዳይ ላይ አንድ ምሳሌ ብቻውን ጠቅላላውን የእግዚአብሔርን ጥበብ ላያቀርብ እንደሚችል ዴሬክ ኪድነር ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የሆኑ ሁለት ምሳሌዎችን በመጠቀም ያስረዳል፤ “ብዙ እጆች ሥራን ያቀላሉ የርእሱ የመጨረሻው ቃል አይደለም፤ ምክንያቱም ሠራተኞች ሲበዙ ድስቱ ሊያርር ይችላል”።[69] ብዙ ሠራተኞች የቤተክርስቲያን ምግብ ቶሎ እንዲደርስ ያደርጋል። ነገር ግን ኩሽና የሚገኙ ሁሉ ወጡ ውስጥ ጨው የሚጨምሩ ከሆነ ምግቡ የማይበላ ይሆናል።

### ጠቃሚ ሥራ

የመጽሐፈ ምሳሌ ጠቢብ ተማሪ መሆን ከፈለክ በምታጠናበት ርእስ ላይ የሚናገረውን ሁሉ መፈለግ አለብህ። ነገር ግን በአንድ ርእስ ላይ የሚናገሩ ምሳሌዎችን የያዙ ጥቅሶችን ሁሉ አንተም ሆንክ እኔ ማስታወስ አንችልም። መዝገበ ቃላት እና ርእሳዊ መጽሐፍ ቅዱሶች ሊያግዙህ ይችላሉ፤ ነገር ግን ብዙ ጊዜ ቁልፍ ጥቅሶችን ይዘነጋሉ። ለምሳሌ 15፥27ን የ17፥8 ማመዛዘኛ ምሳሌ አድርገው አያቀርቡም፤ ምክንያቱም 15፥27 ጉቦ የሚለውን ቃል አይጠቀምም። የሚያስፈልግህ ምሳሌ መጽሐፍ ላይ በርእስ የተሰናዳ፣ ወሳኝ ጥቅሶች የተዘረዘሩበት፣ ስሜት የሚሰጥህ የተሟላ ማጣቀሻ ነው። እንደዚህ አይነት መሳሪያ ለማግኘት ብቸኛው መንገድ በራስህ ማዘጋጀት ነው።

እግዚአብሔርን ከምሳሌ መጽሐፍ መስበክ እንድትችል እግዚአብሔርን ከምሳሌ ለማጥናት የሚከተለውን ማድረግ አለብህ፤ ለአንድ ወር በየቀኑ ከመጽሐፈ ምሳሌ አንድ ምዕራፍ አንብብ። ስታነብ ማስታወሻ ደብተር አጠገብህ አኑረህ ጠቃሚ እንደሆነ የምታስበውን ማንኛውንም ርእስ — ትዕቢት፣ ትህትና፣ ሞኝነት፣ ስንፍና፣ ተግሳጽን መቀበል፣ የወሲብ ንጽሕና፣ የንግድ እንቅስቃሴ፣ ቤተሰብ፣ ሀብት፣ ምላስ — ሁሉንም ጻፍ። በእነዚህ ርእሶች ስር ስለርእሶቹ የሚናገሩ ጥቅሶችን መዝግብ (አንዳንድ ጥቅሶች ከአንድ የበለጠ ቦታ ይመደባሉ)። በወሩ መጨረሻ መጽሐፈ ምሳሌን ለማጥናት በዋጋ የማይተማመን መሳሪያ ይኖርሃል። በዚያ የርእስ ማውጫ

ስብከትህ በርእሰ ጉዳዩን ላይ ሁሉንም የሰሎሞን ጣፋጭ ቸኮሌቶች እንዳካተተ እርግጠኛ በመሆን ከምሳሌ መጽሐፍ መስበክ ትችላለህ።

**ማጠቃለያ**

መጽሐፈ ምሳሌ ራስን-መርጃ ሳይሆን የቅድስና መጽሐፍ እንደሆነ በማስታወስ ልዝጋ። ልዩነት ምንድነው? ራስን-መርዳት ስነ ምግባራዊ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚደረግ የሰው ጥረት ነው። ያለ ክርስቶስ የሚደረግ ለውጥ ነው። መንፈስ ቅዱስ የተተወበት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው። እንደዚህ አይነቱ ለውጥ ያንተ ግብ አይደለም። ምሳሌን ስትሰብክ አላማህ መጥፎ ሰዎችን ጥሩ ማድረግ አይደለም፤ የሞቱ ሰዎችን ሕግ ለማድረግ ነው። ያን ማድረግ የሚችለው ክርስቶስ ብቻ ነው። ያንተ ግብ ያለ ክርስቶስ ጣልቃ ገብነት በራሱ የተሟላ ጥሩ ስነ ምግባራዊ ሕይወት መኖር እንዲችሉ አማኞች የምሳሌን መጽሐፍ እንዲተገብሩ ማበረታታት አይደለም። ምሳሌን በዚያ መልኩ መጠቀም መሳሌን በስህተት መጠቀም ነው።

ምሳሌን ስትሰብክ ክርስቶስን ከኋላ አታስቀር። ይልቅ ከኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራ ከራቀ የመጽሐፈ ምሳሌን ጥበብ መኖር የማይችል (እና የማይጠቅም) እንደሆነ ሕዝብህን በቋሚነት አስታውስ። የሕዝብህን ትኩረት በውስጣችን በሚኖር በመንፈስ ቅዱስ በኩል ሕይወታችንን ወደሚቀይረው ወደ ክርስቶስ አድርግ። የመጽሐፈ ምሳሌን አንበሳ ፍታው፤ ይህን ስታደርግ ግን ከይሁዳ ነገድ የሆነውን አንበሳ አትርሳ። ከምሳሌ መጽሐፍ የምታቀርበው ስብከት ራስን ስለማሻሻል የተሰጠ ስነ ምግባራዊ ትምህርት ሳይሆን ክርስቲያናዊ ስብከት መሆኑን እርግጠኛ ለመሆን መጽሐፈ ምሳሌን በዚህ አዕምሮ አጥና ደግሞም ስበክ፤ “እንግዲህ ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ተቀበላችሁት በእርሱ ተመላለሱ” (ቆላ 2፥6)።

**<u>የመልመጃዎቹ መልሶች ቁልፍ</u>ትይዩነትን መለየት**

18፥21 ተመሳሳይ 17፥27 ተመሳሳይ 29፥17 ተመሳሳይ 19፥21 ተጻራሪ 24፥16 ተጻራሪ 27፥17 አወዳዳሪ 25፥15 ተመሳሳይ 17፥28 ተመሳሳይ 29፥25 ተጻራሪ 26፥21 አወዳዳሪ 29፥11 ተጻራሪ 25፥28 አወዳዳሪ 25፥21 ተመሳሳይ 28፥13 ተጻራሪ 17፥17 ተመሳሳይ 29፥25 ተጻራሪ 25፥23 አወዳዳሪ 16፥28 ተመሳሳይ 29፥23 ተጻራሪ 21፥25 ተመሳሳይ 26፥14 አወዳዳሪ **ፍጹም የሆኑ ምሳሌዎችን ከታመነባቸው ምሳሌዎች መለየት**

6፥16-19 ፍጹም 3፥3-4 የታመነበት 3፥9-10 የታመነበት 23፥4-5 የታመነበት 21፥31 ፍጹም 28፥23 የታመነበት

## ምዕራፍ አሥራ ሁለት

## መዝሙሮችን ማጥናት

ጆን ካልቪን እንዲህ ብሏል፤ የሰው ልጅ ሁለቱ ትልልቅ አስፈልጎቶች ራስን በትክክልም ማወቅ እና እግዚአብሔርን በትክክል ማወቅ ናቸው። ራሳችንን በትክክል ማወቅ ማለት ኃጢአተኞች፣ ረዳት አልባ፣ ከርታታ መሆናችንን ማወቅ ነው፤ ምክንያቱም እንዲህ አይነቱ ዕውቀት እግዚአብሔርን ወደማወቅ ይጠቁመናል። “በራሳችን ተስፋ መቁረጥ ሳንጀምር እርሱን መፈለግ መጀመር አንችልም”።[69]በተጨማሪም እግዚአብሔር በትክክል ማወቅ የሚያስፈልገን ከከርታታነታችን የምንድነው እግዚአብሔርን በማወቅ (እና በእርሱ በመታወቅ) ብቻ ነው (ገላ 4፥9)።

ካልቪን ትክክል ከሆነ — እንደሆነ አምናለሁ — እያንዳንዱ ሰባኪ ከመዝሙር መጽሐፍ በዓመት ቢያንስ ብዙ ጊዜ መስበክና አለበት። ለምን? መዝሙሮች ስለ ራስ እና ስለ እግዚአብሔር ትክክለኛውን ዕውቀት በማስተማር የተካኑ ናቸው። መጀመሪያ መዝሙሮች ስለ ራስህ ትክክለኛውን ዕውቀት፣ ኃጢአትህን እና ድካምህን ያስተምሩሃል።

> በአመጻ ተወለድኩ፤ እናቴም በኃጢአት ጸነሰችኝ። (5፥15)
>
> መተላለፎቼ ከራሴ በላይ ከፍ ብለዋል፤ እንደ ከባድ ሸክም በጣም ከብደውኛል። (38፥4)
>
> ስለ ኃጢአቴ ዝም ባልኩ ጊዜ ሰውነቴ ቀኑን ሙሉ በመቃተት አለቀ። (32፥3)
>
> ቀኖቻችን ሁሉ በቁጣህ አልቀዋል፤ ዘመናቶቻችንን እንደ ሸረሪት ድር ጨርሰናል። (90፥9)
>
> በእርግጥ እያንዳንዱ ሰው እስትንፋስ ነው። (39፥5)
>
> ብቸኛ እና የተጎሳቆልኩ ነኝና ራራልኝ። (25፥16)
>
> ጌታ ሆይ ጠላቶቼ እንደምን በዙ! ብዙዎች በእኔ ላይ እየተነሡ ነው። (3፥1)
>
> ልቤ በጣም አዝኗል፤ የሞት ጣር በላዬ ወድቋል። (55፥4)

[69] John Calvin, Institutes of the Christian Religion, 2 vols., trans. by Ford Lewis Battles, ed. by John T. McNeill, vol. 20 in The Library of Christian Classics (Philadelphia: The Westminster Press, 1960), 1:37.

ነገር ግን ያለ ትክክለኛው የእግዚአብሔር ዕውቀት ራስን በትክክል ማወቅ ብቻውን ጥቅም አልባ ነው፤ እግዚአብሔርን በትክክል ማወቅን ከመዝሙር መጽሐፍ በላይ ግልጽ አድርጎ የሚያስተምር የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ይለም።

አምላካችን እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። (99፥9)

እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ ነው … ሰው ንስሐ ካልገባ ሰይፉን ይስላል። (7፥11–12)

አምላካችን በሰማይ ነው፤ ደስ ያለውን ሁሉ ያደርጋል። (115፥3)

እግዚአብሔር ተናገረ፤ እኔም ይህንን ብቻ ሰማሁ፤ ኃይል የእግዚአብሔር ነው። (62፥11)

ከመገኘትህ ወዴት እሸሻለሁ? (139፥7)

እግዚአብሔር ሆይ ዙፋንህ ከዘላለም እስከ ዘላለም ነው። (45፥6)

እግዚአብሔር ሩህሩህ እና መሀሪ፣ ለቁጣ የዘገየ እና ምህረቱ የበዛ ነው። (103፥8)

ጌታ ትልቅ ነው፤ ምስጋናውም ብዙ ነው … ታላትነቱም አይመረመርም። (145፥3)

ጌታ መልካም መሆኑን ቀምሳችሁ ዕዩ። (34፥8)

**ተግዳሮት እና ብድራት**

መዝሙሮችን ማጥናት የፈሪዎች ተግባር አይደለም። በአንዱ መዝሙር በተራራ ጫፍ ላይ እግዚአብሔርን በማመስገን ትቆማለህ፤ በቀጣዩ ደግሞ ጥግ ታች የሌለው የፍርሃት ሸለቆ ውስጥ ትጣላለህ። በእርግጥ ዘማሪው አንዳንድ ጊዜ በአንድ መዝሙር ከተራራ ወደ ሸለቆ ይወስድሃል። በተጨማሪም በእኛ እና በብሉይ ኪዳን ባሕል መካከል የልዩነት ክፍተት አለ። በሀብታም ሴት ቤት ብዙ ጫማዎች እንዳሉ ሁሉ በመዝሙር መጽሐፍ ብዙ ዘውጎች (ጥበብ፣ ሹመት፣ ኀዘን፣ ምስጋና፣ ወዘተርፈ) አሉ። ይህ በቂ ካልሆነ መዝሙሮች ዝማሬዎች ወይም ግጥሞች ናቸው፤ ትሬምፐር ሎንግማን ቅሬታ እንደሚያቀርበው "በየትኛውም ቋንቋ ግጥም ለመመርመር ከባድ ነው።[70]

[70] Tremper Longman, III, How to Read the Psalms (Downers Grove, Ill.: Intervarsity Press, 1988), 14.

ነገር ግን መዝሙርን የመስበክ ሽልማት እነርሱን የማጥናት ጥረት ይጠይቃል። መዝሙሮችን ለመስበክ ቸልተኛ ከሆንክ ውጤቱን በጉባኤህ ላይ ሞክረው። መዝሙር 23 ስለምን እንደሆነ እና ማቴዎስ 3 ስለምን እንደሆነ ጠይቃቸው። እያንዳንዱ ሰው የመዝሙር 23 መሠረታዊ ይዘት እና መልእክት ምን እንደሆነ ያውቃል፤ ማቴዎስ 3 ይዘቱ ምን እንደሆነ አንድም ሰው ላያውቅ ይችላል። ምን ለማለት ነው? በመዝሙሮች እግዚአብሔር እውነትን የሚያስተላልፈው በኃይለኛ፣ በሚማርክ መልኩ ነው። ይህ ኃይል ወደ ቆሻሻ እንዲጣል አትፍቀድ! መዝሙሮችን ስበክ! አንበሳውን (አምልኮን) ከእስራቱ ፈተህ ልቀቀው። እርሱ ዘሎ ሲወጣ፣ ጎፈሬውን ሲያራግፍ፣ በእግዚአብሔር ግርማዊ ድምጽ ሲያጓራ የጣኦት አምልኮ እና በራስ መጠመድ ከፊቱ ይሰወራሉ።

የመዝሙር መጽሐፍ እንዴት መጠናት እንዳለበት ለመዳሰስ የሚያስፈልግ አንድ ምዕራፍ አይደለም፤ አንድ መጽሐፍ እንጂ። ስለዚህ መዝሙሮችን ለማጥናት፣ በስዕላዊ መግለጫ ለማስቀመጥ፣ እና ማውጫ ለማዘጋጀት በአራት መመሪያዎች ራሴን እገድባለሁ።

### 1) ትይዩ አወቃቀርን ተመልከት

እንደ መጽሐፈ ምሳሌ ሁሉ መዝሙሮችን ማጥናት ትይዩ መዋቅርን በመረዳት ይጀምራል። ዴሬክ ኪድነር ስለ መዝሙር መጽሐፍ እንዲህ ይጽፋል፣ “የዚህ ግጥም መሠረታዊ መገለጫ አንዱን ሐሳብ ከሌላው ጋር የሚያዛምድበት ወይም የሚያስተጋባበት መንገድ ነው።”[71] ተመሳሳይ እና ተጻራሪ ትይዩነቶች ይበዛሉ፤ ነገር ግን ሁሉም አይነት ትይዩነት በመዝሙር መጽሐፍ ውስጥ ይገኛል።

ተመሳሳይ ትይዩነት (ሀ=ለ)

“ነፍሴ ሆይ፥ ለምን ታዝኛለሽ?

ለምንስ ታውኪኛለሽ?” (42፥5)

ጥምር ትይዩነት (ሀ+ለ)

“አቤቱ፥ በልቤ ሁሉ አመሰግንሃለሁ፥

ተአምራትህንም ሁሉ እነግራለሁ።” (9፥1)

[71] Derek Kidner, Psalms 1-72: An Introduction and Commentary, Tyndale Old Testament Commentaries (Downers Grove, Ill.: Intervarsity Press, 1973), 2.)

ተጻራሪ ትይዩነት (ሀ≠ለ)

“ክፉ አድራጊዎች ይጠፋሉና፤

እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉ ግን እነርሱ ምድርን ይወርሳሉ።” (37፥9)

ተወዳዳሪ ትይዩነት (ሀ=ለ!)

“ዋላ ወደ ውኃ ምንጭ እንደሚናፍቅ፥

አቤቱ፥

እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች።” (42፥1)

**መዝሙሩ ታሪካዊ ዳራ ካለው መርምር**

ዘማሪዎቹ አንድ ክፍል ውስጥ ተቀምጠው ስለ እግዚአብሔር ድንቅ ግጥሞችን በመጻፍ እንዲያቀናብሩ የሙዚቃ ድርጅት የሚከፍላቸው ባለሙያዎች አልነበሩም። ስለ ራሳቸው ሕይወት እና ስለ እግዚአብሔር ለመጻፍ መንፈስ ቅዱስ የመራቸው ሰዎች ነበሩ። ስለራሳቸው ሕመም እና ደስታ ጽፈዋል፤ ከአደጋ ሲያመልጡ ሲደሰቱ ስለ እግዚአብሔር ድርሻ ጽፈዋል፤ በአገራቸው መቅሰፍት እና ነጻ መውጣት ላይ የእግዚአብሔርን ድርሻ ጽፈዋል።

ለምሳሌ ዳዊት በአብዛኛው ስለ እውነተኛ የሕይወቱ ሁኔታ ጽፏል፤ ስለዚህ ብዙ መዝሙሮቹ በሆነ ታሪካዊ ክስተት ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ያንን ክስተት ለይቶ ማወቅ መዝሙሩን ለመተርጎም እና ለመስበክ ቁልፍ ይሆናል።[72]

አንዳንድ ጊዜ እንደ መዝሙር 3 “ዳዊት ከልጁ ከአቤሴሎም በሸሸ ጊዜ የዘመረው መዝሙር” ብሎ ርእስ ስለሚሰጥ ቀላል ነው። መዝሙር 3ን በ 2ኛ ሳሙኤል 15–17 በአቤሴሎም የአምጽ ክስተት ብርሃን እንድትተረጉም ግልጽ ያደርገዋል። ዳዊት “በበኔ ላይ የሚቆሙት ብዙ ናቸው።” ደግሞም “ከሚከብቡኝ

[72] Kenneth L. Barker, "Praise," in Cracking Old Testament Codes: A Guide to Interpreting the Literary Genres of the Old Testament, ed. by D. Brent Sandy and Ronald L. Giese, Jr. (Nashville, Tenn.: Broadman & Holman Publishers, 1995), 227.

ከአእላፍ ሕዝብ አልፈራም።" (3፥1፣6) ብሎ ሲጽፍ በዘይቤ እየተናገረ አልነበረም። ስለ አቤሴሎም እና ስላስከተለው ጭፍራ እየተናገረ ነበር። "ሴራውም ጽኑ ሆነ፤ ከአቤሴሎምም ጋር ያለ ሕዝብ እየበዛ ሄደ።" (2ኛ ሳሙኤል 15፥12)

መዝሙር 51 መግለጫ ያዘለ ነው፤ "ወደ ቤርሳቤህ ከገባ በኋላ ነቢዩ ናታን ወደ እርሱ በመጣ ጊዜ የዳዊት መዝሙር" ምንም እንኳ መዝሙር 32 እና መዝሙር 38 ገላጭ ርእስ ባይኖራቸውም ከአሳፋሪው የቤርሳቤህ ክስተት በኋላ የተጻፉ ናቸው።

**መዝሙር 24**

በሌላ ጊዜዎች ለመዝሙሩ መወለድ ምክንያት የሆነውን ታሪካዊ ሁኔታ ማወቅ በጣም ከባድ ይሆናል፤ ነገር ግን መዝሙሩ ስለተጻፈበት ሁኔታ ይዘቱ የማያሳስት ፍንጭ ይሰጣል። ለምሳሌ የምሳሌ 24ን ግማሽ ተመልከት።

እናንት መኳንንቶች፥

በሮችን ክፈቱ፥ የዘላለም ደጆችም ይከፈቱ፥

የክብርም ንጉሥ ይግባ።

ይህ የክብር ንጉሥ ማን ነው?

እግዚአብሔር ነው፥

ብርቱና ኃያል፥

እግዚአብሔር ነው፥

በሰልፍ ኃያል። (24፥7–8)

በመዝሙር 24 ዳዊት እግዚአብሔር ራሱ በኢየሩሳሌም ለመኖር እየገባ ስለሆነ የከተማው በሮች በተጠንቀቅ እንዲቆሙ ይጣራል። ይህ በዳዊት ሕይወት የተከሰተውን ነገር ያንጸባርቃል? አዎ።[73] ከሳሙኤል ጊዜ አንሥቶ የቃልኪዳኑ ታቦት ከኢየሩሳሌም በስተምስራቅ በምትገኝ በቂርያት ይዓሪም በተባለች ትንሽ ከተማ ተቀምጦ

[73] Kidner, Psalms 1-72, 113.

ነበር። ታቦቱ ለማረፍ የመጣው በሊቀ ካህኑ በኤሊ ዘመን በፍልስጥኤማውያን ከተማረከበት ጊዜ በኋላ መመለሱን ተከትሎ ነው። (2ኛ ሳሙ 4፥1–7፥2)

አሥርቱን ትእዛዛት ከማስቀመጫ ሳጥንነት በላይ የቃልኪዳኑ ታቦት የምህረት መቀመጫ፣ የማይታየው የእስራኤል አምላክ የሚታይ ዙፋን ነበር። ዳዊት መዝሙር 24ን የጻፈው የሚታየው የእግዚአብሔር ምድራዊ ዙፋን ከቂርያት ይዓሪም ወደ ኢየሩሳሌም የተዘዋወረበትን ለመዘከር ነው።[74] በዘጸአት ጊዜ ግብጻውያንን ያሸነፈው እና በቅርቡ አምስቱን የፍልስጤም ከተሞች ያንበረከከው እግዚአብሔር በሰልፍ አሸናፊ የሆነው ጌታ ወደ ቤት እየመጣ ነበር።

ዳዊት የሚገርም ገጣሚ ነበር፤ ስለ እግዚአብሔር ክብር ለሕዝቡ አልተናገረም፤ ታቦቱ ለሚያልፍባቸው የኢየሩሳሌም በሮች ነው የተናገረው። ድል ያደረገ ንጉሥ ወደ ዋና ከተማው ሲገባ በሩን የሚጠብቁ ወታደሮችም ራሳቸውን ቀና በማድረግ ቀጥ ብለው ይቆማሉ። በዚህ ጊዜ የሚታየው የእግዚአብሔር ዙፋን ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ ዳዊት በሮቹ በተጠንቀቅ እንዲቆሙ ይጣራል። ቀጥ ብለው የሚቆሙበት ምክንያት እግዚአብሔር በበሮቹ በሚያልፍበት ጊዜ እንዳይገፋአቸው ነው።

የተቀረው የመዝሙር 24 ክፍል ታሪካዊ መቼቱን ስትመለከት ወደ ትኩረት ይመጣል። እግዚአብሔር መኖሪያውን በኢየሩሳሌም እያደረገ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን እንደ ሌሎች ሕዝቦች አሻንጉሊት አማልክት የአንድ ሰፈር መለኮት አይደለም። ድንበሩ ከኢየሩሳሌም የሰፋ ነው፤ “ምድርና ሞላዋ ለእግዚአብሔር ናት፥ ዓለምም በእርስዋም የሚኖሩ ሁሉ።” (ቁ.1) የያህዌህ አገዛዝ በኢየሩሳሌም ቅጥር የተገደበ አልነበረም።

ነገር ግን ዳዊት በቁጥር 3–4 ላይ በተቀደሰው በእግዚአብሔር ተራራ ላይ መኖር የሚችሉት ጽዱ እጅ እና ንጹሕ ልብ ያላቸው እንደሆኑ ለምን ማረጋገጫ ይጨምራል? ከሦስት ወራት በፊት ዳዊት ታቦቱን ለመጀመሪያ ወደ ኢየሩሳሌም ጊዜ ለማንቀሳቀስ ሲሞክር እግዚአብሔር ታቦቱን የነካውን ዑዛ የተባለውን ሰው ቀሰፈው (2 ሳሙ 6፥6–7)። “ይህ ነገር ሰዎችን ይገድላል!” የሚለው በኢየሩሳሌም ጎዳናዎች ላይ አስደንጋጭ ማጉረምረም ነበር። ዳዊት ቁጥር 3–4ን ያካተተበት ምክንያት በተገቢው መንገድ ከያዙት ከእግዚአብሔር ጋር በደህና መኖር እና በረከቶቹን ማጣጣም እንደሚችሉ ለማስረገጥ ነው። (ቁ.5ሀ)

[74] Gustav Friedrich Oehler, Theology of the Old Testament, trans. by George E. Day, fourth ed. (New York: Funk & Wagnalls Company, 1888), 257.

ታሪካዊ ሁኔታዎችን ተመልክቶ  የሆነ መዝሙር ላይ መጨን ትልቅ ወንጀል ነው። ነገር ግን የመዝሙሩ ርእስ ወይም ይዘት ወደሆነ ታሪካዊ ክስተት የሚጠቁም ከሆነ መዝሙሩን ስታጠና እና ስትሰብክ ክስተቱን ማጣቀስ አለብህ።

### 3) የአንድን መዝሙር መዋቅር በመጠቀም ማውጫ አዘጋጅለት

አንድን መዝሙር ስታነብ እንደ አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ከሆንክ፣ አንዲት ስንኝ መዘህ በመውሰድ በዚያ ስንኝ ላይ ብቻ ታተኩራለህ። ያን ማድረግ ቀላል ነው፤ ምክንያቱም መዝሙሮች በሚያጽናኑ በሚያነቃቁ፣ በሚያሳምኑ፣ እና አዕምሮን በሚይዙ ነጠላ ዐ.ነገሮች የተሞሉ ናቸው። ቢሆንም ይህ ልምምድ አደገኛ ነው፤ በተለይ ከመዝሙር መጽሐፍ ለመስበክ እያጠናህ ከሆነ። ያንተን ሐሳቦች መዝሙር ላይ መጨን ወይም በዘማሪው መልእክት ትንሽ ክፍል ላይ ብቻ ማተኮር አትፈልግም፤ የመዝሙሩን ሙሉ መልእክት መስበክ ትፈልጋለህ። ይህንን ማድረጊያ ምርጡ መንገድ የስብከትህን ማውጫ መዝሙሩ እንደ ሸክላ ቅርጽ እንዲያስይዘው መፍቀድ ነው። የሚመስል፣ ማውጫ መዝሙር ላይ ከመጨን ይልቅ የመዝሙሩን መዋቅር በመከተል ማውጫ አዘጋጅ። ሦስት ምሳሌዎችን እንመልከት፤ መዝሙር 3፣ 23፣ እና 33።

#### መዝሙር 3

መዝሙር 3 ማውጫ ለማዘጋጀት ቀለል ያለ ነው፤ ምክንያቱም ሴላ የሚለው የእብራይስጥ ቃል በዳዊት እሳቤ አመክንዮአዊ እረፍትን ወይም መሸጋገሪያን ያሳያል። (ሴላ የማይተረጎመው ቃል የመዝሙርን ማረፊያ አርኬ ያሳያል፤ ሁልጊዜ ግን አይደለም።)[75]

አቤቱ፥ የሚያስጨንቁኝ ምንኛ በዙ!

በኔ ላይ የሚቆሙት ብዙ ናቸው።

ብዙ ሰዎች ነፍሴን

አምላክሽ

አያድንሽም አልዋት። (3፥1–2)

አንተ ግን አቤቱ፥

[75] Craigie, Psalms 1-50, 76.

መጠጊያዬ ነህ፥

ክብሬንና ራሴንም ከፍ ከፍ የምታደርገው

አንተ ነህ።

በቃሌ ወደ እግዚአብሔር እጮሃለሁ፥

ከተቀደሰ ተራራውም ይሰማኛል። (3፥3–4)

እኔ ተኛሁ አንቀላፋሁም፤

እግዚአብሔርም ደግፎኛልና ነቃሁ።

ከሚከብቡኝ ከአእላፍ ሕዝብ አልፈራም።

ተነሥ፥ አቤቱ አምላኬ ሆይ፥

አድነኝ፤

አንተ የጠላቶቼን መንጋጋ መትተሃልና፥

የክፉዎችንም ጥርስ ሰብረሃልና።

ማዳን የእግዚአብሔር ነው፥

በረከትህም በሕዝብህ ላይ ነው። (3፥5–8)

ዘማሪዎች በመዝሙሮቻቸው ውስጥ እንደ መንገድ ዳር ምልክቶች ወደ አጠቃላዩ መልእክት የሚጠቁሙ ቁልፍ ቃላትን ሲያካትቱ እንግዳ ነገር አይደለም። በመዝሙር 3 መዳን ተብሎ የተተረጎመው ቃል 3፥2 እና 3፥8 ላይ ይገኛል። የማዳንን አውድ በአዕምሮ በመያዝ የመዝሙር 3 ምስላዊ መግለጫችንን መመልከት እና በምንባባዊ ምልክት ማውጫ በማዘጋጀት የሦስቱን ክፍሎች ማጠቃለያ መስጠት ቀለል ያለ ነው። ሁለቱ የመክፈቻ ጥቅሶች ዳዊት ላይ የመጣውን አደጋ፣ የአቤሴሎምን ሴራ እና በሰፊው የተደገፈው የአባቱን መንግሥት ለመገልበጥ ያደረገውን ሙከራ ይናገራሉ። ቁጥር 3–4 ዳዊት በእግዚአብሔር ላይ መደገፉን እና የዚህንም ሦስት ምክንያቶች ይገልጻሉ። የመጨረሻው ክፍል ስለ ዳዊት መዳን ይነገራል፤ እግዚአብሔር በቀድሞ ጊዜ የዳዊትን ጠላቶች

ሲያሸንፍ በማየቱ ላይ የተመሠረተ መልካም እንቅልፍ እና የልብ ሰላም ነው። እግዚአብሔር የጎልያድን ጥርሶች ከሰባበረ እቤሴሎምንም ይቆጣጠራል። አንተ እና ጉባኤህ ተግባራዊ የምታደርጉት ስነ መለኮታዊ መልእክት ምንድነው? ማዳን የእግዚአብሔር ነው (ቁ.8) ዳዊት የአቤሴሎም አደጋ በገጠመው ጊዜ እንዳደረገው ሁሉ በእርሱ ላይ በታማኝነት ለሚደገፉ በጸጋው መዳንን ያካፍላቸዋል።

**መዝሙር 23**

እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥

የሚያሳጣኝም የለም።

በለመለመ መስክ ያሳድረኛል፤ በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።

ነፍሴን መለሳት፥ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ።

በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤

በትርህና ምርኵዝህ እነርሱ ያጸናኑኛል።

በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ፤

በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ፥

ጽዋዬም የተረፈ ነው።

ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፥

በእግዚአብሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።

ዳዊት ይህንን መዝሙር የገነባው በሁለት ስዕሎች ላይ ነው፤ በሁለት የእግዚአብሔር ጥበቃ ማብራሪያዎች ላይ ነው፤ እረኛ (ቁ. 1–4) እና የድግስ ጋባዥ (ቁ. 5)። እረኛ ይጠብቃል፣ ይመራል፣ ደግሞም ሕይወትን ይሰጣል። የድግስ ጋባዥ ያስደስታል። የእግዚአብሔር የተትረፈረፈ እንክብካቤ ውጤቶች 23፥6 ላይ ተዘርዝረዋል። መዝሙሩን በዚህ መልክ ማጠቃለል እንችላለን፤ “በጨለማ በምትፈተንበት ወቅት እንኳ በእግዚአብሔር ጥበቃ እና ፍቅር እርግጠኛ መሆን እንደምትችል መዝሙር 23 ውስጥ ልብ የሚያሞቁ ሁለት የእግዚአብሔር ጸጋ ማብራሪያዎችን ታገኛለህ።” የምስላዊ መግለጫ ትልቅ አድናቂ የሆንኩበት አንዱ ምክንያት የመዝሙርን ቅርጽ

እና መልእክት በፍጥነትና እንዳገኝ የሚረዳኝ ሌላ ስለሌለ ነው። የመዝሙር 23ን ምስላዊ መግለጫ ስመለከት የሳር ማጨጃው ሞተር ተፈታቶ ሲያይ፣ "እንዴት እንደሚሠራ አሁን ገባኝ!" እንዳለው ሳር አጫጅ እሆናለሁ።

**መዝሙር 33**

አንዳንድ ጊዜ መዝሙሩ የተገነባውን ስነ መለኮታዊ ሐሳብ በመመልከት ማውጫ ሊዘጋጅለት ይችላል። መዝሙር 33 ለዚህ ምሳሌ ያቀርባል። የመዝሙሩ አጀማመር እንደ አብዛኞቹ መዝሙሮች 33፥6–19 ላይ ወዳለው የመዝሙሩ ሐተታ በሚመራሀ ለአምልኮ የመግቢያ ጥሪ ነው (33፥1–5)። 33፥20–22 ላይ ከሦስተኛ መደብ (እሱ፣ እነሱ፣ አሕዛብ፣ ንጉሡ፣ ወዘተርፈ) ወደ አንደኛ መደብ (የእኛ፣ እኛ) የተደረገው ለውጥ ከመዝሙሩ ሐተታ ወደ ጸሐፊው ድምዳሜ የተደረገውን ሽግግር ያሳያል።*[76]

በመዝሙሩ ሐተታ ጸሐፊው በሦስት የእግዚአብሔር ባሕርያት ላይ ያተኩራል። አንደኛ በተናገረው ቃል ብቻ መላለሙን ወደ መኖር በመጥራት አስደናቂ ችሎታው የተብራራው የእግዚአብሔር ኃይል፤ "በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፥ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ … ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን ትፍራው፥ በዓለም የሚኖሩ ሁሉም ከእርሱ የተነሣ ይደንግጡ። እርሱ ተናግሮአልና፥ ሆኑም፤ እርሱ አዘዘ፥ ጸኑም" (33፥6፣ 8–9)። ተወዳዳሪ የሌለው የእግዚአብሔር ኃይል የእርሱን ሉዐላዊነት—ዕቅዱ እንደሚጸና ይወስናል፤ "እግዚአብሔር የአሕዛብን ምክር ያጠፋል፥ የአሕዛብንም አሳብ ይመልሳል። የእግዚአብሔር ምክር ግን ለዘላለም ይኖራል፥ የልቡም አሳብ ለልጅ ልጅ ነው" (33፥10–11)። በ33፥13 ዘማሪው ትኩረቱን ወደ እግዚአብሔር ሁሉን ዐዋቂነት ያዞራል፤ "እግዚአብሔር ከሰማይ ተመለከተ፥ የሰውንም ልጆች ሁሉ አየ። … እርሱ ብቻውን ልባቸውን የሠራ ሥራቸውንም ሁሉ የሚያስተውል" (33፥13፣ 15)። የመዝሙሩን ይዘት የሚያጠቃልል ማንኛውም ማውጫ እነዚያን ባሕርያት ማካተት አለበት፤ የዚህ ስብከት መሸመቻ ዘንቢል በውስጡ ሦስት ብርትኳኖች ይኖሩታል። ግን እነዚያ ሦስት ባሕርያት ለምን? ዘማሪው ስለ እግዚአብሔር ጠንካራ ሐሳቦችን በዘፈቀደ እየጻፈ ነው? አይመስለኝም።

**የመዝሙር 33 የሕይወት ሁኔታ**

የሚቻል ከሆነ ወደ ሁለተኛው መርሆአችን ወደ መዝሙሩ ታሪካዊ ሁኔታ ለአንድ አፍታ እንመለስ። መዝሙር 33 የሚከተሉትን ስንኞች ይይዛል፤ "ንጉሥ በሠራዊቱ ብዛት አይድንም፥ ኃያልም በኃይሉ ብዛት አያመልጥም።

---

*Always pay attention to such transitions between first, second, and third person. Not only do they identify who is speaking to whom, they can also mark a move from one section of a psalm to another.

ፈረስም ከንቱ ነው፥ አያድንም፤ በኃይሉም ብዛት አያመልጥም።" መዝሙሩን ስታጠና እነዚህ ሁለት ስንኞች ከቦታቸው ውጭ የገቡ ይመስላሉ።ስለ እግዚአብሔር ሁሉን ታዋቂነት ከመናገሩ በፊት እና በኋላ ያሉት ስንኞች። ይህ ድንገተኛ የሠራዊት፣ የተዋጊዎች፣ የፈረሶች፣ እና የጦር ሜዳ ሐሳብ ለምን? ስለዚህ ነገር ዶግማዊ መሆን ባልችልም ዘማሪው 33፥16–17 ላይ ስለ እግዚአብሔር ኃይል፣ ሉዐላዊነት፣ እና ሁሉን ዐዋቂነት እንዲጽፍ ያስገደደውን የራሱን ሁኔታ እየሰጠህ እንደሆነ እገምታለሁ።

አሸዋ በሳራ በረሃ የተለመደ እንደሆነው ሁሉ ጦርነት በጥንቷ እስራኤል የተለመደ ነበር። ፍልስጥኤማውያን ወይም ፈርዖን በምድርህ ላይ ካልዘመቱ ዘላኖቹን አማሌቃውያን ወይም ደም የተጠሙትን አሞናውያን እየተፋለምክ ሊሆን ይችላል። በየጠዋቱ በጊዜ ተነሥተህ የትኛው ጦር ደጅህ እንደሰፈረ ለማወቅ በርህን መክፈት አለብህ። በዚህ መቼት የእግዚአብሔርን ተወዳዳሪ የሌለው ኃይል ለራስ ማስታወስ የዘፈቀደ ስነ መለኮታዊ ስህተት አይደለም። የአሕዛብን ዕቅድ የሚያፈርሰውን የእግዚአብሔርን ኃይል ማሰላሰል ከንቱ ስነ መለኮት አይደለም። እግዚአብሔር ከሰማይ የሰዎችን ልጆች መመልከቱ ጠቃሚ ቢሆንም እርሱን መመልከቱ በብዙ እጥፍ ጠቃሚ እንደሆነ የዚህ መዝሙር ጸሐፊ ይናገራል፤ "እነሆ፥ የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደሚፈሩት ናቸው፥ በምሕረቱም ወደሚታመኑ" (33፥18)። ሠራዊትን፣ ጦረኞችን፣ ፈረሶችን፣ እና ውጊያዎችን ያለ ሰዎች የድል ተስፋ በመግጠም ዘማሪው እግዚአብሔር የሚፈሩትን እንደሚመለከት በማወቁ በልዩነት ይጽናናል።

በሌላ አገላለጽ የመዝሙሩ ጸሐፊ አደገኛ ሁኔታ ውስጥ በገባ ጊዜ ያጽናኑት ሦስት የእግዚአብሔር ባሕርያት ላይ ትኩረት ያደርጋል። የዚህን መዝሙር ስነ መለኮታዊ ሐሳብ የትኛው የብዙ ቁጥር ስም ሊያቅፈው ይችላል? እንደዚህ አይነት ሐሳብ አቀርባለሁ፤ "በመዝሙር 33 እግዚአብሔርን መፍራት ሌሎች ፍርሃቶችን ሁሉ እንደሚያስወግድ ፍርሃት እንደሆነ የሚያስታውሱ ሦስት የእግዚአብሔር ባሕርያትን እናገኛለን።"

### 4) የሚደጋገሙ ቃላትን ወይም ሐሳቦችን ተመልከት

መዝሙር 121 ላይ የመዝሙሩ ጸሐፊ የዕብራይስጡ ግንደ ቃል ሻማር (መጠበቅ ወይም መጋረድ) በብዙ ቅርጽ ስድስት ጊዜ ይጠቀማል።[77] በስዕላዊ መግለጫችን አቅልሜአቸዋለሁ።

ዓይኖቼ ወደ ተራሮች አነሣሁ፤

 ረዳቴ ከወዴት ይምጣ?

[77] John E. Hartley, "rm;v '" in Theological Word Book of the Old Testament, 2 vols., ed. by R. Laird Harris, Gleason L. Archer, Jr., and Bruce K. Waltke (Chicago: Moody Press, 1980), 2:939.

ረዳቴ ሰማይና ምድርን ከሠራ

ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።

እግርህን ለመናወጥ አይሰጠውም፤

የሚጠብቅህም አይተኛም።

እነሆ፥ እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም

አያንቀላፋምም።

እግዚአብሔር ይጠብቅሃል፥

እግዚአብሔርም በቀኝ እጅህ በኩል ይጋርድሃል።

ፀሐይ በቀን አያቃጥልህም

ጨረቃም በሌሊት።

እግዚአብሔር ከክፉ ሁሉ ይጠብቅሃል፥

ነፍስህንም ይጠብቃታል።

ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም

እግዚአብሔር መውጣትህና መግባትህን ይጠብቃል።

ቁጥር 1–2 ላይ ረዳቴ ከሚለው ቃል ጋር ሲጣመር ዘማሪው መጠበቅ እና መጋረድ የሚሉትን ቃላት መደጋገሙ ወደዚህ ሐሳብ ያለስህተት ይጠቁምሃል።

መዝሙር 121 ከልዩ ታሪካዊ ሁኔታ ጋር የተሳሰረ ነው።[78] "የከፍታ መዝሙር" ተብሎ ይጠራል።* አይሁዳውያን እንደ ፋሲካ ያሉ አመታዊ በዓላትን ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ሲጓዙ ከሚዘምሯቸው አስራ አምስት

*(Don't get the impression that this is true of all psalms. Many have no discernable historical situation.)

መዝሙሮች (መዝሙር 120–134) ውስጥ የሚመደብ በመሆኑ ነው።[79] እነዚህ መዝሙሮች የከፍታ መዝሙሮች የተባሉበት ምክንያት ወደ ኢየሩሳሌም የሚወስዱት ሁሉም መንገዶች ወደ ላይ ስለሚመሩ ይሆናል። ከምስራቅ፣ ከምዕራብ፣ ከሰሜን ወይዘሮ ከደቡብ ወደ ኢየሩሳሌም ስትቀርብ የምትደርሰው ወደ ከፍታ በመውጣት ነው።

ምጣድ በሚመስለው የፍልስጤም ሙቀት ለቀናት በመራመድ ላይ ሳሉ የሚያመልኩ ሰዎች የጋረዳቸውን ድንጋይ ሲያልፉ ወይም በአሸዋማው መንገድ ከፍታ ላይ ሲወጡ ኢየሩሳሌምን እና ማዕከሉ የተጌጠውን በፊታቸው የሚያብረቀርቀውን መቅደስ ድንገት ያያሉ። ለደከማቸው መንገደኞች ምን አይነት ዕይታ ነው! ወደ ላይ እየተመለከቱ ተጓዦቹ የትኛውም ሕንፃ የማይዘውን እግዚአብሔርን እያመሰገኑ መዘመር ይጀምራሉ፤ “ዓይኖቼ ወደ ተራሮች አነሣሁ፤ ረዳቴ ከወዴት ይምጣ? ረዳቴ ሰማይና ምድርን ከሠራ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።” (121፥1–2) ምንም እንኳ በመንገዳቸው ቢደክሙም፣ በፍልስጥኤም ፀሐይ ዐይናቸው ቢቀላም፣ በድንጋያማው መንገድ ቢያብጥም፣ ረጅም ርቀት ባለው ጎዳና እግራቸው ቢዝልም ጠባቂያቸው እንደማይተኛ ደግሞም እንደማያንቀላፋ ያውቃሉ።

**በመዝሙር 33 የሚደጋገሙ ቃላት**

ተደጋጋሚ ቃላት የአንድን መዝሙር ሐሳብ የሚያስተዋውቁ ነጭ መብራቶች ናቸው። መዝሙር 33 ላይ እንደሚታየው በአንድ መዝሙር ውስጥ ያለን የምንባብ ክፍል ሲያስተዋውቁም ይችላሉ። በመዝሙር 33፥13–15 ጸሐፊው ሁሉ የሚለውን ቃል መደጋገሙ ያለጥርጥር በዚያ ክፍል ወደተዳሰሰው የእግዚአብሔር ባሕርይ ይጠቁማል፤ የእግዚአብሔር ሁሉን ዐዋቂነት፤ እርሱ ሁሉን ዐዋቂ የመሆኑ እውነታ።

እግዚአብሔር ከሰማይ ተመለከተ፥

የሰውንም ልጆች <u>ሁሉ</u> አየ።

ከማደሪያው ቦታ ሆኖ

በምድር ወደሚኖሩ <u>ሁሉ</u> ተመለከተ፥

እርሱ ብቻውን

[79] Derek Kidner, Psalms 73-150: An Introduction and Commentary, Tyndale Old Testament Commentaries (Downers Grove, Ill.: Intervarsity Press, 1975), 429.

ልባቸውን የሠራ ሥራቸውንም ሁሉ የሚያስተውል። (33፥13–15)

**ማጠቃለያ**

የመዝሙር መጽሐፍን ስለማጥናት ብዙ ነገር ማለት ይቻላል፤ ነገር ግን እነዚያ አራት መርሆዎች ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ ይጠቁማሉ፤ የትይዩነትን መዋቅር ተመልከት፤ ታሪካዊ ሁኔታ እንዳለው ፈልግ፤ የመዝሙሩን ቅርጽ ተከትለህ የስብከትህን ማውጫ አቀናብር፤ ደግሞም ተደጋጋሚ ቃላትን እና ሐሳቦችን ተመልከት።

አዲስ ኪዳንን እንድትሰብክ በደስታ አበረታታሃለው፤ ስለ ኢየሱስ የማርቆስን መልካም ዜና ስበክ፤ የጳውሎስን ጠንካራ ትምህርተ ድነት ስበክ። ነገር ግን ይህንን ስታደርግ መጽሐፈ ምሳሌን እና መዝሙሮችን እንዳትረሳ። የሆነ ቀን መጥቼ ቤትክርስቲያንህን እጎበኛለሁ፤ ያን ጊዜ የጉባኤህ መጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ሰባኪው በተደጋጋሚ ከመስበኩ የተነሣ አርጅተው፣ ታጥፈው፣ እና ቆሽሸው ማግኘት እፈልጋለሁ። እስር ቤቱን ክፈት! አንበሶቹን ፍታ!

# ማጠቃለያ

## ገላጭ ጥናት

ሁሉም ሰው የራሱ ጀግና አለው፤ ይህ ሰባኪዎችንም ይጨምራል። የቤተ-ክርስቲያን ታሪክ ተማሪ ከሆንክ፤ አንዳንድ የእኔ ጅግኖችን እንደምትጋራ ተስፋ አደርጋለሁ። ለምሳሌ አንዱ ጅግናዬ የግርክ ቤተ-ክርስቲያን አባት የነበረው ዮሐንስ አፈወርቅ ነው። ጥቅስ በጥቅስ እያብራራ ይሰብክበት የነበረው መንገድ እጅግ ልዩ ነው። በዘመኑ የነበሩ ሰዎች "ወርቃማ አንደበት" ብለው ይጠሩት ነበር። ሌላኛው ደግሞ ማርቲን ሉተር ነው፤ በማርቲን ሉተር በሮማ ካቶሊክ ቤተ-ክርስቲያን የተሸሸገውን ሐሰተኛ አስተምህሮና ድርጊት ለመናድ እግዚአብሔር የእርሱን ስብከቶች ተጠቅሟል። እውቁ የነገረ መለኮት ሰው ዮሐንስ ካልቪንም ገላጭ ስብከት ዘዴን የሚጠቀም ሰው ነበረ። እሁድ እለት ሁለቴ ይሰብካል፤ ከወር ሁለቱን ሳምንት በየእለቱ ይሰብካል፤ በጄኔቫ በነበረው የ25 ዓመታት አገልግሎት መጽሐፍ ቅዱስን ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ገላጭ በሆነ መንገድ ሰብኳል።

በእስትላንድ ዮሐንስ ኖክስ፣ በእንግሊዝ ዮሐንስ ዊክልፍ፣ሁግ ላትመር፣ ቶማስ ዋስቶን፣ ዮሐንስ ኦውን፣ ዮሐንስ ቡናያን፣ ዮሐንስ ዌስሊ እና ጆርጅ ዋይትፍልድ እጅ በእጅ በመቀባበል የክርስቶስ ኢየሱስን ወንጌል የሰበኩ ሰዎች ናቸው። በአሜርካ ዮናታን ኤድዋርድስ በከፋ ኃጢአት ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በነበልባሉ እግዚአብሔር ምህረት እንዲያገኙና በእጆቹ እንዲያርፉ ስብከቱ ትልቅ ሥራ ሰርቷል። በ1800ዎቹ በእንግሊዝ ቻርለስ ሰፐርጅን የሰባኪዎች ንጉስ ተብሏል።

### አዲስ ጀግና

እንደ ሰባኪዎች ሁላችንም ጀግኖች ይኖሩናል። ይህንን መጽሐፍ ሳጠቃልል ግን አዲስ ጀግና ላስተዋወቅህ እፈልጋለሁ። ጸሐፊው ዕዝራ። በነህምያ በተመራው የመነቃቃት ዘመን እንደ መንፈሳዊ ሰው ዕዝራ በብሉይ ኪዳን ዘመን የምናገኘው ታላቅ የመድረክ ሰው ነበረ።

> *ሰባተኛውም ወር በደረሰ ጊዜ የእስራኤል ልጆች በከተሞቻቸው ነበሩ። ሕዝቡም ሁሉ በውኃው በር ፊት ወዳለው አደባባይ እንደ አንድ ሰው ሆነው ተሰበሰቡ እግዚአብሔርም ለእስራኤል ያዘዘውን የሙሴን ሕግ መጽሐፍ ያመጣ ዘንድ ጸሐፊውን ዕዝራን ተናገሩት።........ የእግዚአብሔርንም ሕግ መጽሐፍ*

*አነበቡ ዕዝራም እግዚአብሔርን ማወቅ ያስተምርና ያስታውቅ ነበር፥ ሕዝቡም የሚነበበውን ያስተውሉ ነበር።* ነህ 8፥1፤8

ጸሐፊው ዕዝራ ገላጭ ስብከትን በሚገባ ተላብሷል። ቅዱሳት መጽሐፍትን አነበበ፤ ክፍሉን አብራራ፤ ከዚያም ክፍሉን አዘመደ። ከዛ ሁሉ በላይ ግን ዕዝራ ገላጭ ጥናትን ተላብሷል። ያ ነው እርሱን የእኔ ጀግና ያደረገው። ሁሉም ሰው መስበክ ይፈልጋል፤ ዕዝራ ግን እግዚአብሔርን ለመስበክ አስቀድሞ ማጥናት እንደሚያስፈልግ ተረድቷል።

ዕዝራ 7፡6 ስለ እርሱ ሲናገር "የእስራኤልም አምላክ እግዚአብሔር በሰጠው በሙሴ ሕግ ፈጣን ጸሐፊ ነበረ የአምላኩም የእግዚአብሔር እጅ በእርሱ ላይ ነበረችና ንጉሡ የሻውን ሁሉ ሰጠው።" ይላል። ልጅ እያለሁ አንድ ጨዋታ እንጨወት ነበረ፤ ጨዋታው የሚጠራውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በፍጥነት ከፍቶ ከፍ ባለ ድምጽ ማንበብ ነበረ። በፍጥነት ከፍቶ ከፍ ባለ ድምጽ ያነበበ ሰው የጨዋታው አሸናፊ ነው። ለእኔ ዕዝራ የዚህ ጨዋታ የሁል ጊዜ አሸናፊ ነው።

የዕዝራን ክህሎትና ችሎታ በተመለከተ ምንም ምስጢር የለም። "ዕዝራም የእግዚአብሔርን ሕግ ይፈልግና ያደርግ ዘንድ፥ ለእስራኤልም ሥርዓትንና ፍርድን ያስተምር ዘንድ ልቡን አዘጋጅቶ ነበር።" (ዕዝ 7፡10) የእግዚአብሔርን ሕግ በተመለከተ ዕዝራ ሦስት የመሰጠት መለኪያዎች አሉት፤ ማጥናት፣ መኖር/መተግበር እና መስበክ።[80] ጠቢቡ ሰለሞን እንደሚያስታውሰን *በሦስትም የተገመደ ገመድ ፈጥኖ አይበጠስም* (መክ 4፡12)።

## ሦስቱ የዕዝራ መሰጠቶች/ቁርጠኝነቶች

የመጀመሪያው ዕዝራ የእግዚአብሔርን ሕግ ለማጥናት ልቡን አዘጋጅቶ፤ ፈጽሞ ሰጥቶ ነበረ። ለማጥናት ተብሎ የተተረጎመው ቃል፤ ለመመርመር ወይም በጥንቃቄ መፈለግ ሊባል ይችላል። ዕዝራ እግዚአብሔር ቃል ፊት የሚቀርበው በጉጉት፣ በንቃትና በትጋት ነው። ለምን፣ እንዴት፣ መቼ፣ የት፣ ምን ያህል ጊዜ ወዘተ የመሳሰሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ አያቆምም።

መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት እንደ ዕዝራ ዓይነት መሰጠት መያዝ ቀልል ስራ አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ ከባድ ሥራ ነው፤ እኛ ደግሞ ላይ ላዩን መሮጥ የምንወድ ነን። የአፍርካ ጉባኤዎች ገላጭ ስብከት ለማዘጋጀት

---

[80] George J. Zemek, "Grammatical Analysis and Expository Preaching," in Rediscovering Expository Preaching, John MacArthur, Jr. and The Master's Seminary faculty, (Dallas, Texas: Word Publishing, 1992), 163-5.

የሚያስፈልገው ጊዜና አቅም አይገነዘቡም፤ ስለዚህ የምታገለግላቸው ሰዎች ከስብከትህ በፊት ስለምታጠፋው ጊዜ ግድ አይላቸውም፤ መኖሩንም አያስታውሱም። ብዙ ጊዜህን ይፈልጋሉ፤ ያለ ቀጠሮ ይመጣሉ፤ ብዙ ሰዓትህን ይወስዱብሃል። ስለዚህ እንደ ዕዝራ ለመሆን በሌሊት የምትነሳ መሆን አለብህ፤ሌሊት ተነስ፤ ከአስረ አንድ ሰዓት እስከ ጠዋቱ ሁለት ሰዓት አጥና። በነዚህ ሰዓታት የሚፈልግህ ሰው አይኖርም፤ ስልክም ቢሆን ብዙ አይረብሽም። በማለዳ ማጥናት ቀሪውን ቀንህን ለሌሎች አገልግሎቶች እንድትሰጥ ረደሃል።

በጊዜ ሂደት የቤተ-ክርስቲያንህ ሰዎች የጥናት ሰዓትህን ማክበር ይጀምራሉ፤ በተለይም ደግሞ በስብከትህ የሚታይ ለውጥ ካስተዋሉ። አንድ  ጊዜ በለቤቴ አንድ በቤተ-ክርስቲያንችን የለ ወጣት ልጅ እናት ልትጎበኝ ቤታቸው ሄደች፤ እናትየው በለቤትሽ የት ነው ሲሉ ጠየቋት፤ በለቤቴም ለስብከት እየተዘጋጀ ነው፤ እያጠና ነው አለቻቸው፤ ሴትየው ትንሽ አሰብ አድርገው ለመስበክ ማጥናት ያስፈልገዋል ማለት ነው ብለው ጠየቁ። ይህ ንግግራቸው ዘመናቸውን ሁሉ ምን ዓይነት ስብከት ሲሰሙ እንደኖሩ የሚነግረን ነገር አለ። ነፋስና ትርጉም አልባ ነገር ከሰበክህ ሰው ለመስበክ ማጥናት አያስፈልግም ብሎ ይደመድማል። ነገር ግን ገላጭ የሆነ በብዙ ደስታና ፍቅር የተሞላ፣ በሕይወት ለመተግበር የሚሞግት ስብከት የምስትሰብክ ከሆነ ጉባኤህ የጥናት ሰዓትህን ያከብርልሃል፣ ለዝግጅት የምትፈልገውን ጊዜ ሁሉ ይፈቅድልሃል።

ሌላው የምታገለግለው ጉባኤ ለስብከትህ ዝግጅት ጊዜ እንዲሰጥህ ማድረጊያው ዘዴ፤ እነርሱ አንባቢ እንዲሆኑ መምከርና ማበረታታት ነው። ብዙዎቹ አፍርካዊያን አንባቢዎች አይደሉም። ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስንና ሌሎች ጠንካራ ክርስቲያናዊ ሥነ-ጽሑፎችን ማንበብ ሲጀምሩ የስብከት ዝግጅት ምን ያህል ጥናትና ንባብ እንደሚፈልግ ወደ መረዳት ይመጣሉ። በተጨማሪም ባነበቡ ቁጥር የገላጭ ስብከት አፍቃሪዎች ወደ መሆን ይመጣሉ። የሚያነቡ ቤተ-ክርስቲያናት ከገላጭ ስብከት ውጭ የሚመርጡት የላቸውም።

ስለዚህ ዕዝራ የአንተም ጀግና መሆን አለበት፤ ምክንያቱም እርሱ የእግዚአብሔርን ቃል ከመስበኩ በፊት በሚገባ የሚያጠና ሰባኪ ነውና። ያ ብቻ ሳይሆን ዕዝራ የእግዚአብሔርን ህግ የሚያደርግ የተግባር ሰው ነው። ምንም እንኳ እጅግ ታላቅ ሰባኪ ብትሆን ቃሉን የማትኖር ከሆነ ስብከትህ በዜሮ ይባዛል። ሰጋራ የሚያጬሱ ሃኪሞች ሁሌም ይገርሙኛል፤ የሚያውቁትን የማይኖሩ ናቸው። ልክ እንደዚሁ የሚሰብኩትን የማይኖሩ ሰባኪዎችም ያው ናቸው። ስለዚህ ዕዝራ የእግዚአብሔርን ህግ ለማጥናት ብቻ ሳይሆን ለማድረግም ልቡን ማዘጋጀቱ ለእኛ ምሳሌ ያደርገዋል።

የዕዝራ ሦስተኛው መሰጠት፤ የእግዚአብሔርን ሕግ ለማስተማር ነው። ውሃ እንደ ተጠሙ በጎች ሕዝቡ ዕዝራ ጋር ተሰብስበው ያደምጡ ነበረ። *በሁለተኛውም ቀን ከሕዝቡ ሁሉ የአባቶች ቤቶች አለቆች ካህናቱም ሌዋውያኑም የሕጉን ቃል ይተረጉምላቸው ዘንድ ወደ ጸሐፊው ወደ ዕዝራ ተሰበሰቡ።* (ነህ 8፡13) የእግዚአብሔር ቃል የሕይወት ውሃ ነው፤ ዕዝራ ደግሞ ውሃውን እየቀዳ የሚያጠጣ ሠራተኛ።

## የመጨረሻ ቃል

ዕዝራ ከእኔ ጀግኖች መካከል አንዱ ነው፤ ይህ መጽሐፍ እርሱን እናንተ ጀግናም እንደሚያደርገው ተስፋ አደርጋለሁ። በአጭር ቃል ዕዝራ ጥሩ አድርጎ የሰበከው ጥሩ አድርጎ ስለጠና ነው። መድረክ ላይ ቆመህ ነጎድጓዳማ ድምጽ ልታሰማ ትችላለህ፤ እግዚአብሔር በቃሉ ያለውን ካለልክ ግን ስብከትህ ከተራ ጫጫታና ከነፋስ አይለይም። ነገር ግን በዚህ መጽሐፍ እንደተማርከው ልብህን ለገላጭ ስብከት ብታዘጋጅና በዚያ መንገድ ብትሄድ፤ ዝናቡ መዝነብ ይጀምራል፤ ውሃው ይፈሳል ሕይወትም ይሰጣል ምድረ በዳውም ይለመልማል።

ስንዴውን መግብ፤ ዝናቡን አምጣ። ለንጽጽር የማይቀርበውን የእግዚአብሔርን ቃል ጥቅም በብዙ መንገድ ልትገልጥ ትችላለህ። መጽሐፍ ቅዱስ የአብ ድምጽ ነው፣ የወልድ ገላጭ ነው፣ የመንፈስ ሰይፍ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል የሚመስል ቃል የለም። ስለዚህ ልብህን ዕዝራ ባስቀመጣቸው ሦስት መሰጠቶች ላይ አሰርፈህ ቃሉን ስበክ። ይህንን ስታደርግ ለማጥናት ትኩረት ስጥ፤ ምክንያቱም ለእግዚአብሔር ለመሰበክ፤ ለእግዝአብሔር ማጥናት አለብህና።

ዕዝራ

በማጥናት

የእግዚአብሔርን ሕግ

በማድረግ

እና

በማስተማር

ለእስራኤልም ሥርዓቱንና ሕጉን

ራሱን ፈጽሞ ሰጥቶ ነበረ (ዕዝ 7፡10)

በዕዝ 7፡10 ጸሐፊውን ዕዝራን የገላጭ ሰባኪዎች ጀግና ያደረገው ሦስት መሰጠት/ቁርጠንነት አለ።

# አባሪ

## ስዕላዊ ንድፍ የማውጣት መልመጃ

በዚህ መጽሐፍ የተማርካቸውን ክህሎቶች ለማዳበር የሚከተሉ ጥቅሶችን በመጠቀም ሥዕላዊ ንድፍ ማውጣትን፣ የትርጓሜ መግለጫ ወይም ዝርዝር ማውጣትን እንዲሁም በለብዙ ቁጥር ስሞችን ማጠቃለያ ሥራ።

1 ጴጥ 1፡14-16 1 ጴጥ 5፡6-7 1ጴጥ 2፡1-3 2ጢሞ 3፡16-17

ቆላ 2፡8-12 ኤፌ 4፡1-3 ዕብ 12፡1-2 ፊል 2፡14-16

መዝ 23 ቲቶ 3፡4-7

የአንተን መልመጃ ከጨረስህ በኋላ አባሪ ውስጥ ያስቀመጥሁት በማየት መልስህን አነጻጽር።

ፍጹም የጠራ ሥራ ለሚሹ ማስጠንቀቂያ አለኝ። ስዕላዊ ንድፍ ስታወጣ አንድ መርጃ መሳሪያ እየተጠቀምክ እንጂ አንተ የአርት ሰው አይደለህም ስለዚህ የተቻለህን አድርግ። በትክክል ለመሳል ሞክር። አንዳንድ ስህተቶች የስብከትህን መልዕክት ሊቀይሩ ይችላሉና ጥንቃቄ አድርግ። በሌላ በኩል ደግሞ በሙዝየም የሚቀመጥ ጥበብ በመሳል ጊዜ አትፍጅ።

**<u>1 ጴጥሮስ 1፡14-16 (አመ.ት)</u>**

| | |
|---|---|
| ታዛዦች ልጆች እንደመሆናችሁ መጠን | |
| ባለመወቅ ትኖሩበት የነበረውን | አንጻራዊ |
| ክፉ ምኞት አትከተሉ | ዋና ግስ |
| ነገር ግን | የዋና ግስ ማነጻጸሪያ |
| የጠራችሁ እርሱ ቅዱስ እንደሆነ | አንጻራዊ |
| እናንተም በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ | |
| ምክንያቱም | ምክንያት |

እኔ ቅዱስ ነኝና ምክንያት

እናንተም ቅዱሳን ሁኑ

ተብሎተጽፎአልና ምክንያት

-

ይህ ምንባብ በእግዚአብሔር የተጠሩ ወንድና ሴት ልጆቹ እንደ እግዚአብሔር እውነተኛ ልጆች እንዴት መኖር እንዳለባቸው የሚረዳ ስለ ግላዊ ቅድስና ሁለት ምስጢሮችን ይገልጥልናል።

ከመዳናችሁ በፊት ወደነበረው የኑሮ ዘይቤ አትለወጡ

ሀ) የልጅነት ማስወገድ (እንደ ታዛዦች ልጆች)

ለ) በመረጃ የተደገፈ ማስወገድ (ክፉ ምኞት አትከተሉ)

አዳኝህን እግዚአብሔርን መምሰል

ሀ) የመለወጥ/ የመምሰል ግዴታ (ትዕዛዝ)

ለ) ለመለወጥ የምትመስለው (ቅዱሱን)

ሐ) የመለወጥ ልክ/መዳረሻ (በኑሮ ሁሉ)

መ) የመለወጥ ስልጣን (የብሉይ ኪዳን ጥቅስ)

## 2 ጢሞ 3፡16-17

ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው ዋና ግስ

ለማስተማር መስተዋድድ

ለመገሠጽ

ለማቅናት

ለመምከር

በጽድቅ መንገድ

ይኸውም

የእግዚአብሔር ሰው

ለመልካም ስራ ሁሉ ብቁ ሆኖ እንዲገኝ ነው ውጤት

_

2 ጢሞ 3፡16-17 ስለ እግዚአብሔር ቃል ሥልጣን፤ ይኸው ቃል ለሰባኪዎች እንዲሁም ለክርስቲያኖች ውጤታማነት ያለውን ሚና የሚያሳይ ሁለት እውነቶችን ያውጃል፡፡

የቅዱሳት መጽሐፍት ምንጭ

ሀ. መደቡ (በእግዚአብሔር)

ለ. መመሪያው (እስትንፋሰ መለኮት)

2. የቅዱሳት መጻሕፍት ጠቃሚነት

ሀ. ለአስተምህሮ

ለ. ለእምነት

ሐ. ለማቅናት

መ.ለትምህርት

ሠ. ለማብቃት

- የማብቃቱ ተጠቃሚ (የእግዚአብሔር ሰው)
- የማብቃቱ ስፋት (ለመልካም ሥራ ሁሉ)

ቆላ 2፡8-12

1. ማንም ማርኮ እንዳይወስዳችሁ

ሀ. በ ፍልስፍና

እና

ለ. ከንቱ ማግባቢያ

ሐ. በክርስቶስ ላይ ሳይሆን

መ. በሰዎች ልማድ

ሠ. በዚህ ዓለም

መሠረታዊ ልማድ

2.

ሀ. የመለኮት ሙላት ሁሉ በእርሱ

በአካል ይኖራል

ለ. እናንተም የመለኮት የገዥነትና የሥልጣን ሁሉ ራስ በሆነው በክርስቶስ ሙሉ ሆናችኋል

ሐ. እርሱ የአለቅነትና የሥልጣን ሁሉ ራስ ነው

መ. በክርስቶስ መገረዝ

በእጅ ባልተደረገ

የሥጋን ኀጢአታዊ ባህርይ አስወግዳችሁ

በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ

እርሱን ከሙታን ባስነሳው

በእግዚአብሔር ሐይል

በማመን

ከእርሱ ጋር

ተነስታችኋል።

---

ቆላ 2፡8-12 የሁለት ተቃራኒ የሥነ-መለኮት አስተምህሮዎችን በማነጻጸር በቤተ-ክርስቲያ ምን ማስተማር እንዳለብንና እንደሌለብን ይነግረናል።

1. የሰይጣን በኩል ሥነ መለኮት

    ሀ. የሰው ጥበብ

    ለ. ከንቱ ማባበያ ጥበብ

    ሐ. የሰዎች ልማድ ጥበብ

    መ. ዓለማዊ ጥበብ

    ሠ. ከክርስቶስ ያልሆነ ጥበብ

2. የእግዚአብሔር በኩል ሥነ-መለኮት

    ሀ. የክርስቶስ መለኮታዊነት

    ለ. የክርስቶስ ሥራ

    ሐ. የክርስቶስ ሥልጣን

    መ. በክርስቶስ የውስጥ መገረዝ

        መለኮታዊ ምንጩ

        መንፈሳዊ ባሕርዩ

        ከመንፈሳዊ ጥምቀት ጋር በትይዩ መሄዱ።

**ማስተወሻ**

ስለ ስዕላዊ ንድፍ አወጣጥ ለመልመጃነት የቀረቡ ጥቅሶች ብዙ ናቸው፤ ከላይ በዚህ ክፍል መግቢያ ጠቅሰናቸዋል። ነገር ግን የእንግሊዘኛው መልመጃ የተሰራው የእንግልዝኛ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ነው፤ ያንን በቀጥታ ተርጉሞ ማስቀመጡ አስቸጋሪ ነው ምክንያቱም የእንግልዘኛና አማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶች የሐሳብ ፍሰትና አገባብ ይለያል። ስለሆነም ከላይ የቀረቡትን ጥቂት ምሳሌዎች በማየት ቀሪዎቹን ጥቅሶች እንድትሰሩባቸው በትህትና እንጠይቃለን።